# መንፈስ ቅዱስ

## እንደ መግቢያ


ጆን ቢቨሬ

ከ ኤዲሰን ቢቨሬ ጋር




መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ እጋዥ ዲቪዲ የታከለበት

የተከበርህ ወዳጄ፣

የእግዚአብሔር ደስታና የልብ ፍስሐ ነህ። ትልቁ የእርሱ ፍላጐት ከአንተ ጋር መቀራረብና በአንተ መታወቅ ነው። ከእርሱ ጋር እየተቀራረብህ ስትሄድ፣ በዚህ ምድር የእርሱን መንግሥት በማስፋፋት አብረኸው እንድትሠራ እግዚአብሔር ጥሪ አቅርቦልሃል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ተናገረው፣ <<እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን>> (ኤፌሶን 2፥10)።

እንደ የእግዚአብሔር ልጆች ሁላችንም እርሱን አባታችንን ደስ ማሰኘት እንፈልጋለን። ይሁን እንጂ፣ ኢየሱስ ራሱ በግልጥ የተናገረውን ማለትም፣ የእግዚአብሔርን ዕቅድ የመፈጸም ኃይል የሚገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተቀራርቦ በመኖር የመሆኑ ሐቅ በቀላሉ ይሳተናል። እግዚአብሔር ለእርሱ እንድንሠራ ብቻ ሳይሆን፣ ከእርሱ ከራሱ ጋር አብረን እንድንሠራም ጭምር ጋብዞናል። የልብ ወዳጃችን መሆን፣ እያንዳንዱን የሕይወታችንንም ቅጽበት መካፈል ይፈልጋል። ሊያናግረን፣ ሊያበረታታንና ኃይሉን ሊሰጠን ፈቃደኛ ነው። በመንፈሱ አማካይነት የሚሰጠንን መቀራረብና ኅብረት የሚበልጥ ምንም ዐይነት ኅብረትም ሆነ መቀራረብ የለም።

ይህን መልእክት ለእናንተና በዓለም ዙሪያ ላሉ መሪዎች እንዳካፈል ጌታ ልቤን አነሣስቶአል። የፍቅሬ መገለጫና እናንተን ለመርዳት የማደርገው እገዛ አካል አድርጋችሁ ተቀበሉት። ለምታውቋቸው ሁሉ አካፍሉት። ለእናንተም ሆነ እናንተ ለምትመሩዋቸው ወገኖች የጠለቀና በዕድሜ ዘመን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የማድረግ ጅማሬ እንደሚሆንላችሁ እምነቴ ነው።

የእግዚአብሔር ልጆች ከሆናችሁ እንደማይተዋችሁና እንደማይጥላችሁ መንፈስ ቅዱስ ቃል ገብቶላችኋል። ምንጊዜም ቢሆን የእርሱ ወዳጅነት አይለያችሁም። በእነዚህ ገጾች ውስጥ የተካተቱ እውነቶች የእኔን ሕይወት ለውጠውታል፤ የእግዚአብሔርን ቃል እያጠናችሁ ስትሄዱ እናንተም ሥር ነቀል መገለጥ እንድትለማመዱ ጸሎቴ ነው። ይህ መልእክት እናንተንም ላይ ሆነ በእናንተ አገልግሎት ሥር ያሉት ላይ ምን ዐይነት በጐ ተፅዕኖ እንዳሳደረ መስማት እፈልጋለሁ።

በክርስቶስ ወንድማችሁ

John Bevere



John Bevere
JohnBevere@ymail.com

Messenger International
MessengerInternational.org

# መንፈስ ቅዱስ

እንደ መግቢያ

ጆን ቢቨሬ

ከ ኤዲሰን ቢቨሬ ጋር

መንፈስ ቅዱስ - እንደ መግቢያ
The Holy Spirit an Introduction

ጆን ቢቨሬ - ከኤዲሰን ቢቨሬ ጋር
John Bevere With Addison Bevere

*©2015 Messenger International*
*www.Messengerinternational.org*
*Originally Published in English*

ከwww.Cloudlibrary.org በነጻ ለመውሰድ በአማርኛ ያሉ ተጨማሪ መጻሕፍት፡- ተስፋ እንዳትቆርጥ የሚያስፈልግህ ኃይል - ጽናት የሰይጣን ሽንገላ - የጽናት መጽሐፍ የጥናት መመሪያና በጽሞና ማሰላሰያ - በጆን ቢቨሬ - እንስት አንበሶቹ ይነሣሉ - በሊዛ ቢቨሬ፡ ፡ እንዲሁም የ30 ደቂቃ መልእክቶች የያዙ 12 ቪድዮና ኦዲዮ ሲዲዎች፡፡

ለማባዛት፣ በኢንተርኔት ለማሰራጨት፣ ጠቃሚ ሐሳቦችን ለመጠቀም ወይም ይህን የአማርኛ መልእክት ከሌሎች ጋር ለመከፋፈል ትበረታታላችሁ፡፡

የመጽሐፉን ደራሲ ለማግኘት - *Johnbevere@ymail.com*
*Translated to Amharic by - Tesfaye Mesfin*
*Computer Setting by - Betelhem Minas*

# ማውጫ

ስለዚህ አሳታፊ መጽሐፍ . . . . . . . . . . . . . . . . . . VI

መግቢያ በኤዲሰን ቢቨሬ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . VII

1. መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

2. የመንፈስ ቅዱስ ሰብዕና . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 39

3. ሦስት የግንኙነት ደረጃዎች . . . . . . . . . . . . . . . . 79

4. ከመንፈሱ ኃይል መቀበል . . . . . . . . . . . . . . . . 113

5. የመንፈስ ቋንቋ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 157

በውይይት መልክ ጥያቄና መልስ . . . . . . . . . . . . 201

ድነት እንዴት እንደምትቀበሉ . . . . . . . . . . . . . . . . 227

ማስታወሻዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 231

# ስለዚህ አሳታፊ መጽሐፍ

እንደ ማንኛውም መጽሐፍ ሁሉ ይህንንም መጽሐፍ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ማንበብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የበለጠ ግላዊ ተመክሮ እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ፣ አማራጭ አሳታፊ ክፍሎቹ ላይ ጠለቅ ያለ ጥናት እንድታደርጉ እንመክራለን፡፡

እያንዳንዱ የዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ከተሰጡት ተጓዳኝ በግል ማጥኛና ማሰላሰያ ጋር፣ በአምስት ዕለታዊ ምንባቦች ተከፍሎአል፡፡ በእያንዳንዱ ቀን አንድ ምንባብና አንድ በግል ማጥኛና ማሰላሰያ መምረጥ ትችላላችሁ፤ ወይም እነዚህን ትምህርቶች በሚያመቻችሁ ሁኔታ ልትጠቀሙባቸው ትችላላችሁ፡፡ በቡድን እያጠኑ ያሉ ወገኖች የአንዱን ምዕራፍ ምንባብና የጥሞና ማሰላሰያ በአንድ ሳምንት ውስጥ እንዲያጠናቅቁ እናሳስባለን፡፡

በዚህ መጽሐፉ ላሉት እያንዳንዱ ምዕራፍ፣ አንድ ክፍለ ትምህርት ተሰጥቷል፡፡ የእያንዳንዱ ምዕራፍ የውይይት ጥያቄዎች ያሉት ከጽሞና ማሰላሰያዎቹና ማጥኛዎቹ በኋላ ነው፡፡

መልካም ጊዜ ይሁንላችሁ!

# መግቢያ

በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት እንድረዳው ወላጅ አባቴ መጀመሪያ የጠየቀኝ ጊዜ የሰማሁትን ማመን አቅቶኝ ነበር፡፡ ምናልባት በሚገባ አልጸለየበትም ይሆናል በማለትም አስቤ ነበር፡፡ እውነቱን ለመናገር በበኩሌ ለዚህ የበቃሁ ነኝ ብዬ ራሴን አልቆጥርም፡፡

ሌሎች አማራጮችን እንዲፈልግና በጉዳዩ አጥብቆ እንዲጸልይበት (ምናልባት ለዓመት ለሁለት ዓመት) በአክብሮት አባቴን ጠይቄው ነበር፡፡ ሆኖም አንድ ቀን በጸሎት ካሳለፈ በኋላ፣ እኔ ራሴ ለሥራው የማስፈልግ መሆኔን በልበ ሙሉነት ነገረኝ፡፡ ወጣቶች መንፈስ ቅዱስን በቸልታ እንዳይመለከቱት አባቴ አጥብቆ እንደሚፈልግ አውቃለሁ፡፡ እንደ አንድ በሃያዎቹ ዓመታት መካከል እንዳለ ወጣት እኔ ውስጥ ላለው ነገር ዋጋና ላቅ ያለ ግምት እንደሚሰጥም ይገባኛል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ማን መሆኑንና እንዴት እንደሚሠራ ካልተረዱ ወጣቶችም ሆኑ ሽማግሌዎች ብዙዎች ይህን ርዕሰ ጉዳይ መንካት እንደማይፈልጉ እኔም ሆንኩ አባቴ በሚገባ እናውቃለን፡፡

ስለዚህ ምንም እንኳ ግር ቢለኝም፣ አባቴ ላቀረበው ጥያቄ እንዴት እምቢ ማለት እችላለሁ? እያቅማማሁ ተስማማሁ፡፡ ከዚያ በኋላ የሆነውን ሕይወት ለዋጭ ጉዞ ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በተመለከተ ስለ አያሌ አስደናቂ ነገሮች እግዚአብሔር ዐይኖቼን ሲከፍትልኝ፣ ከዚያ በፊት ጨርሶ በማላውቀው አዲስ ብርሃን ቅዱሳት መጻሕፍትን ማየት ጀመርኩ፡፡ ብዙም ሳልቆይ መንፈስ ቅዱስ፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም በተሳሳተ መንገድ የሚታይ አካል መሆኑን ተረዳሁ፡፡ እጅግ በጣም ብዙዎች ሲባል የሰሙትን ስምና ተግባር ይሰጡታል፤ በእውነተኛ ማንነቱ የምናውቀው ግን እጅግ በጣም ጥቂቶቻችን ነን፡፡

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንድትጓዙ በማድረግ፣ ለመንፈስ ቅዱስ ማንነት እንደ መግቢያ የሚሆናችሁን ሐሳብ ማመቻቸት ነው፡፡ አንዳንድ የዚህ መጽሐፍ ገጽታዎች ጠንከር

ያሉ ቢሆኑ እንኳ፣ ጊዜና ጉልበታችሁን ብታፈሱበት የማይቆጭ ጉዞ እንደሚሆንላችሁ ከወዲሁ አረጋግጥላችኋለሁ፡፡

ይህ መጽሐፍ እያነበባችሁ እያለ፣ ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራችሁ መንፈስ ቅዱስን ጠይቁት፡፡ ቃሉ ላይ ያልተመሠረተ ማንኛውንም ቀደም ሲል ይዛችሁት የነበረ እምነት ያስወግዳል፡፡ የአንድ ቤት እምነት ወይም እንቅስቃሴ «ንብረት» አለመሆኑን፣ በአንድ ትውልድ ወይም ዘመን ሊገደብ የማይቻል መሆኑንም ትገነዘባላችሁ፡፡ እርሱ የተላከው ኢየሱስን ለመግለጥና መላው የክርስቶስን አካል ኃይል ለማስታጠቅ ነው፡፡ ልባችንን መኖሪያው አድርጓል፤ ሕይወታችንን መልክና ቅርጽ እንደሚያስይዝም ቃል ገብቷል፡፡ እኛ ማድረግ ያለብን እንዲቆጣጠረን መፍቀድ ብቻ ነው፡፡

እርሱን የመሰለ ወዳጅና ረዳት የትም ማግኘት አይቻልም፡፡ በሕይወት በሚገጥማችሁ ውጣ ውረድም ሆነ ደስታ መንፈስ ቅዱስ ሁሌም በታማኝነት ከእናንተ ጋር ይሆናል፡፡ የእርሱ ናፍቆትና ደስታ በመሆናችሁ፣ እንደማይጥላችሁና እንደማይተዋችሁ ቃል ገብቷል፡፡ ከድንቆች ሁሉ የበለጠ ድንቅ የሆነው እርሱን ለማወቅ ተዘጋጁ!

—Addison Bevere, COO, Messenger International

ሁላችንም በእርሱ አማካይነት በአንዱ መንፈስ ወደ አብ መቅረብ እንችላለንና፡፡
(ኤፌሶን 2፥18)

# 1

# መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

*አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ **መንፈስ ቅዱስ** ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኃል፤ እኔ የነገርኳችሁንም ሁሉ ያሳስባችኃል፡፡*

- ዮሐንስ 14፥26

ቀን 1

ቀኑ የአዲስ ዓመት ዋዜማ ነበር፡፡ በውስጤ እንድጾምና እንድጸልይ በጣም እየተሰማኝ ነበር፡፡ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ መጽሐፎች የትኛውን ላንብብ?›› በማለት ጌታን ጠየቅሁ፡፡ ‹‹ሐዋርያት ሥራን›› የሚል መልስ በማግኘቴ በጣም ነበር የተገረምኩት፡፡

ለመሆኑ፣ የተገረምኩት ለምን ነበር? ምክንያቱም፣ ቀደም ሲል በነበረኝ የጾም ጊዜ፣ ‹‹የሐዋርያት ሥራን አንብብ›› የሚል ቀጥተኛ ምሪት ነበር ያገኘሁት፡፡ ባለፈው የጾም ጸሎት ጊዜዬ ከሐዋርያት ሥራ ያየሁት በሐዋርያው ጳውሎስ ሕይወት ተፈጥሮ የነበረውን የዓላማና የምሪት ግጭትና የዚያ ውጤት የሆነውን ከባድ ጊዜ ነበር፡፡ ምን ማለቴ እንደ ሆነ ልግለጽ፡፡

ለአሕዛብ ወንጌል እንዲሰብክ እግዚአብሔር ጳውሎስን መርጦት ነበር፡ ፡ ይህን አስመልክቶ፣ ‹‹እኔም ለዚህ ወንጌል ለአሕዛብ የምሥራች ነጋሪና ሐዋርያ፣ አስተማሪም ሆኜ ተሾምሁ›› ብሎ ነበር (2 ጢሞቴዎስ 1፥11)፡፡ ይህ በጣም ግልጥና ዓላማ ላይ ያነጣጠረ ምሪት ነበር፡፡ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ይህንን ተልዕኮውን ደጋግሞ ተናግሮታል፡፡ በመጀመሪያው ሐዋርያዊ ጉዞው ጅማሬ ላይ፣ ‹‹እኛም ወደ አሕዛብ ዞር ለማለት እንገደዳለን፤ ደግሞም ጌታ

እንዲህ ብሎ አዞናል፤ ድነትን እስከ ምድር ዳርቻ ታደርስ ዘንድ፣ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌሃለሁ›› (ሐዋርያት ሥራ 13÷46-47)፡፡ በሁለተኛውም ጉዞው፣ ‹‹ከእንግዲህ ወደ አሕዛብ እሄዳለሁ›› በማለት በግልጥ ተናግሮአል (ሐዋርያት ሥራ 18÷6)፡፡ ለሮም ሰዎችም፣ ‹‹የአሕዛብ ሐዋርያ እንደ መሆኔ መጠን አገልግሎቴን በትጋት እፈጽማለሁ›› በማለት ጽፎላቸዋል (11÷13)፡፡ ይህን አባባሉን በጽሑፎቹ ሁሉ ማየት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ፣ ወገኖቹ የሆኑት አይሁድ ድነትን ሲያገኙ ለማየት ከነበረው ፍላጐት የተነሣ፣ በሚሄድበት ከተማ ሁሉ ደጋግሞ ወደ ምኩራቦች ይሄድ ነበር፡፡ ወደ አሕዛብ ከመሄዱ በፊት ምንጊዜም ቢሆን ወደ አይሁድ ነበር የሚሄደው፤ እንዲያውም ብዙ ጊዜ ወደ አሕዛብ ለመሄድ የሚገደደው አይሁድ የሚያቀርበውን መልእክት ችላ ሲሉበት ወይም ሲቃወሙት ነበር፡፡ ደጋግሞ እንደ ታየው የጳውሎስ ስደትና መከራ ምንጭ ራሳቸው አይሁዳውያን ነበሩ፡ ፡ ሕዝቡን እያነሳሡ በሐዋርያውና በአሕዛብ መሪዎች መካከል አለመግባባት ይፈጥሩ ነበር፡፡ ጳውሎስ ላይ ከደረሰው ከአብዛኛው ዐመፅ፣ እስራት፣ ድብደባና መከራ በስተ ጀርባ ይህንኑ ከፋፋይ ተንኰላቸውን ማየት ይቻላል፡፡ አንድ በጣም አስፈላጊ ማሳሰቢያ መናገር እፈልጋለሁ - እግዚአብሔር ለአይሁድ በጣም ያስባል፡፡ ያዕቆብን፣ ጴጥሮስንና ዮሐንስን የመሳሰሉ ሐዋርያት ወደ እነርሱ የተላኩት በዚህ ምክንያት ነበር፤ ‹‹እንደ አዕማድ የሚቆጠሩት ያዕቆብ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስም የተሰጠኝን ጸጋ ባስተዋሉ ጊዜ ለእኔና ለበርናባስ የትብብር ቀኝ እጃቸውን ሰጡን፤ ከዚያም እኛ ወደ አሕዛብ፣ እነርሱ ደግሞ ወደ አይሁድ እንዲሄዱ ተስማሙ›› (ገላትያ 2÷9)፡፡

መጀመሪያ በነበረኝ የጾም ጊዜ የተገለጠልኝ መልእክት በጣም ግልጥ ነበር፡፡ ‹‹ልጄ፣ እኔ በጠራሁህ ጸጋ ውስጥ ተመላለስ፡፡ የገዛ ራስህ ተቆርቋሪነት ወይም ፍቅር በሕይወትህ ካለው መለኮታዊ ተልዕኮ እንዲያዘናጋህ አትፍቀድ›› የሚል ነበር መልእክቱ፡፡ እንግዲህ ይህን የመሰለ ግልጥ መልእክት ከእግዚአብሔር መስማቴን ሳስታውስ፣ ይህንኑ የሐዋርያት ሥራን በድጋሚ እንዳነብ እግዚአብሔር ለእኔ መናገሩ ነበር በጣም ያስገረመኝ፡፡ በዚያ ላይ ደግሞ እንደ አማራጭ ሌሎች ስድሳ አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት መኖራቸው ግልጥ ነው!

ሆኖም፣ መታዘዜ በጣም ደስ ይለኛል፤ በዚህ ጊዜ የሐዋርያት ሥራን ሳነብ፣ ፍጹም የተለየ ነገርን ማየት ቻልኩ (ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል

በእርግጥ ሕያው መሆኑ ነበር)፡፡ በዚህ ጊዜ ከእያንዳንዱ ገጽ ማየት የቻልኩት የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባሎች ምን ያህል መንፈስ ቅዱስን ይፈልጉ፣ በእርሱ ይታመኑ፣ ስለ እርሱ ይናገሩ እንደ ነበር ነው፡፡ በሕይወታቸው ሁነኛ ቦታ ነበረው፣ በሚያደርጉት ማንኛውም ነገር እርሱ ተሳትፎ ነበረው፡፡ አገልግሎታቸውን በማስፋት፣ ለአገልግሎት አስፈላጊ ሰዎችን በመምረጥ፣ ዕቅድ በማውጣት፣ እና በእንቅስቃሴያቸው ሁሉ፣ ትልቁ ድርሻ የእርሱ ነበር፡፡ ቀጥሎ ያሉት ለማሳየነት ከሐዋርያት ሥራ የተወሰዱ ናቸው፡፡

- ‹‹ሐናንያ ሆይ፣ መንፈስ ቅዱስን ትዋሽና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን ልብህን ለምን ሞላው?›› (ሐሥ 5፥3)፡፡
- ‹‹የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ ዘንድ እንዴት እንዲህ ተስማማችሁ?›› (ሐሥ 5፥9)፡፡
- ‹‹እኛም ለእነዚህ ነገሮች ምስክር ነን፤ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው›› (ሐሥ. 5፥32)፡፡
- ‹‹እናንተ መንፈስ ቅዱስን ሁልጊዜ ትቃወማላችሁ›› (ሐሥ 7፥51)፡፡
- ‹‹መንፈስ ቅዱስም ምንም ሳላወላውል ከእነርሱ ጋር እንድሄድ ነገረኝ›› (ሐሥ 11፥12)፡፡
- ‹‹ከእነርሱም አንዱ… ታላቅ ራብ እንደሚሆን መንፈስ ቅዱስ አስመልክቶት ተናገረ…›› (ሐሥ 11፥28)፡፡
- ‹‹በርናባስና ሳውልም በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ›› (ሐሥ 13፥4)፡፡
- ‹‹ለመንፈስ ቅዱስም ለእኛም መልካም መስሎ ታይቶናል›› (ሐሥ 15፥28)፡፡
- ‹‹ቃሉን በእስያ እንዳይሰብኩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው…›› (ሐሥ 16፥6)፡፡
- ‹‹ወደ ቢታንያ ሊገቡ ሞከሩ፤ ነገር ግን መንፈስ አልፈቀደላቸውም›› (ሐሥ 16፥7)፡፡
- ‹‹ጳውሎም፣ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን በመንፈስ ቅዱስ ለአይሁድ ይመሰክር ነበር›› (ሐሥ 18፥5)፡፡
- ‹‹ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? አላቸው›› (ሐሥ 19፥2)፡፡

- ‹‹ጳውሎስ… ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ በመንፈሱ ወስኖ›› (ሐሥ 19፥21)፡፡
- ‹‹በምሄድባቸው ከተሞች ሁሉ መንፈስ ቅዱስ… ይመሰክርልኛል›› (ሐሥ 20፥23)፡፡
- ‹‹ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ጠባቂ አድርጎ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ›› (ሐሥ 20፥28)፡፡

እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ብዙ ጥቅሶችን ማግኘት ቻልኩ፡፡ በጣም ግልጽ የሆነው አሳዛኙ እውነት፣ በዚህ ዘመን በየቤተ ክርስቲያኖቻችን ይህን የመሰለ አሠራር አለማየታችን ነው፡፡ ሐዋርያት ሥራ ውስጥ ላሉ አማኞች የዕለት ተዕለት ጉዳይ የሆነው ነገር፣ አሁን ግን እጅግ ሲበዛ ብርቅ ሆኖአል፡፡ ይህን ስል በሌሎች ሕይወት ስላለው ጉድለት ሳይሆን፣ በመጀመሪያና በተቀዳሚ ደረጃ በእኔ በራሴ ሕይወት ስላለው ጉድለት መናገሬ ነው፡፡ እያነበብኩ እያለ ከእርሱ ጋር ጊዜ ከማሳለፍ፣ እርሱን ከመፈለግ፣ በእርሱ መሪነት ከመደገፍ፣ ለእርሱ ከመታዘዝ ከእርሱ ጋር ተገቢ ኅብረት ከማድረግና ብርቱ ከሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ መነካት በጣም የራቅሁ መሆኔን ተረዳሁ፡፡ ታዲያ፣ ይህ ለእኔ ግልጽ ከሆነልኝ ያንን ለእናንተ ከማካፈል እንዴት ወደ ኋላ ማለት እችላለሁ?

## ግንባር ቀደም ቃሎች

ወደዚህ በጣም ጠቃሚ ርዕሰ ጉዳይ የበለጠ እየገባን ስንሄድ፣ በጣም ግልጽ እየሆኑ ስለሚመጡ ግንባር ቀደም ቃሎች ጥቂት ገለጻ እንዳደርግ ፍቀዱልኝ፡፡

በመጀመሪያ፣ ያለ መንፈስ ቅዱስ ምንም ዐይነት የክርስትና ሕይወት የለም፡፡

- ያለ መንፈስ ቅዱስ፣ የክርስትና ሕይወት፣ ደረቅ፣ አታካችና አሰልቺ ነው፡፡
- ያለ መንፈስ ቅዱስ ሥራችን፣ አድካሚና ፍሬ ቢስ ነው፡፡
- ያለ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የለም፡፡

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ተገቢ ቦታውን ካልያዘ ከሁለት ነገሮች አንዱ ይሆናል፡፡

- ቤተ ክርስቲያን ማኅበራዊ ክለብ ትሆናለች፡፡
- ወይም ተራ ሃይማኖታዊ ተቋም ትሆናለች፡፡

እውነቱ ግን…

- ያለ መንፈስ ቅዱስ መገለጥ የለም፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ ቅዱሳት መጻሕፍት ሕይወት ሰጪ አይሆኑም፤ ምክንያቱም፣ «ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል» ተብለናል (2 ቆሮንቶስ 3፥6)፡፡
- ያለ መንፈስ ቅዱስ ራእይ የለም፡፡
- ያለ እርሱ ደስታ የለም፡፡
- ያለ እርሱ ሰላም የለም፡፡
- ያለ መንፈስ ቅዱስ ነጻነት የለም፡፡

ጌታ መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ (2 ቆሮንቶስ 3፥17)፡፡

«የጌታም መንፈስ ባለበት…» የሚሉትን ቃሎች ተመልከቱ፡፡ እስቲ ስለዚህ ጉዳይ እናስብ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ አጽናፈ ዓለሙን ሁሉ የሞላ ነው፤ እርሱ ሁልጊዜ ሁሉም ቦታ ነው፡፡ ዳዊት፣ «ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?» ብሏል (መዝሙር 139፥7)፡፡ መልሱ አንድና አንድ ብቻ ነው - የትም! ዳዊት በመቀጠል፣ «ወደ ሰማይ ብወጣ አንተ በዚያ አለህ፤ መኝታዬንም በሲኦል ባደርግ በዚያ ትገኛለህ፡፡ በንጋት ክንፍ ተነሥቼ ብበር፣ እስከ ባሕሩ ዳርቻ መጨረሻ ብሄድ፣ በዚያም ቢሆን፣ እጅህ ትመራኛለች፤ ቀኝ እጅህም አጥብቃ ትይዘኛለች» ይላል (መዝሙር 139፥8-10)፡፡ እጅግ ሲበዛ ግልጽ ነው፡፡ እርሱ ሁሌም ሁሉ ቦታ ነው!

ቀጥሎ ማቅረብ ያለብን ጥያቄ፣ «ታዲያ፣ ሁሉም ቦታ ነጻነት አለ ማለት ነው?» የሚል ነው፡፡ የጳውሎስን ቃል ልብ አድርጉ፤ «የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ፡፡» እርሱ ሁሉም ቦታ መሆኑን ተመልክተናል፤ ታዲያ፣ በእውነት ሁሉም ቦታ ነጻነት አለ? በማለት በድጋሚ ብንጠይቅ መልሱ፤ በፍጹም የለም የሚል ነው የሚሆነው፡፡ መዝናኛ ቦታ ነጻነት የለም፤

መጠጥ ቤቶች ውስጥ ነጻነት የለም፤ ሆስፒታሎች ውስጥ ነጻነት የለም፡ ፡ ምንም ነጻነት በሌለባቸው፣ ሰፈሮች፣ ትምህርት ቤቶች፣ መኖርያ ቤቶች እንዲያውም ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ እንኳ ተገኝቼ አውቃለሁ፡፡ እንዲህ ከሆነ፣ ከላይ የተመለከትነው ቃል ምንድነው የሚለው? የሚከተለው ትርጉም የበለጠ ትክክል ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ፡፡

መንፈስ ጌታ በሆነበት ቦታ ሁሉ፣ በዚያ ነጻነት አለ፡፡
(2 ቆሮንቶስ 3፥17 ደራሲው የሰጠው ፍቺ)

እዚህ ላይ ጌታ የሚለው ቃል ኪይሪዮስ (Kyrios) ነው፡፡ ‹‹በሥልጣኑ የላቀ››[1] ተብሎ መተርጐም ይችላል፡፡ አብዛኞቹ መዝናኛ ቦታዎች፣ መጠጥ ቤቶች፣ እስር ቤቶች፣ ሆስፒታሎች ወይም መኖሪያ ቤቶች፣ እንዲያውም ቤተ ክርስቲያኖች እንኳ መንፈስ ቅዱስ ባለ ሥልጣን እንዲሆናቸው ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ ነጻነትና ለሁሉም የሚሆን ፍትሕ የሚኖረው እርሱን በላቀ ሥልጣኑ በሚቀበሉት ቦታ ነው፡፡

## የዚህ መልእክት ዓላማ

የዚህ መልእክት ዓላማ እናንተን ከመንፈስ ቅዱስ ማንነት ጋር ማስተዋወቅ ነው፡፡ እርሱን በተመለከተ ብዙ ቅጽ መጽሐፎች ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ስለ እርሱ ለመናገር ቀኖች፣ ወሮች፣ ሌላው ቀርቶ ብዙ ዓመቶች እንኳ አይበቁም፡፡

እኔና ሊዛ ከተጋባን ከሰላሣ ዓመት በላይ ሆኖናል፡፡ ከማንም የበለጠ አውቃታለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ አሁንም ቢሆን ስለ እርሷ ሰብዕና፣ ደስ ስለሚያሰኛት ነገር፣ ስለ ፍላጐቷና አኳኋንዋ ብዙ ያላወቅኋቸው ነገሮች አሉ፡ ፡ በቅርቡ ሰላሣኛ የትዳር በዓላችንን ለማክበር ያህል ብቻችንን ሆነን ጥቂት ቀኖች አሳልፈን ነበር፡፡ በእነዚያ ቀኖች ስላሉዋት ሕልሞች፣ ስለ ምርጫዎቿ እንዲሁም ስላሉዋት ችሎታዎች ከዚያ በፊት የማላውቃቸው ብዙ ነገሮች ማወቅ ችያለሁ፡፡

በጐልፍ ጨዋታ ሊዛ ምን ያህል ተፈጥሮአዊ ችሎታዎችን የታደለች

መሆንዋን የተረዳሁት አሁን በቅርቡ ነበር። ያም ሆኖ፣ የበለጠውን ጊዜ ብቻችንን ማሳለፍ ስለ ነበረብን ደጋግመን ጐልፍ አልተጫወትንም።

በእያንዳንዱ ምሽት ራት እየበላን እያለ፣ ከዚያ በፊት አካፍላኝ ያልነበረ ጥበብ፣ ዕውቀት፣ ደስ የሚያሰኛትንና በጣም የምትጓጓለትን ነገር በተመለከተ ታጫውተኝ ነበር። በአጭር አነጋገር ጨርሶ ይኖራል ብዬ ያልጠበቅሁት ጥልቀትና ስፋት እዚህች ሚስቴ የሆነችው ሴት ውስጥ መኖሩ በጣም አስገርሞኝ ነበር።

የሊዛን ጥበብና ዕውቀት በጥቂት ገጾች ዘርዝሮ መጨረስ በፍጹም የማይቻል ነው። ምናልባትም ጥቂት መጻሕፍት እንኳ ላይበቁ ይችላሉ፡ ፡ ይሁን እንጂ፣ እኔ ማድረግ የምችለው እንዴት እርሷን ማግኘትና ከእርሷ ጋር መነጋገር እንደምትችሉ ለእናንተ መናገር ነው። በመጠኑም ቢሆን ደስ ስለሚያሰኛት ነገር፣ ስለ ፍላጐትዋና እንዴት ከእርሷ ጋር አብሮ መሥራት እንደሚቻል መናገር እችላለሁ። ጠንካራና ደካማ ጐኗን፣ የምትወደውንና የምትጠላውን ነገር በተመለከተ መናገር እችላለሁ። ስለ እርሷ የምነግራችሁ በጣም ጥቂት ቢሆንም፣ የበለጠ እርሷን ለመቅረብ የሚስችላችሁ መንደርደሪያ ሊሆናችሁ ይችላል።

እንግዲህ ጥቂት ዐሥር ዓመታት ዕድሜ ያላት የእኔን ሚስት በተመለከተ ሁሉንም መናገር እንደማልችል ግልጽ ከሆነ፣ ዘላለማዊውን መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ እንዴት ሁሉንም መናገር እችላለሁ? በፍጹም አልችልም! እኔ ማድረግ የምችለው ስለ እርሱ ማንነት በጣም በጥቂቱ መናገር ብቻ ነው። ስለ ሰብዕናው፣ ደስ ስለሚያሰኘውና ስለሚወደው ነገር ከቅዱሳት መጻሕፍት በጣም በጥቂቱ የተረዳሁትን ማካፈል ብቻ ነው። ከእርሱ ጋር ሊኖረን ስለሚችል መቀራረብና እንዴት ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ እንደሚቻል በትንሹ መናገር እችላለሁ። ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መቀራረብ በጣም አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ መሆኑንና እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን ፈቃድ በመፈጸም ረገድ፣ እንዴት ኃይል ሊሰጠን እንደሚችል መናገር እችላለሁ። እነዚህ መሠረታዊ ግንዛቤዎች፣ በጥልቀትና ትርጉም ባለው መልኩ ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ እንድትችሉ እናንተን ያነሳሡዋችኋል።

ቀን 2

## ትልቅ ስሕተት

መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ብዙዎች የሚሳሳቱት፣ በመጀመሪያ ደረጃ፣ እርሱን እንደ አንድ አካል ሳያውቁ ስለ አሠራሩና ስለ ኀይሉ ለማወቅ መሞከራቸው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ አካል መሆኑን - እርሱ ቅዱስ፣ ዘላለማዊ ጠቢብ፣ ዘላለማዊ ኃያል፣ ያም ሆኖ ግን፣ እጅግ ሲበዛ ርኅሩኅና የእኛ ነገር በቀላሉ የሚገባው መሆኑን፣ በልባችንና በአእምሮአችን ማመን በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ እርሱ የእኛ አክብሮት፣ ፍቅር፣ መገዛት የሚገባው መሆኑን፣ እምነታችን ልንጥልበትና ሙሉ በሙሉ ልንደገፍበት የሚገባው መሆኑን እናምናለን? ወይስ መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የሚሠርጽ አንድ ዐይነት ተፅዕኖ ፈጣሪ ነገር ወይም ከግንዛቤ በላይ የሆነ አንድ ዐይነት ኃይል መሆኑን ነው የምናምነው? በተለምዶ አነጋገር፣ ‹‹የልግሥና መንፈስ›› ወይም፣ ‹‹የፉክክር መንፈስ›› እንላለን፤ እርሱን በተመለከተ ያለንስ አመለካከት ከዚህ ምን ያህል የተለየ ይሆን?

ሁለተኛው የተሳሳተ አመለካከት እጅግ ጠባብ፣ ጥሬ፣ እንዲያውም መናፍቃዊ ነው፡፡ እንደዚያ የምናስብ ከሆነ፣ ለትዕቢትና ዕብሪት ያጋልጠናል፤ ያ ደግሞ ሌሎች ወዳልደረሱበት የክርስትና ከፍታ ደርሰናል ብለን እንድናስብ ሊያደርገን ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ፣ እርሱ ባለ ዘላለማዊ ግርማ፣ ክብር፣ ውበት፣ ጥበብ፣ ዕውቀትና ቅድስና መሆኑን ካመንን፣ እንደ የሥላሴ አካልነቱ ከአብና ከወልድ ጋር ሕይወታችንን የመግዛት ሥልጣን እንዳለውና ከዚያም የተነሣ ሕይወታችንን ማስተካከል እንደሚችል ካመንን፣ በቅዱስ አክብሮት በፊቱ እንሰግዳለን፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስ አንድ ዐይነት ተፅዕኖ ወይም በጣም የላቀ ኃይል እንደ ሆነ የሚያምን ሰው፣ ‹‹በብዛት መንፈስ እፈልጋሁ›› ይላል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ እርሱ አካል መሆኑን፣ የራሱ ሰብዕና ያለው መሆኑን የሚያምን ሰው፣ ‹‹ለእርሱ ሁለንተናዬን እንዴት መስጠት እችላለሁ?››[2] ይላል፡፡

## ስለ እርሱ ያለን አመለካከት

የእግዚአብሔርን መንፈስ በተመለከተ እንደ አካል ሳይሆን፣ አንድ ዐይነት ተፅዕኖ ወይም ኃይል እንደ ሆነ ብዙዎች የሚያስቡት ስለ እርሱ ሲነገር ከመስማት የተነሣ ነው፡፡ በጣም የሚያሳዝነው፣ እርሱን እንደ አካል ለማክበር ፈቃደኞች ባለ መሆናችን፣ የእርሱ ሓልዎት ወይም መገኘት ብዙዎቻችንን የሚያመልጠን መሆኑ ነው፡፡ ለእርሱ የሚገባው አክብሮት በሌለበት ቦታ የእግዚአብሔር መንፈስ አይገለጥም (ማቴዎስ 13÷54-58፤ መዝሙር 89÷7)፡ ፡

መንፈስ ቅዱስ አካል ነው ስል፣ እርሱ፣ ‹‹ሰብዓዊ ፍጡር›› ነው ማለቴ እንዳይደለ ማሳሰብ እፈልጋለሁ፡፡ በቀላል አነጋገር እርሱ የራሱ ሰብዕና ባሕርያት አሉት ማለቴ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር እንጂ፣ ሰብዓዊ ፍጡር አይደለም፡፡ ሰዎች ግን በእግዚአብሔር መልክና አምሳል መፈጠራቸውን ማስታወስ አለብን፡፡ ስለ ሆነም፣ እርሱ እንደ እኛ ሳይሆን፣ ከፈቃዱና ከሐሳቡ ጋር በመስማማት እኛ እንደ እርሱ መሆን አለብን፡፡

እንደ ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ፣ እጅግ ቅዱስ መሆኑን ሳይሆን፣ እርሱ አንድ ዐይነት ‹‹ቅዱስ ነገር›› እንደ ሆነ ማሰብ መርጠናል፡፡ እርሱ የቅርብ ወዳጃችን መሆን ይፈልጋል፤ ያም ሆኖ እኛ፣ በሕይወታችን ሊኖረው የሚገባውን ተሳትፎ ገድበነዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ ከማንኛውም ግንኙነት ይበልጥ ከእርሱ ጋር ሊኖረን የሚገባውን የተሟላ ግንኙነት ችላ ብለናል፤ ይህ አሳዛኝ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ ሰብዕና ያለው አካል መሆኑን የሚያመለክቱ ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንመልከት፡፡

- እርሱ አእምሮ አለው - ያውቃል (ሮሜ 8÷27 ይመ)፡፡
- እርሱ ፈቃድ አለው (1 ቆሮንቶስ 12÷11 ይመ)፡፡
- እርሱ ስሜት አለው - ፍቅርና ደስታን የመሳሰሉ (ሮሜ. 15÷30፤ ገላትያ 5÷22 ይመ)
- እርሱ ያጽናናል (ሐዋርያት ሥራ 9÷31 ይመ)፡፡
- እርሱ ይናገራል (ዕብራውያን 3÷7)፤ እንዲያውም በግልጽ ይናገራል (1 ጢሞቴዎስ 4÷1 ይመ)

- እርሱ ያስተምራል (1 ቆሮንቶስ 2፥13 ይመ)።
- ልናሳዝነው እንችላለን (ኤፌሶን 4፥30 ይመ)።
- ልንሰድበው እንችላለን (ዕብራውያን 10፥29 ይመ)።
- ልንቃወመው እንችላለን (ሐዋርያት ሥራ 7፥51 ይመ)።
- ሰዎች ዋሽተውታል (ሐዋርያት ሥራ 5፥1-11 ይመ)።

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነዚህ ባሕርያቱ መናገሩ ግልጽ ከሆነ፣ ታዲያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ የተረዱት ለምንድነው? በማለት መጠየቅ ይኖርብናል።

## ርግብ

ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲያስቡ ብዙዎች ወዲያውኑ ወደ አእምሮአቸው የሚመጣው ከርግብ ጋር የተያያዘ ምስል ነው። እንዲህ ያለው ሐሳብ በመጀመሪያ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው ለምንድነው? ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ ርግብ ሆኖ ታይቶ ያውቃል? መልሱ፣ በፍጹም ታይቶ አያውቅም ነው። ከአራቱም ወንጌሎች እንደምንመለከተው መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ኢየሱስ ላይ ወርዶ ነበር (ማቴዎስ 3፥16፤ ማርቆስ 1፥10፤ ሉቃስ 3፥22፤ ዮሐንስ 1፥32 ይመ)። ታዲያ፣ ማንኛችንም ብንሆን፣ ‹‹እንደ ነፋስ ትሮጣለች›› ወይም፣ ‹‹ጉልበቱ እንደ በሬ ጉልበት ነው›› እንል የለ? ታዲያ እንዲህ ስንል፣ እርሷ ነፋስ ናት ወይም እርሱ በሬ ነው ማለት ነው? በፍጹም አይደለም! በተመሳሳይ መንገድ፣ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ላይ እንደ ርግብ ወረደ ማለት እርሱ ርግብ ነው ማለት አይደለም።

ምናልባትም፣ ‹‹ግን'ኮ እርሱ በዙፋኑ ፊት በሚያበራ መብራት ተመስሎ ተገልጧል›› የሚል ይኖር ይሆናል (ራእይ 4፥5)። አዎን፣ እንደዚያ ይላል፤ ግን'ኮ ይኸው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹…በሽማግሌዎቹም መካከል የታረደ የሚመስል በግ ቆሞ አየሁ›› ይላል (ራእይ 5፥6)። ዮሐንስ ኢየሱስን በዚህ መልኩ ገልጦታል። መቼም ኢየሱስ አራት እግር ያለው እንስሳ እንዳይደለ እኔና እናንተ በሚገባ እናውቃለን። ስለሆነም፣ መንፈስ ቅዱስ፣ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት እያበራ ያለ አንድ ዐይነት እንግዳ እሳት አይደለም።

## ታዲያ፣ መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

መንፈስ ቅዱስ ሦስተኛው የሥላሴ አካል መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ግልጥ አድርጓል፡፡ ዘፍጥረት 1፥26፣ ‹‹እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን በአምሳላችን እንሥራ አለ›› ይላል፡፡ ‹‹ሰውን በመልኬ፣ በአምሳሌ ልሥራ›› አለማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ ፍጥረትን ወደ ሕልውና የማምጣቱ ሥራ የሦስት የተለያዩ አካሎችን የተለያየ ተሳትፎ አስፈልጓል፡፡ እግዚአብሔር ራሱን እንደ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ገልጧል፡፡

የአብን፣ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን የተለየ መገለጫ ለማየት እስቲ ሐዋርያት ሥራ 10፥38 እንመልከት፡፡

> እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በኃይል ቀባው፤ እርሱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለ ነበረ በደረሰበት ሁሉ መልካም እያደረገ በዲያብሎስ ሥልጣን ሥር የነበሩትን ሁሉ ፈወሰ፡፡

እዚህ ላይ እግዚአብሔር አብ ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ እንደ ቀባው እናያለን - ሦስት የተለያዩ አካላት ለአንድ ዓላማ በአንድነት ሠሩ፡፡

እስቲ፣ ሌላም ምሳሌ እንይ፣

> ኢየሱስም እንደ ተጠመቀ ከውሃው ወጣ፤ ወዲያውኑ ሰማይ ተከፍቶ የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድበት አየ፡፡ እነሆ ‹‹በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው›› የሚል ድምፅ ከሰማይ ተሰማ፡፡
>
> (ማቴዎስ 3፥16-17)

ስለ ኢየሱስ መጠመቅ ከሚናገረው ከዚህ ክፍል ሦስቱ የሥላሴ አካላት መገለጣቸውን ልብ አድርጉ፡፡ በመጀመሪያ ኢየሱስ በዮሐንስ ተጠመቀ፤ ከዚያ መንፈስ ቅዱስ እርሱ ላይ ወረደ፤ በመጨረሻም፣ ‹‹በእርሱ ደስ የሚለኝ

የምወደው ልጄ ይህ ነው›› በማለት እግዚአብሔር አብ ከሰማይ ተናገረ፡፡ እዚህም ላይ ለአንድ ዓላማ ሦስቱም አካላት በአንድነት ሠሩ፡፡

ይህን እውነት ለመረዳት እንዲያግዘን አንድ መሠረታዊ ምሳሌ ላቅርብ፡፡ ውሃ (H2O) በሦስት የተለያየ መልክ ሊገለጥ ይችላል፡፡ እንደ የአየር ሁኔታው H2O ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዝ መልክ ሊይዝ ይችላል፡፡ እንዲህም ሲሆን የውሃው ይዘት ቅንጣት ታህል ለውጥ አያደርግም፤ ግን እንደ አየሩ ሁኔታ የሚገለጥበት መንገድ ይለያያል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ በተለያየ መልኩ ቢገለጥም፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ማንነትና ባሕርይ ፍጹም አይለወጥም፡፡ ወልድን ስታዩ፣ አብን ማየታችሁ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ወልድን ለእኛ እንዲገልጥልን ተላከ፡፡ (ዮሐንስ 17፥21፤ ኤፌሶን 1፥17-18 ይመ.)፡፡ እግዚአብሔር በዓላማው አንድ ነው፤ ያም ሆኖ፣ ራሱን በሦስት አካላት ገልጧል፤ ሦስቱም ራሱን የቻለ ሥራ አላቸው፡፡ ሦስት አካላት ቢኖሩም፣ አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ፡፡ ዘዳግም 6፥4፣ ‹‹እስራኤል ሆይ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው›› ይላል፡፡ ሮሜ 3፥30፣ ‹‹የሚያጸድቅ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነውና›› ይላል፡፡ እንዲሁም ያዕቆብ 2፥19፣ ‹‹አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ታምናለህ፤ መልካም ነው›› ይላል፡፡ ይህ እውነት የተቀረው የመጽሐፉ አካል ሁሉ ማእዘን ድንጋይ ነው፤ ሦስት የተለያዩ አካላት፣ ነገር ግን አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ፡፡

ቀን 3

## የመጀመሪያው አካል

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠው የመጀመሪያው የመለኮት አካል መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ፣ ‹‹በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ›› በማለት ይጀምራል (ቁጥር 1)፡፡ ቁጥር ሁለትን ስናነብ፣ ‹‹ምድርም ቅርጽ የለሽና ባዶ ነበረች፤ የምድርን ጥልቅ ስፍራ ሁሉ ጨለማ ውጦት ነበር፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሆች ላይ ይረብብ ነበር›› የሚል እናገኛለን፡፡ እርሱ በመደበኛ ስሙ የተጠራ የመጀመሪያ የሥላሴ አካል ነው ማለት ይቻላል፡፡

ምናልባትም፣ ይህ ጥቅስ'ኮ፣ ‹‹በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትና ምድርን

ፈጠረ›› ነው የሚለው፤ ታዲያ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በመጀመሪያ የተጠቀሰ የሥላሴ አካል መንፈስ ቅዱስ ነው ማለት እንዴት ይቻላል?›› የሚል ጥያቄ ይነሣ ይሆናል። ጥሩ ጥያቄ ነው፤ ግን፣ እግዚአብሔር፣ ‹‹ሰውን እንደ መልካችንና አምሳላችን እንፍጠር›› ማለቱን አስታውሱ። ቁጥር አንድ ላይ ያለው የሚያመለክተው የሥላሴ አካላትን ሁሉ እንጂ፣ አንዱን አካል ብቻ አይደለም። ስለሆነም፣ በተግባሩ መጀመሪያ የተጠቀሰ የሥላሴ አካል መንፈስ ቅዱስ ነው ቢባል ያስኬዳል። ቁጥር ሁለት ላይ፣ ‹‹የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሆች ላይ ይረብብ ነበር›› የሚል እናነባለን።

እስቲ፣ ወደ መጀመሪው ጥያቄ እንመለስ፣ ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? እርሱ በዚህ ምድር እጅግ ድንቅ፣ ግሩም፣ አዛኝ፣ በቀላሉ የሚሰማውና እጅግ ኃያል አካል ነው። ምናልባትም፣ ‹‹በዚህ ምድር›› መባሉ ቅር አሰኝቷችሁ ይሆናል። ግን እውነት ነው። መረዳት ያለብን እግዚአብሔር አብ በዚህ ምድር አለመሆኑን ነው፤ እርሱ በሰማይ ዙፋኑ ላይ ነው። ኢየሱስም ቢሆን በዚህ ምድር አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በሰማይ በእግዚአብሔር ቀኝ መቀመጡን ነው የሚነግረን (ማርቆስ 16፥19 ይመ)። ሐዋርያት ሥራ 1፥9-11 ላይ፣

> ይህን ካለ በኋላ እያዩት (ደቀ መዛሙርቱ) ወደ ላይ ዐረገ፤ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረችው። እርሱም በሚሄድበት ጊዜ ትኩር ብለው ወደ ሰማይ ሲመለከቱ፣ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ድንገት አጠገባቸው ቆሙ፤ እንዲህም አሏቸው፤ ‹‹እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ፣ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ እዚህ የቆማችሁት ለምንድን ነው? ይህ ከእናንተ ዘንድ ወደ ሰማይ ሲያርግ ያያችሁት ኢየሱስ፣ ልክ ወደ ሰማይ ሲወጣ እንዳያችሁት በዚሁ ሁኔታ ይመለሳል›› የሚል እናነባለን።

ምናልባት መላእክት ሊሆኑ የሚችሉ እነዚህ ሁለት ሰዎች፣ ኢየሱስ በሄደበት ሁኔታ እንደሚመለስ ግልጽ አድርገዋል። በደመና ታጅቦ እንደ ሄደ በደመና ታጅቦ ይመለሳል ማለት ነው። ታዲያ፣ እስከ ዛሬ ድረስ ኢየሱስ

በደመና ታጅቦ ተመልሷል? መልሱ፣ አልተመለሰም ነው፡፡ ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ ኢየሱስ በሰማይ በእግዚአብሔር ቀኝ ነው ማለት ነው፡፡

እስጢፋኖስ በድንጋይ ተቀጥቀጦ ሲገደል የሆነውን አስቡ፡፡ ሐዋርያት ሥራ 7፥55-56 ላይ፣ ‹‹እስጢፋኖስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት፣ የእግዚአብሔርን ክብር፣ እንዲሁም ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፣ ‹‹እነሆ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ! አለ›› የሚል እናነባለን፡፡ ይህም ቢሆን የሚያመለክው አሁን ኢየሱስ በአባቱ ጐን መሆኑን ነው፡፡

ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት ኢየሱስ በዚህ ሁኔታ ነው ያለው፡፡ እርሱ በዚህ ምድር አይደለም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ልባቸው ውስጥ እንደሚኖር ይናገራሉ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ልባችንን መኖሪያው ያደረገ መንፈስ ቅዱስ ማለትም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስና የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ተብሎ መጠራቱን ማስተዋል በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ጥቂት ምሳሌዎች እንይ፣

ፊልጵስዩስ 1፥19 ላይ ጳውሎስ፣ ‹‹በእኔ ላይ የደረሰው ነገር፣ በጸሎታችሁ አማካይነትና ከኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ በተሰጠኝ ረድኤት ለመዳኔ እንደሚሆን ዐውቃለሁና›› ይላል፡፡ በእርሱ ቦታ ለመሆን መንፈስ ቅዱስ እንዲመጣ እርሱ መሄድ እንዳበት ኢየሱስ በጣም ግልጽ አድርጓል፡፡ እዚህ ላይ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው በአካል ተገልጦ ስለ ነበረው ኢየሱስ ሳይሆን፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ (ረዳት ስለ ሆነው) ነው፤ ምክንያቱም ኢየሱስ በዚህ ምድር አልነበረም፡፡

ማቴዎስ 10፥20 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹በእናንተ የሚናገረው የሰማዩ አባታችሁ መንፈስ እንጂ፣ እናንተ አይደላችሁምና›› ብሏል፡፡ ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ደቀ መዛሙርቱ በወንጌል ምክንያት የሚሰደዱበትና መከራ የሚቀበሉበት ጊዜ እንደሚመጣ ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ የእግዚአብሔር አብ መንፈስ፣ (መንፈስ ቅዱስ) መናገር ያለባቸውን ቃል አንደበታቸው ውስጥ ያደርጋል፡፡

አሁን እየጻፍኩ ያለሁት ቃሎች እንኳ የእኔ አእምሮ ወይም ልምምድ ውጤት አይደሉም፤ የአባቴ መንፈስ በእኔ ውስጥ አድሮ እያስተማረ ነው፡ ፡ በራሴ ብርታት ለማስተማር የሞከርኩበት ጊዜ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፤

ውጤቱ ግን አሳዛኝ ውድቀት ነበር፡፡ አሁን የሆንኩትን የሆንኩት በጸጋው ነው፤ መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠኝ ኃይል ነው፡፡ ለጸጋው መንፈስ ራሴን በትሕትና ሳስገዛ (ዕብራውያን 10፥29) ድካሜን ወደ ብርታት ይለውጣል፡፡

## ሦስቱ የሚሠሩት እንዴት ነው?

«ሦስት በአንድ» የተሰኘው አስተሳሰብ ከሰብዓዊ አእምሮ ችሎታ በላይ በመሆኑ መረዳት ይከብዳል፡፡ 1 ቆሮንቶስ 12፥5-7 ሦስቱ በአንድነት ስለሚሠሩበት ሁኔታ ጥቂት ግንዛቤ ይሰጣል፡፡

> አገልግሎትም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ጌታ ግን አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፣ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው፡፡ (1 ቆሮንቶስ 12፥5-7)

ይህን ክፍል ስናነብ፣ እግዚአብሔር አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተለያየ ድርሻ እንዳላቸው እንመለከታለን፡፡ አብ ይሠራል ወይም ይጀምራል (ቁ. 6) ወልድ ያስተዳድራል (ቁ. 5)፣ መንፈስ ቅዱስ ይገልጣል (ቁ. 7) ግን ሁሉም ለአንድ ዓላማ ይሠራሉ፡፡

እኔና እናንተ ቤት መሥራት ብንፈልግ ምንድነው የምናደርገው? ቤቱን የሚሠሩልን መሐንዲስ፣ ተቆጣጣሪና የተለያዩ ሠራተኞች ያስፈልጉናል፡፡ በዚህ ምሳሌ መሠረት እግዚአብሔር አብ መሐንዲስ ነው፤ ኢየሱስ ተቆጣጣሪ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ቤቱን በሚሠሩ ሠራተኞች ይመሰላል፡፡ እርሱ የፍጥረት «ገላጭ» ነው፡፡ ቤቱን በመሥራት ረገድ፣ የሦስቱም ድርሻ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## የእግዚአብሔር ጣት

እስቲ አሁን ደግሞ፣ በሁለት የተለያየ አቀራረብ የተነገረ አንድ ሁኔታ እንመልከት፡፡ ኢየሱስ አንድ አጋንንት የነበሩበትን ሰው ፈውሶ ነበር፡፡

ሕዝቡ በጣም ተደነቀ፤ ፈሪሳውያን ግን፣ ይህ ሰው አጋንንትን የሚያወጣው በአጋንንት አለቃ ስም ነው በማለት አሰቡ (ማቴዎስ 12፥23-24 ይመ)፡፡ ቁጥር 28 ላይ ደግሞ፣ ‹‹ነገር ግን እኔ አጋንንትን የማስወጣው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀርባለች›› በማለት ኢየሱስ መልስ መስጠቱን እናነባለን፡፡

ሉቃስም እንዲሁ ይህንኑ ታሪክ ቢያቀርብም፣ አቀራረቡ ከማቴዎስ በመጠኑ ይለያል፡፡ ሉቃስ 11፥20፣ ‹‹እኔ ግን አጋንንትን የማወጣው በእግዚአብሔር ጣት ከሆነ፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ እንደ መጣች ዕወቁ›› ይላል፡፡ ሉቃስም ሆነ ማቴዎስ የሚያመለክቱት መንፈስ ቅዱስን ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ጸሐፊዎች እንደሚያደርጉት ሉቃስ መንፈስ ቅዱስን ከማንነቱ በተለየ ሥራው ይገልጠዋል፡፡ ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ፣ ‹‹የእግዚአብሔር ጣት›› ነው የሚል መደምደሚያ ላይ መድረስ እንችላለን፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንደ የእግዚአብሔር ጣት ብቻ ሳይሆን፣ እንደ የእግዚአብሔር እጅ፣ እንደ የእግዚአብሔርም ክንድ ተመስሏል፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን፣ ‹‹በኃያል እጅና በተዘረጋች ክንድ›› እንዳዳነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (መዝሙር 136፥12)፡፡ መዝሙር 8፥3፣ ‹‹የጣቶችህን ሥራ ሰማያትን ስመለከት፣ በስፍራቸው ያኖርሃቸውን ጨረቃና ከዋክብትን ሳይ›› ይላል፡፡ ከዋክብትና ፕላኔቶችን በስፍራቸው ያደረገ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ብዙ አማኞች አያውቁም፤ ፍጥረቱን ሁሉ የሚገልጥ እርሱ ነው፡፡ ዘፍጥረት 1፥2፣ ‹‹የእግዚአብሔም መንፈስ በውሆች ላይ ይረብብ ነበር›› የሚል አንብበን እንደ ነበር አስታውሱ፡፡

የእግዚአብሔርን መንፈስ ታላቅነትና ክብር በተመለከተ በጣም ከምወዳቸው ምንባቦች አንዱ ኢሳይያስ 40፥12-15 ያለው ሲሆን፣ እንዲህ ይነበባል፣

> ውሆችን በዕፍኙ የሰፈረ፣ ሰማያትን በስንዝሩ የለካ፣ የምድርን ዐፈር በመስፈሪያ ሰብስቦ የያዘ፣ ተራሮችን በሚዛን፣ ኮረብቶችንም በመድሎት የመዘነ ማነው? የእግዚአብሔርን መንፈስ የተረዳ፣ አማካሪውስ ሆኖ ያስተማረው ማን ነው? ዕውቀትን ለማግኘት

እግዚአብሔር ማንን አማከረ? ትክክለኛውንስ መንገድ ማን አስተማረው? ዕውቀትን ያስተማረው፣ የማስተዋልንም መንገድ ያሳየው ማን ነው? እነሆ አሕዛብ በገንቦ ውስጥ እንዳለች ጠብታ ናቸው፤ በሚዛን ላይ እንዳለ ትብያ ይቈጠራሉ፤ ደሴቶችንም እንደ ደቃቅ ዐፈር ይመዝናቸዋል፡፡ (ኢሳይያስ 40፥12-15)

ቁጥር አሥራ ሁለት ላይ፣ ‹‹ሰማያትን በስንዝሩ (በጣቱ) የለካ ማነው?›› የሚል እናነባለን፡፡ ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ ማንነት በሥራው ተለይቶ እንደ ነበር መመልከት እንችላለን፡፡ እስቲ፣ ረጋ ብላችሁ አስቡ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ውቅያኖሶችን ሁሉ በእጁ ይዞአል፡፡ ምን ያህል ብርቱ እንደ ሆነ አያችሁ? ያም ሆኖ ግን፣ ከአብና ከወልድ ጋር በመስማማት ትሑት ሆኖ እኛ ውስጥ ለመኖር መጥቷል፡፡ ምንኛ አክብሮዊ ፍርሃት የሚቀሰቅስ ድንቅ ነው!

ቀን 4

## መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው

እስቲ አሁን ደግሞ ሰውን በመፍጠር ረገድ መንፈስ ቅዱስ ስለ ነበረው ድርሻ እንመልከት፡፡ ‹‹እግዚአብሔር አምላክ ከምድር ዐፈር ወስዶ ሰውን አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ›› (ዘፍጥረት 2፥7)፡፡ አዳምን ያበጀና በአፍንጫው ሕይወት የዘራ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ይህ እውነት መሆኑን የማውቀው እንዴት ነው? ኢዮብ 33፥4፣ ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጥሮኛል፤ ሁሉን የሚችለውም አምላክ እስትንፋስ ሕይወት ሰጥቶኛል›› ይላል፡፡ አዳምን ማበጀትና በአፍንጫው ሕይወት መዝራት ብቻ ሳይሆን፣ እኔና እናንተንም አበጅቶናል፤ ሕይወትንም ዘርቶብናል፡፡ መዝሙር 139፥13፣ ‹‹አንተ ውስጣዊ ሰውነቴን ፈጥረሃልና፤ በእናቴም ማሕፀን ውስጥ አበጃጅተህ ሠራኸኝ›› ይላል፡፡ የምናየው ነገር ሁሉ እውን የሆነው የአብን ፈቃድ ለመፈጸም መንፈስ ቅዱስ በመሥራቱና በመንቀሳቀሱ ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር መሆኑ ለእናንተ በጣም ግልጽ እንደ ሆነ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ አሁን ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ለእርሱ የተሰጡ የተለያዩ ስሞች እንመልከት፡፡ እርሱ፣

- መንፈስ ቅዱስ (96 ጊዜ)
- የጌታ መንፈስ (28 ጊዜ)
- የእግዚአብሔር መንፈስ (26 ጊዜ)
- የዘላለም መንፈስ (ዕብራውያን 9፥14)
- ረዳት (ዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ኢየሱስ አራት ጊዜ በዚህ ስም ጠርቶቷል)
- አጽናኝ
- ቅዱሱ (መዝሙር 78፥41)
- ጌታ (2 ቆሮንቶስ 3፥17)
- የእውነት መንፈስ (4 ጊዜ)
- የክርስቶስ መንፈስ (ሮሜ 8፥9፤ 1 ጴጥሮስ 1፥11)
- የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ (ፊልጵስዩስ 1፥19)
- የምክር መንፈስ (ኢሳይያስ 11፥2)
- የዕውቀት መንፈስ (ኢሳይያስ 11፥2)
- የኃይል መንፈስ (ኢሳይያስ 11፥2)
- የማስተዋል መንፈስ (ኢሳይያስ 11፥2)
- የጥበብ መንፈስ (ኢሳይያስ 11፥2)
- እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ (ኢሳይያስ 11፥2)
- የአባታችሁ መንፈስ (ማቴዎስ 10፥20)
- የክብር መንፈስ (1 ጴጥሮስ 4፥14)
- የሞገስ መንፈስ (ዘካርያስ 12፥10፤ ዕብራውያን 10፥29)
- የፍርድ መንፈስ (ኢሳይያስ 4፥4)
- የሚያቃጥል መንፈስ (ኢሳይያስ 4፥4)
- የሕይወት መንፈስ (ሮሜ 8፥2)
- የፍቅር መንፈስ (2 ጢሞቴዎስ 1፥7)
- የኃይል መንፈስ (2 ጢሞቴዎስ 1፥7)

- ራስን የመግዛት መንፈስ (2 ጢሞቴዎስ 1፥7)
- የትንቢት መንፈስ (ራእይ 19፥10)
- የመገለጥ መንፈስ (ኤፌሶን 1፥17)
- የቅድስና መንፈስ (ሮሜ 1፥4)
- የቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ (ዳንኤል ውስጥ 4 ጊዜ)

ይህ ሁሉ ለእርሱ ይገባዋል፤ እርሱ ኃያል ነው፤ እርሱ ከአእምሮ በላይ ነው!

## ኢየሱስ፣ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ተደግፎአል

ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ይደገፍ ነበር፡፡ በመንፈስ ተፀነሰ፤ ከመንፈስ ተማረ፤ በዮርዳኖስ ወንዝ በመንፈስ ኃይል ተሞላ፤ በመንፈስ እስከ ተጠመቀ ጊዜ ድረስ ምን ተአምር አላደረገም (በቃና ዘገሊላ ኢየሱስ ስለዳረገው ተአምር ዮሐንስ የሚናገረውን ተመልከቱ፤ ዮሐንስ 1፥29-34 እና 2፥1-11)፡፡ በመንፈስ ተመራ፤ የተናገረው መንፈስ ሲናገር የሰማውን ብቻ ነበር፡፡

ዮሐንስ 14፥10 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹የምነግራችሁ ቃል ከራሴ አይደለም፤ ነገር ግን ሥራውን የሚሠራው በእኔ፣ የሚኖረው አብ ነው›› ብሏል፡፡ ኢየሱስ ‹‹በሰማይ ያለው አባቴ›› ሳይሆን፣ ‹‹በእኔ የሚኖረው አብ›› ማለቱን ልብ አድርጉ፡፡

በኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ዘመን ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ ሁሌም አብረው ነበር የሚሠሩት፡፡ እንዲያውም፣ ኢየሱስ፣ ‹‹ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም›› ብሎ ነበር (ዮሐንስ 5፥19)፡፡ እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ ተልዕኮውን ለመፈጸም ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መሥራት ካስፈለገው፣ እኔና እናንተስ ተልዕኮአችንን ለመፈጸም ምን ያህል የመንፈስ ርዳታ ያሻን ይሆን?

ከኢየሱስ የበለጠ መንፈስ ቅዱስን የሚያውቅ ማንም የለም፤ ስለ ሆነም የመንፈስ ቅዱስን ድርሻ፣ ሰብዕና፣ ባሕርያት፣ ኃይልና በሕይወታችን የሚያስገኘውን ሌሎች ችሎታዎች በተመለከተ ኢየሱስ የተናገረውን እንመልከት፡፡ ዮሐንስ 14፥15-18 ላይ፣

ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ። እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል። እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፤ ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው አይችልም። እናንተ ግን አብሮአችሁ ስለሚኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን ታውቁታላችሁ። ወላጅ እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ ብሎ ነበር።

እዚህ ምንባብ ውስጥ ብዙ ቁም ነገር አለ። በመጀመሪያ ኢየሱስ፣ ‹‹ብትወዱኝ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ›› ማለቱን ተመልክተናል። ስለ መንፈስ ቅዱስ ከመናገሩ በፊት ኢየሱስ የእርሱን ሥልጣንና የእርሱን ጌትነት መቀበል እንደሚገባ ማሳሰቡን መረዳት ተገቢ ነው። ትእዛዞቹን በመፈጸም ረገድ ለእርሱ መታዘዝ እንደሚገባን ከፍ ያለ አጽንዖት ሰጥቷል፤ ‹‹እኛም ለእነዚህ ነገሮች ምስክር ነን፤ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው›› በማለት ጴጥሮስ ይህን እውነት ያረጋግጣል (ሐዋርያት ሥራ 5፥32)። እግዚአብሔር ለሚታዘዙት መንፈስ ቅዱስን ይሰጣል።

ዮሐንስ 14፥16 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል›› ማለቱን አስተውሉ። ሌላ የሚለውን ቃል ግሪኩ ምን እንደሚለው እንመልከት። አዲስ ኪዳን ውስጥ አማርኛችን ሌላ ለሚለው ቃል ግሪኩ ሁለት ቃሎች አሉት። እነዚህ ግሪክ ቃሎች *ሄቴሮስ (heteros)* እና አሎስ *(allos)* ናቸው። ሄቴሮስ፣ ‹‹*ልዩ የሆነ ሌላ*›› ማለት ነው አሎስ፣ ‹‹*አንድ ዐይነት ወይም ተመሳሳይ የሆነ ሌላ*›› ማለት ነው።[3] ለመሆኑ ኢየሱስ እዚህ ላይ የተጠቀመው የትኛውን ቃል ነበር?

መልሱን ከመስጠቴ በፊት በእነዚህ ሁለት ግሪክ ቃሎች መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት አንድ ምሳሌ ላቅርብ። ለምሳሌ አንድ ዐይነት ፍራ ፍሬ ማለትም ፓም ሰጠኋችሁ እንበል። ፓሙን ከበላችሁ በኋላ፤ ‹‹ሌላ ፍራ ፍሬ ልስጣችሁ?›› በማለት ጠየቅኋችሁ።

እናንተ፣ ‹‹አዎን›› ስትሉ እኔ ብርቱካን ብሰጣችሁ፣ ‹‹ሌላ›› ሰጠኋችሁ ማለት ነው። የሰጠኋችሁ፣ *የተለየ ዐይነት ሌላ ነው*። እውነት ነው ብርቱካን አንድ ዐይነት ፍራ ፍሬ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ በዐይነቱ ከፓም የተለየ ነው።

ይህ ሄቴሮስ ለሚለው አንድ ምሳሌ ነው፡፡

ግን፣ ሌላ ፍራ ፍሬ እንድሰጣችሁ ስትጠይቁኝ ሁለተኛ ፓም ከሰጠኋችሁ አንድ ዐይነት የሆነ ሌላ ሰጠኋችሁ ማለት ነው፡፡ ይህ አሎስ ለሚለው አንድ ምሳሌ ነው፡፡

አሁን ወደ መጀመሪያው ጥያቄ እንመለስ፡፡ አብ ሌላ አጽናኝ እንደሚሰጠን ኢየሱስ ሲናገር ሌላ ለሚለው በየትኛው ቃል ነበር የተጠቀመው? አሎስ በሚለው ቃል ነበር የተጠቀመው፡፡ ስለሆነም፣ «አብ እኔን የመሰለ ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል» ማለቱ ነበር፡፡ እርሱና መንፈስ ቅዱስ፣ አንድ ዐይነት እንደ ሆኑ ኢየሱስ እየተናገረ ነው፡፡

ቀን 5

## የዕድሜ ዘመን ወዳጃችን

ዮሐንስ 14፥16 ላይ ኢየሱስ የተጠቀመበት ሌላ ቃል ረዳት የሚለው ነው፡፡ ረዳት ለሚለው ግሪክኛው ቃል ጰራቅሊጦስ ነው፡፡ ዮሐንስ መልእክት ውስጥ ኢየሱስም ጰራቅሊጦስ ተብሎ ተጠርቷል፤ «ልጆቼ ሆይ፣ … በአብ ዘንድ ጠበቃ (ጰራቅሊጦስ) አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1 ዮሐንስ 2፥1) ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ የረዳትነትን ወይም ጰራቅሊጦስ የመሆንን ሥራ ይሠራሉ፡፡ ታዲያ፣ የግሪኩ ቃል ምንድነው የሚለው? በዘመኑ ቋንቋ ስለ አንድ ሰው የሚሟገት ጠበቃ ማለት ነው፡፡[4] አማካሪ ወይም አሠልጣኝ - እንዲያውም የዕድሜ ዘመን አሠልጣኝ ለማለትም ጥቅም ላይ ይውላል፡ ፡

ጰራቅሊጦስ የሁለት ቃላት ጥምር ነው፤ ፓራ (*Para*) እና ካሊዮ (*kaleo*) የተሰኙ፡፡ ፓራ፣ «በጣም ቅርብ»[5] ማለት ነው፡፡ ከጢሞቴዎስ ጋር የነበረውን የቀረበ ግንኙነት ለማመልከት ጳውሎስ በዚህ ቃል ተጠቅሟል፡፡ የጢሞቴዎስን ያህል ለጳውሎስ የቀረበ ማንም አልነበረም (ፊልጵስዩስ 2፥20 ይመ)፡፡ ሚስቴ ሊዛ ለእኔ ፓራ ነች፡፡ በዚህ ምድር የእርሷን ያህል ለእኔ የቀረበ ማንም የለም፡፡ ስለሆነም ከእርሷ ጋር ያለኝን ቀረቤታ በተመለከተ በዚህ ቃል መጠቀም እችላለሁ፡፡

ሁለተኛው ግሪክ ቃል ካሊዮ ሲሆን፣ «መጠቆም ወይም መጥራት»[6] ማለት

ነው፡፡ ሐዋርያቱ ስለ ጥሪያቸው በሚናገሩበት ጊዜ ይህ ቃል በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ለምሳሌ ‹‹ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ተጠርቻለሁ›› ሲል ጳውሎስ የተጠቀመው፣ ካሊዮ በተሰኘው ግሪክ ቃል ነበር፡፡ ስለ ጥሪ ሲታሰብ ፍጻሜና ተግባርን የሚያጭሩ ሐሳቦችን ያነቃቃል፡፡

እነዚህ ሁለት ግሪክ ቃሎችን በአንድነት ስናደርግ፣ ኢየሱስ መናገር የፈለገውን አስመልክቶ በጣም የበለጠ መረዳት ይሰጠናል፡፡ በመሠረቱ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ሊያሠለጥነን፣ ምሪት ሊሰጠን፣ ሊያስተምረንና በሕይወት ጉዞአችን ሊመክረን በጣም ቅርብ ሆኖ መንፈስ ቅዱስ ለዘለቄታው ከእያንዳንዳችን ጋር እንደሚሆን ማመልከቱ ነበር፡፡ የተጠራው ወይም የተሰጠው ተግባር ይኸው ነው፤ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል እኛን ለመርዳት ለዘለቄታው ከእኛ ጋር ይሆናል! መንፈስ ቅዱስ ለዘላለም ከእኛ ጋር እንደሚሆን ኢየሱስ ተናግሯል (ዮሐንስ 14፥16)፡፡ አይተወንም ደግሞም አይጥለንም፡፡ ምንኛ ድንቅ የተስፋ ቃል ነው! በመሠረቱ እርሱ የጀመረውን ሥራና አገልግሎት በሕይወታችን እንደሚያስቀጥል ኢየሱስ እየተናገረ ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች፡ ‹‹ኢየሱስ አጠገቤ ቢሆን ኖሮ፤ ብዙ ጥያቄ አቀርብለት ነበር›› በማለት ሲናገሩ ብዙ ጊዜ እሰማለሁ፡፡ እነዚያን ጥያቄዎች ለምን ለመንፈስ ቅዱስ አያቀርቡለትም? ይህ ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለን አሳተሳሰብ የሚፈተንበት አቅጣጫ ነው፡፡ እርሱ በቅጡ የማይታወቅ አንድ ዓይነት ፍጡር እንደ ሆነ የምናስብ ከሆነ፣ ሊያስተምረንና ሊያሠለጥነን ብቁ መሆኑን በማሰብ ወደ እርሱ አንመጣም፡፡ መንፈስ ቅዱስ አምላክ እንጂ፣ በቅጡ የማይታወቅ አንድ ዓይነት ፍጡር አይደለም፡፡ እርሱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚናገርለት መሆኑን በእውነት የምናምን ከሆነ፣ ሁሉን ዐዋቂ፣ ሁሉን ቻይ፣ ሊያስተምረን፣ ሊረዳንና ሊያሠለጥነን ፈቃደኛና ደግሞም ችሎታ ያለው መሆኑን በማወቅ እንቀርበዋለን፣ አዎን፣ እጅግ የቅርባችን በመሆን ሊያናግረን ይፈልጋል፡፡

በጣም የሚያሳዝነው ግን፣ መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን በጣም ችላ የተባለ አካል መሆኑ ነው፡- ተገቢው ክብር ሳይሰጠውና ሌላው ቀርቶ አንዴ እንኳ ስሙ ሳይነሣ ምን ያህል ጊዜ በአንድነት ተሰብስበን ይሆን? ለዘለቄታው በእኛ ውስጥ እንዲኖርና ከእኛም ጋር እንዲመላለስ ስለ ተላከው መንፈስ ቅዱስ አንድ ቃል እንኳ ሳንናገር ምን ያህል ቀኖች እያሳለፍን

ይሆን?

## አስደንጋጭ ቃል

ዮሐንስ 16፥7 ላይ፣ ‹‹ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ…›› በማለት ኢየሱስ አንድ በጣም የሚገርም ቃል ይናገራል፡፡

ምንባቡን ከመመልከታችን በፊት እስቲ አንድ ዐይነት ስዕል ልሳልላችሁ፡፡ ኢየሱስ ከሦስት ዓመት በላይ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ነበር፡፡ የተናገረው ቃል በሙሉ ሲፈጸም አይተው ነበር፡፡ ነፋሱን ‹‹ፀጥ በል›› ብሎ ነበር፣ ፀጥ አለ፡፡ ‹‹በእንደዚህ ያለ ቦታ አንድ አህያ ታገኛላችሁ›› ብሎ ነበር፤ ልክ እርሱ እንዳለው ሆኖአል፡፡ አሳልፎ የሚሰጠው ሰው ማንነት ሳይታወቅ እንኳ፣ አብረውት ከነበሩት አንዱ እንደሚከዳው ተናግሮ ነበር፡፡ የበለሷ ዛፍ እንድትደርቅ ተናገረ፤ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ እንዳለው ሆነ፡፡ ኢየስስ የተናገረው ማንኛውም ነገር ልክ እርሱ እንዳለው ነበር የሚሆነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ቃል፣ ‹‹ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ›› በሚል መንደርደሪያ ነበር የጀመረው፡፡ ኢየሱስ መናገር የፈለገው ነገር ደቀመዛሙርቱ ማመን ከሚችሉት በላይ ነበር፤ ስለሆነም የሚነገራቸው እውነት መሆኑን እርግጠኞች እንዲሆኑ ፈልጓል፡፡

ታዲያ፣ ኢየሱስ መናገር የፈለገው ምን ነበር? ‹‹ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፣ መሄዴ ይበጃችኋል፡፡ እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ (ጰራቅሊጦስ) ወደ እናንተ አይመጣም፤ ከሄድሁ በኋላ ግን እርሱን ወደ እናንተ እልካለሁ›› (ዮሐንስ 16፥7)፡፡

እስቲ አንድ አፍታ ራሳችሁን በደቀ መዛሙርቱ ቦታ አድርጋችሁ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የምታወቁት መሪያችሁ ትቶአችሁ ሊሄድ እንደ ሆነና የእርሱ መሄድ ለእናንተ እንደሚጠቅም ሲነገራችሁ ምን ሊሰማችሁ እንደሚችል አስቡ፡፡ እኔ እዚያ ቦታ ብሆን ኖሮ፣ ንግግሩን ማመን ይከብደኝ ነበር፡፡ እርሱ እግዚአብሔር ከሆነ፣ መጀመሪያውኑ ትቶአችሁ ባይሄድ አይሻልም ነበር? እርግጠኛ ነኝ፣ ደቀ መዛሙርቱ እንደዚያ ነበር ያሰቡት፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ንግግሩን፣ ‹‹እውነት እላችኋለሁ›› በማለት መጀመር ነበረበት፡፡

የኢየሱስ መሄድ ለደቀ መዛሙርቱና እኔና እናንተን ጨምሮ ለሚመጡ አማኝ ትውልዶች ሁሉ የሚጠቅመው ወይም የሚበጀው እንዴት ነው? እስቲ እንዲህ አስቡ፣ ኢየሱስ ይህን ምድር ትቶ ካልሄደ፣ ከእኛ ጋር እንዲሆን መንፈስ ቅዱስ አይመጣም ነበር፡፡ ከኢየሱስ አንድ ነገር ከፈለግሁ ብዙ ኪሎ ሜትሮች ተጉዤ እርሱ ወዳለበት መሄድ ሊኖርብኝ ነው፡፡ እርሱን ለማግኘት ከሩቅ ቦታ የመጡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ተራዬ እስኪደርስ መጠበቅ ሊኖርብኝ ነው፡፡ ሁሉም የሚጠይቀው ጥያቄ፣ የሚያቀርበው ስጦታ ሊኖር ይችላል፡፡ ሆኖም ኢየሱስ ከዚህ ምድር ሄዶአል፡ ፡

በጣም ደስ የሚለው ግን ሁሌም ከእኛ ጋር እንዲሆን መንፈስ ቅዱስ መጥቷል፡፡ እርሱ አይተኛም ፣ እርሱ አይደክምም፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለን አመለካከት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ከተለወጠ፣ ‹‹የእኔ መሄድ ይበጃችኋል›› በማለት ኢየሱስ መናገሩ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ግልጽ ይሆንልናል፡፡

መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ያደርግ የነበረውን ሁሉ ማድረግ እንደሚችል አስታውሱ፡፡ እንደ ኢየሱስ ያስተምራል፤ የእግዚአብሔርን ነገሮች ሁሉ ይገልጻል፤ ልክ እንደ ኢየሱስ ሆኖ ከእኛ ጋር ይሆናል! እርሱ ምን ያህል ድንቅ መሆኑን ማየት ቻላችሁ? አሁን ይህን እየጻፍኩ እያለሁ እንኳ ሕይወቴን ለእርሱ ድምፅና መገኘት ዝግ ያደረግሁበትን አቅጣጫ መንፈሱ እያሳየኝ ነው፡፡ በድጋሚ ለመናገር እርሱ መሪያችን ነው፤ መካሪያችን፣ ጠባቂያችንና አሠልጣኛችን ነው - በእያንዳንዱ የሕይወት ገጽታችን ሁሉ እርሱ ያስፈልገናል፡፡

በሚቀጥለው ምዕራፍ ከታላቁ አምላካችን ጋር ተቀራርቦ መኖር ምን ማለት እንደ ሆነ እናጠናለን፡፡

ቀን 1 ማሰላሰያ

# መንፈስ ቅዱስን ማወቅ

*እኔም አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል - እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፡፡*

- ዮሐንስ 14፥16-17

መንፈስ ቅዱስ በእርግጥም ድንቅ ነው! በክርስቶስ ካገኘነው ድነት ቀጥሎ እርሱ ከማንኛውም የበለጠ ክቡር ስጦታ ነው፡፡ ለመሆኑ፣ መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? የአያሌ መጻሕፍት ደራሲና የዕድሜ ዘመን ፓስተር የነበረው **ኤ.ደብልዩ ቶዘር** እንዲህ ይላል፡-

> ‹‹መንፈስ ቅዱስ አንድ ዐይነት አነቃቂ ስሜት አይደለም…እርሱ አካል ነው፡፡ በጣም እርግጠኛ ሁኑ - እርሱ አካል ብቻ ሳይሆን ሰብዕና ያሉት ባሕርያትን ሁሉ አሟልቶ የያዘ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድና አእምሮ እንዲሁም ስሜት፣ ዕውቀት አለው፤ ይራራል፣ መውደድ፣ ማየት፣ ማሰብ፣ መስማትና መናገር ይችላል፤ ማንኛውም ሰው እንዳለው ሁሉ እርሱም ፍላጎት አለው››[1]

ይህን ጥናት ከመጀመርህ በፊት መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ የነበረህ መረዳት ምን ነበር? መንፈስ ቅዱስ ለአንተ በግል ማን መሆኑን አስመልክቶ ይህ ጽሑፍ ግንዛቤህን እንዴት ነበር ያሰፋው?

ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ለመንፈስ ቅዱስ የተሰጡ ስሞችን በጥንቃቄ አሰላስል (ገጽ 17 ተመልከት)፡፡ እነዚህ ስሞች ስለ እርሱ ማንነት ምን አስተማሩህ?

መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ዕኩል የሆነ አካል መሆኑን ማወቅ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ጤናማ ግንኙነት እንዲኖር በማድረግ ረገድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ቶዘር በመቀጠል፡-

> ‹‹ወልድ የሆነውን ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ነው፤ አብ የሆነውን ሁሉ መንፈስ ቅዱስም ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡ ታዲያ ማንን የሚመስል ሆኖ አገኘኸው? እርሱ በትክክል እንደ ኢየሱስ ነው፡፡ አዲስ ኪዳንን አንብባችኋል፤ ኢየሱስ ምን እንደሚመስል ካወቃችሁ መንፈሱም ምን እንደሚመስል ታውቃላችሁ››[2]

መንፈስ ቅዱስን በአዲስ መልኩ ማየት ቻላችሁ? በሕይወታችሁ ከእርሱ ጋር ግንኙነት ለማድረግ እነዚህ የተለያዩ የባሕርያቱ ገጽታዎች ምን ያህል አበረታቷችሁ?

---

---

---

---

---

---

---

**ተጨማሪ ጥናት**
ዮሐንስ 12፥44-45፤ 14፥8-11፤ 2 ቆሮንቶስ 4፥4፤ ቆላስይስ 1፥15-19፤ ዕብራውያን 1፥3፡፡

ቀን 2 ማሰላሰያ

# እርሱ አምላክ ነው፤ አንድ ዓይነት ተፈጥሮ አይደለም

*ጌታ መንፈስ ነው*

- 2ኛ ቆሮንቶስ 3፡17

የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችሁ መጠን፣ ክቡር ስጦታ ማለትም መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጣችሁ እግዚአብሔር ቃል ገብቶላችኋል (ገላትያ 4፥6 ይመ.)፡፡ የእርሱ መንፈስ ሰማይ ላይ የሚንሳፈፍ አንድ ዐይነት ረቂቅ ኃይል አይደለም፡፡ መንፈስ ቅዱስ ቅንጣት የሚያህል ነገር እንኳ ያልጎደለው የእርሱ የራሱ ሙላት ነው፡፡

በአሥራ ዘጠነኛው መቶኛ ዓመት የነበረውና ከ200 በላይ መጻሕፍትን የደረሰው **አንድሪው ሙሬ** መንፈስ ቅዱስ፤ ‹‹ከአብና ከወልድ ጋር አንድ ነው፤ እርሱ ‹ፍጹምና ሙሉ› የእግዚአብሔርን ክብር መገለጥ ያመጣል›› ይላል፣ በመቀጠልም፡-

> ‹‹በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተስፋዎች ሁሉ፣ በኢየሱስ በኩል የተገለጠውና ለእኛ የመጣልን መለኮታዊ ጸጋ ሁሉ፣ **መንፈስ ቅዱስ** አሁን የእኛ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በእርሱ በኩል የእግዚአብሔር ተስፋዎች ሁሉ ተፈጽመዋል፤ በክርስቶስ የሚገኘው ጸጋና ድነት ሁሉ በግል የእኛና በልምምድ የምንገነዘበው ሆኗል››[3]

ልብ አደረጋችሁ! በመንፈስ ቅዱስ በኩል፣ የእግዚአብሔር ተስፋዎች ሁሉ ተፈጽመዋል፤ በግል የእኛና በልምምድ የምንገነዘበው ሆኗል፡፡ ይህ የአንድ ሰው አስተያየት ሳይሆን የቅዱሳት መጻሕፍት እውነት ነው፡፡ ቀጥሎ ያሉትን ክፍሎች በጥንቃቄ አንብቧቸው፣ አሰላስሏቸው፡፡

> በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ
>
> – ኤፌሶን 1፥3

> በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ የመለኮቱ ኃይል ሰጥቶናል
>
> – 2ኛ ጴጥሮስ 1፥3

> እንደ ተጻፈው፣ ዐይን ያላየውን፣ ጆሮ ያልሰማውን፣ የሰውም ልብ

> ያላሰበውን፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቷል፡፡ እግዚአብሔር ይህን በመንፈሱ አማካይነት ለእኛ ገልጦልናል
> – 1ኛ ቆሮንቶስ 2፥9-10

በእነዚህ ጥቅሶች በኩል መንፈስ ቅዱስ ምን አስተማራችሁ?

የእርሱን ማንነት አስመልክቶ ቀደም ሲል የነበራችሁን አስተሳሰብ በመያዝ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሐልዎትና ኃይል በሕይወታችሁ እየወሰናችሁት ይሆን? ቆም በሉና ጸልዩ፡፡ የትኛውን አስተሳሰባችሁ እንዲለውጥላችሁ እንደሚገባ እንዲያሳያችሁ ጠይቁት፡፡ ምን ነበር የተረዳችሁት?

**ተጨማሪ ጥናት**

‹‹በመንፈስ››፣ ‹‹በመንፈስ በኩል›› እና ‹‹ከመንፈስ›› የሚሉትን ሐረጎች ከኦንላይን ፊለጉና አጥኑ (www.biblia.com). እንዲሁም 1 ቆሮንቶስ 12፥4-11፤ ገላትያ 5፥5፤ 2 ተሰሎንቄ 2፥13 አሰላስሉ፡፡

ቀን 3 ማሰላሰያ

# እርሱ የሕይወት መንፈስ ነው

*ምክንያቱም የሕይወት መንፈስ ሕግ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቷችኋል፡፡*

- ሮሜ 8፥2

መንፈስ ቅዱስ የቅድስና መንፈስ ነው! ምንኛ ድንቅ ስም! አስቡት፤ ሕይወት ሁሉም ነገር ነው፡፡ ጤናን፣ ዕድገትን፣ ንቃትን፣ ብርታትን፣ ጥንካሬንና ጉልበትን የመሳሰሉትን የሕይወት ገጽታዎች ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ በሕይወት መንፈስ ውስጥ ምንም ዐይነት የሞት ጽላሎት አይኖርም፣ ምንም ሕመም ወይም ደዌ፣ ድካምና ዝለት፣ መሻገት ወይም መበስበስ የለም - በማንኛውምና በየትኛውም መልኩ ሞት የለም፡፡

ፍጥረት በተገኘበት ጊዜ የሕይወት መንፈስ ነበር፤ በማንኛውም የምድር ገጽታ ሕይወት የዘራ እርሱ ነው፡፡ ዓለም-አቀፍ ሚሲዮናዊና ወንጌላዊ የነበርው **ሌስተር ሱምራል** እንዲህ በማለት ይህን ያረጋግጣል፡-

> ‹‹በጽሑፍ በሰፈረው ቃል ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ የምንመለከተው ከዘፍጥረት 1፥2 ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ገጽ እና ሁለተኛው ቁጥር ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራና እንቅስቃሴ መነገሩ ትኩረት የሚያሻው ነው፡፡ አጽናፈ-ዓለምን ወደ ሕላዌ የማምጣት ሥራ ነው፤ ከምስቅልቅል ውስጥ ውበትና ተወዳጅ ነገርን የማምጣት ሥራ ነው፡፡ ምድር ባዶና ቅርጽ-የለሽ ነበረች፡፡ እግዚአብሔር ዕፁብ በሆነ ሥራው ላይ ነበር፤ መንፈስ ቅዱስ እርሱን ለመርዳት ተንቀሳቀሰ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በውሆች ላይ ይረብብ ነበር፡፡ ከምስቅልቅሉ ውስጥ አጽናፈ-ዓለም ተገኘ››፡፡[4]

በሕይወትህ ውስጥ ባዶነትና ምስቅልቅል እንዳለ ይሰማሃል? መንፈስ ቅዱስ ውበትን፣ ሥርዓትንና ነፃነትን እንዲያስገኝ የምትፈልገው በየትኛው የሕይወት አቅጣጫህ ይሆን? ያን እንዲያሳይህ በጸሎት ጠይቀው፡፡ ልክ በፍጥረት ጊዜ እንዳደረገው በእነዚህ የሕይወት ገጽታዎችህም እንዲንቀሳቀስና ውበትንና ሥርዓትን እንዲያስገኝ በመጸለይ ነገርህን ሁሉ በጸሎት አሳልፈህ ስጠው፡፡

ፊልጵስዩስ 4፥6-8፤ 1ኛ ጴጥሮስ 5፥7፤ መዝሙር 37፥4-6 አውጣና አንብብ።

በዕለት ተዕለት ሥራ ብዛት ታክተህ ይሆን? የሕይወት መንፈስ በራሱ ኃይል ሊያበረታህ ይፈልጋል። ከእርሱ ጋር ጊዜ ስታሳልፍና እርሱን እያወቅህ ስትሄድ ብርታትህን ያድሳል። ጊዜ ውሰድና እነዚህን ኃያል የእግዚአብሔር የተስፋ ቃላት አሰላስል፤

> አታውቅምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፤ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው። አይደክምም፣ አይታክትም፣ ማስተዋሉም አይመረመርም። ለደከመው ብርታት ይሰጣል፤ ለዛለው ጉልበት ይጨምራል።
>
> \- ኢሳይያስ 40፥28-29

> ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ የሚኖር ከሆነ፣ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው በውስጣችሁ በሚኖረው በመንፈሱ ሟች ለሆነው ሰውነታችሁ ሕይወትን ይሰጣል።
>
> \- ሮሜ 8፡11

> ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ።
>
> \- ፊልጵስዩስ 4፥13

በእነዚህ ጥቅሶች በኩል መንፈስ ቅዱስ ምን እያስተማረህ ነው? መንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ ብርታት እንዲሞላህና ሕይወትህን ኢየሱስ በዚህ ምድር በተመላለሰ ጊዜ እንደ ነበረው እንዲያደርገው ጸሎትህን ጻፍ።

---

---

---

**ተጨማሪ ጥናት**
ዘፍጥረት 1፥2፤ ነህምያ 9፥6፤ ኢሳይያስ 40፥12-15፤ መዝሙር 8፥3-9፣104፣ 24-30፤ ኢዮብ 33፥4

ቀን 4 ማሰላሰያ

# ሙሉ በሙሉ በእርሱ መደገፍ አለብን

*በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት፡፡*

- ዘካርያስ 4፥6

የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ ማለትም በአብ መንፈስ ይደገፍ ነበር፡፡ ከመፀነሱ አንሥቶ እስከ ትንሣኤው በሕይወቱ የተፈጸመ ማንኛውም ነገር የመንፈስ ሥራ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣

በመንፈስ እንደ ተፀነሰ - **ማቴዎስ 1፡20፤ ሉቃስ 1፡31-35**
በመንፈስ እንደ ተመራ - **ማቴዎስ 4፡1፤ ሉቃስ 4፡1**
በመንፈስ ኃይል እንደ ተሞላ - **ሉቃስ 4፡14፤ 18-19፤ ዮሐንስ 3፡34**
በመንፈስ እንደ ተማረና ለእርሱ እንደ ታዘዘ - **ዮሐንስ 5፡19-20፤ 30፤ 14፡10** ይናገራል፡፡

*ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «እውነት እላችኋለሁ፣ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ፣ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያደርጋልና፤ አብ ወልድን ስለሚወድ የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል፣ ትደነቁም ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ነገር ያሳየዋል...እኔ ብቻዬን ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም፤ የምፈርደው የምሰማውን ብቻ ነው፤ የላከኝን እንጂ፣ የራሴን ፈቃድ ስለማልሻም ፍርዴ ትክክል ነው»፡፡*

- ዮሐንስ 5፥19-20፣ 30

ኢየሱስ ምን ያህል በመንፈስ ቅዱስ ይደገፍ እንደ ነበር የተናገረውን በጥንቃቄ አሰላስል (ከላይ ያለውን)፡፡ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ስለ ነበረው ግንኙነት መንፈስ ቅዱስ ምን አስተማረህ? ይህ በእንዴት ዐይነት ሁኔታ አደፋፈረህ፣ በእንዴት ዐይነት ሁኔታ ልብህን አነሣሣው?

ሐዋርያት ሥራ 5፥32፤ ሮሜ 8፥16፤ ገላትያ 4፥6፤ 1ኛ ዮሐንስ 3፡24 እና 4፡13 አንብብ። መንፈስ ቅዱስንና ከእርሱ ጋር ሊኖረን የሚገባውን ግንኙነት በተመለከተ በተደጋጋሚ የተነሡና ያስተዋልካቸው ሁለት እውነቶች ምንድን ናቸው?

በገላትያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ነበሩት አማኞች፣ መንፈስ ቅዱስ ምን ያህል ለእኛ አስፈላጊ መሆኑን አንዳንድ ጊዜ እንዘነጋለን። ገላትያ 3፡2-9 ከሉቃስ 11፡13 ጋር አብረህ በጥንቃቄ አንብብ። ቀጣይ የመንፈስ ቅዱስ ርዳታን መቀበልን በተመለከተ የተማርኸው ምንድን ነው? በሕይወትህስ እንዴት ተግባራዊ ታደርገዋለህ?

ቀን 5 ማሰላሰያ

# እርሱ ለዘላለም ወዳጅህ ነው!

*እኔ አብን እለምናለሁ፤ እርሱም ከእናንተ ጋር ለዘላለም የሚኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፡፡*

- ዮሐንስ 14፥16-17

መንፈስ ቅዱስ ወዳጅህ መሆን ይፈልጋል! ለዘለቄታው ከአንተ ጋር የሚኖር፣ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ የሚረዳህ ወዳጅህ መሆን ይፈልጋል፡፡ መጽሐፍ፣ ‹‹በውስጣችሁ ያሳደረው መንፈስ አብዝቶ ይቀናል›› ይላል (ያዕቆብ 4፥5)፡፡

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እውነተኛ ወዳጅነት በዋጋ የማይተመን ነው፡፡ የእርሱ ሓልዎትና ኃይል ምንም ነገር የማይተካከለው ዘላለማዊ ርካታ ይሰጣል፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር ኢየሱስ፣ ‹‹እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ከቶ አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ ከውስጡ የሚፈልቅ የዘላለም ሕይወት ውሃ ምንጭ ይሆናል›› አለ (ዮሐንስ 4፥14)፡፡ ወንጌላዊና ምሑር የነበረው **አር.ኤ.ቶሪ** ይህን ጥቅስ ሲያብራራ እንዲህ ነበር ያለው፣

> ‹‹እዚህ ላይ ውሃ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ዓለም በፍጹም ማርካት አይችልም፡፡ ማንኛውንም ዓለማዊ ርካታ በተመለከተ፣ ‘ማንም ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ይጠማል፡፡’ ማለት ይቻላል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ግን ማንኛውንም የተጠማ ነፍስ የማርካት ኃይል አለው፡፡ የሰውን ልብ የሚያረካ መንፈስ ቅዱስና እርሱ ብቻ ነው፡፡
>
> ልብህ ውስጥ ለሚመነጨውና ለሚፈሰው መንፈስ ቅዱስ ራስህን ከሰጠህ በፍጹም አትጠማም፡፡ በምን ዐይነት መነገር በማይችል ደስታ፣ በምን ዓይነት መግለጥ በማይቻል ርካታ፣ የእርሱ ሕያው ውሃ የብዙዎችን ነፍስ አርክቶ ይሆን፡፡ በውስጣችሁ ይህ ሕያው ምንጭ አለ? ያንን ምንጭ የደፈነ ምንም ነገር የለም? ለዘላለም ሕይወት በሚሆን ሁኔታ እየፈለቀ ነው?›[5]

ቶሪ ያቀረባቸው ጥያቄዎችን እንደ ገና አስቡ፣ ‹‹በውስጤ ይህ ምንጭ አለ? መግለጥ የማይቻለውን የመንፈስ ርካታ እየተለማመድሁ ነው? ካልሆነ፣ ለምን?›› ከዚያም በየዕለቱ ራስህን ለእርሱ ለመስጠት አንተ ማድረግ ያለብህን እንዲያሳይህ መንፈስ ቅዱስን ጠይቀው፡፡ የተረዳኸውን ጻፍ፡፡

በጌታ ፊት ፀጥ በል (ጌታ በሆነው መንፈስ ቅዱስ ፊት)፡፡ ራሱን እውን እንዲያደርግልህ - ከዚህ በፊት ከነበረው ይልቅ ራሱን እውን እንዲያደርግልህ ጠይቀው፡፡ በፍቅሩ፣ በሞገሱና በሰላሙ እንዲያጥለቀልቅህ ጠይቀው፡፡ በፊቱ ፀጥ በል፤ እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ተለማመድ፡፡ እርሱ የሚነግርህን ሁሉ ጻፍ፡፡

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ራስህን ለመሆን ነጻ ነህ፡፡ በውስጥህ ያለውን ሆነ፣ በውጭ ያለውን ስለ አንተ ሁሉንም ያውቃል፡፡ ‹‹ራስህን ማግኘት›› ያቃተህ በሚመስል ጊዜ ያለህበትን ቦታ በትክክል ይነግርሃል፡፡ ሊያበረታህ፣ ሊያጽናናህና ሊመራህ ለዘላለም በውስጥህ ይኖራል፡፡ በማንኛውም ጊዜ፣ በየትኛውም ቦታ ወደ እርሱ ቅረብ፡፡ አታደክመውም፤ አታታክተውም፤ ሁሌም ይቀበልሃል፡፡ እርሱ ምርጥ ወዳጅህ ነው!

**ጸሎት**

መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ ስለ አንተ ማንነት ያለኝን መረዳት አስፋው፡፡ ሰብዕናህንና እንደ ረዳት ያለህን ድርሻ ከዚህ በፊት ከነበረኝ የበለጠ እንዳይ እርዳኝ፡፡ ሓልዎትህን፣ ኃይልህን ወይም ድምፅህን በሕይወቴ ውሱን እንዳላደርግ ርዳኝ፡፡ ለራሴ፣ ለቤተ ሰቤና ለመላው ቤተ ክርስቲያን ይህን እጸልያለሁ፡፡ በኢየሱስ ስም አሜን፡፡

# የውይይት ጥያቄዎች

1. ያለ መንፈስ ቅዱስ የክርስትና ሕይወታችን፣ ደረቅ፣ አሰልቺና ኃይል የለሽ ይሆንብናል፡፡ ታዲያ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሲሆን ሕይወታችን ምን ይመስል ይሆን? የሚቻልህን ያህል ሊኖሩ የሚችሉ በጐ መገለጾችንና የተለያዩ ገጽታዎችን ዘርዝር፡፡

*ጌታ መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ፡፡*

- 2 ቆሮንቶስ 3፥17

2. መንፈስ ቅዱስ አንድ ዓይነት ምስጢራዊ ኃይል አይደለም፡፡ እርሱ የእግዚአብሔር አብንና ወልድን ሙላት የሚያመጣልን የመለኮት አካል ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስን እንደ አንድ ዓይነት ምስጢራዊ ኃይል ወይም ስሜት የማየት ጥቂት ውጤቶች ምንድናቸው? እርሱን በእውነተኛ ማንነቱ፣ ማለት እግዚአብሔር መሆኑን የማየት በጐ ውጤቶችስ ምንድናቸው?

3. ለጥንት አማኞች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው መንፈስ ቅዱስ የነበረው ድርሻ በጣም የተለመደ ነበር፤ በዚህ ዘመን አማኞች መካከል ግን ሲበዛ ብርቅ ነው፡፡ እርሱን እንዳንለማመድ፣ እርሱን እንዳንፈልግ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ አመራርና ብርቱ ኃይል እንዳንደገፍ ያደረጉን አንዳንድ ምክንያቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ታስባላችሁ?

4. በአሁኑ ጊዜ ኢየሱስ በአካል ያለው የት ነው? እንደ አማኝ እርሱ እናንተ ልብ ውስጥ እየኖረ ነው? የድነት ልምምዳችንና እግዚአብሔር ልባችንን መኖሪያው ያደረገበትን ምስጢር በተሻለ ወይም ይበልጥ ትክክል በሆነ ሁኔታ እንዴት ትገልጡታላችሁ?

**መሪዎች፣** የጥናት ቡድኑ ለመጀመሪያው ጥያቄ ማርቆስ 16፥19፤ ሐዋርያት ሥራ 1፥9-11፤ 7፥55-56፤ ሮሜ 8፥34፤ ቈላስይስ 3፥1፤ ዕብራውያን 10፥12-13 ለተቀረው ደግሞ ሮሜ 8፥9-10፤ 1 ቆሮንቶስ 3፥16፤ 6፥19፤ 1 ዮሐንስ 3፥24 እንዲመለከት አድርጉ፡፡

*ኢየሱስም እንዲህ አለው፣ «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱ እንመጣለን፤ ከእርሱም ጋር እንኖራለን፡፡»*

- ዮሐንስ 14፥23

5. ጌታ አምላካችን አንድ እግዚአብሔር ነው፤ ያም ሆኖ ግን አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመባል የሚታወቁ ሦስት የተለያዩ አካላት አሉት፡፡ የሥላሴ አካላትን ዋና ዋና ተግባርና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም እንዴት በአንድነት እንደሚሠሩ ግለጥ፡፡

መሪዎች፣ የጥናት ቡድኑ 1 ቆሮንቶስ 12፥5-7 በተጨማሪም ከዘፍጥረት 1 ስለ ፍጥረት አመጣጥ የሚናገረውን እንዲሁም ዮሐንስ 5፥17፣ 19-20 ላይ ኢየሱስ የተናገረው እንዲያነብ አድርጉ፡፡

**የእግዚአብሔር አብ መንፈስ = የክርስቶስ መንፈስ = መንፈስ ቅዱስ**

6. መንፈስ ቅዱስ አጽናኛችን (ረዳታችን) - ማለትም ጰራቅሊጦስ እንደ ሆነ ኢየሱስ ተናግሮአል፡፡ ዕለት ዕለት ከእግዚአብሔር ጋር በምናደርገው ጉዞ፣ ‹‹ሊያሠለጥነንና ሊመክረን ለዘላለም ከእኛ ጋር ነው፡፡›› በየዕለቱ ከእርሱ ጋር ኅብረት እንድታደርግ ይህ ግንዛቤ የሚያነሣሣህና የሚያበረታታህ በእንዴት ዓይነት መንገድ ነው?

7. ከዚህ በፊት ያላየኸው አሁን ግን ማየት የቻልከው አዲስ የመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ ምንድነው? እርሱ በሕይወትህ ማን መሆኑን በተመለከተ ዓይኖችህን የከፈተውና መረዳትህን ያዳበረው እንዴት ነበር?

**ምዕራፉ በአጭሩ፤**

- **መንፈስ ቅዱስ፣** የእግዚአብሔር አብንና ወልድን ሙላት ወደ እኛ የሚያመጣ የሥላሴ አካል ነው።
- እርሱ እግዚአብሔር እንጂ፣ አንድ ዓይነት ረቂቅ ኃይል አይደለም።
- እርሱ በጊዜና በስፍራ አይወሰንም፤ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ካሉ ሰዎች ጋር በአንድ ጊዜ መገናኘትና እነርሱን መርዳት ይችላል።
- በጥንት አማኞች ሕይወት ዘወትር ተሳትፎ ነበረው፤ ዛሬም ቢሆን በማንኛውም የሕይወት ገጽታችን ተሳትፎ ማድረግን አጥብቆ ይፈልጋል።
- ያለ እርሱ ምንም ዓይነት የክርስትና ሕይወት የለም፤ የእርሱን ድንቅ ኅብረት ለሚቀበሉ ግን እጅግ የበዛ የጀብድ ሕይወት አለ።
- በግል ሕይወታችሁ እርሱን ዕወቁ!

# 2

# የመንፈስ ቅዱስ ሰብዕና

*የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡*

- 2 ቆሮንቶስ 13፥14

## ቀን 1

ከአንድ ግለ ሰብ ጋር የጠበቀ መቀራረብ እንዲኖረን ከፈለግን በመጀመሪያ ያንኑ ሰው በሚገባ ማወቅ ይኖርብናል፡፡ በተቻለ መጠን የሚወደውን፣ የሚጠላውን፣ ዓላማውንና ፍላጐቱን በሰፊው ማወቅ ከእርሱ ጋር የጠለቀ ወዳጅነት እንዲኖረን በማድረግ ረገድ ጠቀሜታው የጐላ ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ለመቀራረብ በመጀመሪያ ሰብዕናውን ማወቅ አለብን፡፡

ካለፈው ምዕራፍ እንደ ተመለከትነው ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ ‹‹መሄዴ ይበጃችኃል፤ እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣም፤ ከሄድሁ ግን እርሱን ወደ እናንተ እልካለሁ›› በማለት አስገራሚ ቃል ነግሮአቸው ነበር (ዮሐንስ 16፥7)፡፡ ቀደም ሲል፣ ‹‹አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተሰወረውንም እናገራለሁ›› በማለት የነገራቸው ይኸው ኢየሱስ ራሱ ነበር (ማቴዎስ 13፥35)፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ ከነበሩ መምህራን ሁሉ ይልቅ ታላቅ መምህር የሆነው ኢየሱስ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የነበረውን ድብቅ ምስጢር ግልጥ ያደረገ ኢየሱስ፣ ለእነርሱም ሆነ ወደ ፊት ለሚመጡ

አማኞች ሁልጊዜ አብሮአቸው የሚዘልቅ ወዳጃቸው መንፈስ ቅዱስ እንጂ እርሱ ራሱ አለመሆኑን የቅርብ ተከታዮቹን ለማሳመን እየሞከረ ነበር፡፡ ይገርማል! የእናንተን አላውቅም፤ እኔን ግን መንፈስ ቅዱስን የበለጠ ማወቅ እንድፈልግ ያደርገኛል፡፡

> እስቲ 2 ቆሮንቶስ 13፥14 በመመልከት እንጀምር፤ ጳውሎስ እንዲህ አለ፣ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡

እያንዳንዱ የሥላሴ አካልን በተመለከተ ጉልህ ለሆነው ነገር ጳውሎስ አጽንዖት እየሰጠ ነው፡፡ ‹‹የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ…›› በማለት ይጀምራል፡፡ እንደ አማኞች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለሚኖረን ድንቅ ግንኙነት የማዕዘን ድንጋይ የሆነውን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረግነውን ዕርቅ መዘንጋት የለብንም፤ ከአዳኛችንና ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ውጪ ይህ እውን አይሆንም ነበር፡፡ ይህ ጸጋ በልፋታችን የምናገኘው ወይም እንደ ሽልማት የምንቀበለው ሳይሆን፣ የኃጢአት ይቅርታን፣ ድነትንና ኃይል መቀበልንም የሚጨምር የእርሱ የራሱ ሕይወት ስጦታ ነው፡፡

በመቀጠል ጳውሎስ፣ ‹‹የእግዚአብሔር ፍቅር…›› ይላል፡፡ አራቱ ወንዶች ልጆቼን ምን ያህል እንደምወድ ሳስብ፣ ከእነርሱ አንዱ ጋር ብቻ የሚኖረኝ ሕይወት ምን ሊመስልእንደሚችል ማሰብ ይከብደኛል፡፡ በተለይ ደግሞ አንድ ልጅ ብቻ ቢኖረኝና ጠላቶቼ ለሆኑ ሰዎች እንዲሞት እርሱን አሳልፌ መስጠት እንዳለብኝ ማሰብ ፍጹም ከአእምሮዬ በላይ ነው የሚሆነው፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለእኛ በነጻ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ፣ እኛ የእርሱ ጠላቶች ነበርን (ሮሜ 5፥10)፡፡ ምንኛ ድንቅ ፍቅር! እግዚአብሔር አብ ስለ ወደዳችሁ ደስ አይላችሁም? ጠላቶቹ የነበራችሁ ቢሆንም፣ አሁን ልጆቹ አድርጓችኋል፤ ስለ ሆነም ለእናንተ ያለው ፍቅር ምንኛ ታላቅ እንደ ሆነ ማየት ይቻላል፡፡ ልክ እንደ ገዛ ራሱ ልጅ፣ በተለየና ፍጹም በሆነ ፍቅር ይወዳችኋል፡፡

ልጆቼን በሚገባ እወዳቸዋለሁ፤ ያም ሆኖ ግን፣ የእኔ እነርሱን መውደድ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ፍቅር ጋር በፍጹም አይስተካከልም፡፡ ቃሉ እንዲህ

ይላል፤ «ይህን ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣ መላእክትም ይሁኑ አጋንንት፣ ያለውም ይሁን የሚመጣው፣ ወይም ማንኛውም ኃይል፣ ከፍታም ይሁን ጥልቀት፣ ወይም የትኛውም ፍጥረት፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ካለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም» (ሮሜ 8፥38-39)፡፡ እንዴት የሚገርም ተስፋ ቃል ነው! ከእግዚአብሔር ፍቅር የሚለያችሁ ምንም ነገር ባለ መኖሩ አታመሰግኑም?

አሁን ደግሞ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈው የመጨረሻ መልእክት መሆኑን እያሰብን እስቲ 2 ቆሮንቶስ 13፥14 እንመልከት፡፡ ይህ መልእክት ልዩ ጥበብና መገለጥ የሞላበት ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጳውሎስ ሲጽፍ፣ ይህን ለመልእክቱ መደምደሚያነት የመረጠበት ምክንያት ምን ይሆን? «የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡» ኅብረት (Communion) የሚለውን ቃል ጳውሎስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ማያያዙን ልብ አድርጉ፡፡ እንደ ማንኛውም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንዳደገ ልጅ ኅብረት (Communion) የሚለውን ቃል ስመለከት ትዝ የሚለኝ የቅዱስ ቁርባን ኅብስትና ወይኑ ነው፡፡ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለዚያ እንዳይደለ ግን ግልጥ ነው፡፡ ታዲያ፣ «የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት» ሲል ምን ማለት ነው? ወደ መጀመሪያው ግሪክ ቃል ስንመለስ ኅብረት ለሚለው ግሪክኛው ቃል ኮይኖኒያ (Koinonia) ነው፡፡ ለዚህ ግሪክኛ ቃል ካገኘሁዋቸው ትርጉሞች ጥቂቶቹ - ኅብረት፣ ባልንጀራነት፣ ግንኙነት፣ ቀረቤታ፣ በአንድነት መከፋፈል፣ ማኅበራዊ ተራክቦ፣ ኢጋርነት፣ ሽርካነትና እርሱ በርስ መተባበር የተሰኙት ናቸው፡፡ አዎን፣ ረዘም ያለ ብርቱ ቃላት ዝርዝር ነው! እስቲ፣ እነዚህን በሦስት ምድብ ለይቼ እንዳስቀምጥ ፍቀዱልኝ፡፡

- ኅብረት
- ኢጋርነት
- ቀረቤታ

## ኅብረት አንድነት ማለት ነው

ኅብረት የሚለውን ቃል መዝገበ ቃላቱ፣ «ወዳጅነት፣ ግንኙነት፣ ባልንጀራነት፣

በአንድነት መከፋፈል›› በማለት ይተረጉመዋል፡፡ በጣም የሚቀራረቡ ጓደኛሞች ኅብረት አላቸው፤ በአንድነት ይከፋፈላሉ፤ አብረው ይነጋገራሉ፤ በእያንዳንዱ ሕይወት ውስጥ የሚሆነውን በንቃት ይከታተላሉ፡፡

ቀደም ሲል እንደ ተናገርኩት ጐልፍ መጫወት እወዳለሁ፡፡ ብዙ ጊዜ ጐልፍ የምጫወተው በጣም ከምቀርባቸው ወዳጆቼ ጋር ነው፡፡ እየተጫወትን እርስ በርስ እንነጋገራለን፡፡ ሐሳባችን የሚከፋፈለው በጣም በጥቂቱ ስለ ሆነ፣ ያ ጊዜ ለእኛ በጣም ምርጥ ከሚባሉ ጊዜዎች አንዱ ነው፡፡ የኮሌጅ ተማሪ እያለሁ ቴኒስ እጫወት ነበር፤ ሆኖም ቴኒስ የመጫወት አንዱ ችግር አብሮኝ ከሚጫወተው ሰው ጋር መነጋገር የማይቻል መሆኑ ነው፡፡ ጐልፍ መጫወት ከምወድበት ምክንያት አንዱ አብሮኝ ከሚጫወተው ጋር መነጋገርና ማውራት ስለምችል ነው፡፡ ከጐልፍ ጨዋታ በጣም ጥሩ ጓደኞች ማግኘት ችያለሁ፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ‹‹ኅብረት›› ፈጥሬአለሁ ማለት ነው፡፡ እንግዲህ ሚስቴ አብራኝ ጐልፍ እንድታጫውት የምፈልገው ለምን እንደ ሆነ አሁን ግልጽ የሆነላችሁ ይመስለኛል፤ ምክንያቱም በዚህ ምድር ከእርሷ ጋር አብሮ የመሆንን ያህል በጣም ደስ የሚያሰኘኝ ነገር የለም!

በጣም ከምቀርባቸው ጓደኞቼ ጥቂቶቹ የሚሴንጀር ኢንተርናሽናል አባሎች ናቸው፡፡ ስለ ዕቅዳችን፣ ተግዳሮቶቻችንና ግባችን ብዙ ጊዜ እንነጋገራለን፡፡ በእነርሱ ወዳጅነትና ጓደኝነት በጣም እተማመናለሁ፡፡ እነዚህ ድንቅ ወንዶችና ሴቶች እጐኔ ባይሆኑ ኖሮ፣ ዛሬ ምን ላይ እሆን እንደ ነበር አላውቅም፡፡ በየጊዜው እርስ በርስ እንገናኛለን፤ እንዲህ ያለ ኅብረት ባይኖረን ኖሮ፣ ማስተማር፣ መድረስና መታደግ የተሰኘው የሚሴንጀር ኢንተርናሽናል ተልዕኮ እውን አይሆንም ነበር፡፡

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባላቸው ኅብረት ሐዋርያት በጣም ይተማመኑ እንደ ነበር ከቅዱሳት መጻሕፍት መረዳት ይቻላል፡፡ ከሐዋርያት ሥራ፣ ‹‹አሁንም እዚያ ስደርስ የሚደርስብኝን ባላውቅም፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኢየሩሳሌም እንድሄድ ግድ እያለኝ ነው፡፡ ነገር ግን በምሄድባቸው ከተሞች ሁሉ እስራትና መከራ እንደሚጠብቀኝ መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልኛል›› የሚል እናነብበናል (ሐዋርያት ሥራ 20፥22-23)፡፡ እፊት ለፊቱ ስላለው ነገር ጳውሎስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተነጋግሮ ነበር፡፡ እስራትና መከራ እንደሚጠብቀው መንፈስ ቅዱስ ለጳውሎስ የነገረው በአንድ ከተማ ብቻ

እንዳልነበር አስተውሉ፡፡ ይልቁንም፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከነበረው የዘወትር ኅብረት የተነሣ እስራትና መከራ እንደሚጠብቀው የነገረው በሚሄድባቸው ከተሞች ሁሉ ነበር፡፡

የእናንተን እርግጠኛ ባልሆንም፣ በበኩሌ በጣም ከምቀርባቸው ወዳጆቼ አንዱ እስራትና መከራ እንደሚገጥመኝ በምሄድበት ቦታ ሁሉ ቢነግረኝ ኖሮ፣ አንዳንድ ጥያቄዎች አቀርብለት ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ ‹‹አሁንስ፣ ሐሳብህን አልለወጥህም?›› ወይም፣ ‹‹ምናልባት፣ ዕቅዳችንን በመጠኑ ማስተካከል ይኖርብን ይሆን›› ወይም፣ ‹‹ምናልባት የሚገጥመኝ ይህን ያህል ከባድ መከራ ሳይሆን ጥቂት አዳጋች ሁኔታዎች ብቻ ቢሆኑስ?›› እለው ነበር፡፡ ጳውሎስ በሚገጥመው መከራ መንፈስ ቅዱስ ደስ እያለው ባይሆንም፣ ፊት ለፊቱ ላለው ከባድ ነገር እያዘጋጀው ነበር፤ እርስ በርስ ካላቸው ጥብቅ ኅብረት የተነሣ ጳውሎስ ያንን መቀበል ይቻለዋል፡፡

አንዳንድ መስማት የማልፈልጋቸው ነገሮችን መንፈስ ቅዱስ ነግሮኝ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ ስለ እነዚያ ነገሮች ደጋግሜ እርሱን ጠይቄ ነበር (ምናልባት፣ የተለየ መልስ በመጠበቅ)፤ ሆኖም፣ በየጊዜው የተቀበልኩት ያንኑ መልእክት ነበር፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚኖረን ግንኙነት የዚህ ዓይነት ከሆነ፣ ውሎ አድሮ ዝም ይለናል፡፡ ምናልባትም፣ ‹‹ይህን በተመለከተ በግልጽ ነግሬሃለሁ፤ የሰጠሁህን ምሪት መቀበል አለመቀበል የአንተ ምርጫ ነው›› የማለት ያህል ሊሆን ይችላል፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በጣም የጠበቀ ኅብረት ሲኖራችሁ፣ አንዳንዴ መስማት የማትፈልጉትን ነገር ሊነግራችሁ ይችላል፡፡

ሐዋርያት ሥራ 10 ላይ ጴጥሮስ የዚህ ዓይነቱን ምሪት ከመንፈስ ቅዱስ ተቀብሎ እንደ ነበር እንመለከታለን፡፡ ድነት ለአሕዛብም ጭምር መሆኑን የሚያመለክት ራእይ እግዚአብሔር ለጴጥሮስ ሰጥቶት ነበር፡፡ ቁጥር 19 ላይ፣ ‹‹ጴጥሮስ የራእዩን ነገር በማሰላሰል ላይ ሳለ መንፈስ እንዲህ አለው - እነሆ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል›› የሚል እናነባለን፡፡ እነዚህ ሰዎች ጴጥሮስን ወደ አንድ አሕዛብ መቶ አለቃ ቤት ሊወስዱት እየመጡ ነበር፤ እንደ አንድ አጥባቂ አይሁዳዊ ጴጥሮስ ወደ እንዲህ ያለ ሰው ቤት መሄድ በፍጹም አይፈልግም፡፡ ስለዚህም፣ ‹‹ስማ፣ አንተን ለማግኘት ሰዎች መጥተዋል፤ አብረሃቸው እንድትሄድ እፈልጋለሁ፤ እዚያ የምትሠራው ነገር አለ›› በማለት

እቅጩን ነገረው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ምሪት ጴጥሮስን ደስ እንደሚያሰኘው መንፈስ ቅዱስ ያውቅ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ምንም ተጨማሪ ገለጻ ሳይሰጠው ምሪት ብቻ ሰጠው፡፡

ጥቂት ምዕራፎች ወደ ኋላ ስንሄድ በመንፈስ ቅዱስ መተማመንን በተመለከተ አንድ ሌላ ምሳሌ እንመለከታለን፡፡ «የጌታም መልአክ ፊልጶስን፣ ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ በሚያወርደው በምድረ በዳው መንገድ ሂድ አለው» (ሐዋርያት ሥራ 8÷26)፡፡ እዚህ ላይ አንድ የእግዚአብሔር መልአክ ለፊልጶስ ምሪት ሲሰጠው ነው የምንመለከተው፡፡ የጌታ መልአክ ለፊልጶስ ተገለጠለት ሳይሆን፣ «የጌታም መልአክ ፊልጶስን… አለው» ነው የሚለው፤ ማንኛውም ትርጉም ይህንኑ ነው የሚያረጋግጠው፡፡ ለመሆኑ፣ ይህ ለየት ያለ ምሪት ይህን ያህል አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ከዚህ ምንባብ በመነሣት ጴጥሮስ የመንፈስ ቅዱስንና የመልአክን ድምፅ ለይቶ መረዳት ይችል ነበር ማለት እንችላለን፤ ምክንያቱ ጥቂት ቆየት ብሎ፣ «መንፈስም ፊልጶስን፣ ሂድ ወደዚህ ሰረገላ ቅርብ አለው» የሚል እናነባለን (ሐዋርያት ሥራ 8÷29) ሌላው ቀርቶ፣ የመንፈስንና የመልአክን ድምፅ እንኳ መለየት እስኪችል ድረስ ፊልጶስ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ተለማምዶ ነበር!

የሚስቴን ድምፅ በጣም ከመልመዴ የተነሣ፣ እርሷን ባላየት እንኳ የእርሷ ድምፅ መሆኑን ለይቼ ማወቅ እችላለሁ፡፡ ሰዎች በሞሉበት ክፍል ውስጥ በተለያየ ቦታ ተቀምጠን ቢሆን እንኳ፣ ከዚያ ሁሉ ሰው መካከል የእርሷን ድምፅ እለየዋለሁ፡፡ የጥንት አማኞች የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ለይተው የሚያውቁት ይህን ያህል ነበር፡፡ ሉቃስ የሐዋርያት ሥራን እየጻፈ እያለ፣ ፊልጶስ ይህን ታሪክ ሲነግረው ይታየኛል፡፡ ምናልባትም፣ «በከተማ እያለሁ የተናገረኝ መንፈስ አልነበረም፤ ያን የነገረኝ መልአክ ነበር፡፡ ወደ ሰረገላው እንድቀርብ የነገረኝ ግን መንፈስ ነበር» ሳይለው አልቀረም፡፡ እኛስ ድምፁን ያን ያህል ለይተን እናውቃለን? ወይስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሊኖረን ወደሚገባው የበለጠ ጥብቅ ግንኙነት ገና አልገባንም?

ፊልጶስ በዚያ ምድረ በዳ በነበረ ጊዜ፣ ወደ አንድ ሰረገላ እንዲቀርብ መንፈስ ቅዱስ ነገረው፡፡ ለመሆኑ፣ ከዚያ ሰው ጋር የመገናኘቱ ፋይዳ ምንድነው? ሰረገላው ላይ ያለው ሰው በመላው ኢትዮጵያ ሦስተኛው ከፍተኛ ባለ ሥልጣን ነበር፡፡ ከነበረው ሥልጣንና ተሰሚነት የተነሣ፣ የእርሱ ድነት

ወንጌል በአገሩ እንዲዳረስ በር ይከፍታል፡፡ ፊልጶስ ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ንቁ ባይሆን ኖሮ፣ ያ ትልቅ ዕድል ያመልጠው ነበር፡፡

ከጥቂት ምዕራፎች በኋላ ጢሞቴዎስን፣ ጳውሎስንና ሲላስን የሚመለከት ሌላ ታሪክ እናያለን፡፡

> ጳውሎስና ባልደረቦቹ [ጢሞቴዎስና ሲላስ] ቃሉን በእስያ እንዳይሰብኩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው በፍርግያና በገላትያ አገር አልፈው ሄዱ፡፡ ወደ ሚስያም በተቃረቡ ጊዜ ወደ ቢታንያ ሊገቡ ሞከሩ፤ ነገር ግን የኢየሱስ መንፈስ አልፈቀደላቸውም፡፡ (ሐዋርያት ሥራ 16፥6-7)

መንፈስ ቅዱስ፣ ‹‹ከለከላቸው››፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ አልፈቀደላቸውም›› ማለቱን ልብ አድርጉ፡፡

በመጀመሪያዎቹ አማኞችና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ምን ያህል የቀረበ ግንኙነት እንደ ነበር ማየት ቻላችሁ? ዛሬስ፣ ከዚያ የተለየ መሆን አለበት? ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል የተሻለ መንገድ አላችሁ? ሐዋርያቱ ይህን ያህል በመንፈስ ቅዱስ ይደገፉ የነበረው የዘመኑ ቴክኒዎሎጂ ስላልነበራቸው፣ የጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሠራር ኋላ ቀር ስለ ነበር ይሆን? በፍጹም አይደለም! የትኛውም ቴክኒዎሎጂ ወይም ዘዴ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ መተካት አይችልም፡፡ እነዚያ መሪዎች መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ተሳትፎ እንዲያደርግ ይጠብቁ ነበር፤ የእርሱን መገኘት ይጠባበቁና ይጋብዙ ነበር፡፡ ዛሬም ምንም የተለወጠ ነገር የለም፡፡ ዛሬም ቢሆን መንፈስ ቅዱስ፣ ልክ እንደ እነርሱ ከእኛም ጋር ቀረቤታ ባለው ኅብረት መመላለስ ይፈልጋል፡፡

እኔና ሊዛ በቤት ውስጥ ምንም ሳንነጋገር ሰዓቶች ወይም ቀኖች ብናሳልፍ ምን ሊመስል እንደሚችል ማሰብ ትችላላችሁ? በፍጹም የማይታመን ነው የሚሆነው፡፡ እንደዚያ ያለውን ትዳር ማን ይፈልጋል? ሚስቴን በጣም እወዳታለሁ፤ ወደ እርሷም መቅረብ እፈልጋለሁ፡፡ ስትናገር መስማት እፈልጋለሁ፤ ድምፅዋ ለእኔ ሙዚቃ ነው፡፡ በዚህ ምድር ካሉ ሰዎች ሁሉ አብራኝ እንድትሆን የምፈልገው ያለ ጥርጥር እርሷን ነው፡፡ በተመሳሳይ

መንገድ መንፈስ ቅዱስም ከእናንተ ጋር የጠበቀ ኅብረት ማድረግ ይፈልጋል፡፡

ባለፉት ሃያ አራት ዓመታት በተለያየ ጊዜ ብቻዬን ሆቴል ውስጥ ባሳልፍም፣ ብቸኝነት ተሰምቶኝ አያውቅም፡፡ እያንዳንዱን ቅጽበት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እያሳለፍኩ እስከ ሆነ ድረስ እንዴት ብቸኝነት ሊሰማኝ ይችላል? ምንጊዜም እርሱ ከእኔ ጋር ነው፡፡ ስለሆነም ሆቴል ክፍል ውስጥ የማሳልፈው ጊዜ እንዲባክን አልፈልግም፡፡ «ብቻዬን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መሆን ስለምፈልግ ከጉዞ ቡድኑ ጋር ጊዜ ማሳለፍ አልፈልግም» በማለት አልፎ አልፎ ለሥራ ባልደረቦቼ እናገራለሁ፡፡ እርሱ ሲናገረኝ መስማት ደስ ያሰኘኛል፡፡ እባካችሁ በተሳሳተ መንገድ አትረዱኝ፤ ከሰዎችም ጋር አብሮ መሆን ደስ ያሰኘኛል፣ እንዲያውም በጣም ነው የምወደው! መናኝ ወይም የግድ ብቻዬን መሆን የምፈልግ ሰው አይደለሁም፡፡ ሰዎችን ከልቤ እወዳለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ለሚኖረኝ ጊዜ (ኅብረት) ከልቤ ከበሬታ እሰጣለሁ፡፡

ቀን 2

## ኅብረት አጋርነት ነው

ኮይኖንያ የሚለውን ቃል ለመግለጽ ጥቅም ላይ መዋል የሚችል ቀጣዩ አማርኛ ቃል አጋርነት ነው፡፡ አጋርነትን በተመለከተ ምሳሌ የሚሆነንን ሐሳብ ከሉቃስ ወንጌል እንመለከታለን፤ «እንደዚያም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፤ መረባቸውም ይበጣጠስ ጀመር፡፡ በሌላ ጀልባ የነበሩት ባልንጀሮቻቸው መጥተው እንዲያግዙዋቸውም በምልክት ጠሯቸው፤ እነርሱም መጥተው ሁለቱን ጀልባዎች በዓሣ ሞሏቸው፤ ጀልባዎቹም መስመጥ ጀመሩ» (ሉቃስ 5፥6-7)፡፡ ማገዝ ለሚለው ግሪኩ ቃል ሜቶኮስ፣ (Metochos) ሲሆን (የኮይኖኒያ ተመሳሳይ ቃል)፣ «አጋዥ፣ ባልንጀራ፣ አብሮ ሠራተኛ»[1] ተብሎ መተርጐም ይችላል፡፡ እነዚህ ሰዎች የሥራ አጋሮች ነበሩ እንግዲህ ከዚህ መስተጋብር የምንረዳው መልካም አጋርነት ግንኙነትና አብሮ መሥራትን የሚጠይቅ መሆኑን ነው፡፡ ሰዎቹ አጋሮቻቸውን ጠሩ፤ እነርሱም መጥተው ረዷቸው፡፡

አሁን ደግሞ መላው አዲስ ኪዳን ውስጥ ምናልባት እጅግ አነቃቂና ተስፋ

ሰጪ ሊሆን የሚችል አንድ ቃል እንመልከት፡፡ ጳውሎስ እንዲህ አለ፤ ‹‹እኛ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ነን›› ይላል፡፡ ለሰማያትና ምድር ፈጣሪ ለመሥራትና ከእርሱም ጋር አብረን የመሥራት ዕድል ተሰጥቶናል፡፡ ይህን በሌላ መልክ ስንገልጠው፣ ከእግዚአብሔር ጋር በአጋርነት አብረን የምንሠራ ሰዎች ነን ልንለው እንችላለን፡፡ ምንኛ ድንቅ ጥሪ ነው!

ውጤታማ የሥራ አጋሮች በማግኘትም ሆነ በማጣት አብረው የመሥራትን ልምድ ያዳብራሉ፡፡ ተወልጄ ያደግሁት በሚቺጋን ሐይቅ አካባቢ ሲሆን፣ በባሕር ላይ መንሳፈፍ በሕይወቴ በጣም ደስ ከምሰኝባቸው ነገሮች አንዱ ነበር፡፡ በቤተ ሰባችን ጀልባ መቅዘፍ በጣም ደስ ይለኝ ነበር፤ መቅዘፍን በተመለከተ ለሁለት ዓመት ያህል ትምህርት ተከታትዬ ነበር፤ እንዲያውም በቀዘፋ ውድድር እንኳ ተካፍዬ አውቃለሁ፡፡ በመጀመሪያው ሩጫ ከአንድ ታዋቂ ካፒቴን ጋር እንድሠራ ነበር የተነገረኝ፡፡ የዚያ ካፒቴን ቡድን በጣም ምርጥ ከሚባሉት አንዱ ነበር፡፡ በመጀመሪያው ሩጫ ያለ ቦታዬ የተገኘሁ ያህል ተሰምቶኝ ነበር፡፡ ካፒቴኑ ትእዛዝ ሲሰጥ ቡድኑ ወደ ተግባር ገባ፡፡ እያንዳንዱ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበትና ጀልባው ውስጥ መያዝ የነበረበትን ቦታ በትክል ያውቅ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እኔ፣ በጣም ፈሪ ነበርሁ፤ እንቅስቃሴዬም ያልተቀናጀ ነበር፡፡ ምን ማድረግ እንዳለብን ተነግሮኝ የነበረ ቢሆንም፣ የሥራ ድርሻዬን በተመለከተ የነበረኝ ልምድ የዳበረ አልነበረም፡፡ ሌሎቹ ሰዎች በጋራ የመንቀሳቀሱን ጥበብ አዳብረዋል፤ እኔ ግን ያንን ገና አልተማርኩም ነበር፡፡

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አጋር መሆን፣ ከዚያ ቡድን ጋር በአጋርነት የመንቀሳቀስ ያህል ነበር፡፡ ከእርሱ ጋር መሥራት አለባችሁ፡፡ የመጀመሪያው ስብከቴን ሕዝብ ፊት ያቀረብኩ ጊዜ ሚስቴና ጓደኛዋ ፊት ለፊቱ ወንበር ላይ ሆነው እንቅልፋቸውን እየለጠጡ ነበር፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ መንቀሳቀን ገና አላዳበርኩም ነበር፡፡ የኋላ ኃላ ግን ንግግር ሳደርግ ከእርሱ ጋር አብሮ መሥራትን ተምሬአለሁ፡፡ መጻፍን በተመለከተም ይኸው ነበር፡፡ የመጀመሪያ መጽሐፌን ሳዘጋጅ፣ ተስፋ መቁረጥ የሞላበት ድፍን አንድ ዓመት ወስዶብኝ ነበር፤ በዚያ ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተባብሮ መሥራትን ገና እየተማርኩ ነበር፡፡ በኋላ ግን መጻፍ በጣም ቀላልና ፈጣን ሆነልኝ፡፡ በእነዚህ ሁለት ነገሮች እርሱ ድርሻ እንዳለው፣ እኔም የራሴ ድርሻ እንዳለኝ

ተምሬአለሁ - እርሱ የሚፈልገው እንደዚያ እንዲሆን ነው!

ሐዋርያት ሥራ 15 ላይ አጋርነት በተግባር ሲገለጥ እንመለከታለን፡፡ ሐዋርያቱ ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ አማኞች ሁሉ የሚላክ ደብዳቤ እያረቀቁ ነበር፡፡ ደብዳቤው ውስጥ፣ ‹‹ለመንፈስ ቅዱስም ለእኛም መልካም መስሎ ታይቶናል›› የሚል ቃል ነበረበት (ሐዋርያት ሥራ 15፥28)፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ አጋርነትን ተግባር ላይ እናያለን፡፡ አንድን ሁነኛ ጉዳይ በተመለከተ መሪዎች የመንፈስ ቅዱስንና የራሳቸውን ሐሳብ ገልጸዋል፤ ውሳኔ ማሳለፉ ላይ ሁለቱም ወገኖች ተሳትፈዋል፡፡ ሁለቱም ወገኖች ድርሻ ነበራቸው፡፡ ሁለቱም በመንግሥቱ ሥራ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡

አጋርነትን በተመለከተ ከብሉይ ኪዳንም የምንመለከተው አለ፡፡ አብርሃም በመምሬ ትልልቅ ዛፎች አቅራቢያ በነበረ ጊዜ ሰዶምና ገሞራን ለማጥፋት ስለ ነበረው ዕቅድ ሊነግረው እግዚአብሔር ወደ እርሱ መጥቶ እንደ ነበር አስታውሱ (ዘፍጥረት 18 ይመ.)፡፡ እግዚአብሔር አብርሃምን እንደ አጋር ቆጥሮታል፡፡ እግዚአብሔርና አብርሃም አብረው ወደ ሜዳው እየሄዱ እያለ፣ ‹‹እነዚህን ሁለት ከተሞች ለማጥፋት አስቤአለሁ፤ አንተስ ምን ይመስልሃል?›› አለው (አባባሉ የደራሲው ነው)፡፡ የወንድሙ ልጅ የሚኖረው ከእነዚህ ከተሞች በአንዱ ስለ ነበር አብርሃም ሐሳብ ገብቶት ነበር፡፡ ጥቂት ከተነጋገሩ በኋላ ዐሥር ጻድቃን ከተገኙ እነዚያን ከተሞች እንደማያጠፋ አብርሃም እግዚአብሔርን እሺ አሰኘ፡፡

እግዚአብሔር የአብርሃምን ሐሳብ ማክበሩ ግልጽ ነበር፡፡ እንዲያውም ዘፍጥረት 18፥17 ላይ፣ ‹‹እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን?›› ብሎአል፡፡ እርሱ የነበረውን ዕቅድ አብርሃም እንዲያውቅ እግዚአብሔር ፈልጓል፡፡ ለምን? ምክንያቱም፣ አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ጥብቅ ኅብረት ወይም አጋርነት ስለ ነበረው፡፡

ከሙሴም ሕይወት ተመሳሳይ ነገር እንመለከታለን፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን፣ ‹‹አሁንም በእነርሱ ላይ ቁጣዬ እንዲነድና እንዳጠፋቸው ተወኝ፤ ከዚያም አንተን ለታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ›› አለው (ዘፀአት 32፥10)፡፡ ይህን ከሰማ በኋላ ከቁጣው እንዲመለስና ሐሳቡን እንዲለውጥ ሙሴ እግዚአብሔርን ለመነ፡፡ ይህን ብናነብም ሐሳቡን አድበስብሰን ማለፍ በዚህ ዘመን ላለነው ለእኛ በጣም ቀላል ነው፡፡ እስቲ ቆም በሉና እንዲህ አስቡ፤

ሌላው ቀርቶ፣ ‹‹ተወኝ›› ቢለው እንኳ ሙሴ፣ ለእርሱም ሆነ ለሕዝቡ የተሻለ ነው የሚለውን ሐሳብ ለእግዚአብሔር መናገር ችሎአል፡፡ እንዲህ የሆነው ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር አጋር ሆኖ ይሠራ ስለ ነበር ነው፡፡

እዚህ ላይ ግን፣ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑንና ምን ጊዜም ቢሆን፣ ከእኛ ክብርና መፈራት እንደሚገባው መገንዘብ አለብን፡፡ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራው ወይም አጋሮቹ የምንሆነው ከእርሱ ጸጋና ኃይል የተነሣ ብቻ ነው፡፡ በእርሱ ታላቅ ዕቅድና ሐሳብ ውስጥ ድርሻ እንዲኖረን መርጧል፡ ፡ በዚያ ምርጫው እኛን ማሳተፉ ምን ያህል ታላቅ መብት ነው!

እነዚህ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉ ሁለት ታላላቅ ምሳሌዎች ናቸው፤ ይሁን እንጂ፣ እውነቱ አብርሃምም ሆነ ሙሴ አሁን እኛ ያለን መብት ያልነበራቸው መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ ታላላቅ የእምነት ሰዎች መንገድ የእግዚአብሔር አጋሮች የሆኑባቸው የተለዩ ጊዜዎችና ወቅቶች ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ፣ መንፈስ ቅዱስ እኛ ውስጥ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ ይኖራል፡፡ እርሱ አልፎ አልፎ እስኪጐበኘን ድረስ መጠበቅ፣ ወይም እርሱን ለማግኘት ወደ ሲና ተራራ መውጣት የለብንም፡፡ ዘወትር ወደ እርሱ የመቅረብ መብት ተሰጥቶናል፡ ፡ ከሁሉም የበለጠ የሚገርመው ደግሞ ከእኛ ጋር በአጋርነት መሥራት መፈለጉ ነው፤ እርሱ እያንዳንዱ ርምጃችን ይመራል፤ ሐሳባችንን ይሰማል፡፡

መንፈስ ቅዱስ ሁሉጊዜ ከእኛ ጋር መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ በፍጹም አይተኛም፤ ጨርሶ አያንቀላፋም፡፡ በቅርቡ ከሌሊቱ 8፡20 ላይ ከእንቅልፌ ነቅቼ ነበር፤ በቀኑ ጊዜ በነበረኝ አገልግሎት በጣም ደስ ብሎኝ ስለ ነበር ተመልሼ መተኛት አልቻልኩም፡፡ ስለዚህ ተነሣሁና ከአጋሬ ጋር መነጋገር ጀመርኩ፡፡ እርሱ ሁሌም ንቁ ነው፡፡ ‹‹ጆን በዚህ ሰዓት የምትቀሰቅሰኝ ለምንድነው?›› አይለኝም፡፡ በአንጻሩ ግን ሚስቴ፣ ‹‹ለመሆኑ፣ በዚህ ሌሊት የምትቀሰቅሰኝ ለምንድነው?›› ልትለኝ ትችላለች፤ እኔም እንቅልፏን እንደምትወድ ስለማውቅ፣ በተቻለ መጠን ልቀሰቅሳት አልፈልግም፡፡ እርሷም እኔን ከእንቅልፌ መቀስቀስ እንደማትፈልግ አውቃለሁ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ግን፣ በየትኛውም ሰዓት ከእኔ ጋር ለመሆን ፈቃደኛ ነው፡፡ ስለ ቀጣዩ ቀን ውሎ ከእኔ ጋር መነጋገር በጣም ይፈልጋል፤ እንዲያውም አንዳንዴ ምን ሊሆን እንደሚችል መጠነኛ ዕይታ ሊሰጠኝ እንኳ ይችላል፡፡ እያንዳንዱን ቀን በእርሱ ፊት ወይም ሓልዎት ውስጥ ሆኜ መጀመርን የምወደው በዚህ

ምክንያት ነው፡፡ እርሱ አጋሬ ነው፤ ከእርሱ ጋር የሚኖረኝ ኅብረት የቀኑ ውሎዬ ሁነኛ አካል ነው፡፡

በዚህ ኅብረት ውስጥ ዋናው አጋር መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ማስታወስ ጠቃሚ ነው፡፡ በኤፌሶን ለነበሩ መሪዎች ጳውሎስ ሲናገር፣ ‹‹ለራሳችሁና መንፈስ ቅዱስ ጠባቂ አድርጐ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ፣ በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ›› አለ (ሐዋርያት ሥራ 20÷28)፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹ኢየሱስ ጠባቂ አድርጐ በላዩ ለሾማችሁ መንጋ ሁሉ ተጠንቀቁ›› አለ ማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን፣ ‹‹በገዛ ደሙ›› ዋጀ፡፡ የሥላሴ አካል የሆነው መንፈስ ቅዱስ፣ በአሁኑ ዘመን በዚህ ምድር ነው ያለው፤ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ይሾማል፤ ጉዳይዋን ሁሉ ያስተዳድራል፡፡ ኃላፊው እርሱ አለው - ወይም በሌላ አነጋገር እርሱ ዋናው ባለ ድርሻ ነው፡፡ በእኛ ውስጥና ከእኛ ጋር አብሮ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ፣ ጳውሎስ በጣም ይገነዘባል፡፡

ለዚህ ሌላ ምሳሌ የሚሆነን ሐዋርያት ሥራ 13 ላይ ይገኛል፡፡ ‹‹እነዚህም ጌታን እያመለኩና እየጾሙ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ፣ በርናባስንና ሳውልን እኔ ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ፡፡ … በርናባስና ሳውልም በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ›› (ቁጥር 2 እና 4)፡፡ እዚህም ላይ መንፈስ ቅዱስ በአጋርነት፣ (በኅብረት) ከሐዋርያቱ ጋር ሲሠራ እንመለከታለን፡፡ ኢየሱስ ከአብ ጋር በሰማይ ነው ያለው፡፡ በእንዲህ ያለ አስደናቂ ሕይወት የእኛ አጋር እንዲሆን፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድር ተልኳል፡፡

ቀን 3

## ጥብቅ የእርስ በርስ ግንኙነት

እስቲ እንደ ገና 2 ቆሮንቶስ 13÷14 እንመልከት፤ ‹‹የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ፤ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡›› ኅብረት ለሚለው ቃል ‹‹አንድነት›› እና ‹‹አጋርነት›› የሚል ትርጉም ሰጥተን እንደ ነበር ይታወሳል፤ አሁን ደግሞ እነዚህ ሁለት ቃሎችን በተመለከተ ካገኛችሁት አዲስ መረዳት አንጻር ይህ ጥቅስ ተመልከቱ፡፡ የጳውሎስ አነጋገር ስፋትና ጥልቀት ምን ያህል እንደ ነበር ተገነዘባችሁ?

ግን እዚያም ላይ አላበቃም፡፡ ኮይኖንያ የሚለው ቃል፣ ‹‹ጥብቅ እርስ በርስ ኅብረት›› ማለትም ነው፡፡

አሁን ደግሞ በወጣትነት ዘመኔ ከነበረኝ አስተሳሰብ አኳያ ይህን ልበል፤ ጥብቅ የእርስ በርስ ኅብረት ስለሚለው ቃል ሳስብ ቶሎ ወደ አእምሮዬ የሚመጡት ቢትልሶች ናቸው፡፡ ወጣት በነበርኩ ጊዜ ፓል ምካርትኒ የሚል ስም ከሰማሁ፣ (ይኼ እንግዲህ ቢትልሶች ከመለያየታቸው ረጅም ዘመን በፊት መሆኑ ነው) ሌሎች ቢትልሶች ማለትም ጆን ሊኖን፣ ጆርጅ ሐሪሰንና ሪንጎ ስታር ትዝ ይሉኛል፡፡ በዚያ ዘመን ቢትልሶችን እንደ ግለ ሰብ አላሰባቸውም ነበር፤ ለእኔ እንዲሁ ቢትልሶች ብቻ ነበሩ፡፡

‹‹ጥብቅ የእርስ በርስ ኅብረት›› ለሚለው ሌላ ምሳሌ የሚሆኑን ሦስቱ ስቱጂዎች ናቸው፡፡ ከሞይ፣ ላሪ እና ከርሊ ውጪ ሦስቱ ስቱጂዎች ተብለው መጠራት አይችሉም፡፡ ከመካከላቸው አንዱን ብቻ ይዛችሁ፣ ስለ እነርሱ ብትነጋገሩ ጉዳዩ አስቂኝ ነው የሚሆነው፡፡ ሦስቱ ስቱጂዎችን ታላቅ ያደረጋቸው ሦስቱም በአንድነት ያከናወኑት ነው፡፡ አንዱ በሌላው ተደጋፊ ነበር፡፡

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ጥብቅ የእርስ በርስ ኅብረት ስለ ነበራቸው ሰዎች ሳስብ መጀመሪያ ወደ አእምሮዬ ከሚመጡት ሰዎች አንዱ ዶክተር ፓል ዮንጊ ቾ ነው፡፡ ዶክተር ቾ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ውስጥ በጣም ትልቅ ከሆኑ ቤተ ክርስቲያኖች የአንዱ ፓስተር ነው፡፡ በ1980 ለመጀመሪያ ጊዜ ሳገኘው የተሰማኝን በፍጹም አልረሳውም፡፡ እኔ አባል የነበርኩበትን ቤተ ክርስቲያን ለመጐብኘት ለመጀመሪያ ጊዜ መምጣቱ ነበር፤ ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ከነበረኝ ኃላፊነት የተነሣ እርሱን የመቀበልና የማስተናገድ ዕድል ነበረኝ፡፡ ዶክተር ቾን ባገኘሁበት ዘመን ከዚያ ቀደም ሲል ለዓመታት ብዙ አገልጋዮችን ተቀብዬ አስተናግጄ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከዶክተር ቾ ጋር ፊት ለፊት መገናኘት ለእኔ ፍጹም የተለየ ነበር፡፡ መኪናዬ ውስጥ ሲገባ፣ የጌታ መገኘትም አብሮት እንደ ገባ ተሰማኝ፡፡ ወዲያውኑ ማልቀስ ጀመርኩ፤ እንባ ፊቴ ላይ ይወርድ ጀመር፡፡ ከአገልግሎቱ በፊት እንዲረበሽ ስላልፈለግሁ ዝም ለማለት ሞከርኩ፤ ቆየት ብሎ ግን አንድ ቃል መናገር እንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡ ድምፄን ዝግ አድርጌ፣ ‹‹ዶር ቾ፣ የእግዚአብሔር መገኘት እዚህ መኪና ውስጥ አለ›› አልኩት፡፡ ፈገግ ብሎ ራሱን እየነቀነቀ፣ ‹‹አውቃለሁ›› አለኝ፡፡

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን ኅብረት አስመልክቶ ዶክተር ቾ ብዙ መጻፉንና ብዙ መስበኩን ግምት ውስጥ ሳስገባ፣ ከእርሱ ጋር ፊት ለፊት መገናኘቴ ለእኔ የተለየ ትርጉም ሰጥቶኛል፡፡ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ያህል በየቀኑ እንደሚጸልይ፣ ይበልጥ ደግሞ በመንፈስ እንደሚጸልይ ሲናገር ሰምቻለሁ፡፡ ዶክተር ቾ ምርጥ የሚለውን ሰዓት ለመንፈስ ቅዱስ መስጠትን ተቀዳሚ ጉዳይ አድርጎአል፤ በዚህም ምክንያት በሕይወቱ የነበረው የእግዚአብሔር መገኘት እጅግ ብርቱ ነበር፡፡

ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ እሑድ በአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰብኬ ነበር፡፡ በዚያ ከሰዓት በኃላ ለምሽቱ አገልግሎት ወደዚያ ቤተ ክርስቲያን ስንመለስ፣ ከአምልኮ በኃላ ለአርባ አምስት ደቂቃ ማስተማር ነበረብኝ፡፡ ግን እኔ ያንን ሳላደርግ መንፈስ ቅዱስ ይንቀሳቀስ ጀመር፤ ሰዎች ይድኑና ይፈወሱ ጀመር፡፡ ለሁለት ሰዓት ያህል የመናገር ዕድል አላገኘሁም ነበር፡፡ መጨረሻ ላይ ወደ መድረክ ከመውጣቴ በፊት ፓስተሩ እያለቀሰ ወደ እኔ መጥቶ፣ «ጆን ይህን ቤተ ክርስቲያን ላለፉት ስምንት ዓመቶች መርቻለሁ፤ እንደ ዛሬው ግን የእግዚአብሔር መገኘት በኃይል ተሰምቶኝ አያውቅም!» አለኝ፡፡ እኔም ወዲያውኑ፣ «ለዚያ ምክንያት አለ፡፡ ዛሬ ጠዋት ስለ መንፈስ ቅዱስ ተነጋግረን ነበር፤ ስለ እርሱ ከተናገራችሁ እርሱ ራሱን ይገልጣል» አልኩ፡፡ እንግዲህ እኔና እናንተ እንደ «ተራ» አማኞች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ጥብቅ የእርስ በርስ ኅብረት ሲኖረን፣ የሚሆነውን ለማሳየት ይህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡

## ኅብረት መቀራረብ ነው

ኮይኖንያ የሚለው ቃል የመጨረሻ ትርጉም፣ «መቀራረብ» ማለት ነው፡ ፡ በመሠረቱ 2 ቆሮንቶስ 13÷14 ላይ ጳውሎስ ኮይኖንያ በሚለው ቃል ሲጠቀም ምን ማለቱ እንደ ነበር ይህ ቃል በተሻለ ሁኔታ ይገልጠዋል፡፡ መቀራረብ መዳበር የሚችለው ኅብረት ወይም አጋርነት ሲኖር ብቻ ነው፤ ይሁን እንጂ አንድምታው ከእነዚህ ሁለት ቃሎችም ያልፋል፡፡ መቀራረብ የልብን ጥልቅ ሐሳብ፣ ምስጢርንና ምኞትንም ሁሉ ይጨምራል፡፡

ዘ ሜሴጅ የተሰኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፣ «እጅግ ጥብቅ የሆነው

የመንፈስ ቅዱስ ወዳጅነት ከእናንተ ጋር ይሁን›› ይላል (2 ቆሮንቶስ 13÷14)፡፡ መቀራረብ የወዳጅነት በጣም ጥልቅ ደረጃ መሆኑን ነው የማየው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ወዳጃችሁ መሆን እንደሚፈልግ፣ ከእናንተ ጋር ኅብረት ማድረግ እንደሚፈልግ፣ በፍጹም አትርሱ፡፡ ያዕቆብ 4÷5፣ ‹‹በውስጣችን ያሳደረው መንፈስ አብዝቶ ይቀናል›› ይላል፡፡ እኔና እናንተን በተመለከተ ይቀናል፤ ጊዜና ትኩረታችንን እንድንሰጠው እጅግ ይፈልጋል፡፡ አስቲ አስቡ፣ መንፈስ እግዚአብሔር ነው፤ ከእርሱ የሚሰወር ምንም የለም፡፡ ጥበቡ፣ ዕውቀቱ፣ መረዳትና ማስተዋሉ ገደብ የለሽ ነው - እርሱ ራሱን ሊገልጥላችሁ ይፈልጋል፡፡ ስለ አንድ ከፍ ያለ ዋጋ ያለው ነገር ካወቅሁ ወይም ከተረዳሁ፣ ያንን ለሚቀርቡኝ ሰዎች ለማካፈል በጣም እጓጓለሁ፡፡ እናንተም እንደዚያ እንደምትሆኑ አስባለሁ፤ መንፈስ ቅዱስም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

ብዙ ጊዜ አማኞች መንፈስ ቅዱስን ባገለለ መልኩ፣ ወደ ኢየሱስ መቅረብ ይሞክራሉ፡፡ ይህ ፈሪሳውያን ካደረጉት ስሕተት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ኢየሱስን፣ ‹‹እኛስ በዝሙት የተወለድን አይደለንም፤ አባታችን አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው›› አሉት፡፡ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፣ ‹እግዚአብሔር አባታችሁ ቢሆን ኖሮ፣ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና በወደዳችሁኝ ነበር፤ እርሱ ላከኝ እንጂ፣ በገዛ ራሴ አልመጣሁም›› (ዮሐንስ 8÷41-42)፡፡ ፈሪሳውያን ኢየሱስን ባገለለ መልኩ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ፈልገው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ከዚያ የተለየ ሐሳብ እንዳለው መቀበል አልፈለጉም፡፡ እርሱና አባቱ አንድ እንደ ሆኑ ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ነግሮአቸው ነበር፡፡ እንዲያውም በኋላ ላይ፣ ‹‹እኔን ብታውቁኝ ኖሮ አባቴንም ባወቃችሁት ነበር›› ብሏል (ዮሐንስ 14÷7)፡፡ ፈሪሳውያን ግን ያን መስማት አልፈለጉም፡፡ በልጁ (በወልድ) በኩል ወደ እግዚአብሔር (አብ) መምጣት ስላልፈለጉ በእውነት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አልቻሉም፡፡

በተመሳሳይ መንገድ ከእንግዲህ በዚህ ምድር እንደማይሆንና ረዳታችን እንዲሆን (ልክ አዳኛችን ኢየሱስን የሚመስለውን) እግዚአብሔር አባት መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ኢየሱስ ግልጽ አድርጎአል (ዮሐንስ 16÷7)፡፡ ወልድ አብን ለመግለጥ እንደ ተላከ ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም ወልድን ለመግለጥ ተልኳል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ማክበር እንደሚወድ ማስታወስ ይኖርብናል፡፡ ስለሆነም በእርግጥ የበለጠ ስለ ኢየሱስ ማወቅ የምትፈልጉ

ከሆነ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሰፊ ጊዜ ማሳለፍ አለባችሁ፡፡ መንፈስ ኢየሱስን በጣም ግልጽ ያደርግላችኋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ መንፈስ ቅዱስ የሚገለጠው እርሱ ራሱ ሲከበር ነው፡፡ መንፈስን ስናከብረው፣ እርሱ ራሱን ይገልጥልናል፣ በአስደናቂው የእርሱ መገኘትና እርሱ ስለሚገልጠው ጌታ የበለጠ በመረዳት ደስ እንሰኛለን፡፡

በአገልግሎት ካሳለፍኳቸው ሰላሣ ዓመቶች በላይ፣ ይህን እውነት የሚተካ ምንም አላገኘሁም - ኢየሱስን በሚገባ ያወቁ ሰዎች፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የጠበቀ መቀራረብ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ኢየሱስን የሚገልጥልን መንፈስ ራሱ ከመሆኑ አንጻር ይህ የተሟላ ትርጉም ይኖረዋል፡፡

## የመንፈስን ሰብዕና መረዳት

ከአንድ ሰው ጋር በጣም መቀራረብ የምፈልግ ከሆነ፣ የዚያን ሰው ሰብዕና ማወቅ መፈለግ አለብኝ፡፡ እንዲህ ያለው ግንዛቤ፣ ከዚያ ሰው ጋር ያለንን ግንኙነት እንደሚጠናክረውና ከእርሱ ጋር ላለን መቀራረብ ጥልቀት እንደሚሰጠው ግልጽ ነው፡፡

ለብዙ ዓመታት ያህል ከአራቱም ወንዶች ልጆቼ ጋር ያለኝ መቀራረብ አንድ ዓይነትና ተመሳሳይ ነበር፡፡ በመሠረቱ ይህ አንዳንድ ጥያቄዎች ያስነሣል፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ልጅ የግሉ ሰብዕና አለው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከእኔ ይልቅ ሚስቴ ንቁ ናት፤ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት በሚገባ እንዳስተውል የረዳችኝም እርሷ ናት፡፡ እያንዳንዱን ልጅ ልዩ የሚያደርገውን ሰብዕና መረዳቴ ከእነርሱ ጋር የነበረኝን ግንኙነት አጠናክሮልኛል፡፡

ከሚስቴ ጋር ካለኝ ጥብቅ መቀራረብ የተነሣ፣ እርሷ ራሷን ስለምትገልጥበት ሁኔታ በቀላሉ ማወቅ እችላለሁ፡፡ ከሰላሣ ዓመት በላይ በትዳር የኖርን እንደ መሆናችን መጠን፣ እንዲህ ያለውን ጥብቅ መቀራረብ ማዳበር ችለናል፤ መቀራረብ ሰፋ ያለ ጊዜ የመስጠት ውጤት ነው፡፡ ሊዛ በዐይኗ አንድ ነገር ካመለከተኝ ምን ማለቷ ሊሆን እንደሚችል አንድ ገጽ ሙሉ መጻፍ እችላለሁ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ እርሷ አንዲት ቃል ሳትናገር፣ ምን እንደምትፈልግ የማውቅበት ጊዜ አለ፡፡ አብረን ብዙ ከመኖራችን የተነሣ ምን ዐይነት ምግብ እንደምትወድና እንደምትጠላ አውቃለሁ፡፡ ይህ ተራ ምሳሌ እንደ ሆነ

አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ አብዛኞቹ ግላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ነገሩ እውነት ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ መቀራረብ በአንድ ቀን የሚመጣ አይደለም፡፡ ለዓመታት ሰፋ ያለ ጊዜ መስጠትና ግንኙነትን ማዳበርን ይጠይቃል፡፡ ከእኔ የበለጠ ሚስቴ የምትወደውንና የምትጠላውን የሚያውቅ የለም፤ ከሚስቴ የበለጠ እኔ የምወደውንና የምጠላውን የሚያውቅ የለም፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ከእርሱ ጋር ለመገናኘትና በእርሱ ፊት ሰፋ ያለ ጊዜ ለማሳለፍ ፈቃደኞች ስንሆን፣ መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ያለን መረዳት በዚያው መጠን ያድጋል፡፡

ቀን 4

## ባሕርዩን ማወቅ

ከዮሐንስ 14 እስከ 16 ባሉት ምዕራፎች ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፣ አሥራ ዘጠኝ ጊዜ እርሱ፣ የእርሱ፣ ራሱ በተሰኙ ተውላጠ ስሞች ተጠቅሟል፡ ፡፡ መንፈስ ቅዱስ አካል መሆኑ ምንም ጥርጥር የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡ በድጋሚ ለመናገር ያህል፣ መንፈስ ቅዱስ አካል ነው ስል፣ ልክ እንደ እኛ የሰው ልጅ ነው ማለቴ አይደለም፡፡ የሰው ልጆች በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠሩ መሆናቸውን አስታውሱ፡፡ ይህም ማለት፣ ‹‹ሰብዕና›› በማለት የምንጠራው አንዳንድ ገጽታዎች፣ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ያንጸባርቃሉ ማለት እንጂ፣ እግዚአብሔር በትክክል እንደ እኛ ነው ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም፣ የእርሱ አካልነት፣ እኛ ገደብ ወይም ልክ ልናበጅለት የማይቻለን አንዳንድ ገጽታዎች ይኖሩታል፡፡

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንዴት እንደምቀራረብና እንዴት ከእርሱ ጋር መንቀሳቀስ እንዳለብኝ በመጣም የረዱኝ አንዳንድ የተማርሁዋቸው ነገሮች አሉ፡፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ ለመናገር ጥቅም ላይ የዋሉ ተውላጠ ስሞችን በግሪኩ ትርጉም መሠረት ሳጠና የተረዳሁት የግሪኩ ተውላጠ ስሞች ምንም ዐይነት ጾታ (የወንድም ሆነ የሴትን) የማያመለክቱ መሆናቸውን ነው፡፡ እየተናገረ ያለው ስለ አንድ አካል እስከ ሆነ ድረስ፣ ለሴትም ሆነ ለወንድ ጥቅም ላይ መዋል ይችላሉ፡፡

በአማርኛም ሆነ፣ በእንግሊዝኛ እንዲህ ያለ ተውላጠ ስም የለንም፡፡ እርሱ ወይም እርሷ የሚሉ ተውላጠ ስሞች አሉን፡፡ በእንግሊዝኛው ቃል It

የሚለው ቃል ዕቃን ወይም እንስሳን ለማመልከት ብቻ ጥቅም ላይ ይውላል፣ አማርኛችን ግን ይህ መግለጫ የለውም፡፡ እርሱ ስንል ወንድን ያመለክታል፤ እርሷ ስንል ሴትን ያመለክታል፡፡ የወንድን ወይም የሴትን ጾታ የማያመለክት ከጾታ ነጻ የሆነ ተውላጠ ስም የለንም፡፡ አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ግሪክ ቋንቋ ግን ወንድ ወይም ሴት መሆኑን የማያመለክት ተውላጠ ስም አለ፤ ብዙ ጊዜ ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው ስለ መንፈስ ቅዱስ በሚነገርበት ጊዜ ነው፡ ፡ ያም ሆኖ ግን የሚያመለክተው አካልን እንጂ፣ ግዑዝ ነገርን እንዳይደለ በድጋሚ መናገር እፈልጋለሁ፡፡

ብሉይ ኪዳንም ውስጥ ተመሳሳይ ነገር ማየት ይቻላል፡፡ በመጀመሪያው ዕብራይስጥ ቋንቋ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ ሲነገር ሴት ልጅ ከምትሠራው አንጻር የተነገረባቸው ብዙ ጥቅሶች አሉ፡፡ (ይህም የሴት አካልን ለማመልከት አይደለም)፡፡ ብዙ ጊዜ ዕብራውያን ሲጽፉ ተግባርን መሠረት በማድረግ ነው (የተደረገውን እንጂ፣ ያደረገው ማን ወይም ምን መሆኑን አያመለክትም)፡፡ በየትኛውም የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በሴት ጾታ አልቀረበም፤ አንዳንድ ሥራዎቹ ግን ሴት ልጅ የምትሠራውን በሚያመለክት መልኩ ቀርበዋል፡፡

ይህ በጣም ጥልቅ ርዕሰ ጉዳይ ነው፤ ያንን እዚህ ለማብራራትም ቦታው አይደለም፤ ያም ሆኖ ግን አንድ ነገር በጣም ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ፣ መንፈስ ቅዱስ አንስታይ ጾታ ነው ብዬ አላምንም፡፡ አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ያለ ትምህርት ያስተምራሉ፤ በበኩሌ ግን መሠረት የለሽና በቂ የቅዱሳት መጻሕፍት ድጋፍ እንደሌለው ነው የተረዳሁት፡፡ እንዲህ ያለውን አስተሳሰብ ከአእምሮአችሁ አውጡ፤ መንፈስ ቅዱስ እንስት አምላክ አይደለም፡፡

እዚህ ላይ መናገር የፈለግሁት ይህን ነው፡፡ እኛ በእርሱ መልክና አምሳል ተፈጠርን እንጂ፣ እግዚአብሔር በእኛ መልክና አምሳል አልተፈጠረም፡፡ ይህ ተራ ነገር እንደሚመስል አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ይህን ጥናት እየገፋን ወደ ፊት ስንሄድ ይህ እውነት በጣም ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ዘፍጥረት 1፥27፣ ‹‹እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክ ፈጠረው፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው›› ይላል፡፡ ከዘፍጥረት መጽሐፍ ወንድና ሴትን በራሱ መልክ እንደ ፈጠረ እናያለን፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ መነሣት ያለበት ጥያቄ፣ እግዚአብሔር ወንድንና ሴትን የፈጠረው በራሱ

መልክ ከሆነ፣ «እንስታዊነት» የምንላቸው ባሕርያት ከእግዚአብሔር የተገኙ ናቸው ማለት አይቻልምን? የመንፈስ ቅዱስ ማንነት፣ እኛ ለተባዕታይም ሆነ አንስታይ ጾታ ካለን ግንዛቤ ያለፈ ወይም የበለጠ ነው ማለት አይቻልምን? አዎን፣ እንደዚያ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ወንድም ሆነ ሴት የተፈጠሩት በእግዚአብሔር መልክ ነው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ የተጠቀምኩት፣ «እርሱ»፣ «የእርሱ» በተሰኙ ቃሎች እንደ ነበር ይታወሳል፤ በዚሁ ሁኔታም እዘልቃለሁ። መንፈስ ቅዱስ እንስታዊ የምንላቸው ዓይነት ባሕርት አሉት የሚለው ሐሳብ እንግሊዝኛ ወይም አማርኛ ተናጋሪ ለሆኑ ሰዎች ግራ የሚያጋባ ነው። ታዲያ፣ ይህን አስመልክቶ የምጽፈው ለምንድነው? ስለ መንፈስ ቅዱስ ያለንን ግንዛቤና ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት በማሻሻል ረገድ እንደሚጠቅመን እርግጠኛ ባልሆን ኖሮ፣ ጨርሶ ይህን ርዕሰ ጉዳይ አላካትተውም ነበር።

## እርሱ በቀላሉ የሚያዝንና ሩኅሩኅ ነው

ወደ ፊት ከመግፋቴ በፊት እስቲ፣ ስለ ራሴ ታሪክ አንዳንድ ነገር ልንገራችሁ፡ ፡ ወላጅ አባቴ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተሳተፈ ሰው ነበር። በአሁኑ ጊዜ ዘጠና ሦስት ዓመቱ ሲሆን፣ በጣም ሲበዛ ነው የምወደው። አባቴ በሕይወት ዘመኔ በጣም የጠቀሙኝ ብዙ ነገሮች አስተምሮኛል። አባቴ ዝግጁ እንድሆን ያላስተማረኝ አንድ ነገር ቢኖር፣ እንዴት ሚስት ማግባት እንዳለብኝ ብቻ ነው። አንድ ጊዜ ጴጥሮስ፣ «አብረዋችሁ ስለሚወርሱ ሚስቶቻችሁን በመረዳት አክብሯቸው» ብሎ ነበር (ትርጒሙ የተወሰደው ከአዲስ ኪዳን ሕያው ቃል ነው - 1 ጴጥሮስ 3፥7)። ሊዛን ባገባሁ ጊዜ፣ «በመረዳት» እያከበርኳት አልነበረም። ከዚያ በፊት ከሊዛ ውጪ ሌላ ሴት ወድጄ ወይም ይህን ያህል ተቀራርቤ አላውቅም ነበር። ስለሆነም፣ ከሌሎች ወንዶች ጓደኞቼ የምጠብቀውን ነበር ከእርሷም እጠብቅ የነበረው። ይህ ደግሞ ትዳር ውስጥ ስኬታማነትን እንደማያስገኝ አንዳንዶቻችሁ መረዳት ትችላላችሁ። ከሴት ልጅ ጋር እንዴት መቀራረብ እንዳለብኝ ገና ብዙ መማር ነበረብኝ።

አንድ መማር የነበረብኝ ትልቅ ነገር ሊዛን በጨዋነት ማናገር ነበር። እንዳለ መታደል ሆኖ ከቤተ ሰቤ ጋር የነበረኝ ግንኙነት ጥሩ አልነበረም። በኋላ ግን መንፈስ ቅዱስ ስለ ወቀሰኝ ይቅርታ መጠየቅና ነገሮችን ማስተካከል ችያለሁ። አንድ ጊዜ ከልጆቼ አንዱ ጋር በጣም ተጋጨሁ፤ ስለዚህም ወደ እርሱ ሄጄ ይቅርታ መጠየቅ ነበረብኝ። እርሱም ወዲያውኑ ይቅርታ አደረገልኝና በመካከላችን የነበረ ነገር ሁሉ እንደ ገና ተስተካከለ። ሊዛን በተመለከተ ግን ነገሩ የተለየ ነበር። ወንዱ ልጄ ላይ በወሰድሁት ጠንከር ያለ ርምጃ ለጥቂት ቀኖች በጣም አዝና ነበር። በመሠረቱ እንዲህ መሆኑ ግንኙነታችን ውስጥ የነበረው ስስነት ተፈጥሮአዊ ውጤት እንጂ፣ ይህን ያህል እኔ ላይ ተሰናክላለች ወይም ቂም ይዛለች ማለት አልነበረም። ከወንዱ ልጄ ጋር ዕርቅ ያደረግሁት ወዲያውኑ ቢሆንም፣ ከሚስቴ ጋር የነበረኝን ግንኙነት ለማስተካከል ግን በመጠኑም ቢሆን ነገሮችን አወጣ አወርድ ነበር። ከልጄ ጋር ከተጋጨሁ ሁለት ቀን በኋላ፣ «ልጃችንን የምትናገርበት ሁኔታ በጣም አሳዝኖኛል» አለችኝ። ይህ የሊዛ የተለየ የሕይወት ስጦታ መሆኑን መረዳት ችዬአለሁ። እንደ ብዙዎች ሴቶች ሁሉ እርሷም ቤተ ሰባዊ መቀራረብን የምታጠብቅና፣ ለእርሷ ቅርብ ከሆኑት አንዱ ሲጐዳ ማየት የማትፈልግ ናት።

ምናልባት መንፈስ ቅዱስም እኛ በተለምዶ የእንስታዊ ፀባይ የሚል ስያሜ የምንሰጠው ዐይነት ባሕርይ ይኖረው ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስ፣ «የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ» ይላል (ኤፌሶን 4፥30)። *Sparkling Gems from the Greek*, በሚል መጽሐፉ ሪክ ሬነር እንዳመለከተው፣ እዚህ ላይ ማዘን የሚለው ቃል፣ «ጥልቅ ሀዘንና ጉዳት» የሚል ሐሳብ አለው። በጣም የሚቀራረቡ ሁለት ሰዎች ብቻ የሚረዱት ዓይነት ጉዳት ወይም ሕመም ያመለክታል። ስለሆነም፣ ጳውሎስ በመሠረታዊ ይዘቱ «በጣም የወደዳችሁን ሰው አታሳዝኑት ወይም አታስከፉት» እያለ ነው ማለት ይቻላል። እስቲ ይህን ክፍል በዐውዱ መሠረት እናንብበው፤

> እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎችን የሚያንጽና ሰሚዎችን የሚጠቅም ቃል እንጂ፣ የማይረባ ቃል ከአፋችሁ አይውጣ። ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ፤

፡ መራርነትን ሁሉ፣ ቁጣንና ንዴትን፣ ጭቅጭቅንና ስድብን፣ ከማንኛውም ክፋት ጋር ከእናንተ ዘንድ አስወግዱ፡፡ እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ፣ እናንተም ይቅር ተባባሉ፤ እርስ በርሳችሁ ቸሮችና ሩኅሩኆች ሁኑ፡፡

(ኤፌሶን 4፥29-32)

*መንፈስ ቅዱስ ምን ያህል ሩኅሩኅና በቀላሉ የሚጐዳ መሆኑን አያችሁ?*

ሩኅሩኅነት መደነቅ ያለበት ጠንካራ ጐን ነው፡፡ ጳውሎስም ርኅሩኆች እንድንሆን ነግሮናል፡፡ ከሚስቴ ጋር ያለኝ ግንኙነት ጤናማና ሕይወት ያለው እንዲሆን የምፈልግ ከሆነ፣ ሩኅሩኅ መሆንና በዚያ መሠረትም ልጆቼን ማናገር ይኖርብኛል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ጤነኛና ሕይወት ያለው ግንኙነት እንዲኖረን ከፈለግን፣ እርሱን የሚያሳዝኑትን ነገሮች ለይተን ማወቅና መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ መንፈስን ማሳዘን ወይም ማስከፋትን ተከትለው ከሚመጡ መጥፎ ፀባዮች ማለትም፣ ከማይረባ ቃል፣ ከመራራነት፣ ከቁጣ፣ ከንዴት፣ ከጭቅጭቅና ከስድብ ጋር በማያያዝ ጳውሎስ ማቅረቡ የተለየ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ያደርገዋል፡፡ ሚስቴ አዝና የነበረው እንዲህ ባለው ፀባይ መሆኑ ነገሩን ተመሳሳይ ያደርገዋል፡፡ በድጋሚ ለመናገር ያህል፣ ብዙ ጊዜ እኛ የሴቶች ፀባይ ነው በማለት የምንጠራቸው አንዳንድ በጐ ባሕርያት መንፈስ ቅዱስም ይኖረው ይሆን? በማለት እጠይቃለሁ፡፡

ጳውሎስ፣ ‹‹ኢየሱስን አታሳዝኑ›› አላለም፤ ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር አብን አታሳዝኑ›› አላለም፤ ይልቁን ለይቶ በማመልከት፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑ›› ነበር ያለው፡፡ መንፈስ ቅዱስ የእኛን ልብ መኖሪያው አድርጐአል፡፡ ወደምንሄድበት ሁሉ ይሄዳል፤ ያ ደግሞ የቀረበ ግንኙነትን ነው የሚያመለክተው፡፡ ስለዚህም በሕይወታችን እየሆኑ ባሉ ነገሮች ያዝናል፤ ይከፋል፡፡

እስቲ ይህን ከተለየ አንጻር ማየት ሞክሩ፡፡ አንድ ሰው እኔን ቢያውከኝ ምንም ማለት ላይሆን ይችላል፤ ሚስቴን ቢያውካት ግን ትልቅ ችግር ላይ ይወድቃል፡፡ ‹‹ማንም ሰው በሰው ልጅ ላይ (ኢየሱስ) የሚናገረው ክፉ ቃል ይቅር ይባላል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገረው ክፉ ቃል ግን በዚህም ሆነ

በወዲያኛው ዓለም ይቅር አይባልም›› በማለት ኢየሱስ ሲናገር ተመሳሳይ ነገር ማመልከቱ ነበር (ማቴዎስ 12÷32)፡፡ እግዚአብሔር አብ፣ (የአባቱን ፈቃድ ብቻ እንዲናገር ግልጽ ባደረገው ወልድ በኩል ራሱን የገለጠው) ለመንፈስ ቅዱስ ይህን ያህል ከለላ ማድረጉ አይገርምም? ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሊኖረን የሚገባውን ግንኙነት በተመለከተ፣ አብ እንዲህ ያለ ከለላ አላደረገም፤ መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ግን እንደዚያ አድርጓል፡፡

በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለው ግንኙነት ሙሉ በሙሉ መረዳት የማንችለው ምስጢር ነው፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባለን ግንኙነት ይህን ልዩነት መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ ከእርሱ ጋር የሚኖረንን መስተጋብራዊ ግንኙነት አጥብቀን መያዝና መጠንቀቅ አለብን፡፡ ልናሳዝነው፣ አንዳንዴም በጣም ልናስከፋው እንደምንችል ማስታወስ አለብን፡፡ ከእርሱ ጋር በሚኖረን ግንኙነት ይህን መገንዘብ፣ ይህን ያህል አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ምክንያቱም፣ ከእርሱ ጋር ሊኖራችሁ የሚገባውን ግንኙነት በሚገባ ካልተረዳችሁ፣ በሕይወታችሁ የእርሱ መገኘት እንዳይገለጥ ዕንቅፋት ልታኖሩ ስለምትችሉ ነው፡፡

ቀን 5

## እርሱ ስሱ ነው (Sensitive) ሆኖም ብርቱ ነው

መንፈስ ቅዱስ አጽናኝ ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ለመሆኑ፣ ትንንሽ ልጆች አንድ ዓይነት ጉዳት ሲደርስባቸው ብዙ ጊዜ ቶሎ ሮጠው የሚሄዱት ወደ ማን ነው? ብዙ ጊዜ ወደ እናታቸው ነው የሚሄዱት፡፡ እንግዲህ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር አንዳንድ የአሜሪካ ክፍለ ሀገሮች የወጣቶችን ወንጀል የሚዳኙ ሴት ባለ ሥልጣናት መሆን አለባቸው የሚል ፖሊሲ የቀረጹት፡፡ ሐዋይ በቅርቡ የታሠሩ ወጣት ወንጀለኞች ጉዳይ በማስተናገድ ረገድ ሴቶች የመጀመሪያው እንዲሆኑ የሚያበረታታ ፖሊሲ አላት፡፡ እነዚህ ወጣቶች ለሴት ባለ ሥልጣኖች የተሻለ ምላሽ እንደሚሰጡ ተረድተዋል፡፡ በተፈጥሮአቸው ሴቶች የማጽናናትና የማበረታታት ችሎታ አላቸው፡፡ አሁንም በድጋሚ ለመናገር ያህል መንፈስ ቅዱስ ሴት ነው እያልኩ አይደለም፡፡

በአንዳንድ መንገድ መንፈስ ቅዱስን ከንጉሥ ዳዊት ጋር አመሳስለዋለሁ፡

፡ ዳዊት ምን ያህል ሩኅሩኅ እንደ ነበር ልብ አድርጋችኋል? ምንም እንኳ የአቤሴሎምን ዐመፅ እንዲያስቆሙ ለወታደሮቹ የተናገረ እርሱ ራሱ ቢሆንም፣ አቤሴሎም የሞተ ጊዜ አምርቶ አልቅሶአል (2 ሳሙኤል 19 ይመ)፡፡ ከተለያየ አጋጣሚዎች ዳዊት ሲያለቅስና መዝሙር ሲጽፍ እናያለን፡ ፡ በጣም የጠበቀና የጠለቀ ጓደኝነትን በማመልከት ረገድ፣ ከዮናታን ጋር የነበረው ግንኙነት ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ካሉት በሙሉ በጣም ምርጥ የሚባል ታሪክ ነው፡፡ ያም ሆኖ ግን ዳዊት ጦረኛ መሆኑን፣ ግዙፉን ሰው ጐልያድንና ሺህ ሰዎችን የገደለ መሆኑን አትርሱ፡፡ ምርጥ የሚባሉ ጦረኞች - ምናልባትም በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ታላላቅ የሚባሉ አርበኞች መሪ ነበር (2 ሳሙኤል 23 ይመ)፡፡ እንዲያውም በአንድ ወቅት ዳዊት ለተከታዮቹ እህልና ውሃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልነበረውን ንፉግ ሰውዬ ለመግደል ዐቅዶ ነበር፡፡ (1 ሳሙኤል 25 ይመ)፡፡ ዳዊት ጀግና ጦረኛ እንጂ፣ ሴታ ሴት የሚባል ዐይነት አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ፣ አዛኝና ሩኅሩኅም ነበር፡፡

መንፈስ ቅዱስ የኃይል መንፈስ ተብሎ መጠራቱንም ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ (ኢሳይያስ 11፥2 ይመ.)፡፡ እርሱ እጅግ ብርቱ ነው፣ በምንም ዐይነት ደካማና ዐቅመ ቢስ አይደለም፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ የሚራራ ልብ ያለውና ነገሮች በጥልቀት የሚሰሙት ነው፡፡ ከአንደበታችን በሚወጡ ቃሎችና በምናደርገው ነገር ሊያዝን፣ ሊከፋ ይችላል፡፡ ምንኛ ድንቅ አምላክ ነው!

የእርሱን ባሕርይና ሰብዕና በሙላት መረዳት ቢያቅታችሁ እንኳ መደንገጥ የለባችሁም፡፡ የእርሱ ባሕርይና ሰብዕና በእኛ መረዳት ወይም አለመረዳት የሚወሰን እንዳይደለ ሁሌም ማስታወስ አለባችሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ወደ እርሱ በቀረብን መጠን ራሱን እንደሚገልጥልን ቃል ገብቷል፡፡ ምንኛ ድንቅ ግብዣ ነው!

ቀደም ብዬ እንዳመለከትኩት የመንፈስ ቅዱስን ምስጢርና ክብር እኔ ሙሉ በሙሉ መግለጥ አልችልም (1 ቆሮንቶስ 2፥6-16 ይመ)፡፡ የእኔ ዓላማ የእርሱን ታላቅነትና ሓልዎት በሕይወታችሁ መለማመድ እንድትችሉ እርሱን ለእናንተ ማስተዋወቅ ብቻ ነው፡፡

## እንዳታሳዝኑት ተጠንቀቁ

በቅርቡ ለተወሰነ ጊዜ ቴሌቪዥን ላለማየት ተዐቅቦ አድርጌ ነበር፡፡ የበለጠውን ጊዜ ለጸሎትና ለቃሉ ሰጥቼ ስለ ነበር፣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረኝ ኅብረትና ግንኙነት በጣም ብርቱ ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ልጆቼ ተሰብስበው ፊልም እያዩ ወደ ነበረበት ሳሎን ገብቼ ነበር፡፡ በመሠረቱ ፊልሙ መጥፎ የሚባል አልነበረም፣ ግን እኔ የገባሁት አንድ ሰው ሲገደል የሚያሳይ ቦታ ላይ ሲደርስ ነበር፡፡ ቶሎ ክፍሉን ለቅቄ ወጣሁ፡፡ ምክንያቱም ከእርሱ ጋር በነበረኝ ጥልቅ ኅብረት ለመንፈስ በጣም ንቁ መሆንን አዳብሬ ነበር፤ እየታየ በነበረው ምስል እርሱ ምን ያህል ሊያዝን እንደሚችል እኔንም ተሰምቶኝ ስለ ነበር ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ እኛን ማደሪያው ያደረገን ለዘለቄታው እንደ ሆነ በፍጹም መዘንጋት የለብንም፡፡ ፊልም ወደሚታይበት ቦታ ስትገቡ፣ ቅዱስና ዘላለማዊ ብርቱ የሆነው የአጽናፈ ዓለሙ አምላክም ከእናንተ ጋር ነው፡፡ እንደማይጥላችሁና እንደማይተዋችሁ ቃል ገብቶአልና ምንጊዜም ከእናንተ ጋር ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ እርሱን የሚያሳዝን ሁኔታ ውስጥ ስትሆኑ በድንገት ፀጥ ይላል፡፡

መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝን ሁኔታ ውስጥ ስንሆን ወይም እርሱን የሚያስከፋ ነገር ስንናገር ወይም ስናደርግ ምንድነው ማድረግ ያለብን? ወዲያውኑ ይቅርታ መጠየቅ አለብን፤ ይሁን እንጂ፣ ይቅርታ አጠያየቃችን ከጥልቅ ልቦናችን መሆን አለበት፤ እንዲሁ ለደንቡ ብቻ መሆን የለበትም፡፡ ሚስቴን ካሳዘንኳት፣ ‹‹እስቲ አሁን ነገሮችን ማስተካከል እንሞክር›› የሚል ዐይነት ይቅርታ አጠያየቅ ልባዊ አይደለም፡፡ ሚስቴም ይህን ትረዳለች፡፡ ኅብረታችንን ያበላሸውን ዕንቅፋት በእውነት ከማስወገድ ይልቅ ይቅርታ አጠያየቄ ሕይወት ዘና እንዲልልኝ ብቻ እንደ ሆነ ታውቃለች፡፡ በመሠረቱ፣ እርሷ የምትፈልገው ኅብረታችንን የሚያበላሽ ምንም መጥፎ ነገር እንዳይኖርና ኅብረታችን ማስመሰል ያለበት እንዳይሆን እንጂ፣ እኔን መኮነን ወይም በዋነኛነት እኔን በደለኛ ማድረግ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መንገድ የእግዚአብሔር መንፈስ እኛን በተመለከተ አብዝቶ ይቀናል፤ ልባዊ መቀራረብ እንጂ፣ እንዲሁ ላይ ላዩን የሆነ ግንኙነት እንዲኖር አይፈልግም፡፡

ከልጆቼ አንዱን መራራ በሆነ ንግግር አሳዝኜው የነበረበት ጊዜ እንደ ነበር ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ ገልጬ ነበር፡፡ ይህ ከሆነ ጥቂት ቀኖች በኋላ ጸሎት ክፍሉ ውስጥ እያለሁ መንፈስ ቅዱስ ይህንኑ ጉዳይ በተደጋጋሚ ወደ ልቤ ያመጣው ነበር፡፡ እንዲህ የሚያደርገው በእኔ ላይ ለመፍረድ አልነበረም፡፡ ከእርሱ ጋር ያለኝን ኅብረት በተመለከተ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ ነበር መንፈስ ቅዱስ ያንን ያሳሰበኝ የነበረው፡፡ በወቅቱ ምን ያህል በጣም እንዳሳዘንሁት አልተረዳሁም ነበር፤ ያን ለማስተካከል ይቅርታ ብጠይቅም፣ ከእውነተኛ አምላካዊና ልባዊ ሀዘን አልነበረም፡፡ ይበልጥ ያሳሰበኝ፣ የሻከረውና የተጣመመው ነገር ተስተካክሎ እኔም ዘና ያለ ሕይወት እንዲኖረኝ ብቻ ነበር፡፡ እርሱ - ማለትም መንፈስ ቅዱስ ግን በጨዋነት እኔን መውቀሱንና መጐትጐቱን በመቀጠሉ፣ መጨረሻ ላይ፣ እውነተኛና ጥልቅ አምላካዊ ፀፀት ወዳለበት ቦታ አመጣኝ፤ ይህም ነፍሴን፣ (አእምሮዬን፣ ፈቃዴንና ስሜቴን) አነጻ፡፡

የፈጸሙት በደል ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ኅብረትና ግንኙነት አሽክሮት በነበረ ጊዜ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የጻፈው በተመሳይ ሁኔታ ነበር፡፡ (ቃሎቹን ስታነቡ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፉ መሆናቸውን በልባችሁ ያዙ)፡፡

> ይህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነው ሐዘን እንዴት ያለ ትጋት፣ እንዴት ያለ መልስ የመስጠት ችሎታ፣ እንዴት ያለ ቁጣ፣ እንዴት ያለ ፍርሀት፣ እንዴት ያለ ናፍቆት፣ እንዴት ያለ ተግሣጽ እንዳስገኘላችሁ ተመልከቱ፡ (2 ቆሮንቶስ 7፥11)

በበጉ ደም ይቅር የተባልንና የነጻን በመሆኑ፣ እግዚአብሔር ይመስገን፡ ፡ ሆኖም እኛ አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅ ያደረግን ቢሆን እንኳ፣ እርሱን ባሳዘንበት ሁሉ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለንን ግንኙነት በየጊዜው ማደስ ይኖርብናል፡፡ የቆሮንቶስ ሰዎች ወደ እውነተኛ ሐዘን እስኪመጡ ድረስ ጳውሎስ እንዳደረገው ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስም ከእርሱ ጋር ሊኖረን ለሚገባው እውነተኛ ኅብረት አብዝቶ የሚቀና በመሆኑ እኛን መውቀሱን ይቀጥላል፡፡ እኔ የተለማመድኩት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሐዘን፣

ነገሮችን እንዳስተካክልና የተቋረጠው ኅብረት እንደ ገና እንዲቀጥል ትጋት ሰጥቶኛል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ይቅር ለማለት ፈጣን በመሆኑ እግዚአብሔር ይመስገን!

መንፈስ ቅዱስ ጨዋ፣ ርኅሩኅና አጽናኝ መሆኑን (ብዙ ጊዜ እነዚህ ባሕርያት የሴቶች እንደ ሆኑ እናስባለን)፣ ሆኖም ብርቱ፣ ኃያልና እንደ ጦረኛ መሆኑንም በፍጹም መዘንጋት የለብንም (ብዙ ጊዜ እነዚህ ባሕርያት የወንዶች እንደ ሆኑ እናስባለን)፡፡ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረን ከተፈለገ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ባሕርያት የምንማራቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ እርሱ ባስቀመጠው መርኅ ከእርሱ ጋር መገናኘት አለብን፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ማንነትን በተመለከተ ያለን መረዳት እያደገ ሲሄድ፣ ከሁሉን ቻዩ ጋር የጠለቀ ኅብረት እንለማመዳለን፡፡

ከሚስቴ ጋር ጥሩ ግንኙነት እንዲኖረኝ ከፈለግሁ፣ እርሷን ደስ ስለሚያሰኙ ነገሮች መነጋገር አለብኝ፡፡ በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙና የእርሱ ፈቃድ የሆኑ ነገሮችን በየጊዜው መማር ይኖርብናል፡፡ ቃሉን በማንበብና በእርሱ ፊት ሰፊ ጊዜ በማሳለፍ ታላቅነቱን እየተረዳን ስንሄድ፣ እርሱ ደግሞ ራሱን ሊገልጥልን ታማኝ ነው፡፡

ቀን 1 ማሰላሰያ

# የእግዚአብሔን ድምፅ መስማት ትችላላችሁ!

*ከእግዚአብሔር የሆነ እግዚአብሔር የሚለውን ይሰማል...*

- ዮሐንስ 8፥47

የእግዚአብሔርን ድምፅ መስማት ትችላላችሁ! እርሱ ዛሬም ቢሆን ለሕዝቡ ይናገራል፤ ክቡር በሆነው መንፈስ ቅዱስ ይናገረናል፡፡ ጥልቀት ባለውና ይበልጥ ግላዊ በሆነ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲኖረን ለማስቻል፣ ጸሐፊዎቹ **ሔንሪ ብላኬቢ** እና **ክላውዴ ኪንግ** ይህን ያካፍሉናል፣

> ‹‹በሐዋርያት ሥራ ውስጥ እግዚአብሔር በግልጽ ለሕዝቡ ተናግሮአል፡፡ ዛሬም ቢሆን በግልጽ ይናገረናል፡፡ ከሐዋርያት ሥራ አንሥቶ እስከዚህ ጊዜ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ በኩል እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሲናገር ነበር... ምክንያቱም፣ እርሱ ሁሌም አማኙ ውስጥ ይኖራል፣ እርሱ በመረጠው የትኛውም ጊዜ፣ በየትኛውም መንገድ በግልጽ ሊናገራቸው ይችላል፡፡[1]

እርሱ መልካም እረኛ መሆኑንና፣ ድምፁን የምንሰማና የምናውቅ እኛም በጐቹ እንደ ሆንን ኢየሱስ ተናግሮአል፡፡ ዮሐንስ 10፥3-5፣ 11፣ 14፣ 27 ላይ የተናገረውን አሰላስሉ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ያስተማራችሁ ምንድነው?

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

ለመንፈስ ቅዱስ ከተሰጡ ስሞች አንዱ የእውነት መንፈስ የሚለው ነው፡፡ እንዲህ የተባለው ለምንድነው? ብላኬቢ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፣

> ‹‹...የእግዚአብሔር መንፈስ ካልገለጠልን በቀር እኔና እናንተ የእግዚአብሔርን እውነት መረዳት አንችልም፡፡ እርሱ መምህራችን ነው፡ ፡ እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስተምራችሁ በእርሱ ፊት ተቀመጡ፤ ምላሽ ስጡት፡፡ እየጸለያችሁ እያለ የእግዚአብሔር ቃል፣ እናንተ ልብ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ለማጽናት እንዴት እንደሚጠቀምበት ተጠባበቁ፡፡ በዙሪያችሁ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ምን እያደረገ እንደ ሆነ ተመልከቱ፡፡ በዙሪያችሁ እየሠራ ያለው አምላክ፣ ስትጸልዩ የሚናገራችሁና በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የተናገራችሁ ያው አምላክ ነው፡፡ ራሱን፣ ዓላማውንና መንገዶቹን ለመግለጽ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ በጸሎት፣ በሁኔታዎችና በመንፈሱ በኩል ይናገራል፡፡››[2]

*ታዲያ፣ መንፈስ ቅዱስ ግልጥ እንዲያደርግላችሁ እየጠየቃችሁ ያሉ አንዳንድ ዋና ዋና ነገሮች ምንድናቸው? ዮሐንስ 14፥26፤ 15፥26 እና 16፥12-15 ላይ ኢየሱስ የተናገረውን በጥንቃቄ አንብቡና መንፈስ የሚያስተምራቸው አምስት ነገሮች ዘርዝሩ፡፡*

*የእግዚአብሔርን ድምፅ ለማወቅ ቁልፍ ነገር ምንድነው? ብላኪቢ. እና ኪንግ እንዲህ በማለት ይቀጥላሉ፣*

> *‹‹…የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ቁልፉ አንድ ዐይነት ፎርሙላ ማሟላት አይደለም፡፡ የምትከተሉት ዘዴ ወይም ስልት አይደለም፡፡ የእግዚአብሔርን ድምፅ ማወቅ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ፍቅርን መሠረት ካደረገ መቀራረብ ነው… እግዚአብሔር ሲናገር፣ እናንተም ምላሽ ስትሰጡ፣ ውሎ አድሮ የእርሱን ድምፅ የበለጠ ለይታችሁ የምታውቁበት ደረጃ ላይ ትደርሳላችሁ፡፡››*[3]

*የእግዚአብሔርን ድምፅ ለማወቅና ለመስማት ቁልፉ መልካም ግንኙነት ወይም መቀራረብ ነው፡፡ ሄኖክ፣ ኖኅ አብርሃምና ሌሎች ብዙዎች ይህን በቀጥታ ተለማምደዋል፤ እናንተም ትችላላችሁ፡፡ ዮሐንስ 15፥15፤ 1 ቆሮንቶስ 2፥9-10 እና ኤፌሶን 1፥9 ላይ የተንጸባረቀ ከአሞጽ 3፥7 ዳንኤል 2፥22 እና መዝሙር 25፥14 ላይ ያለ የትኛው መርሕ ነው? ‹‹በመጨረሻ ዘመን›› እንደሚኖር ማወቅ ይህ አንተን እንዴት አበረታታህ?*

*ለምሳሌ የሄኖክን ሕይወት (ከዘፍጥረት 5፥21-24)፣ የኖኅን (ከዘፍጥት 6፥9-18)፣ የአብርሃምን (ከዘፍጥረት 18፥16-22) እና የጴጥሮስን (ከሐዋርያት ሥራ 10፥9-23) አውጥታችሁ እዩ፡፡*

ቀን 2 ማሰላሰያ

# የእርሱ መገኘት ለእናንተ እጅግ ወሳኝ ነው

***ፊቴን ፈልጉ ባልህ ጊዜ፣ ልቤ እግዚአብሔር ሆይ፣ ፊትህን እሻለሁ አለች፡፡***

- *መዝሙር* 27፥8

ዳዊት እንደ ማንኛውም ሰው አልነበረም፡፡ አንድ ልቡን የሚያቀጣጥል ናፍቆት ነበር፤ ኀሊናውን የሚያንገበግብ አንድ መሻት ነበር፡፡ እርሱ የእግዚአብሔርን ፊት የሚወድና አጥብቆ የሚፈልግ ሰው ነበር፡፡ ‹‹እግዚአብሔርን አንዲት ነገር እለምነዋለሁ፤ እርሷንም አጥብቄ እሻለሁ›› አለ፤ ‹‹ይኸውም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን ክብር ውበት አይ ዘንድ፣ በመቅደሱም ሆኜ አሰላስል ዘንድ ነው›› አለ (መዝሙር 27፥4)፡፡

በእግዚአብሔር ፊት መገኘትንና ከእርሱም ጋር ኅብረት ማድረግን የሚበልጥ ምንም ዓይነት ክቡር ነገር የለም፡፡ እግዚአብሔር አብና ወልድ ያሉት በሰማይ እንደ መሆኑ መጠን፣ በአማኙ ውስጥ እና በማንኛውም አማኝ በኩል የእግዚአብሔርን መገኘት ለመግለጥ በዚህ ምድር ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ **ብራዘር ሎሬንስ** በመባል ይበልጥ የሚታወቀው ኒኮላስ ሔርማን፣ ‹‹የእግዚአብሔርን መገኘት መለማመድ››ን ተምሮአል፡፡ ሌሎች ያንን እንዲያደርጉ መርዳትንም ተልዕኮው አድርጎታል፡፡ ይኸ በዐሥራ ሰባተኛው መቶኛ ዓመት ገዳም ውስጥ የነበረ አገልጋይ እንደሚነግረን፣

> ‹‹በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ እጅግ ቅዱስና አስፈላጊ የሆነ ልምምድ፣ የእግዚአብሔር መገኘት ወይም ሓልዎት ነው፡፡ ያም ማለት በየትኛውም ወቅት፣ በየትኛውም ቅጽበት በእርሱ መለኮዊ አብሮነት ደስ መሰኘት፣ በማንኛውም መንገድ በማያቋርጥ ሁኔታ ከእርሱ ጋር በትሕትናና በፍቅር መገናኘት ማለት ነው፡፡[4]

እስቲ፣ ቆም ብላችሁ አስቡ፤ የእግዚአብሔር መገኘት ወይም የእርሱ ሓልዎት በሕይወታችሁ ምን ያህል አስፈላጊ ነው? ከዚያ ውጪ ሕይወት ምን እንደሚመስል ታስባላችሁ? የእርሱ ሓልዎት ወይም መገኘት በሌለበት ሁኔታ የዕለት ውሎአችሁን መጀመር ምን ሊመስል እንደሚችል አስቡ፡፡ የእርሱን ስሞችና ተግባሮች ዝርዝር ከልሱ (ገጽ 17 ይመ.)፡፡ ከዚህ አዲስ ዕይታ በመነሣት፣ የእርሱ መገኘት ወይም ሓልዎት ለእናንተ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ጻፉ፡፡

የመንፈስ ቅዱስን መገኘት የምንለማመደው መቼ እና የት ነው? ሎሬንስ እንዲህ ይቀጥላል፣

> ‹‹በእግዚአብሔር መገኘት ወይም ሓልዎት ውስጥ ለመሆን፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሆን የግድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ልባችንን በማንኛውም ጊዜ ከእርሱ ጋር ለመነጋገር መግባት የምንችልበት የግላችን ቤተ መቅደስ ማድረግ እንችላለን፡፡ ይህ ከእርሱ ጋር የምናደርገው ንግግር፣ ማንኛውም ሰው ሊኖረው የሚችል ፍቅርና መግባባት ሊሆን ይችላል፡፡ ታዲያ፣ ያንን ማድረግ ላለመጀመር በቂ ምክንያት አላችሁ?››[5]

ያለ አንዳች ጥርጥር በመንፈስ ቅዱስ መገኘት ውስጥ የምትሆኑበት ሰፌ - ጊዜ ትኩረታችሁን ሁሉ ሙሉ በሙሉ እርሱ ላይ የምታደርጉበት ጊዜ ያስፈልጋችኋል፡፡ ይህም ቃሉን ለማንበብ፣ ለእርሱ ለመናገርና ከእርሱ ለመስማት፣ እርሱን ለማመስገንና ምስጋናውን ለመዘመር፣ እንዲሁም እንዲሁ እፊቱ ለማረፍ የምናውለውን ጊዜ ይጨምራል፡፡ ቆም በሉና እንዲህ ጸልዩ፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ በዚህ የሕይወት ዘመኔ ከአንተ ጋር የሚኖረኝ ጊዜ ምን መምሰል አለበት?›› ወደ ልባችሁ የሚመጣውን ጻፉ፡፡

**ታዲያ፤ የእግዚአብሔርን መገኘት የምትለማመዱት እንዴት ነው?** ብራዘር ሎሬንስ እንዲህ ይላል፣ ‹‹እንዲሁ ራስህን ለእግዚአብሔር አቅርብ… ትኩረትህን የእርሱ መገኘት ላይ አድርግ፡፡ አልፎ አልፎ አእምሮህ ወዲያ ወዲህ ቢል እንኳ አትረበሽ፤ ምክንያቱም መረበሽህ የበለጠ ትኩረትህን ይበታትነዋል፡፡ የተበታተነው ትኩረትህ በጨዋነት ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ አድርግ… ሁልጊዜ ስለ እርሱ ማሰብን የመሰለ ቅዱስ ልማድ አዳብር፡፡››[6] እስቲ ፀጥ በል፤ ከዚያም፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ ትኩረቴ የበለጠ አንተ ላይ እንዲሆን ምን ማድረግ እችላለሁ?›› በማለት ጸልይ፡፡ የሚሰጥህን መልስ አድምጥና የሕይወትህ አካል አድርገው፡፡

**ተጨማሪ ጥናት**

1 ዜና 16፥9-11፤ መዝሙር 22፥26፤ 105፥3-4፤ ምሳሌ 8፥17-18፤ ኢሳይያስ 55፥1-3፣ 6፤ ኤርምያስ 29፥11-13፤ ማቴዎስ 6፥33፤ ዕብራውያን 12፥1-2 ተመልከት፡፡

## ቀን 3 ማሰላሰያ

# እርሱ ወደ እናንተ መቅረብ ይፈልጋል

*‹‹እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ ገብቼ ከእርሱ ጋር እበላለሁ፤ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል፡፡››*

- ራእይ 3፥20

በዚህ ምድር ካለ ማንኛውም ሰው የበለጠ በመንፈስ ቅዱስ በኩል እግዚአብሔር ወደ እናንተ መቅረብ ይፈልጋል፡፡ እርሱ መቀራረብን፣ እጅግ ጥልቅ የሆነ ግንኙነትን፣ እንድትለማመድ ይፈልጋል፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር መቀራረብ ለእግዚአብሔር፣ ‹‹እኔ ውስጥ ያለውን እይ›› የማለት ያህል ነው ተብሏል፤ ይህ በጣም እውነት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ማንም መሄድ ወደማይችልበት - ወደ ነፍሳችንና መንፈሳችን ጥልቅ መሄድ ይችላል፡፡ እርሱ በጊዜና በስፍራ አይወሰንም፡፡ መንፈስ ልባችንን መመርመርና ማወቅ ብቻ ሳይሆን፣ እኛ በእርሱ ውስጥ ማየት እንድንችል፣ የእግዚአብሔርን ልብ ያውቃል፤ ጥልቅ ሐሳቡን፣ ምስጢሩንና ፍላጎቱን ይገልጣል፡፡

*እግዚአብሔር ምስጢሩን ከሚፈሩ ወዳጆቹ አይሰውርም፤ ኪዳኑንም ይገልጥላቸዋል፡፡*

- መዝሙር 25፥14

እንደ ገና ለመናገር፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራን ‹‹የእውነት መንፈስ›› ነው፡፡ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ኢየሱስ ወይም አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልን በተመለከተ መረዳት የምትፈልገው አለ? ጸልይ፤ እውነተኛና ጥልቅ ትርጉሙንና እንዴት ለሕይወትህ ተግባራዊ እንደምታደርገው እንዲያሳይህ መንፈስ ቅዱስን ለምነው፡፡ የተረዳኸውን ጻፍ፡፡

*ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን ኢየሱስ አስረዳቸው፡፡*

- ሉቃስ 24፥27

መንፈስ የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነት ብቻ ሳይሆን፣ እኛንና እኛ ውስጥ ያሉ ነገሮችን በተመለከተም እውነትን ይገልጣል፡፡

አንተ ራስህ ያልተረዳኸው ገጽታ በሕይወትህ አለ? በድንገት በቁጣ ትገነፍላለህ ወይም ያለ አንዳች በቂ ምክንያት በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ስትሆን እጅግ በጣም ትፈራለህ? ምክንያቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መንፈስ ቅዱስ ያውቃል፡ ፡ ጥቂት ቆም በልና እንዲህ በማለት ጸልይ፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ ራሴን በዚህ መንገድ የምገልጥበት እውነተኛ ሥረ ነገር ምንድነው? ነገሮችን በአንተ ዓይን እንዳይ ርዳኝ፡፡ ይህን ማሸነፍ እንድችል አንተ እኔ ውስጥ እንድታደርግ የሚያስፈልገኝ ለውጥ ምንድነው?›› ግልጽ የሆነልህን ጻፍ፡፡

አንተ መረዳት ያልቻልከው ያለፈም ሆነ አሁን ያለ ሁኔታ በሕይወትህ አለ? መንፈስ ያንን ይረዳል፡፡ ጥቂት ቆም በልና፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ ይህን ሁኔታ በተመለከተ እውነቱ ምንድነው? አንተ እንዴት ታየዋለህ? እኔ ውስጥ ማድረግ የምትፈልገው ለውጥ ምንድነው? ያ እውን እንዲሆን እኔ ከአንተ ጋር እንዴት መተባበር እችላለሁ?›› በማለት ጸልይ፡፡ እርሱ የሚገልጥልህን ጻፍ፡፡

**ተጨማሪ ጥናት**

ኢየሱስ ከአብ ጋር ይቀራረብ ነበር፣ ማቴዎስ 14፥22-23፤ 17፥1-5፤ ማርቆስ 1፥35፤ 6፥31፣ 46-47፤ ሉቃስ 5፥16፤ 6፥12

እኛ ወደ እርሱ ስንቀርብ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደ እኛ ይቀርባል፣ መዝሙር 16፥8፤ 34፥18፤ 73፥28፤ 145፥18፤ ዕብራውያን 10፥22፤ ያዕቆብ 4፥8

ቀን 4 ማሰላሰያ

# እንዳታሳዝነው ተጠንቀቅ

*ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳታሳዝኑ ተጠንቀቁ፡፡*

- ኤፌሶን 4፥30

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ማድረግ በዋጋ ከሚተመነው በላይ ነው! የእርሱ መገኘት በማንኛውም የሕይወት ገጽታ ሕይወት ሰጪ ነው፡፡ ለካትሪን ኩህልማን ይህ የዕለት ተዕለት ሕይወት ነበር፡፡ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ስለ መንፈሱ ኃይል ስትናገር ሚሊዮኖች ሰምተዋል፤ ብዙዎችም ተአምራዊ ፈውስ ተለማምደዋል፡፡ The Greatest Power in the World, በሚለው መጽሐፍዋ መንፈስ እንዴት ሊያዝን እንደሚችል እንዲህ በማለት ትገልጻለች፣

> ‹‹…ምንም እንኳ መንፈስ ቅዱስ እጅግ ኃያል የሥላሴ አካል ቢሆንም፣ እርሱ ስስና (Sensitive) በቀላሉ የሚጐዳ ነው፡፡ ይህ ድንቅ የሥላሴ አካል በመራርነት፣ በቁጠኝነት፣ በንዴት፣ በክፉ ንግግር ሊጐዳ እንደሚችል የሚጠረጠር አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር የየዋህነት፣ የትዕግሥት፣ የእርስ በርስ መዋደድ፣ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት የመጠበቅ ተጻራሪ በሆነ ግለ ሰብ ውስጥ ባሉ ማናቸውም ነገሮች ሊያዝን ይችላል ማለት ነው፡፡››[7]

መንፈስ ቅዱስን የሚያስከፋና በሕይወታችን የእርሱ መገኘት እንዳይኖር የሚያደርጉ ነገሮችን ለይቶ ማወቅ በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ መንፈስን ማሳዘን ምን ማለት እንደ ሆነ ዐውዱን ለመረዳት ኤፌሶን ምዕራፍ 4 በጥንቃቄ አንብቡ፡፡ (በተለይ ከ1-6 እና 17-32 ላሉት ትኩረት ስጡ)፡፡

መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑ ከቁጥር 17-24 ባሉት ውስጥ የተጠቀሱ ዝንባሌዎች፣ አስተሳሰቦችና ፀባዮች ምንድናቸው?

ኤፌሶን 4፥17-24 መንፈስን የሚያሳዝኑና መገኘቱ ከእኛ ጋር እንዳይሆን የሚያደርጉ አኗኗሮች፣ ምርጫዎችና አስተሳሰቦች ያመለክታል፡፡

ከቁጥር 25-31 ያሉትን መንፈስን የሚያሳዝኑ ነገሮች በሙሉ አጠቃልላቸው፡፡ ከዚህ ምንባብ ውስጥ ያለ አንድ ሁነኛ ድርጊት ለመጻፍ ጊዜ ውሰድ፡፡

ኤፌሶን 4፥25-31 ሌሎች ላይ የምንፈጽማቸውንና መንፈስን የሚያሳዝኑ፣ እኛንም ከእርሱ የሚለዩ ነገሮች ይገልጻል፡፡

መንፈስን ማሳዘን መቻላችን እውነት ነው፤ መልካሙ ዜና ግን እርሱን ደስ ማሰኘትም የምንችል መሆኑ ነው! ቁጥር 1-7፤ 14-15፤ 25፣ 29፣ እና 32 በጥንቃቄ አንብቡና መንፈስን ደስ የሚያሰኙ ነገሮች ዘርዝሩ፡፡

መልስህን እያዘጋጀህ እያለ እርሱን የማሳዘን ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን አስብ፡፡

መንፈስን ላለማሳዘን ቁልፉ የመንፈስን ንጽሕናና አንድነት መጠበቅ ነው፡ ፡ ትዕቢትና ርኩሰት የመንፈስን ሥራ ሲያሰናክል፣ ትሕትና ግን እንዲለቀቅ ያደርጋል፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ በል፡፡ «አንተን የሚያሳዝን ነገር እያደረግሁ ይሆን?» በማለት ጠይቅ፤ እርሱ የሚገልጥልህ ነገር ካለ ንስሐ አድርግ፤ በትሕትና፣ እርሱን ደስ በሚያሰኝና በሕይወትህም እንዲሠራ በሚጋብዝ ንጽሕና መመላለስ የምትችልበትን ጸጋ እንዲሰጥህ ለምነው፡፡

ቀን 5 ማሰላሰያ

# እናንተ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናችሁ

*እናንተ ራሳችሁ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር አታውቁምን?*

- 1 ቆሮንቶስ 3፥16

ሁሉን ቻይ፣ ሁሉን ዐዋቂ፣ ከጥቃቅን ነገሮች አንሥቶ፣ እስከ ግዙፍ ጋላክሲዎች የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ልባችንን ማደሪያው ማድረግ ፈልጎአል! አዎን እንደ አማኝ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሞት ያስነሣው ያው መንፈስ አንተ ውስጥ ይኖራል!

የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ መሆን ምን ማለት እንደ ሆነ ፓስተር፣ ደራሲና የግሪክ ቋንቋ ምሑር የሆነው **ሪክ ሬነር** እንዲህ በማለት ጽፎአል፡፡

> ‹‹መንፈስ ቅዱስ እናንተ ልብ ውስጥ ለመኖር ሲመጣ፣ ምቹ የሆነ ቤት አዘጋጅቶአል፣ እናንተ ውስጥ ለመኖር ደስ ተሰኝቶአል ማለት ነው! ከዚያም ወደ ውስጥ ይገባል፤ እዚያ ያርፋል፤ በአዲሱ ቤቱ በልባችሁ ውስጥ ለዘላለም መኖሪያውን ያደርጋል!
>
> ድነት ያገኛችሁ ጊዜ ልባችሁ ውስጥ ተአምር ተደርጎ ነበር፡፡ በኃጢአት ምክንያት ሙት የነበረውን መንፈሳችሁን መንፈስ ቅዱስ ሕያው አደረገው፣ ወደ አዲስ ሕይወት አስነሣው፡፡ እናንተ ውስጥ የፈጸመው ሥራ እጅግ ክቡር ከመሆኑ የተነሣ፣ ሥራው ሲጠናቀቅ፣ እርሱ እጅ ሥራዎች መሆናችሁን በግልጽ ተናገረ (ኤፌሶን 2፥10)፡፡ በዚያው ቅጽበት እናንተ እጅግ አስደናቂ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሆናችሁ!››[8]

በምትሄዱበት ቦታ ሁሉ፣ በምታደርጉት ንግግር ሁሉ፣ በምትሳተፉበት ሥራ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ከእናንተ ጋር ነው፡፡ እስቲ ቆም በሉና ይህን በተመለከተ አስቡ፡፡

ይህ እውነት ያበረታታህ፣ ያነቃቃህና ብርታት የሆነህ እንዴት ነበር? የጸሎት ሕይወትህንስ ምን መልክ አስያዘው?

ኤፌሶን 3፥14-20፤ ሉቃስ 12፥11-12፤ ዮሐንስ 14፥12-17፤ ቈላስይስ 1፥27፤ 2 ጢሞቴዎስ 1፥13-14 እና ሮሜ 8፥1-17 ላይ የተሰጡ የእግዚአብሔር ተስፋ ቃሎች አስቡ፡፡

ይህ እውነት ያደፋፈረህና ያስተማረህ እንዴት ነው? የሰጠኸው መልስ በእንዴት ዐይነት ሁኔታ ነበር ወደ ጸሎት የመራህ?

ለመዝናኛ የምትመርጣቸውን፣ ሁልጊዜ የምታይና የምትሰማቸውን ነገሮች አስብ፤ እንዲሁም ብዙ ጊዜ አብረኻቸው የምትሆን ሰዎችንና የምታዘወትራቸው እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ አስብ፡፡

በአሁኑ ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለህን ኅብረት እንዴት ትገልጠዋለህ? ከእርሱ ጋር ጥሩ ኅብረት፣ አጋርነትና ቀረቤታ አለህ? ድምፁን ትሰማለህ፤ የእርሱን እውነተኛ መገኘት በሕይወትህ እየተለማመድህ ነው? በአንተ ውስጥ በምቾት እንዲኖር፣ ሁኔታዎችን የምታነጻበት ጥሩ ጊዜ ነውን? ልብህ ውስጥ ያለውን ሁኔታ እንዲገልጥልህ በጸሎት ጠይቀው፡፡ ምን እያለህ ነው? ምን ዐይነት ርምጃዎች መውሰድ እንዳለብህ አመለከተህ?

*እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮታችሁ ነው፡፡ መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ፡፡*

- ሮሜ 12፥1-2

## የውይይት ጥያቄዎች

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር **ኅብረት** አለን፡፡

ኅብረት በግሪኩ ኮይኖኒያ ሲሆን፣ ‹‹ኅብረት፣ ባልንጀርነት፣ ግንኙነት፣ መቀራረብ፣ በአንድነት መከፋፈል፣ ማኅበራዊ ግንኙነት፣ አጋርነት፣ አብሮ መሳተፍ፣ የጠበቀ የእርስ በርስ መቀራረብ›› ማለት ነው፡ ፡ እንዲህ ያሉ የኅብረት ገጽታዎችን በሦስት ዋና ዋና ምድቦች ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ አንድነት፣ አጋርነትና መቀራረብ፡፡

1. እንደ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች፣ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር የማይቋረጥ ኅብረት (ኮይኖኒያ) ማድረግ ይፈልጋል፡፡ ይህ ኅብረት አንድትን፣ ሕይወትን የመከፋፈል የጓደኝነት ግንኙነትን ሁሉ ይጨምራል፡፡ የመንፈስ ቅዱስን ወዳጅነት መቀበልና ያንን መረዳት አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ምን ይሆን ነበር?

2. ከኅብረት በተጨማሪ መንፈስ ቅዱስ የእኛን አጋርነትም ይፈልጋል፡ ፡ አንድ ውጤት ለማስገኘት ሲባል፣ እርስ በርስ በመረዳዳት አጋሮች የሚያደርጓቸው አንዳንድ ተግባራዊ ነገሮች ምንድናቸው? አብርሃምን ወይም ሙሴን የመሳሰሉ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ተከታዮች ከነበሩ ሰዎች ጋር ሲነጻጸር፣ በዚህ ዘመን እኛ ከእግዚብሔር መንፈስ ጋር ያለንን አጋርነት የተለየ የሚያደርገው ምንድነው? ይህ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ አበረታታህ?

3. ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ከአንድነትና ከአጋርነትም በጣም ያልፋል፡፡ የጠለቀ፣ ልባዊ፣ የእርስ በርስ ግንኙነትን ይጨምራል፡፡ እንደ አማኞች እንዲህ ያለውን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሊኖረን የሚገባውን ኅብረት ደረጃ ማሳደግ የምንችለው እንዴት ነው?

ክብር

አክብሮትን የምንገልጥበት ወይም በቃላትና በተግባር ላቅ ያለ ግምታችንን መስጠት፡፡ በአጭሩ ማክበር ዋጋ፣ ግምት መስጠት፣ መልካም አቀባበልና ከፍ ያለ አመለካከት ነው፡፡

4. ዋናው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የኢየሱስን ማንነት መግለጥና ለእርሱ ክብር ማምጣት ነው፡፡ ክርስቶስን ይገልጣል፤ በእውነት በሚከበርበት ቦታ እርሱ ራሱን ይገልጣል፡፡ ክብር ለተሰኘው ቃል የተሰጠውን ገለጻ በጥንቃቄ ተመልከት፡፡ በግላችንና እንደ ቤት ክርስቲያን መንፈስ

ቅዱስን ማክበር የምንችልባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድናቸው?

5. ምንም እንኳ መንፈስ ቅዱስ (የእግዚአብሔር መንፈስ) ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በእንስታይ ጾታ ባይገለጥም፣ አልፎ አልፎ አንዳንድ ባሕርያቱ፣ ብዙ ጊዜ ሴቶች ላይ የሚታዩ ናቸው፡፡ ዘፍጥረት 1፥27 በጥንቃቄ አንብቡና መንፈስ ቅዱስንም በሚያካትት መልኩ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን እንደሚናገር ግለጹ፡፡ ይህን እውነት መረዳት ከእርሱ ጋር ያላችሁን ግንኙነት በእንዴት ዐይነት ሁኔታ ያሳድገዋል?

6. መንፈስ ቅዱስ በባሕርዩ በጣም ጨዋ፣ ርኅሩኅና አጽናኝ ነው፡፡ ጥንቃቄ ካላደረግን እርሱን ልናሳዝንና ልናስከፋው እንችላለን፣ ከዚህም የተነሣ በሕይወታችን የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሊቋረጥ ይችላል፡፡ ኤፌሶን 4፥29-32 ላይ በጥንቃቄ አሰላስልና መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑ አንዳንድ ነገሮች ግለጥ፡፡ ይህ መንፈስን ማሳዘን 1 ተሰሎንቄ 5፥19-22 ላይ ካለው መንፈስን ማጥፋት የሚለየው እንዴት ነው? ከእንዲህ ያሉ ነገሮች ለመጠበቅ ምን ማድረግ አለብን?

7. ከአንድ ኃጢአት ማለትም መንፈስ ቅዱስን ከመሳደብ በቀር ለሰው የሚታወቅ ማንኛውም ኃጢአት ይቅር ይባላል፡፡ ማቴዎስ 12፥22-32 ላይ ኢየሱስ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ አንብቡ (በተጨማሪም ከማርቆስ 3፥22-30 እና ከሉቃስ 12፥10 አንብቡ)፡፡ ከእነዚህ ጥቅሶች አንጻር መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል ግለጽ፡፡ እርሱን በተመለከተ ኢየሱስ ይህን ያህል አጠንክሮ የተናገረው ለምን ይመስልሃል?

**ምዕራፉ በአጭሩ፤**

- መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት እንዲኖረው ይፈልጋል።
- ኅብረት አንድነትን፣ አጋርነትንና በጣም መቀራረብን ያካትታል።
- ግንኙነት በማደረግና ሕይወትን በመከፋፈል ኅብረት ለዘለቄታ ይቀጥላል።
- አጋርነት አብሮ መሥራትን ይመለከታል፤ ግንኙነቱን በተግባር ማሳየትን ይጨምራል።
- መቀራረብ እኛ የግል ሀሳባችንን፣ ፍላጐታችንንና ምስጢራችን ለመንፈስ ቅዱስ የምናካፍልበት፣ እርሱም ለእኛ ሐሳቡን የሚያካፍልበት የወዳጅነት ከፍተኛ ደረጃ ነው።
- ፍጹም አምላክ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ልባችንን (መንፈሳችንን) ለዘለቄታው መኖሪያው ለማድረግ መርጧል፡ ፡
- መንፈስ ቅዱስን እንዳናሳዝን መጠንቀቅ አለብን፤ ምክንያቱም እርሱ ጨዋና ርኅሩኅ ስለ ሆነ በአነጋገርና በተግባራችን በጣም ሊያዝን ይችላል።

3

# ሦስት የግንኙነቱ ደረጃዎች

*ለወጋችሁ ብላችሁ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ፡፡ እናንተ ግብዞች ኢሳይያስ ስለ እናንተ እንዲህ ብሎ በትንቢት የተናገረው ትክክል ነው፤ ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤ በከንቱ ያመልከኛል፤ ትምህርታቸውም የሰው ሥርዐት ነው፡፡*

- ማቴዎስ 15፥6-9

ቀን 1

ኢየሱስ ይህን አስደንጋጭ ቃል ለፈሪሳውያን የተናገረው ከእግዚአብሔር ቃል የበለጠ ለባሕል ቅድሚያ በመስጠታቸው ነበር፡፡ አንድ በእጄ ያለ መዝገበ ቃላት ባሕልን፣ ‹‹የተወረሰ፣ ተቀባይነት ያገኘ ወይም የተለመደ የአስተሳሰብ፣ የድርጊት እና የፀባይ መመሪያ›› በማለት ይገልጸዋል፡፡ በመሠረቱ ባሕል በራሱ የግድ መጥፎ እንዳይደለ ግልጽ ነው፡፡ እኔም ሆንኩ ወዳጆቼና ቤተ ሰቤ ከፍ ያለ ግምት የምንሰጣቸው ጥሩ ጥሩ ባሕሎች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ፈሪሳውያን ባሕልን (የተለመደ የአስተሳሰብ መንገድን) ከእግዚአብሔር ቃል አስበልጠው ነበር፤ ስለሆነም ቃሉ በሕይወታቸው ውጤት ሊኖረው አልቻለም፡፡ ዛሬም ይህ እውነት ነው፡፡ በጊዜያዊ ስሜቶቻችን፣ ባሕሎቻችን ወይም በሰዎች ፍልስፍና ሳይሆን ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ነው እውነት መተርጎም ያለበት፡፡

የፈሪሳውያን ባሕል በእነርሱና በፈጣሪ መካከል ሊኖር በሚገባው ግንኙነት ክፍተት እንደ ፈጠረ ኢየሱስ ተናገረ፡፡ እንዲያውም የበለጠ እምነታቸውን ያሳረፉት በሰዎች አስተምህሮ በመሆኑ፣ የእነርሱ እግዚአብሔርን ማምለክ

ከንቱ እንደ ሆነ ነበር የተናገረው፡፡ ዕውሮች መሆናቸውን ተረድተው ንስሐ ካልገቡና እውነትን እስካልተቀበሉ ድረስ ፈሪሳውያን ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ በተመሳሳይ መንገድ እኛም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የጠበቀና የጠለቀ ግንኙነት እንዲኖረን ከፈለግን፣ የሰውን ባሕልና አስተሳሰብ ገለል አድገን ስለ እርሱ በቃሉ ውስጥ የተነገረውን እውነት መቀበል ይኖርብናል፡፡ ያ ካልሆነ፣ እንደ ፈሪሳውያን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር በጣም ለመቀራረብ የምናደርገው ሙከራ ውጤት አይኖረውም፡፡

## የመጨረሻው መምህር

የበለጠ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ከመቀራረቤ በፊት መጽሐፍ ቅዱሴን ሳነብ አንዳንዴ፣ እኔ እስከማውቀው ድረስ ከልቤ እግዚአብሔርን እወዳለሁ፤ ግን ይህ ቃል ለእኔ ትርጉም የለሽና ደረቅ ነው እል ነበር፡፡ እውነቱ ግን ያ ሳይሆን፣ የጸሎቴና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ አካል እንዲሆን መንፈስ ቅዱስን አለመጠየቄ ነበር፡፡ በኋላ ግን፣ መጽሐፍ ቅዱስን ልቤ ውስጥ ሕያው የሚያደርግ መንፈስ ቅዱስ ብቻ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ በእርሱ መሪነት መጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ብቻ አይሆንም፣ ይልቁንም ሕይወት ሰጪ ቃላት ይሆናል፡፡ 2 ቆሮንቶስ 3፥6 ላይ እንዲህ የሚል እናነባለን፡፡

> እርሱም በፊደል ላይ ሳይሆን፣ በመንፈስ ላይ የተመሠረተውን የአዲሱ ኪዳን አገልጋዮች እንድንሆን ብቁዎች አደረገን፤ ምክንያቱም ፊደል ይገድላል፤ መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል፡፡

በእግዚአብሔር ቃል የተገለጠውና እኛም የተቀበልነው፣ «አዲሱ ኪዳን» የደንቦችና የሕጎች ዝርዝር አይደለም፡፡ ይልቁን ራሱ ሕይወት ነው፤ ለሚቀበሉትም ሕይወት ሰጪ ነው፡፡ የአዲሱ ኪዳንን ሙላት የምንለማመደው በመንፈስ በኩል ብቻ ነው፤ ምክንያቱም በክርስቶስ ያለንን ታላቅ ማንነት፣ ጥልቅ ምስጢር የሚገልጥ እርሱ ነው፡፡ (የአዲስ ኪዳን መልእክትም ይኸው ነው)፡፡ ስለሆነም፣ መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና የመጨረሻውን መምህር ማለትም መንፈስ ቅዱስን መጋበዝ ያለብን በዚህ ምክንያት ነው፡፡

የሚያስተምረውን ትምህርት ከልቡ ወይም ከፍላጐት የማያስተምር አስተማሪ ገጥሞአችሁ ያውቃል? እንዲህ ያለው ክፍለ ትምህርት በጣም የሚያስጠላ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎቹን የማይወድ አስተማሪስ ገጥሟችሁ ያውቃል? በፍጹም ደስ የማይልና የማይጋብዝ ክፍለ ትምህርት ነው የሚሆነው፡፡ ትልቁ የምሥራች፣ መንፈስ ቅዱስ በጣም ደስ እያለው በከፍተኛ ፍላጐት የእግዚአብሔርን ቃል ምስጢር የሚገልጥና እናንተ ራሳችሁንም የሚወዳችሁ መሆኑ ነው! የእርሱ ፍላጐት ክርስቶስ በነጻ በሰጣችሁ ስጦታዎች እንድትሞሉና በዚያም መሠረት እንድትመላለሱ ነው፡ ፡ ከጠየቅንና (ከለመንን) ከፈለግን፣ እርሱ የሕይወትን ምስጢር ሊገልጥልን ታማኝ ነው፡፡

## ጥሩ አካባቢ እና መገኘቱ

በጣም የሚያሳዝነው፣ መካሪና መሪያችን የሆነው እርሱ በሌለበት ሁኔታ ይህን ድንቅ የክርስትና ሕይወት ለመኖር መሞከራችን ነው፡፡ እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ በዘመናችን ባሉ አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እንግዳ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ ሳናውቀው ጥሩ ወይም ደስ የሚል ሁኔታ ሁሉ የእርሱ መገኘት ምልክት እንደ ሆነ እናስባለን፡፡ የእርሱን መገኘት በእነዚህ ነገሮች ተክተናል፡፡ ጥቂት ግለ ሰቦች የተሳሳተ ምላሽ መስጠታቸው ወይም የእርሱን መገኘት ፍለጋ አንዳንድ እንግዳ ልምምድ ውስጥ መግባታቸው፣ የእግዚአብሔርን መንፈስ መገለጥ ደስ ብሎን እንዳንቀበል አድርጎናል፡፡

እዚህ ላይ በተሳሳተ መንገድ እንድትረዱኝ አልፈልግም፤ በቤተ ክርስቲያናችን አገልግሎት ውስጥ ደስ የሚል ሁኔታ ወይም ደስ የሚል ከባቢ መኖር እንዳለበት አምናለሁ፡፡ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ባሕላዊ ለውጦች ተደርገዋል፤ ከእነዚህም አንዱ ከባቢውን ወይም ሁኔታውን የበለጠ የማሳመር ፍላጐት ነው፡፡ በብዙ የተለያዩ መንገዶች ቤተ ክርስቲያን የበለጠ ወቅታዊና የዓለምን ትኩረት የምትስብ ሆናለች፡፡ ይህ እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኝ አምናለሁ፡፡ ጳውሎስ እንዳለው፣ «እኔ ሰውን ሁሉ በማንኛውም ረገድ ለማስደሰት እንደምጥር እናንተም እንዲሁ አድርጉ፤ ብዙዎችም ይድኑ ዘንድ ለራሴ የሚጠቅመውን ሳይሆን ለእነርሱ

የሚጠቅመውን እሻለሁና›› (1 ቆሮንቶስ 10፥33)፡፡ የግለ ሰቦችን ፈጠራ በማበረታታትና ቴክኖሎጂን በማስፋፋት ረገድ ትልልቅ ነገሮች አድርገናል፤ እኔ በግሌ ከተገናኘሁባቸው እጅግ ደስ የሚሉ ቦታዎች ጥቂቶቹ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን በፈጠራ ሥራ የተካኑ ሰዎች የሞሉባትና ባላሰለሰ ሁኔታ ይህንኑም ወደ ላቀ ደረጃ የምታሸጋግር መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ፣ በነገርዋ ሁሉ መንፈስ ቅዱስን የምትጋብዝ እስካልሆነች ድረስ ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር የኃይል፣ የፍቅርና የሥልጣን ቦታዋን፣ በሙላት መያዝ አትችልም፡፡ ከእርሱ ጋር በሚኖረን ግንኙነት ዋናው ባለ ድርሻ እርሱ መሆኑን አስታውሱ፡፡

በጣም ደስ የሚለው፣ ደስ የሚል ሁኔታ ያለባትና የመንፈስ ቅዱስ መገኘት እውን የሆነባት ቤተ ክርስቲያን እንድትኖረን ማድረግ የሚቻል መሆኑ ነው፡፡ በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች እጅግ ልቀው የተገኙ አብያተ ክርስቲያናትን የመጐብኘት ዕድል ሳገኝ በጣም ነው ደስ የሚለኝ፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ሓልዎት መገለጥ፣ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዳይመጡ ያደርጋል የሚል የተሳሳተ ሐሳብ እንዳይኖራችሁ ተጠንቀቁ፡፡ ሐዋርያቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብረው በመሥራታቸው በኃጢአት የጠፉ ሰዎች ወደ ኅብረታቸው መጡ እንጂ፣ ከኅብረታቸው እንዳልራቁ ማስታወስ አለብን፡ ፡ መንፈስ ቅዱስ ባልተሳተፈበት ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረግ ማንኛውም ዕድገት ወይም መሻሻል ብኩንና ከንቱ ከመሆን አያልፍም፡፡

የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ እንኳ፣ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እስኪቀበል ድረስ ምንም ማድረግ አልፈለገም (ሉቃስ 4፥1-15 ይመ.)፡፡ ሉቃስ 4፥14-15 ላይ፣ ‹‹ኢየሱስም በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ፤ ዝናውም በአካባቢ ባለው አገር ሁሉ ወጣ፤ እርሱም በምኩራባቸው ያስተምር ነበር፤ ሰውም ሁሉ ያመሰግነው ነበር›› የሚል እናነባለን፡፡ ጥቅሱ፣ ‹‹በመንፈስ ኃይል ተመለሰ›› ማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ ምንባቡ ኢየሱስ አርባ ቀን ሙሉ በምድረ በዳ ማሳለፉንና በኋላም በዲያብሎስ መፈተኑን ነው የሚናገረው፡፡ በመንፈስ ኃይል ከምድረ ባዳ ከተመለሰ በኋላ ወደ ናዝሬት ተመልሶ እንዲህ አለ፤

> የጌታም መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድኾች ወንጌልን እንድሰብክ፣
> እርሱ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩት መፈታትን፣ ለታወሩትም ማየትን

እንዳውጅ፣ የተጨቆኑትን ነጻ እንዳወጣ፣ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እንዳውጅ ልኮኛል›› (ሉቃስ 4፥18-19)፡፡

ኢየሱስ የእግዚአብሔር የአባቱን ፈቃድ በምድር መፈጸም የቻለው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመንቀሳቀሱ ነበር፡፡ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በዚሁ ኃይል፣ በመንፈስ ድኾች ለሆኑት ወንጌልን መስበክ፣ ልባቸው የተሰበረውን መፈወስ፣ ለእስረኞች ነጻነትን ማወጅ፣ ለታወሩት ማየትን፣ ለተጨቆኑት ነጻነትን፣ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን አጭር ያለ መሆኑን እውነት በተግባር ማሳየት ትችላለች፡፡ ይሁን እንጂ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የምንደገፍ እስካልሆንን ድረስ፣ ይህን ሰማያዊ ተልዕኮ ማራመድ በፍጹም አንችልም፡፡ ለኢየሱስ የመንፈስ ኃይል አስፈልጎት ነበር - ታዲያ፣ ለእኛስ አያስፈልገንም?

ቀን 2

## «ይበልጥ ኢየሱስን»

የእኔ ትልቁ ፍላጎት አብያተ ክርስቲያኖቻችንን የሚያዘወትሩ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን መገኘት እንዲለማመዱ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች፣ ‹‹በየአብያተ ክርስቲያኖቻችን ይበልጥ ኢየሱስ ያስፈልገናል›› ሲሉ እሰማለሁ፤ በዚህ እኔም ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ፡፡ ግን ኢየሱስን የሚገልጥልን ማነው? መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ቀደም ሲል ከዚህ ጥናት እንደ ተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ የምንንጓለት ሸቀጥ ሳይሆን፣ ልናከብረውና ልንጋብዘው የሚገባን አካል ነው፡፡ በምናደርገው ነገር ሁሉ የእውነት መንፈስ እንዲገኝ የምንፈልገው ለምንድነው? በአንድ ወቅት ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ነበር፤

ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤ አሁን ግን ልትሸከሙት አትችሉም፡፡ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡፡ እርሱ ከራሱ አይናገርም፤ የሚሰማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም ወደ ፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል፣ የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ ያከብረኛል፡፤ የአብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው፤ እንግዲህ፣

የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ ያደርጋል ያልኋችሁ ለዚሁ ነው፡፡ (ዮሐንስ 16÷12-15)

መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ያከብራል፡፡ ኢየሱስ ለእኛ የተገለጠው በመንፈስ ቅዱስ በኩል ነበር፡፡ እግዚአብሔር የወሰነውንና ያቀደውን ማጠፍ አንችልም፡፡ በሕይወታችን ይበልጥ ኢየሱስን የምንፈልግ ከሆነ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የጠበቀ ኅብረት ሊኖረን ይገባል፡፡ መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ መንፈስ የተባለው በዚህ ምክንያት ነው (1 ጴጥሮስ 1÷11፤ ሮሜ 8÷9 ይመ.)፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የሚናገረን ኢየሱስንም በመወከል ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ባለን ሕይወት ላይ፣ «ተጨማሪ ነገር» ሳይሆን፣ የራሱ የክርስቶስ በዚህ ምድር መገኘት ነው፡፡ እርሱ በማይከበርበት ቦታ የእርሱ መገኘት አይገለጥም፡፡ ስለሆነም፣ መንፈስን ማክበር ካልፈለግን፣ በሕይወታችን የክርስቶስ መገኘትና ኃይል አይኖርም፡፡ ዓለም ቤተ ክርስቲያንን ሕይወት እንደሌላትና ዐቅመ ቢስ አድርጎ የሚመለከተው በዚህ ምክንያት ይሆን?

## ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ ወዳጅነት

የኅብረቱ መድረሻ ግብ፣ ጥልቅ እና ግላዊ ወዳጅነት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ የቅርብ ወዳጅህ መሆን ይፈልጋል፡፡ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ኅብረት እንዲኖርህ በጣም ይፈልጋል፡፡ ያዕቆብ፣ «በውስጣችን ያሳደረው መንፈስ አብዝቶ ይቀናል» ይላል (ያዕቆብ 4÷5)፡፡ ለመሆኑ አብዝቶ የሚቀናው ወይም አብዝቶ የሚፈልገው ምንድነው? ከእኔና ከእናንተ ጋር ጥብቅ ወዳጅ መሆንን ነው፡፡ እኛስ ብንሆን፣ በጣም ከምንወዳቸው ሰዎች የምንፈልገው ይህንኑ አይደል? እርሱ አብዝቶ እንደሚቀና ወይም እንደሚፈልግ ልብ አድርጉ፡፡ ከሌላ ሴት ጋር ተገቢ ያልሆነ መቀራረብ ቢኖረኝ ሚስቴ የጥልቅ ልቦናዋን ፍላጎት ለእኔ ማካፈል እንደማትፈልግ ሁሉ፣ እርሱም ተገቢ ካልሆኑ ሌሎች ነገሮች ጋር መጠላለፋችንን በቸልታ አይመለከተውም ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ለእርሱ የተሰጠን እንድንሆን ይፈልጋል፡፡ ቀደም ባለው የዚሁ ምዕራፍ ቁጥር ላይ ያዕቆብ፣ «የዓለም ወዳጅ መሆን

የሚፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል›› ብሎ ነበር (ያዕቆብ 4÷4)፡፡ መዝገበ ቃላቱ ጠላት የሚለውን ቃል፣ ‹‹የጥላቻ ስሜት ወይም ሁኔታ፣ አለመውደድ፣ በጐ ያልሆነ አመለካከት፣ የለየለት ፀብ›› በማለት ይተረጉመዋል፡፡ በጣም ከባድ ቃሎች ናቸው፡፡ እዚህ ላይ፣ የዓለም ወዳጅ መሆን፣ የእግዚአብሔር ጠላት መሆን ነው የተባለው ለምንድነው? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፡፡

የሥጋ ጽኑ ፍላጐት የዓለም ወዳጅ መሆን ነው፡፡ በራስ ወዳድነት ተነሣሥቶ ሀብት፣ ላቅ ያለ ማንነት ወይም ሥልጣን ማሳደድ ነው፡፡ ሥጋዊ እኛነታችንን አለቅጥ ለማርካት መፈለግ ነው፡፡ እንዲህ ያሉ ነገሮችን ማሳደድ ውጤቱ ከንቱነትና ባዶነት መሆኑን መንፈስ ቅዱስ በሚገባ ያውቃል፡፡ የኃላ ኃላ ነፍሳችንን የሚያጠፉ እንዲህ ያሉ ነገሮችን አጥብቀን ስናሳድድ ከፍቅሩ የተነሣ እግዚአብሔር ይቀናል፤ ደግሞም ይጠላል፡፡ እግዚአብሔር ፍጹም አባት መሆኑን አትርሱ፤ እንደ ማንኛውም መልካም አባት ልጆቹ መልካም ከሆነ ነገር ጐድለው መገኘታቸውን ይጠላል፡፡ የዓለም ወዳጅ መሆናችንን በዋዛ የማያየው ከዚህ የተነሣ ነው፡፡ ኢየሱስ የበዛና የተትረፈረፈ ሕይወት እንድትለማመዱ ይፈልጋል (ዮሐንስ 10÷10 ይመ.)፣ ይህን የወልድ ፈቃድ እውን የሚያደርገው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ የሥላሴ አካላት በዓላማ አንድ መሆናቸውን አስታውሱ፡፡ ከልጆቹ ጋር በጣም የቀረበ ግንኙነት እንዲኖረው እግዚአብሔር በጥብቅ ይፈልጋል፡፡ ከዓለም ጋር የተጠላለፈ ሕይወት የምንኖር ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ማድረግን መለማመድ አንችልም፡፡ ምንኛ ከባድ ኪሳራ ነው! የአባታችንን ልብ ምንኛ ያሳዝን ይሆን!

## ከድነት እጅግ ያለፈ

እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ዓላማ ከድነትም በጣም ያለፈ መሆኑን ወደ መረዳት መጥቻለሁ፡፡ ስለሆነም ድነት ላይ ብቻ መወሰናችን ተገቢ አይሆንም፡ ፡ አዎን፣ የድነታችን እውነታ እኛ ከምናስበው ወይም ከምንገምተው በላይ እጅግ ድንቅ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ በመንግሥተ ሰማይ ቦታ ያለን

መሆኑ፣ እግዚአብሔር ሊሰጠን ለሚፈልገው ነገር ሁሉ ጅማሬ ብቻ ነው፡ ፡ እግዚአብሔር ልጁን የላከው በዚህ ምድርም ትርጉም ያለው አስደናቂ ሕይወት እንድንኖር ነው፡፡ ለምን? ምክንያቱም የዚህ ዓለም ፍርሃትና ምኞቶች እስረኞች ከሆንን፣ ውጤት ባለው መንገድ የእርሱን መንግሥት ማስፋፋት በጣም ከባድ ስለሚሆንብን ነው፡፡

አንድ ጊዜ ጳውሎስ፣ ‹‹ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ራስን ማሠልጠን (እግዚአብሔርን መምሰል) ግን ለአሁኑም ሆነ ለሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው ለሁለቱም ይጠቅማል›› ብሎ ነበር (1 ጢሞቴዎስ 4፥8) እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ወይም እግዚአብሔርን መምሰል የሚለውን ቃል ልብ አድርጉ፡፡ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ሊኖረው የሚችል ቀድሞውኑ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ሰው ነው፤ ምክንያቱም፣ እውነተኛ መንፈሳዊነት እግዚአብሔርን መምሰል ነው፡፡ በጣም የማትቀርቡትን ሰው መስሎ መገኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ከሰዎች ጋር ጊዜ ስናሳልፍ፣ እነርሱን እየመሰልን የምንመጣበት ሁኔታ አለ፡፡ የዓለም ወዳጅ መሆንን አስመልክቶ በመቀጠል ያዕቆብ፣ ‹‹ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል›› ያለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ (ያዕቆብ 4፥8)፡፡ እርሱን እየመሰልን እንድንሄድ፣ ከእርሱ ጋር ጊዜ እንድናሳልፍ እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ እውነተኛ መንፈሳዊ የምንሆነው እግዚአብሔርን የበለጠ ስናውቅ ነው፤ እንዲህ ያለውን ጥብቅ መቀራረብ ማዳበር የምንችለው ደግሞ በመንፈሱ በኩል ነው (1 ቆሮንቶስ 2 ይመ.)

ብዙ ጊዜ አማኞች፣ ‹‹ከዓለም ጋር ወዳጅ መሆን የእግዚአብሔር ጠላት መሆን ነው›› የሚለውን ሲያነቡ፣ ወዲያውኑ ሙሉ በሙሉ ከዓለም መለየት እንዳለባቸው ያስባሉ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ይህ የማይሆን አስተሳሰብ ነው፡፡ ለመሆኑ፣ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ከዓለም ካገለለች ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ማምጣት የምትችለው እንዴት ነው? እንደ ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ አርአያ ሊሆነን ይገባል፡፡ በኃጢአት የጠፉ ሰዎች ወደ ኢየሱስ ይሳቡ ነበር፡ ፡ የሃይማኖት መሪዎቹ በንቀት ከሚመለከቷቸው ቀረጥ ሰብሳቢዎችና አመንዝሮች ጋር ኢየሱስ ጊዜ ያሳልፍ ነበር፡፡ እንዲያውም፣ ግብዣቸው ላይ እንኳ ተገኝቷል፤ ሆኖም እርሱን የተለየ የሚያደርገው ነገር ነበር፡፡ በዓለም ውስጥ መሆን፣ ይሁን እንጂ፣ ከዓለም ወገን አለመሆን ምን ማለት እንደ ሆነ ኢየሱስ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡፡ እነዚያ የሃይማኖት መሪዎች

ለሚያንቋሽሿቸው ወገኖች ልቡ ያዝን ነበር፡፡ ለመሆኑ፣ «መንፈሳዊ» የሚባሉ ሰዎች እንኳ ለሚንቋቸው ይህን ያህል ራሱን የሰጠው ለምን ነበር? ትሑት መሆናቸውንና የበለጠውን ዓላማ ይራቡ፣ ይጠሙ እንደ ነበር ስለሚያውቅ ነው፡፡ ግብዣቸው ላይ የተገኘው ከእነርሱ ጋር የዓላማ አንድነት ስለ ነበረው ሳይሆን፣ አዲስ መንገድ ሊያሳያቸው ነበር፡፡

በተመሳሳይ መንገድ፣ እኛም የሞራል ዝቅጠትና ስብራት ውስጥ ወዳሉት ሰዎች እንድንሄድ ተጠርተናል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ እጆችና እግሮች ካልሆነች፣ ሌላ ማን ሊሆን ነው? እኛ የእርሱ አካል ነን፤ ያን ማድረግ የምንችል እኛና እኛ ብቻ ነን፡፡ የሰውን ሕይወት መለወጥ በሚችል የጸጋ ኃይል አሁን በክርስቶስ ውስጥ ነን፡፡ እንደ የእርሱ አምባሳደሮች ወይም እንደራሴዎች (የእርሱን ማንነት በመወከል) በዚህ ምድር እናገለግላለን፡፡ የእግዚአብሔርን እውነትና ብርሃን እኛ ለዓለም ካላደረስን ሌላ ማንም ያንን አያደርግም፡፡

ቀን 3

## ዝምተኛው ጨዋ

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተመላለስኩባቸው ዓመታት የተረዳሁት እርሱ ጨዋ መሆኑን ነው፡፡ የእርሱን ፈቃድ እኛ ላይ አይጭንም፡፡ ከእርሱ ጋር የማንነጋገር ከሆነ፣ እርሱም ዝም ይላል፡፡

ከሃያ አምስት ለበለጡ ዓመታት በዓለም ዙሪያ እየተመላለስኩ አገልግያለሁ፡ ፡ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ከአውሮፕላን ማረፊያ የሚቀበሉኝን ሹፌሮች በተመለከተ አንድ የተረዳሁት ነገር አለ፡፡ ሁሉም ደግና ለአገልግሎት እዚያ በምቆይበት ጊዜ የሚያስፈልጉኝን ነገሮችና መመሪዎች እንዳገኝ በማድረግ ረገድ ብዙ ረድተውኛል፡፡ ሆኖም፣ እነርሱን በተመለከተ የታዘብኩት ነገር፣ ካላናገርኳቸው ጨርሶ የሚያናግሩኝ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ምናልባት መሥራት ወይም ለአገልግሎቱ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች መኪና ውስጥ ማዘጋጀት እፈልግ ከሆነ እንዳያውኩን እኔን እንዳያናግሩ ፓስተሮቻቸው ስለሚነግሯቸው ነው፡፡ ስለዚህም አንዳንዴ፣ እኔ ራሴ ሹፌሩን ስለ ቤተ ሰቡና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን እየሠራ እንደ ሆነ እጠይቀዋለሁ፡፡ ንግግሩን እኔ

ካልጀመርኩ ምንም ትርጉም ያለው የሐሳብ ልውውጥ ሳናደርግ የሆነውን ርቀት ያህል መጓዝ ግድ ነው፡፡

ከመንፈስ ቅዱስም ከዚሁ ጋር የሚመሳሰል ባሕርይ እናያለን፡፡ መጀመሪያ፣ ራሳችንን ድምፁን መስማት በምንችልበት ሁኔታ ካላደረግን ለእኛ አይናገርም፡፡ ከእርሱ ጋር የማንነጋገር ከሆነ፣ ብዙ ጊዜ ዝም ነው የሚለው፡፡ ወደ እግዚአብሔር ስንቀርብ፣ እርሱም ወደ እኛ እንደሚቀርብ ያዕቆብ የተናገረውን አስታውሱ፡፡ የመጀመሪውን ርምጃ የመውሰድ ኃላፊነት አለብን፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ እኛ ራሳችን ከእርሱ ጋር ወደዚህ ድንቅ ኅብረት መግባት ይኖርብናል፡፡ በቀላል አነጋገር ከምንም በላይ ክቡር ወደ ሆነው ወደዚህ ኅብረት እንድንገባ ጥሪ ቀርቦልናል ማለት ነው፡፡ የመጀመሪያውን ርምጃ መውሰድ እኛ ፈንታ ነው፡፡

ይህ ብዙ አማኞች ያላወቁት እውነት ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ ብዙ ጊዜ፣ ‹‹እግዚአብሔር የማይናገረኝ ለምንድነው?›› ወይም፣ ‹‹ለዓመታት እግዚአብሔር ተናግሮኝ አያውቅም›› የሚሉትን የመሳሰሉ ቃሎች እሰማለሁ፡፡ ለመሆኑ፣ እነዚህ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው መንገድ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ እየፈለጉ ነው ወይ? ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ከፈለግን እርሱን ማወቅ መፈለግ አለብን - ይህም ማለት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ወዳጅ መሆንን አጥብቀን መፈለግ ይኖርብናል ማለት ነው፡፡

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ንቁና ጥብቅ ኅብረት እንድታደርጉ እመክራችኋለሁ፡ ፡ እንዴት ፈጥኖ ምላሽ እንደሚሰጥ ስትመለከቱ በጣም ትገረማላችሁ፡፡ ልክ እንደነዚያ ቀደም ሲል እንደ ነገርኳችሁ ሹፌሮች፣ እናንተ ብታናግሩትም ባታናግሩትም ሁሌም ከእናንተ ጋር ነው፤ ምክንያቱም እንደማይተዋችሁና እንደማይጥላችሁ ቃል ገብቷል (ዕብራውያን 13፥5 ይመ.)፡፡ ግን በመጀመሪያ እናንተ ካላናገራችሁት ዝም ይላል፤ እናንተም በሕይወታችሁ የመገኘቱን ሙላት አትለማመዱም ወይም ከእርሱ ጋር ኅብረት የማድረግን ጥቅም አታገኙም፡፡

## የእግዚአብሔር ጥልቅ ነገሮች

እስቲ፣ ዮሐንስ 16 እንደ ገና እንመልከት፣

ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤ አሁን ግን ልትሸከሙት አትችሉም። የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል። እርሱ ከራሱ አይናገርም፤ የሚሰማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም ወደ ፊት ስለሚሆነው ይነግራችኋል፤ የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ ያከብረኛል። የአብ የሆነው ሁሉ የእኔ ነው፤ እንግዲህ፣ 'የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ ያደርጋል' ያልኋችሁ ለዚሁ ነው (ዮሐንስ 16፥12-15)።

ኢየሱስ ይህን የተናገረው ከመሰቀሉ በፊት፣ በሮማውያን ባለ ሥልጣናት በተያዘበትና ወደ ሞት ከተወሰደበት ከዚያ ምሽት ጥቂት ቀደም ሲል ለደቀ መዛሙርቱ ባደረገው የመጨረሻ ንግግሩ ውስጥ ነበር። በእርግጥም ያ ጊዜ የተለየ ትኩረት የሚያሻው ቃል የሚናገርበት ጊዜ ነበር።

ኢየሱስ፣ «ብዙ የምነግችሁ ነበረኝ፤ አሁን ግል ልትሸከሙት አትችሉም» ማለቱን አስታውሱ (ቁጥር 12)። ለእነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ሁሉም ነገራቸው ነበር። ለዓመታት ከእርሱ ጋር ነበሩ። እያንዳንዳቸው እርሱን ለመከተል ቤተ ሰባቸውን፣ ወዳጆቻቸውንና ሥራዎቻቸውን ትተው መጥተዋል። ምናልባትም ደቀ መዛሙርቱ፣ የሚነግረንን ሁሉ ማስተዋል እንድንችል እኛ ማድረግ ያለብን ምንድነው? በማለት እያሰቡ ሊሆን ይችላል። ኢየሱስ ግን፣ «የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል» በማለት ያልተለመደ ዐይነት ተስፋ ቃል ሰጠ (ቁጥር 13)። በሌላ አነጋገር፣ «ምንም እንኳ እኔ አሁን በአካል ከእናንተ ጋር ብሆንም፣ የምሰጣችሁን ሁሉ መቀበል የምትችሉበት ደረጃ ላይ አይደላችሁም፤ ሆኖም፣ መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ፤ እርሱ የእኔን ቃል ይነግራችኋል፤ ፈቃዴን ይገልጽላችኋል፤ ወደ ፊት ለሚመጣውም ያዘጋጃችኋል» ማለቱ ነበር። እንዴት ያለ ድንቅ ተስፋ ቃል! ቀደም ሲል በዚያው ምሽት ኢየሱስ የተናገረውን አስታውሱ፣

ነገር ግን፣ እውነት እላችኋለሁ፤ መሄዴ ይበጃችኋል። እኔ ካልሄድሁ አጽናኙ አይመጣም፤ ከሄድሁ ግን እርሱን ወደ እናንተ እልካለሁ (ዮሐንስ 16፥7)።

ማንኛችንም ብንሆን፣ የምንወዳቸው ሰዎች በቅርበት እንዲያውቁን እንፈልጋለን፡፡ እግዚአብሔርም እንዲሁ ነው፡፡ ኢየሱስ በዚህ ምድር በተመላለሰ ዘመን፣ እግዚአብሔር አባቱ ለሰው ያዘጋጀውን ሁሉ በትክክል የሚያጸባርቅ ሆኖ ነበር የመጣው (ዕብራውያን 1፥1-3፤ ቈላስይስ 1፥15-19 ይመ.)፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንደሚታወቀው አሁን ኢየሱስ ያለው በሰማይ በአብ ቀኝ ነው፡፡ በዚህ ምድር ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እና በእነርሱ ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ነው፤ ስለሆነም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገሮች ማወቅ ከፈለግን፣ የእርሱን መንፈስ ማለትም የእውነትን መንፈስ ማወቅ ይኖርብናል፡፡

## ተጠራጣሪው ቶማስ

ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ዐሥር ደቀ መዛሙርት በሩን ዘግተው አንድ ክፍል ውስጥ ነበሩ፡፡ በድንገት ኢየሱስ ተገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱ በጣም ተደነቁ፤ ደግሞም ደነገጡ፡፡ እርሱ መንፈስ እንዳይደለ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ማሳመን ነበረበት፡፡ ዐሥሩ በትንሣኤው ተአምር ደስ ብሎአቸው ነበር፤ በኋላም ኢየሱስ በተገለጠ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ላልነበረው ቶማስ ይህንኑ ነገሩት፡፡ ይህ ወሬ ሲሰማ ቶማስ፣ ‹‹በምስማር የተቸነከሩትን የእጆቹን ምልክቶች ካላየሁ፣ ምስማሮቹ በነበሩበት ቦታ ጣቴን ካላደረግሁ፣ በጐኑም እጄን ካላስገባሁ አላምንም አለ›› (ዮሐንስ 20፥25)፡፡

ከሰባት ቀን በኋላ ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ሁሉ፣ በአንድ ክፍል ውስጥ እያሉ ኢየሱስ በድንገት ተገለጠ፡፡ ምንም ነገር ከማድረጉና ምንም ከመናገሩ በፊት ወዲያውኑ ወደ ቶማስ ዘወር አለና፣ ‹‹እሺ ቶማስ፣ እስቲ ይህን ጥርጥርህን በተመለከተ አንድ ነገር እናድርግ›› በሚል መንፈስ፣ ‹‹ጣትህን ወደዚህ አምጣ፤ እጆቼንም ተመልከት፤ እጅህን ዘርጋና በጐኔ አስገባ፤ አትጠራጠር፤ እመን አለው (ዮሐንስ 20፥27)፡፡ ቶማስም፣ ‹‹ጌታዬ አምላኬም!›› አለ፡፡ ከዚያ በመቀጠል ኢየሱስ የተናገረውን ተመልከቱ፣

> ቶማስ፣ አንተ ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ግን ብፁዓን ናቸው (ዮሐንስ 20፥29)፡፡

በሌላ አነጋገር ኢየሱስ፣ «ቶማስ፣ ሳያዩ የሚያምኑ እጅግ የተባረኩ ሌሎች ሰዎች አሉ» ማለቱ ነበር፡፡ ይህን ሳስብ ኢየሱስ ቶማስ ላይ ትንሽ ጠንከር ያለ ይመስለኝ ነበር፡፡ ታዲያ፣ አንድ ቀን ጌታ፣ «በመሠረቱ ቶማስን መቆጣቴ አልነበረም፤ ይልቁንም እውነቱን ነበር የነገርኩት፤ በመንፈሴ በኩል የሚውቁኝ ሰዎች ከእኔ ጋር የሚኖራቸው መቀራረብ፣ በአካል ከሚያውቁኝ ሰዎች መረዳት እጅግ ይበልጣል» አለኝ፡፡

ቀን 4

## ሦስት የግንኙነት ደረጃዎች

ታዲያ፣ ይህን ቃል ኢየሱስ ለቶማስ ሲናገር በትክክል ምን ማለቱ ነበር? ለጥያቄው መልስ ለመስጠት የጠለቀና የጠበቀ መቀራረብ የሚገኘው በእምነት እንጂ በማየት እንዳይደለ ገለጻ እንዳቀርብ ፍቀድልኝ፡፡

ሦስት የግንኙነት ደረጃዎች አሉ - በአካል ደረጃ፣ በነፍስ ደረጃ እና በመንፈስ ደረጃ፡፡ ዝቅተኛው (ላይ ላዩን የሆነው) ደረጃ፣ ተፈጥሮአዊ ወይም አካላዊ ደረጃ ነው፡፡ በጣም ታምራለች ወይም በጣም ያምራል፣ ታዲያ ለምን ተገናኝተን አንጨዋወትም የሚሉትን ሐሳቦች የመሳሰሉ አብዛኞቹ በሥጋዊ ግንኙነቶች የሚጀምሩት እዚህ ላይ ነው፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ አብዛኞቹ ሰዎች ትዳር የሚመሠርቱት ይህ የግንኙነት ደረጃ ላይ መሆኑ ነው፡፡ *አሁን ባንግባባም ውለን አድረን መግባባታችን አይቀርም፤ እምነታችን አንድ ባይሆንም፣ የኃላ ወደ ጌታ እንደሚመጣ እርግጠኛ ነኝ* በማለት ያስባሉ፡ ፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፤ እዚህ ደረጃ ላይ ነፍስ ወደ ዕድገት አትደርስም፡፡ ከዚያ ሰርግ ይጀመራል፤ የሽርሽር ቀን ይወሰናል፤ ከዚያ መልስ የትዳር ኑሮ ይጀመራል፡፡ እነዚህ ጥንዶች የጠበቀና የጠለቀ መቀራረብ ሊኖራቸው ይገባ ነበር፤ ያ ካልሆነ ትዳራቸው ሊበጠበጥ እንደሚችል መረዳት ነበረባቸው፡ ፡ ባልና ሚስት የጠበቀና የጠለቀ መቀራረብ ከሌላቸው ሚስት ከጓደኞቿ ጋር የምትፈልገውን ሁሉ ወደ ማሳደድ ትሄዳለች፤ ባልም ከጓደኞቹ ጋር የሚፈልገውን ወደ ማሳደድ ይሄዳል፡፡ ከዚያ በኃላ ያለው እንዲሁ አብሮ መኖር ብቻ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ለጋብቻ ያለው ዕቅድ በፍጹም ይህ አይደለም፡፡

የሚቀጥለው የግንኙነት ደረጃ የነፍስ ወይም የአንድን ሰው ሰብዕና መሠረት የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ደረጃ፣ በዳዊትና በዮናታን መካከል የነበረው ዓይነት ግንኙነት ነው፡፡ ‹‹…የዮናታን ነፍስ ከዳዊት ነፍስ ጋር ተቈራኘች›› (1 ሳሙኤል 18፥1)፡፡ ዮናታን በሞተ ጊዜ ዳዊት፣ ‹‹…ስለ አንተ አዘንሁ፤ አንተ ለእኔ እጅግ ውድ ነበርህ፤ ፍቅርህ ለእኔ ድንቅ ነበር፤ ከሴት ፍቅርም ይልቅ ግሩም ነበር›› በማለት አለቀሰ (2 ሳሙኤል 1፥26)፡፡ ዳዊት እየተናገረ ያለው ተገቢ ቦታውን ስለ ሳተ ዓይነት ግንኙነት አልነበረም፡፡ በመካከላቸው ምንም ዓይነት ሥጋዊ መሳሳብ አልነበረም፡፡ ግንኙነታቸው የነፍስ ስለ ነበር ከማንኛውም ጤናማ ያልሆነ ወይም ተፈጥሮአዊ ካልሆነ ሥጋዊ ግንኙነት የጸዳ ነበር፡፡ ያም ሆኖ፣ ከሥጋዊ ወይም ከአካላዊ ግንኙነት ይበልጥ እጅግ የጠለቀ ግንኙነት ነበራቸው (ዳዊት፣ ‹‹ከሴት ፍቅር ይልቅ›› ያለው ይህንን ነው)፡፡

ትዳር መመሥረት ያለበት የነፍስ ደረጃ ላይ ነው፡፡ እንዲህ ስል በተሳሳተ መንገድ አትረዱኝ፤ የግንኙነቱ አካላዊ ገጽታ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ሚስቴን ያገባሁዋት፣ በአካላዊ ነገርዋ ስለ ተሳብሁ ነበር፤ እርሷ ለእኔ በዓለም ካሉ ሴቶች ሁሉ የበለጠች ቆንጆ ናት፡፡ ይሁን እንጂ፣ በባልና ሚስት መካከል መኖር የሚገባውና መኖርም የሚችል፣ እጅግ በጣም የጠበቀ የግንኙነት ደረጃ አለ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነም፣ የሊዛ ሰብዕና ከአካላዊ ውበቷ የበለጠ ይማርከኛል፡፡

በጣም የሚያሳዝነው ግን፣ በፌስ ቡክ ስለሚተዋወቁ ብቻ ትዳር የመሠረቱ የብዙ ወንዶችና ሴቶች ታሪክ ሰምቻለሁ፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት፣ አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሰበክሁ ነበር፤ ከአገልግሎቱ በኋላ አንድ ሰው ወደ እኔ መጣ፡፡ ከሰውየው ጋር ስድስት ልጆች ነበሩ፡፡ ሁለቱን አቅፎአቸዋል፤ ሁለቱ እግሮቹ ሥር ድክ ድክ ይላሉ፤ ሁለቱ ግን ወዲያ ወዲህ ይሯሯጣሉ፡፡ ሰውየው አንድ ዓይነት ድብርት ውስጥ እንደ ሆነ ይታወቅ ስለ ነበር፤ ‹‹የእኔ ወንድም ደኅና አይደለህም እንዴ?›› በማለት ጠየቅሁት፡፡ ‹‹ደኅና አይደለሁም፤ ሚስቴ በኢንተርኔት ያገኘችውን ወንድ ወዳ ከስድስት ልጆቻችን ጋር ጥላኝ ሄዳለች›› አለኝ፡፡ ከብዙ የትዳር ዓመቶች በኋላ ባልዋን ትታ እስከትሄድ ድረስ የዚህች ሴት፣ ‹‹ነፍስ›› ከአዲሱ ሰውዬ ጋር ተቆራኝታለች፡፡ ተፈጥሮአዊ ከሆነው ልጆችን የመውደድ ዝንባሌ እስክትቆራረጥ ድረስ የዚህች እናት

ነፍስ ትስስር እጅግ የበረታ ሆኖአል፡፡

ብዙ ጊዜ የነፍስ ደረጃ ግንኙነት፣ ምንም ዓይነት አካላዊ መስተጋብር ላይጠይቅ ይችላል፤ ቢጠይቅ እንኳ በጥቂቱ ነው፡፡ ምንም ቅርርብ ሳይኖር እንዲሁ በርቀት ብቻ ያለ ግንኙነት ብዙ ጊዜ በጣም ጥሩ የሚባሉ ትዳሮችን የሚያፈርሰው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ያለ ምንም ሥጋዊ ግንኙነት ወይም አካላዊ መሳሳብ ጥንዶች የነፍስ ግንኙነትን ማሳደግ ላይ ማተኮር ይችላሉ፡፡

## በጣም የላቀ የግንኙነት ደረጃ

በጣም የላቀ ወይም የጠለቀ ግንኙነት በመንፈሳዊ ደረጃ የሚደረገው ግንኙነት ነው፡፡ ኢየሱስ ከቶማስ ጋር ሲነጋገር ያመለከተው ይህን ደረጃ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ጳውሎስ፣ ‹‹በውስጡ ካለው ከራሱ መንፈስ በስተቀር ከሰው መካከል የአንድን ሰው ሐሳብ የሚያውቅ ማን አለ?›› ብሎ ነበር (1 ቆሮንቶስ 2፥11)፡ ፡ በሌላ አባባል ከሰውየው ወይም ከሴትየዋ መንፈስ ጋር መጣጣም ከሌላችሁ በስተቀር የአንድን ሰው እውነተኛ ሐሳብ ወይም ፍላጐት ማወቅ አትችሉም ማለት ነው፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትኩት እኔና ሊዛ ሰላሣኛ የትዳር ዓመታችንን በቅርቡ አክብረናል፡፡ አብረን ባሳለፍነው ጊዜ በጣም ደስ ከሚሉ ትውስታዎች ጥቂቶቹ አንድ ኩሬ አጠገብ ተቀምጠን ስለ እግዚአብሔር ነገሮች የተጨዋወትናቸው ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ፣ ስለዚህ እያካፈልኳችሁ ስላለሁት መልእክት እንኳ እየተነጋገርን ብዙ ጊዜ አሳልፈን ነበር፡፡ እግዚአብሔር ልቤ ውስጥ ስላኖረው ነገር ሳካፍላት፣ መንፈስ የገለጠልኝን የበለጠ ብሩኅ በሚያደርግ ጥበብና መገለጥ ምላሽ ትሰጠኝ ነበር፡፡ ሁለታችንም ጥብቅ የመንፈስ ግንኙነት ስላለን፣ በጣም ጥልቅ በሆነ መንፈሳዊ ደረጃ ኅብረት ሊኖረን ችሏል፡፡

እኔና ሊዛ አብረን ከምንጸልይበት ምክንያት አንዱና ዋናው ይኸው ነው፡ ፡ በመንፈስ ነገሮች ዙሪያ በአንድነት ኅብረት በማድረጋችን በመንፈሳዊ ደረጃ ተሳስረናል፡፡ የሜሴንጀር ኢንተርናሽናል ሠራተኞች እያንዳንዱን ቀን የመጀመሪያ አሥራ አምስት ደቂቃ አብረው በመጸለይ እንዲሳልፉ ያደረግነው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ እንዲህ ያደረግነው የሥራ ባልደረቦቻችን መንፈሳዊ

ትስስር እንዲኖራቸው በማሰብ ነው፡፡ ይህ የጸሎት ጊዜ በባልደረቦቻችን መካከል ባለው ግንኙነት ላይ እጅግ አስደናቂ ነገር አድርጓል፡፡ ማንኛውንም ግንኙነት በተመለከተም ቢሆን፣ ይህ እውነት ነው - በቃሉና በጸሎት ዙሪያ ኅብረት ማድረግ በግለ ሰቦች መካከል ጥልቅ የግንኙነት ደረጃ ይፈጥራል፤ ምክንያቱም ግንኙነቱ መንፈሳዊ በመሆኑ ነው፡፡

መንፈሳዊ ነገሮችን በተመለከተ፣ አእምሮአዊ ውይይት በማድረግና በእውነተኛ መንፈሳዊ ኅብረት መካከል ልዩነት አለ፡፡ አንዳንዴ ሰዎች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግሩኛል፤ ግን፣ እነዚህ ሰዎች የሚነግሩኝ ከመረጃ ያለፈ እንዳልሆነ ይገባኛል፡፡ ይህን እንዴት አወቅሁ? የሚነግሩኝ አታካች ይሆንብኛል፤ አእምሮዬም ይላሽቃል፡፡ የሚናገሩት ከአእምሮአቸው እንጂ፣ ከመንፈሳቸው አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ከመንፈሳቸው የሚናገሩ ሰዎች አሉ፡፡ በመንፈሳዊ ደረጃ፣ የተገናኘን በመሆኑ፣ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ብዙ ሰዓት ብነጋገር እንኳ ምንም ድካም አይሰማኝም፡፡

ቀን 5

## በመንፈሱ በኩል እግዚአብሔርን ማወቅ

እስቲ፣ 1 ቆሮንቶስ 2፥11 በሙሉ እንመልከት፣

> በውስጡ ካለው ከራሱ መንፈስ በስተቀር ከሰው መካከል የአንድን ሰው ሐሳብ የሚያውቅ ማን አለ? እንደዚሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ በስተቀር የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚያውቅ የለም፡፡

እዚህ ላይ ሐሳብ ተብሎ የተተረጐመው ግሪክ ቃል፣ «የማንነት ይዞታ ወይም ውሑድ ነገር» ሊባል ይችላል፡፡ በመሠረታዊ ደረጃ ጳውሎስ፣ የእግዚአብሔርን መንፈስ በማወቅ ካልሆነ በቀር የእግዚአብሔርን እውነተኛ ማንነት (ጥልቅ የልቡን ሐሳብ) ማንም ማወቅ አይችልም ነው የሚለው፡፡ «ማወቅ» ሲባል ጥረት በማድረግ ወይም ያለ ምንም ጥረት ከሚገኝ እንዲሁ ላይ ላዩን ከሆነ ዕውቀት የበለጠ ጥልቅ መረዳት ወይም ግንዛቤ ማለት ነው፡፡ በአንድ አገር ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ሰዎች የአገራቸው መሪ ማን

እንደ ሆነ ያውቃሉ፤ ይሁን እንጂ፣ በግል ከእርሱ ጋር የተገናኘን በጣም ጥቂቶች ነን፡፡ ስለዚህም ጥልቅ ፍላጐቱ፣ እውነተኛ ዓላማው ወይም በእውነት የሚያምነው ምን እንደ ሆነ አናውቅም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በመንፈሱ በኩል ካላወቅነው በስተቀር ስለ እግዚአብሔር ያለን ዕውቀት፣ ‹‹የጋራ ከሆነ፣ የተለምዶ ዕውቀት›› ያለፈ ወይም የበለጠ አይሆንም፡፡

በመቀጠል ጳውሎስ፣ ‹‹ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ፣ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንምና፤ ይህም እግዚአብሔር በነጻ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ ነው›› ይላል (1ቆሮንቶስ 2፥12)፡፡ እንዴት የሚገርም ቃል ነው፡፡ ከእርሱ መንፈስ በስተቀር ማንም እግዚአብሔርን ማወቅ አይችልም (ቁጥር 11)፣ ሆኖም፣ እርሱ ያንን መንፈስ ሰጥቶናል፡፡ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ግንኙነት ካለን፣ በመንፈሳዊ ደረጃ - በላቀና በጠለቀ ደረጃ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ቅርርብ ሊኖረን ይችላል፡፡

ጳውሎስ ከመንፈስ ጋር እንዲህ ያለው ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ ምንም እንኳ እርሱ በአካል ከኢየሱስ ጋር ባይተዋወቅም፣ ‹‹ወንድሞች ሆይ፣ የሰበክሁላችሁ ወንጌል ሰው ሠራሽ አለመሆኑን እንድታውቁ እፈልጋለሁ፤ ከማንም ሰው አልተቀበልሁትም፤ ከማንም አልተማርሁትም፤ ይልቁንስ በመገለጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ ተቀበልሁት›› ብሏል (ገላትያ 1፥11-12)፡፡ ኢየሱስ ለጳውሎስ የተገለጠው በምን ነበር? እርሱ የተቀበለው መገለጥ ከማንኛውም ሰው የመጣ እንዳይደለ ጳውሎስ በግልጥ ተናግሮአል፡፡ ከሰው የተቀበለው ካልሆነ፣ ከኢየሱስ ጋር በአካል ተገናኝቶ የማያውቅ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ይህን መገለጥ ያገኘው በክርስቶስ መንፈስ (በመንፈስ ቅዱስ) በኩል ነበር ማለት ነው፡፡

ጳውሎስ በጣም ጥልቅ በሆነ ሁኔታ ከኢየሱስ ጋር ግንኙነት ሊኖረው የቻለው፣ በአካል ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባለ ማወቁ ይሆን? በአካል ከኢየሱስ ጋር ይተዋወቅ የነበረውና ከእርሱ ጋር አብሮ የገባና የወጣው ጴጥሮስ ሕይወቱ መጨረሻ ላይ በጻፈው መልእክት፣ ‹‹…ወንድማችን ጳውሎስ እንደ ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፤ በመልእክቶቹም ውስጥ በቀላሉ ለመረዳት የሚያዳግቱ ነገሮች አሉ›› ብሎአል (2 ጴጥሮስ 3፥15-16)፡፡ ለዓመታት ፊት ለፊት ከኢየሱስ ጋር የተነጋገረው ጴጥሮስ ነበር፡፡ በመገለጥ ተራራ ኢየሱስ የከበረ ጊዜ እርሱ እዚያ ነበር፡፡ የኢየሱስን መሰቀል በዓይኖቹ አይቷል፤

ከትንሣኤውም በኋላ ከኢየሱስ ጋር ተገናኝቶአል፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ በአካል ከኢየሱስ ጋር ዓመቶች ያሳለፈው ይህ ደቀ መዝሙር፣ ከመንፈስ ቅዱስ የተቀበላቸው አንዳንድ የጳውሎስ መገለጦች ለመረዳት የሚያዳግቱ እንደ ነበሩ ተናግሮአል፡፡ ይህ ከጴጥሮስ ይልቅ ጳውሎስ፣ ከኢየሱስ ጋር እጅግ ጥልቅ ግንኙነት ወደ ማድረግ ደረጃ መግባቱን እንደሚያሳይ እኔ በግሌ አምናለሁ፡፡

በእስትንፋሰ መንፈስ ቅዱስ፣ ጳውሎስ አብዛኞቹን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጽፎአል፤ ያም ሆኖ፣ አንድም ቀን በአካል ከኢየሱስ ጋር ተገናኝቶ አያውቅም፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ምክንያቱም፣ ኢየሱስን በሙላት የሚገልጠው መንፈስ ስለ ሆነ ነው፡፡ ‹‹ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤ አሁን ግን ልትሸከሙት አትችሉም፡፡ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል›› (የተሟላ መገለጥ ይሰጣችኋል) በማለት ኢየሱስ መናገሩን አስታውሱ (ዮሐንስ 16፥12-13)፡፡ አንድም ቀን በአካል አግኝቶት ስለማያውቅ ጳውሎስ በኢየሱስ ያለውን እምነት ከእርሱ ጋ ቀድሞ በነበረው መስተጋብር ላይ መመሥረት አይችልም ነበር፡፡ ከማየት ውጪ ማመንና መቀበል ነበረበት፡፡ እንዲህ ከሆነ፣ መንፈስ ሊገልጥለት የሚፈልገውን ነገር የሚጻረር ማንኛውም ቀድሞ የነበረ የአካላዊ ትውውቅ ወይም ግንኙነት ገጽታ ይወገዳል ማለት ነው፡፡ ከቶማስ ጋር ባደረገው ንግግር ኢየሱስ ያመለከተው ይህንኑ ነው፡፡ ጳውሎስ ከኢየሱስ ጋር በአካል ተገናኝቶ ባለማወቁ፣ ከጌታው ጋር በሚኖረው ግንኙነት ሙሉ በሙሉ መንፈሳዊ በሆነ ግንኙነት መደገፍ ነበረበት ማለት ነው፡፡ ሌላ ምርጫ አልነበረውም፡፡

እንደ ጳውሎስ ሁሉ ከአካላዊ ወይም ከሥጋዊ ግንኙነት የሚነሣ ቀደም ሲል የነበረ የተሳሳተ ሀሳብ ግጭት ሳይኖርብን፣ ኢየሱስን የመከተል ዕድል ለእኔና ለእናንተም ተሰጥቷል፡፡ በጣም የሚያስደንቀው እውነት፣ ኢየሱስን አይተነው ቢሆን ኖሮ ከሚኖረን የበለጠ ወደ ኢየሱስ መቅረብ የምንችል መሆኑ ነው፡፡ በአካል ከኢየሱስ ጋር ባንመላለስ እንኳ፣ በውስጣችን በሚኖረው የክርስቶስ መንፈስ አማካይነት ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ይኖርብናል - እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅና መንፈሳዊ ግንኙነት ይኖረናል ማለት ነው፡፡ እንዴት ይገርማል!

## እጅግ ጥልቅ በሆነ ሁኔታ እርሱን መለማመድ

ሥጋዊ አካላችን ገና ያልተዋጀ መሆኑን እግዚአብሔር ያውቃል። መንፈሳችን ግን ተዋጅቶአል፤ ትክክለኛ የክርስቶስን መልክ የያዘውም መንፈሳችን ነው (1 ዮሐንስ 4፥17 ይመ.) ነፍሳችን በመዋጀት ሂደት ላይ ነው (ያዕቆብ 1፥21 ይመ.)። ሆኖም ሥጋዊ አካላችን ገና መዋጀትን አልተለማመደም።

ምን ያህል በነገሮች በቀላሉ እንደምንሰለች ታዝባችኃል? አንዳንድ ሰዎች አዲስ መኪና ይገዛሉ፤ ከጥቂት ሳምንቶች በኃላ ግን ያረጀ ያህል ይሆንባቸዋል። ይህ ያልተዋጀ አካል ባሕርይ ነው። ሥጋዊው ወይም አካላዊው ጥልቀቱ ትንሽ፣ ዕድሜውም አጭር ነው፤ ቶሎ ያልፋል። ስለሆነም ከእርሱ መልካምነት የተነሣ እግዚአብሔር፣ «በአካል ራሴን ለሕዝቤ አልገልጥም። በእውነት እኔን ማወቅ እንዲችሉ በመንፈሴ በኩል ከእኔ ጋር ኅብረት ማድረግ የሚችሉበትን መንገድ አዘጋጃለሁ» እያለን ነው። ይህ አባባሉ፣ «የእኔን ጥልቅ ሐሳብ ማወቅ ይችሉ ዘንድ፣ እኔ ከምወዳቸው ጋር ዘላቂነት ያለው ግንኙነት አደርጋለሁ» የማለት ያህል ነው።

እንደ ቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ ሙሽራ ነን። እግዚአብሔር ከራሱ ጋር ዘላቂና ሕያው የሆነ ኃብቻ እያዘጋጀልን ነው። በአካል ደረጃ እርሱን ከማወቃችን በፊት፣ እጅግ ጥልቅ በሆነ ደረጃ (በመንፈሳዊ) እርሱን እንድናውቅ ፈቅዷል። በኃላ ላይ ጳውሎስ፣ «ከአሁን ጀምሮ ማንንም በውጫዊ ነገር አንመዝንም፤ ከዚህ ቀደም ክርስቶስን በዚህ መልክ መዝነነው ነበር፤ ከእንግዲህ ግን እንደዚህ አናደርግም» በማለት የጻፈው በዚህ ምክንያት ነበር (2 ቆሮንቶስ 5፥16)። በመንፈስ - በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እርሱን እናውቃለን። ክርስቶስ በአካል የተገለጠበት ጊዜ ነበር። ይሁን እንጂ፣ አሁን በአካል በዚህ ምድር ስላልሆነ፣ በመንፈስ እርሱን የማወቅ ዕድል አለን።

ከመንፈስ ጋር ኅብረት ወደ ማድረግ ልምምድ መግባት የማንፈልግ ከሆነ፣ ወልድን የማወቅ ዕድል አይኖረንም። ኢየሱስን ለእኛ ለመግለጥ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ሐሳብና አእምሮ ውስጥ ያለውን ሁሉ ይመረምራል። ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ ግንኙነት እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ፣ እንዲሁ ላይ ላዩን ከሆነ ዕውቀት ባለፈ በእርግጥ የእርሱን ማንነት ወደ መረዳት ጉዞ መግባት ይኖርባችኃል። ይህ ጉዞ እውን የሚሆነው ከመንፈስ ቅዱስ

ጋር ኅብረት በማድረግ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሠረቱ ባሕሎችን (የተለመዱ የአስተሳሰብ መንገዶች) አጥብቀን መያዝ የሌለብን በዚህ ምክንያት ነው፡፡ የተሳሳተ ግንዛቤ፣ የግላችን የሆነ ትችት፣ ወይም አሉታዊ ልምምዳችን ስለ መንፈስ ቅዱስ ባለን ግንዛቤ ላይ ጥላ እንዲጥሉ ከፈቀድን፣ የእግዚአብሔር መገኘት ክብር በሕይወታችን እንደሚኖር የተሰጠው ተስፋ ቃል በሙላት አይኖረንም፡፡ ከመንፈሱ ውጪ እግዚአብሔርን ማወቅ አንችልም፡፡

እርሱ የሚፈልገው የእናተም ፍላጐት እስኪሆን ድረስ፣ የእርሱ ስሜት የእናንተም ስሜት እስኪሆን ድረስ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ እንደምትችሉ አምናለሁ፡፡ በጣም ጥልቅ የሆነው ግንኙነት ደረጃ - ማለትም መንፈሳዊው ደረጃ ለእናንተም ጭምር ነው፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ፣ እንደ ማንኛውም ሌላ ገጽታ ሁሉ ከፈጣሪያችሁ ጋር የጠለቀ ቅርርብ ይኖራችኋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በቅርበት ከእግዚአብሔር ጋር መመላለስ ከፈለጋችሁ፣ የመንፈስ ቅዱስ ማንነት ለማወቅ መፈለግ ይኖርባችኋል፡፡ እርሱን ማወቅ የምትችሉት እንዴት ነው? ቃሉን በማንበብ፣ በእርሱ ፊት ጊዜ በማሳለፍ ነው፡፡ እግዚአብሔር ወደ እናንተ መቅረብ ይፈልጋል፤ ከእናንተ የሚጠበቀው ወደ እርሱ ለመቅረብ የመጀመሪውን ርምጃ መውሰድ ብቻ ነው፡፡

ከታች ያለው ጥቅስ ላይ ረጋ ብለህ ለማሰላሰል ጊዜ ውሰድ፤ መንፈስ ልብህ ውስጥ እንዲሠራ ፍቀድ፡፡ በእንዲህ ዓይነት መልኩ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ስትል፣ በሕይወትህ የእርሱን መገኘት እንዳትለማመድ ያደረገ ማንኛውንም ዓይነት አስተሳሰብ (መጋረጃ) እንዲያስወግድልህ ጠይቀው፡፡ አንዴ፣ ይህ መጋረጃ ከተወገደ፣ ከዚህ በፊት ባላየኸው ሁኔታ ታየዋለህ፡፡ የእርሱን ፊት እያየህ በመኖር ስትቀጥል፣ (እንደ አንድ ጥሩ ወዳጅ ከእርሱ ጋር ጊዜ ስታሳልፍ)፣ እርሱ ደግሞ እርሱን ወደ መምሰል ደረጃ ይለውጥሃል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፈውን ከታች ያለውን ምንባብ በጥንቃቄ ተመልከቱ፡፡

> ነገር ግን አንድ ሰው ወደ ጌታ ዘወር ሲል መሸፈኛው ይወገዳል፡፡ ጌታ መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ፡፡ እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስታወት እያንጸባረቅን፣ የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው፡፡ (2 ቆሮንቶስ 3፥16-18)

ቀን 1 ማሰላሰያ

# እንደ መምህርህ ተቀበለው

*እናንተ ግን ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በውስጣችሁ ይኖራልና ማንም እንዲስተምራችሁ አያስፈልግም፤ ነገር ግን እውነት እንጂ ሐሰት ያልሆነው የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉም ነገር እንዲያስተምራችሁ ያም እውነት እንጂ ሐሰት እንዳልሆነ እናንተንም እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ፡፡*

— 1 ዮሐንስ 2፥27

መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ብዙ ሥራ አለው፤ ምናልባትም፣ ትልቁ ሥራው አስተማሪ መሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሌም ቢሆን እርሱ ያስተምረናል፡፡ ምሪት ለመስጠት፣ አዛኝና ፍቅር በሆነ መንገድ እኛን ለማረምና ለማስተካከል በውስጣችን የሚኖር ፍጹም አባት ነው፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ዘመን የማይሽራቸው የመንፈስ ቅዱስ ማስተማሪያ መጻሕፍት ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል፣ በጽሑፍ የሰፈረ የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው፡፡ እንደ እርሱ ለማሰብ፣ እንደ እርሱ ለመናገር፣ እና እንደ እርሱ ለመሥራት፣ የሚያስፈልገንን የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም በሚያስፈልገን ትክክለኛ ጊዜ መግለጥ የአስተማሪያችን ሥራ ነው፡፡ ደራሲና ፓስተር የሆነው **ፍራንሲስ ፍራንጂፓን** ማስተዋል ባለበት ሁኔታ እንዲህ ይላል፣

> ‹‹ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመሆን የእግዚአብሔር ቃል፣ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል የምንለወጥበት መንገድ ነው፡፡ ቃሉ እግዚአብሔር ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔር አይደሉም፤ በቃሉ በኩል የሚያልፍ፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ግን እግዚአብሔር ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔርነቱ መከበር አለበት፡፡ ስለሆነም፣ ጌታን በምትፈልግበት ጊዜ… በአእምሮ ብቻ እንዳታነብ ጸልይ፡፡ ይልቁንም በቃሉ አማካይነት እንዲናገርህ መንፈስ ቅዱስን ለምነው… በጌታ ፊት በትሕትና ተንበርክከህ እያለ ቃሉ ነፍስህ ውስጥ ይታተማል፤ ከአንተም ጋር ይዋሃዳል (ያዕቆብ 1፥21)[1]፡፡

እስቲ ጥቂት ቆም በልና፣ ለመሆኑ የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት ነው እየቀረብኩት ያለሁት? እንዲያስተምረኝ መምህሬን እጋብዘዋለሁን? የእኔን ሐሳብ ውስጡ ጨምሬ ነው የማነበው ወይስ እርሱ የሚለውን ብቻ እቀበላለሁ? በማለት ራስህን ጠይቅ፡፡ አሁን ደግሞ ቃሉ ሕያውና የእኔነቴ አካል እንዲሆን ምን የተለየ ነገር ማድረግ አለብኝ? በማለት መንፈስን ጠይቅ፡፡ የምታገኘውን መልስ ጻፈው፤ ተግባርም ላይ አውለው፡፡

መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምረው በጽሞና ጊዜ ብቻ ነውን? አይደለም፡፡ እርሱ ሁሌም ያስተምራል፤ ከእርሱ ጋር ከተስማማን ከእያንዳንዱ ሁኔታ የምንማረው ይኖራል፡፡ ፍራንጂፓን እንዲህ ይላል፤

‹‹…ምንጊዜም እርሳስና ማስታወሻ አይለይህ… የተጠራነው በእርሱ እንድንኖር እንጂ፣ አልፎ አልፎ ጉብኝት እንድናደርግ አይደለም፡፡ በየትኛውም ቦታ፣ ስለ ማንኛውም ነገር፣ መንፈስ ሊናገርህ እስኪችል ድረስ የሚሰማ ጆሮ ማዳበር ይኖርብሃል፡፡ አክብረው እርሱም ያከብርሃል፡፡››[2]

የበለጠ የሚመችህን ማንኛውንም መንገድ መጠቀም ትችላለህ፡፡ ዋናው ነገር አንተ ማድመጥ መቻልህና እርሱ የተናገረውን ማስታወስህ ነው፡፡

እነዚህን ጥቅሶች በጥንቃቄ አሰላስል፡፡ አንተ ሕይወት ውስጥ ስላለው ቃል መንፈስ ግልጽ ያደረገልህ ምንድነው?

**2 ጢሞቴዎስ 3፥16-17፤ 2 ጴጥሮስ 1፥12-21**

**ዘዳግም 6፥6፤ 11፥18፤ መዝሙር 119፥9-11፤ ቈላስይስ 3፥16**

**መዝሙር 19፥8፤ 119፥105፤ 130፤ ምሳሌ 4፥20-23፤ 6፥20-23**

**ዕብራውያን 4፥12፤ ያዕቆብ 1፥21፤ ኤርምያስ 23፥28-29**

*‹‹ወደ እኔ ጩኽ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤ አንተም የማታውቀውን ታላቅና የማይመረመር ነገር እገልጥልሃለሁ፡፡››*

—- ኤርምያስ 33፥3

ቀን 2 ማሰላሰያ

# እንደ ጌታ፣ ለእርሱ ቅድሚያ ስጥ

*ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፣ ‹‹ከሁሉ የሚልጠው ይህ ነው፤ - እስራኤል ሆይ ስማ፣ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ አንተም ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህና በፍጹም ኃይልህ ውደድ፡፡››*

— ማርቆስ 12፥29-30

መንፈስ የሆነው ጌታ እጅግ ይወደናል፣ እኛም ከሁሉ አስበልጠን እንድንወደው ይፈልጋል፡፡ ፍቅራችንና ትኩረታችን፣ ከዓለምና በውስጡ ካሉ ነገሮች ጋር እንዲያያዝ አይፈልግም፡፡ እርሱ እንዲህ ብሏል፤

> ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር አትወደዱ፣ ማንም ዓለምን ቢወድ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤ ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ - የሥጋ ምኞት፣ የዓይን አምሮትና የኑሮ ትምክህት ከዓለም እንጂ፣ ከአብ የሚመጣ አይደለም፡፡ ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘላለም ይኖራል፡፡
>
> - 1 ዮሐንስ 2፥15-17

እነዚህ ተያያዥ ጥቅሶችንም ተመልከት - ማቴዎስ 16፥24-26፤ ቲቶ 2፥12-14፤ ያዕቆብ 4፥4-6፤ ዮሐንስ 15፥18-21፤ ሮሜ 12፥2፡፡

**ሁለንተናዬን ያሳረፍኩት ምን ላይ ነው?** በእውነት ራስህን መርምር፤ እንዲህ በማለት ጠይቅ፣

ጊዜዬንና ትኩረቴን የሚይዘው ማን ወይም ምንድነው? ነጻ ጊዜዬን ምን እያደረግሁ ነው የማሳልፈው?

ይበልጥ የሚያጓጓኝ ማን ወይም ምንድነው? ቴክኖሎጂና አዳዲስ ነገሮች በሕይወቴ ተገቢውን ቦታ ይዘዋል?

ገንዘቤን የማጠፋው በምን ዓይነት ነገሮች ነው?

**አብዛኛው የአእምሮዬን ክፍል የያዘው ምንድነው? አብዝቼ የምናገረው ስለ ማን ወይም ስለ ምንድን ነው? ጸሎቴ ውስጥ ሰፊውን ቦታ የሚይዘው ምንድነው?**

*ቃሎቻችን ሁለንተናችንን የያዙ ነገሮችን ይገልጣሉ፡፡ አፋችን የሚናገረው ከልባችንሞልቶ የተረፈውን እንደ ሆነ ኢየሱስ ተናግሮአል (ሉቃስ 6፥45 ይመ.)፡፡*

**መልሶችህን እንደ ገና ተመልከት፡፡ ‹‹ቅድሚያ የሰጠኃቸው ነገሮችን መልክ እንድታስይዝልኝ አንተ ታስፈልገኝ ይሆን? በሕይወቴ ጣዖት የሆነብኝ ምንድነው? ከአንተ ይበልጥ የምፈልገው ነገር ይኖር ይሆን?›› በማለት መንፈስ ቅዱስን ጠይቀው፡፡ ምን መልስ ያገኘህ ይመስልሃል? ሁለንተናህን እርሱ ላይ እንድታሳርፍ ምን ዓይነት ርምጃ እንድትወስድ ነው እየጐተጐተህ ያለው?**

**ማቴዎስ 6፥19-21 እና ቈላስይስ 3፥1-17 ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል አሰላስል፡፡ ለእግዚአብሔር አምላክህ ታማኝ እንድትሆን መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳህ፣ የምታቀርበውን ራስን የመስጠት ጸሎት ለመጻፍ ተጠቀምባቸው፡፡**

# ቀስ በቀስ በጸጋው ማደግ

*እኛም ሁላችን ባልተሸነፈ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፡፡*

— 2 ቆሮንቶስ 3፥18

ወደ መስቀሉ ከመሄዱ በፊት ጥቂት ቀደም ሲል መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ነበር፣ ‹‹ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤ አሁን ግን ልትሸከሙት አትችሉም፡፡ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል›› (ዮሐንስ 16፥12-13)፡፡

ሁሉን እንደሚያውቅ አምላክ፣ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ብዙ ነገሮች ሊያካፍላቸው ይችል ነበር፤ ሆኖም ገና መረዳት እንደማይችሉ ያውቅ ነበር፡ ፡ ለማደግ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እርሱ ከሞተ፣ ከተነሣና ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ቀስ በቀስ በጸጋው ለማደግ እንዲረዳን አብ፣ መንፈሱን ይልካል፡፡

አንድ ጥሩ አባት ገና አዲስ የተወለደ ልጁ ማንበብና መጻፍ እንዲችል ይጠብቃልን? ገና ዳዴ እያለ ያለ ልጁ መኪና መንዳት እንዲያውቅ ይጠብቃልን? በፍጹም አይጠብቅም፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ መንፈስ ቅዱስም እርሱ ሊነግረን የፈለገውን እውነት መረዳት እስክንችል ድረስ እንድናድግ ይጠብቃል፡፡ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራን ቅዱሳት መጻሕፍትን በተመለከተ ብቻ ሳይሆን ስለ ራሳችን፣ ስለ ልጆቻችን፣ ስለ ጤናችን፣ ስላለንበት ሁኔታና ከዚያም የበለጡ ነገሮችን በተመለከተም እውነቱን ያሳየናል፡፡

የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን ከአንድ የእምነት ደረጃና ክብር ወደ ሌላው እናድጋለን፡፡[3] በዚህ ሂደት የራሳችን ድርሻ አለ፤ የመንፈስ ቅዱስም ድርሻ አለ፡፡ ፊልጵስዩስ 1፥6፤ 2፥12-13፤ 1 ተሰሎንቄ 5፥23-24 እና ዕብራውያን 13፥20-21 ላይ በጥንቃቄ አሰላስል፡፡ በክርስቶስ ማደግን አስመልክቶ በእነዚህ ጥቅሶች አማካይነት መንፈስ ግልጥ ያደረገልህ ምንድነው? ተደጋግሞ የተነገረ ዐቢይ ሐሳብ ማየት ቻልህ?

በአሥራ ዘጠነኛው መቶኛ ዓመት አካባቢ በኢንግላንድ እጅግ ታዋቂ ሰባኪ የነበረው **ቻርለስ ኤች ስፐርጂን** መንፈስ ቅዱስንና በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግን ጨምሮ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በስፋት ጽፎአል፡፡ እንዲህ አለ፤

> ‹‹እኛ ራሳችን ማድረግ ለማንችለው ነገር በኢየሱስ እንተማመናለን፡፡ ሁሉንም ነገር በራሳችን ማድረግ ብንችል ኖሮ፣ ለምን ኢየሱስን ማየት አስፈለገን? ማመን የእኛ ድርሻ ነው፤ እኛን አዲስ አድርጎ መፍጠር የጌታ (የመንፈስ ቅዱስ) ድርሻ ነው፡፡ እርሱ በእኛ ቦታ ሆኖ አያምንልንም፤ እኛም ዳግም የመውለድን ሥራ አንሠራለትም፡፡ እርሱ ለሰጠን ትእዛዝ መታዘዝ ብቻ ለእኛ በቂ ነው፡፡ በእኛ ውስጥ አዲስ ልደት መሥራት ግን የጌታ ነው፡፡››[4]

በመንፈሳዊ ሕይወቴ የበለጠ በሳል መሆን አለብኝ በማለት ራስህን አታስጨንቅ፡፡ ያ እውነት አይደለም፡፡ የበደለኝነት ስሜት እንዲሰማህ ያደርጋል፣ መንፈሳዊ ዐቅምህን ያሚጥጣል እንጂ ምንም አይጠቅምህም፡፡ ቆም በልና፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ አሁን ምን ደረጃ ላይ ነኝ›› (በመንፈሳዊና በብስለት ደረጃ) በማለት ጸልይ፡፡ ምን መልስ አገኘህ?

አንተ ራስህን ማየት ያለብህ፣ መንፈስ አንተን በሚያይበት ሁኔታ ነው፡፡ በየጊዜው በማደግ እንድትቀጥል ያለህበትን ቦታ የመቀበል ጸጋ እንዲሰጥህ ጠይቀው፡፡

ራስህን ለመለወጥ የችኮላ ሙከራ እያደረግህ ነውን? ከሆነ፣ እንዴት? አሁን በተለየ ዓይን ማየት ቻልህ?

ቀን 4 ማሰላሰያ

# እርሱ ለሚፈጥረው መለኮታዊ ግንኙነት ዋጋ መስጠት

*ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን... በወንድማማች መዋደድ አጥብቃችሁ ተዋደዱ፡፡*

— ሮሜ 12፥9-10

የተፈጠርነው ግንኙነት እንዲኖረን ነው - አዎን፣ ከአባትና ከሌሎችም ጋር፡፡ እስቲ አስቡ፤ ግንኙነት ባይኖራችሁ ኖሮ ሕይወታችሁ ምን ይመስል ነበር? ሕይወት ሰጪ ግንኙነቶቻችሁ ሁሉ ቢወሰዱ ኖሮ ምን ይቀርላችሁ ነበር? ብቸኛና ባዶ ሕይወት ብቻ፡፡

ስላለን ግንኙነት ሁሉ እግዚአብሔር ይመስገን! እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ጓደኛ በማንኛውም ዋጋ መተመን ከሚቻለው በላይ ነው፡፡ መልካም ጓደኛ ብረት ብረትን እንደሚስል በአእምሮአዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ሕይወታችን ይስለናል፡፡ መልካም ጓደኛ በፍቅር ስሕተታችን ያሳየናል፤ አስፈላጊ ከሆነም እርምትና ተግሣፅ ይሰጠናል፡፡ መልካም ጓደኛ በስኬታችሁ ደስ ይለዋል፤ በሕይወት አስቸጋሪ ገጠመኞች ወደ ፊት እንድትገፉ ያበረታታችኋል፡፡

*ለሥራቸው መልካም ውጤት ስለሚያገኙ ከአንድ ሁለት መሆን ይሻላል፤ አንዱ ቢወድቅ፣ ባልንጀራው ደግፎ ያነሣዋል፡፡ ቢወድቅ የሚያነሣው ረዳት የሌለው ግን እንዴት አሳዛኝ ነው!*

– መክብብ 4፥9-10

ሦስት የግንኙነት ደረጃዎች እንዳሉ ተመልክተናል - አካላዊ፣ ነፍሳዊና መንፈሳዊ፡፡ ይህ መረዳት አሁን ያለህን ግንኙነት በእንዴት ዐይነት ሁኔታ እንድታየው ረዳህ? ይበልጥ የረዳህ ከማን ጋር ያለህን ግንኙነት አስመልክቶ ነው? ለምን?

ሊኖሩን ከሚችሉ ጥልቅና ትርጉም ያላቸው ግንኙነቶች ዋናዎቹ በመንፈሳዊ ደረጃ የሚኖሩን ግንኙነቶች ናቸው፡፡ ይህ ዓይነቱ ግንኙነት ምን እንደሚመስል ግለጽ? አካላዊ ወይም ነፍሳዊ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን፣ በመንፈሳዊ ደረጃ የሚደረግ ኅብረት አንዳንድ ጠቀሜታዎች ምንድናቸው?

ከእነርሱ ጋር የጠለቀና የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖርህ የምትፈልገው ሰዎች አሉ፡፡ እዚህ ላይ ጥቂት ቆም በልና፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ አንተ ልቤ ውስጥ ካኖርሃቸው ሰዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነትን እንዳዳብር ምን ማድረግ አለብኝ?›› በማለት ጸልይ፡፡ ጸጥ ብለህ አድምጥ፡፡ እርሱ የሚነግርህን ጻፍ፡፡

**መለኮታዊ ትስስርን በተመለከተ ጸሎት**

*መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ መለኮታዊ ትስስር ስጠኝ፡፡ ዮናታን ከዳዊት ጋር፣ ሩት ከኑኃሚን ጋር፣ ዮሐንስ ከኢየሱስ ጋር፣ በነበራቸው ዓይነት ትስስር አንተ እንድቀርባቸው ከምትፈልገው ሰዎች ጋር አስተሳስረኝ፡ ፡ በመንፈሳዊ ደረጃ ካሉት ጋር ጭምር፣ ጤናማ ወዳጅነትን የማዳበር ጸጋ ስጠኝ፡፡ በኢየሱስ ስም አሜን!*

**ተጨማሪ ጥናት...**

ምሳሌ 13፥20፣ 17፥9፣ 17፤ 27፥6፣ 10፣17፤ ዮሐንስ 15፥13፣ 1 ዮሐንስ 1፥7፤ 1 ሳሙኤል 18፥1-4

ቀን 5 ማሰላሰያ

# ጥልቀት ባለው ደረጃ እግዚአብሔርን መለማመድ

*...እግዚአብሔር ልብን ሁሉ ስለሚመረምርና ሐሳብን ሁሉ ስለሚያውቅ የአባትህን አምላክ ዕወቅ፡፡*

– 1 ዜና 28፥9

ትልቁ የእግዚአብሔር ፍላጐት ከእኛ ጋር ጥልቅ ግንኙነት ማድረግ ነው፤ ሕይወታችንን ከእርሱ ጋር እንድናደርግ ጥሪ ያቀርብልናል፡፡ ለመሆኑ፣ ከዚህ የበለጠ ምን መሻት አለ? ጳውሎስ እንዲህ አለ፤ ‹‹ከዚህም በላይ ለእርሱ ብዬ ሁሉን ነገር የተውሁለትን፣ ወደር የሌለውን ጌታዬን ክርስቶስን ኢየሱስን ከማወቅ ታላቅነት ጋር ሲነጻጸር፣ ሁሉንም ነገር እንደ ጉድለት እቈጥረዋለሁ፤ ለእርሱ ስል ሁሉን አጥቻለሁ፤ ክርስቶስን አገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ›› (ፊልጵስዩስ 3፥8)፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስን ጥልቀት መለማመድ **የጂያን ጉየን** ናፍቆት ነበር፡፡ ይህ ጉዳይ ለእርሷ እጅግ ዋነኛ በመሆኑ፣ በዚህ ርዕስ መጽሐፍ ጽፋለች፡፡ ይህች በአሥራ ሰባተኛው መቶኛ ዓመት የነበረች ፈረንሳዊት እንደ ጆን ዌስሊ፣ ሐድሰን ቴይለር እና ዋችማን ኒ የመሳሰሉ አማኞች ላይ በጐ ተፅዕኖ አሳድራለች፡፡ እርሷ ስትጽፍ እንዲህ አለች፡፡

> ‹‹እስቲ ልጠይቃችሁ... እጅግ ጥልቅ በሆነ መንገድ ጌታን ማወቅ ትመኛላችሁን? እንዲህ ያለውን ልምምድ፣ እንዲህ ያለውን ሕይወት፣ እርሱ ለእናንተ የሚቻል አድርጐታል፡፡ እርሱ ለዋጃቸው ልጆቹ ሁሉ በሰጠው ጸጋ በኩል የሚቻል አድርጐታል፡፡ ይህን እውን ያደረገው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነው፡፡ ታዲያ፣ በእንዲህ ዓይነቱ ጥልቀት ያለው መንገድ ጌታን ወደ ማወቅ የምትመጡት እንዴት ነው? ቁልፉ ጸሎት ነው፡፡››[5]

በጥልቀት እግዚአብሔርን በማወቅ ረገድ ጸሎትን እንዴት ትገልጡታላችሁ? የኢየሱስን ጸሎት ከማቴዎስ 6፥5-15 በጥንቃቄ አንብብ፡፡ ከእርሱ የምትማረውና በሕይወትህ ተግባራዊ የምታደርገው ምንድነው?

ቀደም ሲል እንደ ተማርነው ዳግም ስንወለድ መንፈስ ቅዱስ መንፈሳችን ውስጥ ለመኖር ይመጣል፡፡ ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር የሚገናኘው መንፈሳችን ውስጥ ነው፡፡ ጂያን ጉየን እንዲህ በማለት ትቀጥላለች፣

> ‹‹ጌታ የሚገኘው መንፈሳችሁ ውስጥ፣ ጥልቅ እናንተነታችሁ ውስጥ፣ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ነው፤ እሱ የሚያድረው እዚያ ነው፡፡ ጌታ እናንተ ውስጥ ለመኖር እንደሚመጣ ቃል ገብቷል (ዮሐንስ 14፥23)፣ እርሱን የሚያመልኩና ፊቃዱን የሚያደርጉትን እዚያ እንደሚያገኛቸው ቃል ገብቷል፡፡ ጌታ መንፈሳችሁ ውስጥ ያገኛችኋል… የውስጥ ልቦናችሁን ወደ እርሱ ከመለሳችሁ፣ የእርሱን ሓልዎት ትለማመዳላችሁ፡፡››[6]

እጅግ ቅርበት ባለው መንገድ ጌታን ማወቅ የምንችለው በመንፈስ - እርሱ በሰጠን መንፈስ ቅዱስ በኩል ነው (1 ቆሮንቶስ 2፥9-12)፡፡ ቆም በልና፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ ስለ አንተ ያለኝን ግንዛቤ ያጣመመ የተሳሳተ አስተሳሰብ፣ መጥፎ ልምምድ ወይም የግሌ የሆነ ትችት ይኖር ይሆን?›› በማለት ጸልይ፡፡ ጸጥ ብለህ አድምጥ፡፡ ከእርሱ ሓልዎት ያገለለህን ማንኛውንም የአእምሮ ዝንባሌ እንዲያስወግድልህ ለምነው፡፡ ግልጽ የሚያደርግልህ ነገር ካለ ጻፈው፡፡

ይህን እውነት አሰላሰል፤ ትርጉሙን ለልብህ እንዲገልጥልህ መንፈስ ቅዱስን ለምነው፡፡

*ነገር ግን አንድ ሰው ወደ ጌታ ዘወር ሲል መሸፈኛው ይወገዳል፡፡ ጌታ መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ ነጻነት አለ፡፡ እኛም ሁላችን ባልተሸፈነ ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያንጸባረቅን የእርሱን መልክ እንድንመስል ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ከሆነ ጌታ ነው፡፡*

– 2 ቆሮንቶስ 3፥16-18

# የውይይት ጥያቄዎች

1. የሰዎች ባሕልና ወግ ከእግዚአብሔር ቃል የበለጠ ሥልጣን እንዲኖረው ማድረጋቸውን ኢየሱስ ለፈሪሳውያን ተናግሮአል፡፡ ለመሆኑ የሰዎች ባሕል ምንድነው፣ ከፈጣሪ ጋር ያለንን ኅብረት የሚጐዳውስ እንዴት ነው? ከእግዚአብሔር ቃል እውነት የበለጠ ቦታ የተሰጠው ከዘመኑ ባሕል ቢያንስ አንድ ምሳሌ አቅርብ፡፡

2. መንፈስ ቅዱስ ጥሩ ወዳጅህ ለመሆን በጥብቅ ይፈልጋል፤ ከአንተ ጋር የጠበቀ ኅብረት ለማድረግ አብዝቶ ይቀናል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን (የአማኞችን) ትኩረትና ፍቅር ከመንፈስ ዘወር ያደረጉ ነገሮች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ታስባለህ? ከዓለም ጋር ከተጣላለፍን፣ የእርሱን ደስታ፣ ባለቤትነትና ከመንፈስ ጋር ሊኖረን ከሚገባው ኅብረት ይልቅ፣ ማንነታችንን ማስከበር ስንፈልግ ምንድነው የሚሆነው?

3. ከዮሐንስ 20÷29 እንደምንመለከተው ኢየሱስ ለሐዋርያው ቶማስ የነገረው ምን ነበር፡፡ ይህ እውነት በ2 ቆሮንቶስ 5÷16 ጳውሎስ ካቀረበው የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚያያዘው እንዴት ነው፤ ከጌታ ጋር ያለንን ግንኙነት በማሳደግ ረገድ ይህ እውነት ሊረዳን የሚችለው እንዴት ነው?

4. ከሌሎች ጋር ሊኖሩን የሚችሉ ሦስቱ የግንኙነት ደረጃዎች ዘርዝር፡ ፡ እጅግ ጥልቅ የሆነው የትኛው ነው? በዚህ ደረጃ ከሰዎች ጋር መተሳሰር የምንችለው እንዴት ነው?

5. መንፈስ ቅዱስ ውስጥ እጅግ ድንቅ ስጦታ፣ ማለትም በቅርበት እግዚአብሔንር የማወቅ ችሎታ ተሰጥቶናል፡፡ 1 ቆሮንቶስ 2÷11-16 በጥንቃቄ አንብብ፡፡ በእውነት እግዚአብሔርን ማወቅን በተመለከተ፣ በዚህ ምንባብ መንፈስ ቅዱስ እየተናገረ ያለው ምንድነው?

6. ጴጥሮስና ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ማንም ያላገኘውን ልምምድ አግኝተዋል ማለትም ፊት ለፊት ከኢየሱስ ጋር ተገናኝተዋል፡፡ ጳውሎስ ይህ ልምምድ አልነበረውም፤ ያም ሆኖ ግን እግዚአብሔር በኃይል ተጠቅሞበታል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው እንዴት ነው?

የበለጠ ለመርዳት ዮሐንስ 20፥29፣ 2 ቆሮንቶስ 5፥16 እና 2 ጴጥሮስ 3፥15-16 ተመልከት።

7. ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ማደረግን ችላ ካልን፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት ምንድነው የሚሆነው? ፈቃደኛ ከሆንህ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተግባራዊ በሆነ መልኩ ግንኙነት ማድረግ የቻልህበትና የእርሱን ድንቅ ወዳጅነት የተለማመድህበት መንገድ ካለ ለጥናት ቡድኑ አካፍል።

## ምዕራፉ በአጭሩ

- ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅና ጥብቅ ግንኙነት እንዲኖረን ከፈለግን፣ በመንፈሱ በኩል እርሱን ማወቅ አለብን፡፡
- የእግዚአብሔርን ሓሳብ፣ ፈቃድና ዓላማ የሚያውቅና የሚገልጥ መንፈስ ብቻ ነው፡፡
- የእግዚአብሔር መንፈስ ተሰጥቶናል፤ እርሱ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራን ከሁሉም የበለጠ መምህር ነው፡፡
- የዓለም ወዳጅ መሆን፣ በራስ ወዳድነት ስሜት ሥልጣንና ደስታን ማሳደድ - የእግዚአብሔር ጠላት መሆን ነው፡፡
- መንፈስ ቅዱስ ጨዋ ነው፤ ፈቃዱን በኃይል አይጭንብንም ወይም እንድንወደው አያስገድደንም፡፡
- ሦስቱ የግንኙነት ደረጃዎች አካላዊ፣ (ዝቅተኛውና ላይ ላዩን የሆነው) ነፍሳዊ (ወይም ሰብዕናዊ)፣ እና መንፈሳዊ (ጥልቅና፣ በጣም የጠበቀ መቀራረብ ያለበት) ናቸው፡፡
- ከአካላዊው የኢየሱስ ማንነት ጋር በነበረው መስተጋብር እርሱን ከማወቅ ይልቅ በመንፈስ እግዚአብሔርን ማወቅ፣ ጥልቅ እና የበለጠ መቀራረብ ያመጣል የተባለው እንዴት ነው፡፡

# 4

# ከመንፈሱ ኃይል መቀበል

## ቀን 1

ስለ አንድ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ስለ ነበረ ንጉሥ ለማሰብ ጥቂት ጊዜ ውሰዱ። ስለ ቤተ መንግሥቱ፣ ስለሚያደርጋቸው ጦርነቶችና ስላለው ክብር በአእምሮአችሁ ለማየት ሞክሩ። የንጉሡ ሥልጣንና እርሱ የመጣበት ዘር ሐረግ ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ፣ ንጉሦች በሕዝብ ዘንድ እጅግ ይከበራሉ፣ አለ ቅጥ ይፈራሉ፤ ብዙ ሀብት የማከማቸት ዕድልም አላቸው። የንጉሡ ቃል በራሱ ሕግ ነው፤ ፍርዱም የመጨረሻው ነው። አንድ ጥሩ ንጉሥ በእርሱ ኃላፊነት ሥር ላሉ ሰዎች ይከላከላል፤ የአገሩን ድንበር በማስከበር፣ ተጨማሪ ሀብት በማስገኘት፣ የመንግሥትን ጥቅም ያስጠብቃል።

እዚህ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች በጣም ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው፤ ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ጊዜ ፍጹማዊ ሥልጣን እንዲኖራቸው ይደረጋል። እኔ እየተናገርኩ ያለሁት በዲሞክራሲያዊ መንገድ ስለ ተመረጡትና ለተወሰነ ጊዜ ሥልጣን ላይ ስለሚቆዩ መሪዎች ሳይሆን፣ ገደብ የለሽ ሥልጣን ስላላቸው ንጉሦች ነው። እንግዲህ እንዲህ ያለውን ሥልጣኑን ችላ ያለ ወይም ሥልጣን

እንዳለው እንኳ የማያውቅ ንጉሥ አስቡ፡፡ መንግሥቱን በተመለከተ ምን የሚሆን ይመስላችኃል? በተቀናቃኝ ኃይል ይሸነፋል፤ ሕዝቡ ባሪያዎች ይሆናሉ፤ አገሪቱ ያላት ሀብት ሁሉ ይዘረፋል፡፡ አንድ ንጉሥ የንጉሥነት ቦታ ላይ፣ (ማለትም ቤተ መንግሥት መኖሩና የተንደላቀቀ ኑሮ መኖሩ) መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ የንጉሥነትንም ተግባርና ኃላፊነትም መወጣት አለበት፤ ይህ ደግሞ ከተሰጠው የንጉሥነት ሥልጣን የሚመነጭ ነው፡፡ ከንጉሥነቱ ጋር ተያይዞ የሚመጣውን ሥልጣን እስካልተጠቀመበት ድረስ፣ እንዲሁ ቦታው ላይ መቀመጡ ብቻ ምንም ውጤት የለውም፡፡

እንደ እግዚአብሔር ልጆች እኛ ከክርስቶስ ጋር አብሮ ወራሾች ሆነናል፡፡ ሮሜ መልእክት ላይ፣ «ልጆች ከሆን ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣ የእግዚአብሔር ወራሾች ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን» የሚል እናባለን (ሮሜ 8÷17)፡፡ ይህ ሐሳብ ኤፌሶን 2÷6 ላይም ተነሥቷል፤ «እግዚአብሔርም ከክርስቶስ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስ፤ በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፡፡» በክርስቶስ ውስጥና በክርስቶስ በኩል አዲስ ቦታ ላይ ተደርገናል፡፡ ከእንግዲህ በሰማያዊው መንግሥት ንጉሣውያን ቤተ ሰብ (ወራሾች) እንጂ፣ የዚህ ዓለም ልጆች አይደለንም፡፡ የዚህ መንግሥት ወራሾች እንደ መሆናችን መጠን፣ የጌታችንን ተልዕኮ የማስፋፋት ኃላፊነት ተሰጥቶናል፡፡ የእርሱ እንድንሆን ተቀባይነት ያገኘን በመሆናችን፣ የእርሱ ድል እና መንግሥት የእኛም ሆኖአል፡፡ እንዴት የሚገርም እውነት ነው! ይሁን እንጂ፣ ከምሳሌው እንዳየነው ንጉሥ በክርስቶስ ባለን ቦታ ውጤታማ እንድንሆን ከተፈለገ፣ ከእርሱ ጋር ተያይዞ የመጣውን ሥልጣን መረዳትና በዚያም መጠቀም ይኖርብናል፡፡ በዚህ ምዕራፍ መንግሥቱን የማስፋፋት ድርሻችንን መወጣት የምንችልበት ኃይል የተሰጠን መሆኑን በጥልቀት እናጠናለን፡፡ ጴጥሮስ እንዲህ ይላል፣

> እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝብ ናችሁ፡፡ (1 ጴጥሮስ 2÷9)

ወደ ፊት ከመግፋታችን በፊት፣ ምንጊዜም ቢሆን ከሥልጣን የሚቀድመው ቦታው መሆኑን መገንዘብ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ የእርሱ መንግሥት ውስጥ ምንም ነገር ከማድረጋችን በፊት በክርስቶስ ውስጥ ቦታ መያዝ አለብን፡፡

## የሚያስፈልገን ኃይል

ከእነርሱም ጋር በማእድ ተቀምጦ ሳለ እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ ከኢየሩሳሌም አትውጡ፤ ነገር ግን እኔ ስናገር የሰማችሁትን አብ የሰጠውን ተስፋ ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ (ሐዋርያት ሥራ 1÷4-5)፡፡

ኢየሱስ ለሐዋርያት ተስፋውን እንዲጠብቁ ሐሳብ አላቀረበም፤ ወይም ትንሣኤውን እንዲያወጁ አስተያየት አልሰጠም፡፡ ይልቁንም የተሰጠው ተስፋ እውን እስኪሆን ድረስ፣ «ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ ነበር ያዘዛቸው»፡፡ ከመንፈስ ኃይል መቀበላቸው ለመንግሥቱ ሥራ ሁሉ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ፣ ኢየሱስ ለዚህ መመሪያ አጽንዖት መስጠት ነበረበት፡፡ ደቀ መዛሙርቱ የትንሣኤውን ዜና ለማወጅ በጣም መጓጓታቸውንና የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ እስኪቀበሉ ድረስ መጠበቅ እንደማይፈልጉ አውቆአል፡፡ ሐዋርያት ሥራ 1÷3 ላይ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ሲያስተምር በመስማት፣ ከኢየሱስ ጋር የተወሰኑ ቀኖች አሳልፈው እንደ ነበር ተመልክተናል፡፡ ትንሣኤውን በተመለከተ ሐዋርያቱ፣ «የማያጠራጥር ማስረጃ» ማግኘታቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ ክርስቶስ ሞትን ድል እንዳደረገ የተጨበጠ ማስረጃ ስለ ነበራቸው፣ ዓላማቸው ትክክልና እውነት መሆኑን የማንም ድጋፍ አላስፈልጋቸውም፡፡ በሌላ አነጋገር ለወንጌል ሥራ እንቅስቃሴ ለመጀመር ዝግጁ ነበሩ!

ኢየሱስ ግን እነርሱን እየተመለከተ፣ «አገልግሎት አትጀምሩ፡፡ ወንጌልን ለዓለም መስበክ አትጀምሩ፤ የመንፈስን ኃይል እስክትለብሱ ድረስ ቤተ ክርስቲያን አትመሥርቱ» አላቸው (ሉቃስ 24÷49፤ ደራሲው እንዳብራራው)፡ ፡ ኢየሱስ ይህን መመሪያ የሰጠው በግምት 500 ለሚሆኑ ሰዎች ሊሆን

እንደሚችል አስባለሁ (1 ቆሮንቶስ 15፥6 ይመ.)። ሆኖም፣ ሐዋርያት ሥራ 1፥15 ላይ በሰገነቱ የነበሩ ሰዎች ቁጥር ወደ 120 ዝቅ ብሎ እንደ ነበር እንመለከታለን። የተቀሩት 380 ሰዎች የት ሄዱ? እኔ በግሌ እንደማምነው ቀኖች እያለፉ ሲሄዱ፣ በፊት ከነበሩት 500 ሰዎች ብዙዎቹ እየተዉ ሄደው 120 ብቻ ቀርተዋል። ምናልባትም፣ ትተው የሄዱት 380 ሰዎች፣ ወደ ምኩራብ ሄደን የኢየሱስን ከሞት መነሣት አስደናቂ ዜና እንናገር፣ ከዚያም ቤተ ክርስቲያን እንመሥርት። ይህን መልካም ዜና ለሌሎች ሳንናገር አንድ ቀን እንኳ ማለፍ የለበትም በማለት አስበው ይሆናል። ጌታ ባዘዘው መሠረት ለመቆየት ፈቃደኛ የሆኑት 120ዎቹ ብቻ ነበሩ።

ምናልባትም አንዳንዶቻችሁ፣ እውነት ነው፤ ደቀ መዛሙርቱ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት መጠበቅ ነበረባቸው። ምክንያቱም ገና መንፈስ ቅዱስን አልተቀበሉም ነበር። አሁን ግን እኛ ድነት ባገኘን ጊዜ መንፈስ ቅዱስንም ስለ ተቀበልን መንፈስ ቅዱስን እስክንቀበል መጠበቅ የለብንም ትሉኝ ይሆናል።

እንዲህ ከሆነ፣ ዮሐንስ 20፥21-22 የሚለውን ተመልከቱ፣

> ኢየሱስም እንደ ገና፣ «ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እኔን እንደ ላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ አላቸው። ይህን ካለ በኋላም፣ እፍ አለባቸውና እንዲህ አላቸው፣ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ።»

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ላይ እፍ አለባቸውና፣ «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» አላቸው። መቀበል ለሚለው ግሪኩ ቃል፣ «ወዲውኑ ወይም አሁኑኑ»[1] ማለት ነው። ይህ ወደ ፊት የሚሆነውን የሚያመለክት አይደለም። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ነበር። ይሁን እንጂ፣ በበዓለ ሃምሳ ቀን በመንፈስ እስከ ተሞሉ ጊዜ ድረስ ኃይል አልለበሱም ነበር።

## በዓለ ሃምሳ (ጴንጤቆስጤ)

የበዓለ ሃምሳ ቀን በደረሰ ጊዜ፣ ሁሉም በአንድነት በአንድ ስፍራ

ተሰብስበው ነበር፤ ድንገትም እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስ ያለ ድምፅ ከሰማይ መጥቶ ተቀምጠው የነበሩበትን ቤት እንዳለ ሞላው፡፡ የእሳት ምላሶች የሚመስሉም ታዩአቸው፤ ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉ፡፡ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስም እንዲናገሩ በሰጣቸው መጠን በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር፡፡ (ሐዋርያት ሥራ 2፥1-4)

ብዙዎቻችን እሑድ ትምህርት ቤት ውስጥ ስለዚህ ሁኔታ በስዕል እንደ ተመለከትን አውቃለሁ፡፡ የተሰበሰቡት አማኞች ራስ ላይ ትንንሽ ምላስ የሚመስሉ ነገሮች ተቀምጠው አይተናል፡፡ ምናልባትም፣ ይህ በትክክል የተፈጸመውን ነገር ለማመልከት ነገር ጥሩ ማሳያ ሊሆን አይችልም ይሆናል፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን ብዙ ጊዜ እሳት የእግዚአሔርን መገኘት ወይም ሓልዎት ምሳሌ ነበር፡፡ የሐዋርያት ሥራ ጸሐፊ፣ ‹‹የእሳት ምላሶች››ን የእግዚአብሔር መገኘት ለመግለጥ ነበር የተጠቀመበት፡፡ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እዚያ የነበሩ የኢየሱስ ተከታዮች ሁሉ በእግዚአብሔር መገኘት ተከበቡ ወይም ተጠመቁ፡ ፡ ይህ የእግዚአብሔር መገኘት መገለጫ፣ ‹‹እንደ ብርቱ ዐውሎ ነፋስም›› ተብሏል፡፡ ቀደም ሲል ምዕራፍ አንድ ላይ እንደ ተመለከትነው መንፈስ ቅዱስ አካል እንጂ፣ ‹‹ብርቱ ዐውሎ ነፋስ›› አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ፣ የእርሱ ወደዚያ መምጣት ብርቱ በሆነ ዐውሎ ነፋስ አምሳል ተገልጦ ነበር፡፡

ሐዋርያት ሥራ 2፥4 ላይ፣ ‹‹መሞላት›› የሚለው ግሪክ ቃል፣ ቃል በቃል ሲወሰድ፣ መጥገብ[2] ማለት ነው፡፡ መዝገበ ቃላቱ እንደሚለው መጥገብ፣ ‹‹እስኪበቃ ድረስ መውሰድ›› ማለት ነው፡፡ እዚያ ሰገነት ላይ የነበሩ ሰዎች እስኪበቃቸው ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር፡፡ ሁሉም በተገለጠው የእግዚአብሔር መገኘት እስኪጠግቡ ሕይወታቸው ተሞልቶአል፡፡ ከእሳትና ከዐውሎ ነፋስ በተጨማሪ፣ በመንፈስ የመሞላታቸው ሌላው ምልክት አማኞቹ ሁሉ በሌሎች ልሳኖች መናገራቸው ነበር፡፡

ቀን 2

## ልሳን ለምን?

በቀላል አነጋገር ልሳን፣ ቋንቋ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ስፔን በሚባል አገር ብሆንና ስፓኒሽ ቋንቋ አጥርቶ መናገር የማይችል ሰው ቢገጥመኝ፣ ‹‹የመጀመሪያ ቋንቋህ ምንድነው?›› ወይም፣ ‹‹የትውልድ አገርህ ቋንቋ ምንድነው?›› በማለት እጠይቀዋለሁ፡፡ በመሠረቱ የሁለቱም ትርጉም አንድና ተመሳሳይ ነው፡፡ በአንጻሩ አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋ የሚናገርን ሰው የትውልድ አገርህ ቋንቋ ምንድነው በማለት አልጠይቀውም፣ ምክንያቱም የትውልድ አገሬ ቋንቋ በመሆኑ ቋንቋውን አውቀዋለሁ፡፡ ስለሆነም ለእኔ እንግሊዝኛ፣ ‹‹የሚታወቅ ቋንቋ›› ሲሆን፣ ሌላውን ግን፣ ‹‹የማይታወቅ ቋንቋ›› እለዋለሁ፡፡ ይህን በተመለከተ በኋላ በስፋት እነሣለሁ፡፡

በበዓለ ሃምሳ ወይም ጴንጤቆስጤ ቀን ከተለያዩ አገሮች የመጡ አይሁድ ለሃይማኖታዊ በዓል በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ነበር፡፡ ስለሆነም፣ በተለያዩ አገሮች ኗሪ ስለ ነበሩ እነዚያ አይሁዳውያን ብዙ፣ ‹‹የትውልድ አገር ቋንቋ›› ይናገሩ ነበር፡፡

> በዚህ ጊዜ ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ ሁሉ የመጡና እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይሁድ በኢየሩሳሌም ነበሩ፡፡ ይህን ድምፅ ሲሰሙ ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰበሰቡ፤ እያንዳንዱም ሰው – ሰዎቹ በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ በመስማቱ ግራ ተጋባ፣ በመገረምና በመደነቅም እንዲህ አሉ፤ እነዚህ የሚነጋገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደለምን? ታዲያ እያንዳንዳችን በተወለድንበት በራሳችን ቋንቋ ሲናገሩ የምንሰማቸው እንዴት ቢሆን ነው?›› (ሐዋርያት ሥራ 2፥5-8)

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹ይህን ድምፅ ሲሰሙ ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰበሰቡ›› ማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ ይህ ንግግር ብዙዎች በቋንቋዎች ይናገሩ ወደ ነበሩት ሰዎች እንዲሰበሰቡ አደረገ፡፡ እነዚያ የገሊላ ሰዎች፣ (ብዙዎቹ ያልሠለጠኑ ወይም ያልተማሩ እንደ ነበሩ ይታሰብ ነበር) በብዙ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች በመናገራቸው በጣም ተገረሙ፡፡ ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ መገለጥ፣ ገና

የኢየሱስ ተከታዮች ላልሆኑት ሰዎች ምልክት ነበር፡፡

> እኛ አይሁድና ወደ ይሁዲነት የገባን የቀርጤስና የዐረብ ሰዎች ስንሆን፣ ሰዎቹ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በየቋንቋችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን፡፡ ሁሉም በአድናቆትና ግራ በመጋባት፣ «ይህ ነገር ምን ይሆን?» ተባባሉ (ሐዋርያት ሥራ 2፥11-12)፡፡

ይህ የመንፈስ መፍሰስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም ታዋቂ የሆነውን ስብከት እንዲያቀርብ ለጴጥሮስ ምቹ ሁኔታ ፈጠረለት፡፡ በስብከቱ መሐል፣ «ይህን ኢየሱስን፣ እግዚአብሔር ከሞት አስነሣው፤ እኛም ሁላችን ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ካለ በኃላ የመንፈስ ቅዱስን ተስፋ ከአብ ተቀብሎ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው» የሚል ነበረበት (ሐዋርያት ሥራ 2፥32-33)፡፡ ሁሉም የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ማስረጃ እንዳዩና እንደ ሰሙ ልብ አድርጉ፡፡

ከጥቂት ቁጥሮች በኃላ እንደምንመለከተው ሕዝቡ፣ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጡ፡፡

> ሕዝቡም ይህን በሰሙ ጊዜ ልባቸው እጅግ ተነካ፣ ጴጥሮስንና ሌሎቹንም ሐዋርያት፣ «ወንድሞች ሆይ፣ ታዲያ ምን እናድርግ? አሏቸው፡፡ (ሐዋርያት ሥራ 2፥37)

ጴጥሮስ እንዲህ አላቸው፤

> «ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም እንዲሰረይላችሁ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፡፡ የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ፣ እንዲሁም ጌታ አምላካችን ወደ ራሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና (ሐዋርያት ሥራ 2፥38-39)፡፡

የጌታን ስም የሚጠሩ ሁሉ ስለሚቀበሉት ድነት የምሥራች ጴጥሮስ

ሲናገር፣ (ሮሜ 10፥13 ይመ.) የሚያምኑ ሁሉ መንፈስ ቅዱስን መቀበል እንደሚችሉ በጣም ግልጽ አድርጓል፡፡ እንዴት ይገርማል! ይህ ተስፋ ባለፈው ጊዜ ለነበሩ፣ አሁን ላሉትና ወደ ፊት ለሚመጡ አማኞች ሁሉ ነው፡፡

## አራት ታሪኮች (ማስረጃዎች)

የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ከበዓለ ሃምሳ ቀን በኃላ፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ የአራት ሌሎች ተጨማሪ ሰዎች ታሪክ ያቀርባል፡፡ እነዚህን አራት ታሪኮች አንድ በአንድ እያየን ስንሄድ፣ ለሁለት ነገሮች ልዩ ትኩረት እንድትሰጡ እፈልጋለሁ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ከሚያመለክቱ ታሪኮች ከአንዱ በቀር ሁሉም ከድነት ልምምድ የተለዩ ነበሩ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን የተመለከቱ ሰዎች በአዳዲስ አማኞች ሕይወት መንፈስ ቅዱስ የመገለጡን ማስረጃ አይተዋል፤ ደግሞም ሰምተዋል፡ ፡

### <u>ፊልጶስና የሰማርያ ሰዎች</u>

ከእነዚህ አራት ታሪኮች የመጀመሪያውን የምናገኘው፣ ሐዋርያት ሥራ 8 ላይ ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለማካፈል ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ከተማ ተልኮ ነበር፡፡ ወንጌልን በሰበከ ጊዜ በከተማው በሙሉ መንፈሳዊ መነቃቃት ሆነ፡፡ ሽባ ተፈወሰ፤ ርኩሳን መናፍስት ከሰዎች ወጡ፤ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ማዳን ምሥራች ተቀበሉ፡፡

> ነገር ግን ፊልጶስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሰበከላቸውን አምነው በመቀበላቸው ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ፤ ራሱ ሲሞን እንኳ ሳይቀር ተጠመቀ፤ ፊልጶስንም ተከትሎ ሄደ፤ የሚደረገውን ምልክትና ታላቅ ታምራት አይቶም ተገረመ (ሐዋርያት ሥራ 8፥12-13)፡፡

የሰማርያ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን ምሥራች በሰሙ ጊዜ ዳግም ተወልደው ነበርን? አዎን፡፡ አንድ ሰው ወንጌልን ሲያምን ኢየሱስ ክርስቶስን

ይቀበልና የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል፡፡ እነዚህ አዲስ አማኞች በክርስቶስ የማመናቸው ማስረጃ እንዲሆን በውሃ ይጠመቁ ነበር፡፡ ሆኖም፣ ቀጥሎ ካሉት ቁጥሮች እንደምናየው እነዚያ የጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከማመንና ከመጠመቅ በተጨማሪ እነዚያ አዲስ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅም እንደ ነበረባቸው አውቀው ነበር፡፡

> በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል መቀባለቸውን በሰሙ ጊዜ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወደ እነርሱ ላኳቸው፡፡ እነርሱም ሰማርያ በደረሱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ ለሰማርያ ሰዎች ጸለዩላቸው፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቀው ነበር እንጂ፣ ገና መንፈስ ቅዱስ በአንዳቸውም ላይ አልወረደም ነበር፡፡ (ሐዋርያት ሥራ 8፥14-16)

የሰማርያ ሰዎች ወንጌልን እንደ ተቀበሉ ሲሰሙ፣ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ወደ አዲሶቹ አማኞች ለመላክ ሐዋርያት ወሰኑ፡፡ ለሰማርያ ሰዎች እንዲጸልዩላቸው ሐዋርያት ሁለት በጣም የተከበሩ አባሎቻቸውን የላኩት ለምንድነው? የሰማርያ ሰዎች ድነትን ተቀብለው ነበር፤ በውሃ ተጠምቀውም ነበር፡፡ ጴጥሮስና ዮሐንስ የተላኩት፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ እንዲጸልዩላቸው›› ነበር (ቁጥር 15)፡ ፡ ኢየሩሳሌም ከሰማርያ ከሰላሣ አምስት ማይል የበለጠ ርቀት ላይ እንደ ነበረች አስታውሱ፡፡[3] ይህ ርቀት በዚህ ዘመን ብዙ ላይመስል ይችላል፤ ሐዋርያቱ ግን የግል መኪና ወይም ወደዚያ የሚሄዱበት የሕዝብ መመላለሻ አልነበራቸውም፡፡ በእግር ወይም በእንስሳ ጀርባ መጓዝ ነበረባቸው፤ ጉዞው አንድ ወይም ሁለት ቀን ሊወስድ ይችላል፡፡ ቀላል ጉዞ አልነበረም፡፡

አዲሶቹ አማኞች በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቀው እንደ ነበር ልብ ማድረግም ጠቃሚ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ድነት የሚያስገኘው ገና ያልተለማመዱት አንድ ስጦታ ነበር፡፡ ምናልባትም፣ *የድነትን ስጦታ ስንቀበል፣ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ልባችን ወዲያውኑ የእርሱ መኖሪያ ያደርገዋል* በማለት ታስቡ ይሆናል፡፡ በትክክል እውነት ነው፡ ፡ 1 ቆሮንቶስ 12፥3፣ ‹‹በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር፣ ማንም ኢየሱስ ጌታ ነው የሚል የለም›› በማለት በግልጽ ይናገራል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ

በቀር፣ የኢየሱስን ጌትነት መመስከር አንችልም፤ ሆኖም፣ ይህ በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላት የተለየ ነው።

በክርስቶስ የሆኑት ሁሉ መቀደሳቸውንና በመንፈስ ቅዱስ መታተማቸውን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል (1 ጴጥሮስ 1፥2፤ ኤፌሶን 1፥13 ይመ)። ስለሆነም የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን መኖር የድነት ልምምድ አንድ አካል መሆኑ የሚጠረጠር አይደለም። እግዚአብሔር እናንተን ሲያይ፣ የልጁን መንፈስ ያያል። ድነትን ስትቀበሉ፣ ክርስቶስ ውስጥ ቦታችሁን እንደምትይዙ፣ የእርሱ ሕዝብና መንግሥት አካል እንደምትሆኑ፣ ማስታወስ አለባችሁ። ይሁን እንጂ፣ አብን እስከምትጠይቁና እስከምትቀበሉ ድረስ የመንፈስን ኃይል አትሞሉም።

ኢየሱስ እንዲህ አለ፤

> እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ ሳላችሁ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠት ካወቃችሁበት የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ! (ሉቃስ 11፥13)

ኢየሱስ እግዚአብሔርን፣ ‹‹የሰማዩ አባታችሁ›› በማለት ጠርቶታል፤ ስለሆነም እየተናገረ ያለው አማኞችን አስመልክቶ ነበር ማለት ነው። ይህን የምናውቀው በዚሁ የዮሐንስ ወንጌል ውስጥ፣ ‹‹እርሱም የእውነት መንፈስ ነው፤ ዓለም ስለማያየውና ስለማያውቀው ሊቀበለው አይችልም። እናንተ ግን አብሮአችሁ ስለሚኖርና በውስጣችሁ ስለሚሆን ታውቁታላችሁ›› በማለት ኢየሱስ በመናገሩ ነው (ዮሐንስ 14፥17)። ‹‹ዓለም›› ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጪ የሚኖሩትን ሰዎች ይወክላል። የኢየሱስን ጌትነት ያልተቀበለ ሰው፣ መንፈስ ቅዱስን መቀበል እንደማይችል ግልጽ ነው። ስለሆነም መንፈስ ቅዱስን፣ ‹‹ከሰማዩ አባታችሁ›› ለምኑ የሚለው መመሪያ ድነትን የሚመለከት አይደለም ማለት ነው። ይልቁንም ድነትን ያገኙ ወገኖች፣ በኋላ የሚለማመዱትን የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ነው የሚያመለክተው።

አሁን ወደ ሐዋርያት ሥራ 8 እንመለስ።

> ስለዚህ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጃቸውን ጫኑባቸው፤ እነርሱም መንፈስ

ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ ሲሞንም ሐዋርያት እጃቸውን በሚጭኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ አይቶ፣ ገንዘብ አመጣላቸውና እንዲህ አላቸው፤ «እጄን የምጭንበት ሰው ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበል ይህን ሥልጣን ለእኔም ስጡኝ!» (ሐዋርያት ሥራ 8፥17-19)፡፡

ጴጥሮስና ዮሐንስ እጆቻቸውን አማኞች ላይ ጫኑ፤ እነርሱም መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸው በዐይን የሚታይ ነገር እንደ ነበረው ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ሲሞንም ሐዋርያት እጃቸውን በሚጭኑበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ አይቶ» ይላል፡፡ እርሱ ራሱ አማኝ የነበረው ሲሞን በአማኞች ሕይወት በሆነው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል መገለጥ በጣም ተገርሞ ስለ ነበር ይህን ኃይል እንዴት ለሌሎች እንደሚያካፍል እንዲያስተምሩት ገንዘብ ይዞ ወደ ሐዋርያት መጣ፡፡ (ነገሩ ተገቢ አልነበረም፤ ስለሆነም ጴጥሮስ ወዲያውኑ ሲሞንን ገሠጸው)፡፡

ከሐዋርያት ሥራ እንደምንመለከተው በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ተከትሎ የሚታይና የሚሰማ አንድ ውጫዊ መገለጫ ይኖር ነበር - በጣም የተለመደው በልሳን መናገርና ትንቢት መናገር ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስ አማኞች ላይ መውረዱን ሐዋርያቱ ይናገሩ የነበረው፣ ብዙ ጊዜ ይህን በማየት ነበር፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ተከትሎ በልሳን መናገርና ትንቢት መናገር እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ከማይናገርላቸው ጥቂት ክፍሎች አንዱ ይህ በሰማርያ የተፈጸመው ታሪክ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከሁኔታው በመነሣት እንዲህ ያሉ ነገሮች ተፈጽመው እንደ ነበር መናገር እንችላለን፤ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ፣ ቀድሞ አስማተኛ የነበረው ሲሞን በአማኞች ላይ መንፈስ ቅዱስ የመውረዱን ማስረጃ አያይም ነበር፡፡

ቀን 3

## የጠርሴሱ ሳውል

የሳውል ወደ ጌታ መመለስ በጣም ታዋቂ ከሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባቦች አንዱ ነው፡፡ አሁን ግን ይህን አስደናቂ ጉዳይ በተመለከተ ይህን ያህል ግምት ያልተሰጠው ገጽታ ላይ ማተኮር እፈልጋለሁ፡፡ ሐዋርያት

ሥራ 9 ላይ አማኞችን ለማሳደድ ሳውል በደማስቆ መንገድ እንደ ነበር እንመለከታለን፡፡

> ደማስቆ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው ብርሃን ከሰማይ ድንገት በዙሪያው አንጸባረቀበት፤ እርሱም በምድር ላይ ወደቀ፤ በዚያ ጊዜም፣ ‹‹ሳውል፤ ሳውል፤ ለምን ታሳድደኛለህ?›› የሚል ድምፅ ሰማ፡፡ ሳውልም፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ አንተ ማን ነህ?›› አለው፡፡
> እርሱም እንዲህ አለው እኔማ አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ፡ ፡ አሁንም ተነሥተህ ወደ ከተማዪቱ ግባ ማድረግ የሚገባህም ይነገርሃል፡፡ (ሐዋርያት ሥራ 9፥3-6)

ጳውሎስ ኢየሱስን፣ ‹‹ጌታ›› ማለቱን ልብ አድርጉ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወታችን ጌታ ሲሆን፣ ወዲያውኑ ዳግም እንወለዳለን፡፡ የኢየሱስን ጌትነት በተቀበለ ጊዜ ሳውል ወዲያውኑ አማኝ ሆኖ እንደ ነበር አምናለሁ፡፡

ከጌታ ጋር ከተገናኘ በኋላ ሳውል ተጨማሪ መመሪያ እየጠበቀ ቀጣዮቹን ሦስት ቀኖች በጾም ቆየ፡፡ ከዚያ በኋላ ወደ ሳውል እንዲሄድ ጌታ ሐናንያ ለሚሉት ደቀመዝሙ ተናገረ፡፡ ሳውል ምን ያህል በጭካኔ አማኞችን ያሳድድ እንደ ነበር ብዙ ታሪኮች ሰምቶ ስለ ነበር፣ ይህ ምሪት ሐናንያን በጣም አሳስቦት ነበር፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር፣ ‹‹ሂድ ይህ ሰው ስሜን እንዲሸከም የተመረጠ ዕቃዬ ነው›› አለው (ሐዋርያት ሥራ 9፥15)፡፡ ሐናንያ ሳውል ወደ ነበረባት ቤት ሲመጣ እጁን ጫነበትና፣ ‹‹ወንድሜ ሳውል ሆይ፣ ወደዚህ ስትመጣ በመንገድ ላይ የተገለጠልህ ጌታ ኢየሱስ ዐይንህ እንዲበራና በመንፈስ ቅዱስም እንድትሞላ እኔን ልኮኛል አለው፡፡(ሐዋርያት ሥራ 9፥17)፡፡ ሳውል ድነትን ተቀብሎ እንደ ነበር ሐናንያ አውቆአል፤ ‹‹ወንድሜ ሳውል›› በማለት የጠራው በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ምንም እንኳ ሳውል አማኝ ቢሆንም፣ ፈውስ እንዲቀበልና በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ እንዲጸልይለት እግዚአብሔር ሐናንያን መላክ ነበረበት፡፡

ከዚህም ታሪክ የምንመለከተው፣ የድነት ስጦታ እውን ከሆነ በኋላ፣ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት መፈጸሙን ነው፡፡ ሐዋርያት ሥራ 9 ላይ ሳውል፣ (በኋላ ጳውሎስ የተባለው) በልሳን እንደ ተናገረ አልተጠቀሰም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጳውሎስ በልሳን ይናገር እንደ ነበር እርግጠኞች ነን፤ ምክንያቱም በኋላ

ላይ፣ «ከሁላችሁ የበለጠ በልሳን ስለምናገር እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ» በማለት ጽፎአል (1 ቆሮንቶስ 14÷18)። ጳውሎስ በልሳን የተናገረው ሐናንያ እጁን የጫነበት ጊዜ ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ። ምንም እንኳ ድነት ያገኘ ሰው ቢሆንም፣ ጳውሎስ ይህን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት መቀበል ነበረበት፤ ምክንያቱም ለአሕዛብ፣ ለነገሥታትና ለእስራኤል፣ ኢየሱስን ለማስተዋወቅ ጳውሎስ ለሚያደርገው ጥረት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መቀበሉ ለእርሱ እጅግ አስፈላጊ ነበር (ሐዋርያት ሥራ 9÷15 ይመ)።

## ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ

ሐዋርያት ሥራ 10 ቆርኔሌዎስ ከሚሉት ሮማዊ ባለ ሥልጣን ጋር ያስተዋውቀናል። ቆርኔሌዎስ የሚጸም፣ የሚጸልይ፣ እግዚአብሔርን የሚፈራና ለድኾች ቸር የሆነ ሰው እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ወንጌል ለአሕዛብ አልተዳረሰም ነበር፤ ስለሆነም እግዚአብሔር አንድ መልአክ ወደ ቆርኔሌዎስ ላከ። ይሁን እንጂ፣ መልአኩ ለቆርኔሌዎስ የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ አልነገረውም፤ ይልቁንም መልእክተኞች ልኮ ጴጥሮስን እንዲያስመጣው ነበር ያመለከተው። በጣም ከመገረሙና ከመደነቁ የተነሣ ጴጥሮስን እንዲያመጡት መልአኩ ወደ ነገረው ቦታ ወዲያውኑ ሰዎች ላከ።

ጴጥሮስ ኢዮጴ በሚባል ቦታ ነበር፤ እዚያ እያለ ከሰማይ ራእይ አየ። እግዚአብሔር የቀደሰውን ርኩስ ብሎ እንዳይጠራ ለጴጥሮስ ለመናገር በራእዩ ውስጥ እግዚአብሔር የተለያዩ ምስሎች ተጠቀመ (ሐዋርያት ሥራ 10÷9-15 ይመ)። ጴጥሮስ የራእዩን ትርጉም መረዳት እንደሚያዳግተው እግዚአብሔር ያውቅ እንደ ነበር ግልጽ ነው፤ ራእዩን ሦስት ጊዜ ያሳየው በዚህ ምክንያት ነበር። ትርጉሙ ምን ሊሆን እንደሚችል ጴጥሮስ እያሰላሰለ እያለ፣ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ወደ ቤቱ ደረሱ። ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ መንፈስ ቅዱስ ለጴጥሮስ ነገረው። ምንም እንኳ፣ በዘመኑ በነበሩ አይሁድ ባሕል ከአሕዛብ ጋር ሊኖራቸው ከሚገባው ግንኙነት የሚቃረን ቢሆንም፣ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት የሚላከው ለምን እንደ ነበር እግዚአብሔር ለጴጥሮስ አልነገረውም። ወደ

ቆርኔሌዎስ ቤት ሲደርስ ጴጥሮስ እንዲህ አለ፤

> አንድ አይሁዳዊ ከሌላ ወገን ጋር እንዲተባበር ወይም እንዲቀራረብ ሕጋችን እንደማይፈቅድ ራሳችሁ ታውቃላችሁ፤ ነገር ግን እኔ ማንንም ርኩስ ወይም ያልተቀደሰ ነው እንዳልል እግዚአብሔር አሳይቶኛል፤ ስለዚህም በተጠራሁ ጊዜ፣ እነሆ ሳላመነታ መጣሁ፤ እንግዲህ ለምን እንደ ጠራችሁኝ ማወቅ እፈልጋለሁ (ሐዋርያት ሥራ 10፥28-29)፡፡

ጴጥሮስ በራእዩና እግዚአብሔርን በሚፈራ ከዚህ የአሕዛብ ወገን ከሆነ ሰው መካከል የነበረውን ተያያዥነት መረዳት ጀመረ፤ ስለዚህም ለቆርኔሌዎስ ወንጌልን ሰበከለት፡፡ ጴጥሮስ መልእክቱን እያቀረበ እያለ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ተገለጠ፤ እነዚያ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ሰዎች በልሳን ይናገሩ ጀመር፡፡ እንዲህ ያለ ነገር ከዚያ በፊት አይቶ ስለማያውቅ ጴጥሮስ በጣም ተገረመ፡፡

የድነት ስጦታ ለአሕዛብ ጭምር የመሆኑን እውነት ጴጥሮስና አብረውት የነበሩ አይሁዳውያን ለመቀበል እንደሚቸገሩ እግዚአብሔር ያውቃል፡፡ ስለዚህም ጴጥሮስ ለእነርሱ የመጸለይ ዕድል ከማግኘቱ ወይም እነርሱን በውሃ ከማጥመቁ በፊት፣ እግዚአብሔር መንፈሱን አሕዛብ ላይ አፈሰሰ፡፡ ከእስራኤል ሕዝብ ውጪ ያሉ ሰዎችም በድነት ዕቅድ ውስጥ እንደሚካተቱ ይህ በቂ ማስረጃ ነበር፡፡

> ከጴጥሮስ ጋር የመጡት ከተገረዙት ወገን የሆኑት አማኞች፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአሕዛብም ላይ ደግሞ መፍሰሱን ሲያዩ ተገረሙ፤ ይኸውም በልሳን ሲናገሩና እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ስለ ሰሟቸው ነው፡፡ በዚያ ጊዜ ጴጥሮስ እንዲህ አለ፤ እነዚህ ሰዎች እንደ እኛ መንፈስ ቅዱስን ስለ ተቀበሉ እንግዲህ በውሃ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ማን ነው? ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲጠመቁ አዘዛቸው (ሐዋርያት ሥራ 10፥45-48)፡፡

የእግዚአብሔር ኃይል ሲገለጥ (በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውን) ስላዩና

ስለ ሰሙ፣ በአሕዛብ መካከል የታየውን የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ አይሁዳውያኑ መካድ አልቻሉም፡፡ አይሁዳውያኑ አማኞች እጅግ ተገረሙ፡ ፡ እግዚአብሔር ድነትን ለአሕዛብ መስጠት ብቻ ሳይሆን፣ የተለመደውን ቅደም ተከተል ሳይጠብቅ፣ ማለትም መጀመሪያ በሕዝብ ፊት መመስከርንና የውሃ ጥምቀት ሥርዐትን ከመፈጸማቸው በፊት የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ሳከላቸው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እግዚአብሔር በዚህ መልኩ ሲሠራ የምንመለከተው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው፤ ከሌሎች ሁኔታዎች የምንመለከተው የእግዚአብሔር መንፈስ ይፈስ የነበረው ሰዎች ወደ ጌታ ከመጡ በኋላ እንደ ነበር ነው፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ያደረገው፣ የእርሱ ድነት ስጦታ ለአሕዛብም ጭምር መሆኑን ለመቀበል አይሁድ የተለየ ምልክት ይጠይቁ ስለ ነበር መሆኑን አምናለሁ፡፡

## የኤፌሶን ሰዎች

አብረን እንድንመለከት የምፈልገው አራተኛው ታሪክ የሚገኘው ሐዋርያት ሥራ 19 ላይ ነው፡፡ ካደረጋቸው አያሌ ጉዞዎች በአንዱ ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን መጥቶ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እዚያ ሲደርስ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የነበሩ ጥቂት ሰዎች አገኘ፡፡ ከሁሉም በፊት መጀመሪያ ያቀረበላቸው ጥያቄ፣ ‹‹ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?›› የሚል ነበር (ሐዋርያት ሥራ 19፥2)፡፡ በጣም ይገርማል! ለእነዚያ የኤፌሶን ሰዎች ጳውሎስ በመጀመሪያ ያቀረበው ጥያቄ ይህ ከሆነ፣ እኛም ለማንኛውም አዲስ አማኝ ከምናቀርባቸው ጥያቄዎች አንዱ መሆን አለበት፡፡

እንደ ገና ለመጠየቅ ያህል፣ ይህ ጉዳይ ለጥንት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህን ያህል አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? ምክንያቱም፣ የክርስቶስን ተልዕኮ ለመፈጸም፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በጣም አስፈላጊ ስለ ነበር ነው፡፡ ያንን ተልዕኮ የሚያቀጣጥለውን ኃይል ሳንቀበል፣ እኔና እናንተ አንድ ሰዓት እንኳ የምናሳልፈው ለምንድነው (ሐዋርያት ሥራ 1፥8)? በእግዚአብሔር መንግሥት ውጤታማ ለመሆን በክርስቶስ ያለንን ቦታ መያዝና (ድነት) የመንፈስ ቅዱስን ኃይል (በመንፈስ መሞላት) መቀበል ይኖርብናል፡፡

ምንም እንኳ፣ እነዚህ የኤፌሶን ሰዎች የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ቢሆኑም፣ በኢየሱስ በኩል ስላለው ድነት የምሥራች አለመስማታቸውን ጳውሎስ አወቀ፤ ስለዚህም ስለ ወንጌል ነገራቸው፡፡
ቀደም ሲል እንዳልኩት፣ የመንፈስን ኃይል ከመቀበላችን በፊት ክርስቶስ ውስጥ ያለንን ቦታ መያዝ አለብን፡፡ ምናልባት እንኳ ከቆርኔዎስ እንደ ተመለከትነው ውጫዊው የኃይል መገለጥ (በመንፈስ ቅዱስ መሞላት)፣ ከውጫዊው የድነት ምስክርነት (በውሃ መጠመቅ) ሊቀድም ሊሆን ቢችልም፣ ምንጊዜም ቢሆን፣ ድነት ኃይልን ከመቀበል መቅደም አለበት፡፡

ስለሆነም፣ የጳውሎስን ቃል ከሰሙ በኃላ የኤፌሶን ሰዎች መጀመሪያ ‹‹በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠመቁ›› (ሐዋርያት ሥራ 19÷5)፡፡ በሌላ አነጋገር፣ በኢየሱስ ክርስቶስና በእርሱ በኩል ብቻ የሆነውን ድነት ተቀበሉ፡፡ ሆኖም፣ ጉዳዩ እዚያም ላይ አላበቃም፤ ‹‹ጳውሎም እጁን በላያቸው በጫነ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፤ በሌሎች ቋንቋዎች ተናገሩ፤ ትንቢትም ተናገሩ›› (ሐዋርያት ሥራ 19÷6)፡፡

አዲሶቹ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉት በጌታችን በኢየሱስ ስም ከተጠመቁ በኃላ ነበር፡፡ ከጳውሎስ ጋር ከመገናኘታቸው በፊት፣ እነዚህ ሰዎች ስለ ኢየሱስ የሚያወቁት በጣም ጥቂት ነበር፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በኃላ ግን ትንቢት ተናገሩ ማለትም የኢየሱስ ክርስቶስን መልእክት ተናገሩ፡ ፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የማያውቁት ይህ ትንቢት የመናገር ችሎታ እውን የሆነው በመንፈስ ኃይል ነበር፡፡ አንድ አማኝ መጀመሪያ መንፈስ ቅዱስን ሳያውቅ፣ በሥልጣን የእግዚአብሔርን ምስጢር መናገር አይችልም (1 ቆሮንቶስ 2 ይመ)፡፡

ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል መስበክ ስለሌለብኝ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ በራሴ ዐቅም ሰዎች ፊት ቆሞ የመናገር ችሎታ የለኝም፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ በራሴ ዐቅም ጥሩ ጸሐፊም አይደለሁም፡፡ የእንግሊዝኛ ችሎታዬ በጣም መጥፎ ስለ ነበር ወደ ኮሌጅ መግቢያ ፈተና አላለፍኩም ነበር፡፡ ያገኘሁት ውጤት ከ800-370 ነበር፡፡ አሁን የሆንኩትን የሆንኩት በእግዚአብሔር ጸጋና በመንፈስም ኃይል መሆኑን ከእኔ የተሻለ የሚያውቅ የለም፡፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ባይረዳኝ ኖሮ፣ ይህን መጽሐፍ ማዘጋጀት አልችልም ነበር፡፡ የችሎታዬም ሆነ፣ የብርታቴ ምንጭ እርሱ ነው፡፡ ያለ

እርሱ የእኔ የመንግሥቱ ተልዕኮ ሥራ እውን አይሆንም ነበር፡፡ ለእኔ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ ‹‹ገላጭ›› ነው፡፡

ቀን 4

## በልሳን መናገር ተቋርጦአልን?

ፍቅር ከቶ አይወድቅም፤ ነገር ግን ትንቢት ቢሆን ይሻራል፤ ልሳንም ቢሆን ይቀራል፤ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል፣ ምክንያቱም የምናውቀው በከፊል ነው፤ ትንቢት የምንናገረው በከፊል ነው፡፡ ነገር ግን ፍጹም የሆነው ሲመጣ በከፊል የነበረው ይሻራል (1 ቆሮንቶስ 13፥8-10)፡፡

እስከ አሁን ድረስ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን በተመለከተ ከሐዋርያት ሥራ አንዳንድ ታሪኮች ተመልክተናል፤ አሁን ደግሞ ምናልባት በብዙዎቻችሁ አእምሮ ውስጥ ያለ አንድ ጥያቄ ማንሣት እፈልጋለሁ፡፡ አንዳንድ ሰዎች በልሳን መናገር ቀርቷል ወይም ተቋርጦአል ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ እነዚህ ሰዎች እንደ ማስረጃ የሚያቀርቡት 1 ቆሮንቶስ 13 ላይ ያለውን ይህን ምንባብ ነው፡፡ ይህን አስተሳሰብ የሚያምኑ ሰዎች ጳውሎስ፣ ‹‹ፍጹም የሆነው ሲመጣ በከፊል የነበረው ይሻራል›› ሲል ‹‹ፍጹም›› ያለው መጽሐፍ ቅዱስን ነው ይላሉ፡፡ እንግዲህ፣ እንደ እነርሱ ከሆነ ያ ክፍል፣ ‹‹ፍጹም የሆነው መጥቷል፤ ስለዚህ ልሳን ቀርቷል›› ተብሎ ሊነበብ ይችላል ማለት ነው፡፡

ጳውሎስ ምን ማለቱ እንደ ነበር በሚገባ ለመረዳት፣ ይህን ምንባብ በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ጥቅስ ዐውድ መሠረት ሰዎቹ ያቀረቡት አስተሳሰብ በፍጹም የሚያስኬድ አይደለም፡፡ ልሳን ተሽራል ወይም ቀርቷል ከተባለ፤ ዕውቀትና ትንቢትም ተሽረዋል ወይም ቀርተዋል ማለት ነው፡፡ ታዲያ፣ ዕውቀትና ትንቢት ተሽረዋል ወይስ ቀርተዋል? በፍጹም አልተሻሩም፡፡ ታዲያ፣ ጳውሎስ፣ ‹‹ፍጹም›› ሲል ምንን ለማመልከት ነው፡፡ መልሱ ቁጥር 12 ላይ ይገኛል፡፡

አሁን የምናየው በመስተዋት ውስጥ እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፡፡ አሁን የማውቀው በከፊል

ነው፤ በዚያን ጊዜ እኔ ራሴ ሙሉ በሙሉ የታወቅሁትን ያህል አውቃለሁ (1 ቆሮንቶስ 13÷12)፡፡

ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ከኢየሱስ ጋር ፊት ለፊት መገናኘትን በተመለከተ ነው፡፡ «ፍጹም» - ሲል በክብሩ ሙላት ኢየሱስን ማወቅ ማለቱ ነው፡፡ ታዲያ፣ አሁን በዚህ መልኩ ኢየሱስን አውቀነዋል ወይም ተለማምደነዋል? በክብሩ ሙላት እያየነው ነው? በዚህ ምድር ባለው ሕይወታችን ስለ ኢየሱስ ያለን ዕውቀት ወይም ልምምድ በመስተዋት እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በሚመጣው ዘመን እርሱ እኛን እንደሚያውቀን እኛም ኢየሱስን እናውቀዋለን፡፡ ይህ ከኢየሱስ ጋር የመቀራረብ ጥልቅ ልምምድ «ፍጹም» የሆነው የመምጣቱ ምልክት ነው፡፡ ምንም እንኳ፣ ይህ ጉዞ የተጀመረው በዚህ ምድር ቢሆንም፣ በዘላለም ውስጥ እርሱን ፊት ለፊት እስክናይ ድረስ ጉዞው አይጠናቀቅም፡፡

## አራት ዐይነት ልሳኖች

ተደጋግሞ የሚቀርብልኝ ሌላው ጥያቄ፣ «1 ቆሮንቶስ 12÷30 ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን የሚለው ለምንድነው? እንዲህ ማለት፣ ሁሉም በልሳኖች አይናገሩም ማለት አይደለም እንዴ?» የሚል ነው፡፡ አዎን፣ እንደዚያ ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ክፍል ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ለየት ስላለ ዐይነት ልሳን ነው፤ አማኞች ሁሉ በዚህ ዐይነቱ ልሳን አይናገሩም፡፡ ይህን ለመረዳት አዲስ ኪዳን ስለሚያነሣቸው አራት ዐይነት ልሳኖች መመልከት ይኖርብናል፡፡

ለውይይታችን እንዲረዳን፣ እነዚህን ልሳኖች ለግል ጥቅም የሚውሉና ለማኅበሩ ጥቅም የሚውሉ በማለት እከፍላቸዋለሁ፡፡ ሁለቱ ዐይነቶች ለማኅበሩ ጥቅም የሚውሉ ናቸው፡፡ «ማኅበሩ» ስል አንድ ሰው ለሌላ ግለ ሰብ ወይም ሰዎች የሚሰጠው ከመንፈስ የሆነ አገልግሎት ማለቴ ነው፡፡ በአንጻሩ፣ «ለግል ጥቅም» የሚውሉት ሁለቱ ዐይነቶች ከእርሱ ጋር ያለንን መቀራረብ መጠን በመጨመር ወይም ፍጹም በሆነው የእርሱ መረዳት አኳያ ለመማለድ እንደ ግለ ሰብ እኛን በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኙ ናቸው፡፡ እስቲ እያንዳንዱን ተራ በተራ እንመልከት፡፡

አንድ - ለማያምኑ እንደ ምልክት የሆኑ ልሳኖች

የመጀመሪያዎቹ የልሳኖች ዐይነት ለማኅበሩ ጥቅም የሚውሉ ናቸው፡፡

> ስለዚህ በልሳን መናገር ለማያምኑ የሚሆን ምልክት እንጂ፣ ለሚያምኑ አይደለም (1 ቆሮንቶስ 14፥22)፡፡

እነዚህ ልሳኖች ጥቅም ላይ የሚውሉት፣ ከእኛ አእምሮ በላይ በሆነ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ በልምድ ወይም በትምህርት ባላገኘነው፣ በዚህ ምድር ባለ ሌላ ቋንቋ የመናገር ችሎታ ሲሰጠን ነው፡፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን ደቀ መዛሙርት የተናገሩት በዚህ ዐይነት ልሳን ነበር፡፡

> በዚህ ጊዜ ከሰማይ በታች ካለው ሕዝብ ሁሉ የመጡና እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይሁድ በኢየሩሳሌም ነበሩ፡፡ ይህን ድምፅ ሲሰሙ፣ ብዙ ሕዝብ በአንድነት ተሰበሰቡ፤ እያንዳንዱም ሰው ሰዎቹ በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ በመስማቱ ግራ ተጋባ፤ በመገረምና በመደነቅም እንዲህ አሉ፤ እነዚህ የሚነጋገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? ታዲያ፣ እያንዳንዳችን በተወለድንበት በራሳችን ቋንቋ ሲናገሩ የምንሰማቸው እንዴት ቢሆን ነው? እኛ የጳርቴና፣ የሜድ፣ የኢላሜጢም ሰዎች፣ በመስጴጦምያ፣ በይሁዳ፣ በቀጰዶቅያ፣ በጳንጦስ፣ በእስያ፣ በፍርግያ፣ በጵንፍልያ፣ በግብፅ፣ በቀሬና፣ አጠገብ፣ ባሉት በሊቢያ አውራጃዎች የምንኖር ከሮም የመጣን አይሁድና ወደ ይሁዲነት የገባን፣ የቀርጤስና የአረብ ሰዎች ስንሆን፣ ሰዎቹ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በየቋንቋችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን (ሐዋርያት ሥራ 2፥5-11)፡፡

እነዚህ አይሁድ አማኞች በእያንዳንዳቸው የትውልድ (ምድራዊ) ቋንቋ ሲናገሩ ሰሙ፡፡ ይህ ሁኔታ የኢየሱስን ወንጌል በማያምኑ ሰዎች መካከል እግዚአብሔር ሥራ ላይ ለመሆኑ ምልክት ነበር፤ ያ ባይሆንማ ኖሮ፣ እነዚያ ምንም ትምህርት የሌላቸው የገሊላ ሰዎች ጥርት ባሉ ብዙ ቋንቋዎች የእግዚብሔርን ታላቅ ሥራ መናገር የሚችለበት ሌላ መንገድ አይኖርም

ነበር፡፡ በኋላም ከዚህ የመንፈስ ኃይል መገለጥ የተነሣ ብዙዎች ኢየሱስን ወደ ማወቅ መጡ፡፡

ከጥቂት ዓመታት በፊት በኮሎራዶ ሲፕሪንግስ ባለ አንድ ቤተ ክርስቲያን እየሰበክሁ ነበር፡፡ አገልግሎቱ እየተካሄደ በነበረ ጊዜ አብረውኝ ይሠሩ ከነበሩ ሰዎች አንዷ ከቤተ ክርስቲያኑ በስተ ጀርባ ተቀምጣ ነበር፡፡ እኔ እየሰበክሁ በነበረ ጊዜ ሁሉ፣ ቀስ ብላ በልሳን እንድትጸልይ ይሰማት ነበር፡፡ አገልግሎቱ ካበቃ በኋላ ፊት ለፊቷ ተቀምጦ የነበረ አንድ ሰው ወደ እርሷ መጥቶ፣ «የእኔ እናት በጣም ድንቅ ፈረንሳይኛ ነበር የተናገርሽው፡፡ ሌላው ቀርቶ ጥንታዊ በሆነ ፈረንሳይኛ አነጋገር ዘዬ ጥርት ባለ መንገድ ተናግረሻል፡፡ እኔ የፈረንሳይኛ ቋንቋ አስተማሪ ነኝ፤ በሕይወቴ ዘመኔ ሁሉ እንዳንቺ ጥሩ ፈረንሳይኛ የሚናገር ሰው ገጥሞኝ አያውቅም» አለ፡፡

የሥራ ባልደረባዬም፣ «እኔ'ኮ ፈረንሳይኛ መናገር አልችልም» ስትለው፤ ሰውየው እጅግ ነበር የደነገጠው!

«በጣም ጥርት ያለ ፈረንሳይኛ መናገር ብቻ ሳይሆን፣ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ቅዱሳት መጻሕፍትንም ትጠቅሺ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ጆን፣ እነዚያን የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ሕዝቡ አውጥቶ እንዲመለከት ይናገር ነበር፡፡ አንቺ ጥቅሶቹን ትናገሪ የነበረው እርሱ ከመናገሩ በፊት ነበር» አለ፡፡ ይህ ልምምድ፣ በእኔ በኩል እግዚአብሔር ያቀረበውን መልእክት ትክክልነት ለሰውየው የሚያረጋግጥ ነበር፡፡ ልሳን እንደ ምልክት የሚቀርብበት ዋና ምክንያት፣ ገና አማኝ ያልሆነውን ሰው ትኩረት ለመሳብ ነው፡፡

## ሁለት - የሚተረጐሙ ልሳኖች

ሁለተኛውም ዐይነት ልሳን፣ ለማኅበሩ አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ እንደ ምልክት ከሆነው ልሳን በተለየ መልኩ፣ ይህኛው ዐይነት ልሳን በዚህ ምድር የትም ቦታ ያልተነገረ ሰማያዊ ቋንቋ ነው፡፡ «…ለአንዱ በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ ልሳን የተነገረውን የመተርጐም ስጦታ ይሰጠዋል» በማለት ጳውሎስ መንፈሳዊ ስጦታዎች ዝርዝር ውስጥ የጠቀሰው የልሳን ዐይነት የሚተረጐመውን ዐይነት ልሳን ነው (1 ቆሮንቶስ 12÷10)፡፡ እነዚህ ልሳኖች የዚህ ምድር ቋንቋዎች ስላይደሉ መተርጐም

አለባቸው።

ከዓመታት በፊት በሲንጋፖር ባለ አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመስበክ እየተዘጋጀሁ ነበር። በድንገት በዚያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረ አንድ ሰው ተነሥቶ በልሳን መናገር ጀመረ። ይህ ልሳን ምድራዊ ቋንቋ እንዳልሆነ የገባኝ ወዲያውኑ ነበር - ሰማያዊ ቋንቋ ነበር። በዚያ ቦታ የነበረ ሰው ሁሉ በዚህ የመንፈስ መገለጥ በጣም ተገረመ። በዚህ ሰማያዊ ቋንቋ ተናግሮ እንዳበቃ ሰውየው ትርጉሙን መስጠት ጀመረ። ትርጉሙ ለዚያ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ከሰጠኝ መልእክት ጋር በትክክል የሚስማማ ነበር። ጌታ ሆይ፣ ስለዚህ አስደናቂ ማረጋገጫ አመሰግንሃለሁ! አልኩ። በልቤ ውስጥ ያኖረውን ቃል ለማጽናት እግዚአብሔር በዚህ በልዩ ልዩ ልሳኖች የተነገረውን የመተርጐም ስጦታ ተጠቀመ። ያ፣ ለእኔም ሆነ እዚያ ለነበሩ ሰዎች ሁሉ ምልክት ነበር።

እዚህ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ቃል መተርጐም እንጂ፣ ፍቺ መስጠት እንዳልሆነ ልብ አድርጉ። ሰማያዊ ቋንቋዎች (አዲስ ኪዳን ውስጥ ከተጠቀሱት ልሳኖች ከአራቱ ሦስቱ እንዲህ ናቸው) ከሰው አእምሮ በላይ ስለሆኑ ፍቺ ልንሰጣቸው አንችልም፤ ግን ይተረጐማሉ።

በልዩ ልዩ ልሳኖች የተነገረውን መተርጐም ምድብ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም ልሳን ሁሌም መተርጐም ይኖርበታል። ይህ ስጦታ የሚሰጠው በተለይ ቤተ ክርስቲያንን ወይም ማኅበሩን ለማነጽ በመሆኑ፣ ካልተተረጐመ ቤተ ክርስቲያን አትታነጽም (1 ቆሮንቶስ 14 ይመ)።

‹‹ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን?›› በማለት ጳውሎስ የተናገረው እንዲህ ዐይነቱን ልሳን በተመለከተ ነበር። እስቲ ይህንኑ ጥቅስ በዐውዱ መሠረት እንመልከተው።

> እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንደኛ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛ ነቢያትን፣ ሦስተኛ መምህራንን፣ ቀጥሎ ታምራት አድራጊዎችን፣ የመፈወስ ስጦታ ያላቸውን፣ ሌሎችን የመርዳት ስጦታ ያላቸውን፣ የማስተዳደር ስጦታ ያላቸውንና በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች መድቦአል። ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ መምህራን ናቸውን? ሁሉስ ታምራት ያደርጋሉን?

> ሁሉስ የመፈወስ ስጦታዎች አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን? (1 ቆሮንቶስ 12፥28-30)፡፡

ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚደረግ አገልግሎት እግዚአብሔር ስለ መደበው ለማኅበሩ ስለሚሆን ስጦታ ነው፡፡ ሁሉ ሐዋርያት ናቸው? አይደሉም፡፡ ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? አይደሉም፡፡ ሁሉ መምህራን ናቸውን? አይደሉም፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ሁሉስ ለማኅበሩ አገልግሎት ላይ በሚውል ልሳን ይናገራሉ ወይስ ይተረጉማሉ? አይናገሩም፤ አይተረጉሙም፡ ፡ ጳውሎስ ማመልከት የፈለገው ሁላችንም እግዚአብሔር በሕይወታችን ባኖራቸው ስጦታዎች መጠቀም ያለብን መሆኑን ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ሰው ሁሉ ለጉባኤ የሚሆን ልሳን አይኖረውም፡፡

## <u>በሁለቱ ለማኅበሩ በሚሆኑ ልሳኖች መካከል ያለ ልዩነት</u>

በኋላ ላይ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ጳውሎስ በእነዚህ ሁለት ለማኅበሩ በሚሆኑ ልሳኖች መካከል ያለውን ልዩነት ይገልጻል፡፡

> ስለዚህ በልሳን መናገር ለማያምኑ የሚሆን ምልክት እንጂ፣ ለሚያምኑ አይደለም፤ …እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን በአንድነት በተሰበሰቡበት፣ ሁሉም በልሳን በመናገር ላይ ሳሉ (መተርጐም ባለበት ልሳን) እንግዶች ወይም የማያምኑ ሰዎች ወደ ጉባኤው ቢገቡ አብደዋል አይሉምን? (1 ቆሮንቶስ 14፥22-23)፡፡

ልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖች መኖራቸውን ካልተረዳችሁ፣ ጳውሎስ ይህን ሲጽፍ ምናልባት ራሱን እየተቃረነ ነው በማለት ልታስቡ ትችላላችሁ፡፡ መጀመሪያ፣ ‹‹በልሳን መናገር ለማያምኑ የሚሆን ምልክት ነው›› ብሎአል፡ ፡ በኋላ ደግሞ በዚያው በቀጣዩ ቁጥር፣ ‹‹ሁሉም በልሳን በመናገር ላይ ሳሉ እንግዶች ወይም የማያምኑ ሰዎች ወደ ጉባኤው ቢገቡ አብደዋል አይሉምን?›› የሚል እናነባለን፡፡ ይሁን እንጂ፣ አራት ልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖች እንዳሉ በደንብ ስንረዳ፣ ጳውሎስ እየጻፈ ያለው ስለ ሁለት የተለያዩ ልሳኖች መሆኑን

ማየት እንችላለን፡፡

ጳውሎስ በመጀመሪያ የጠቀሰው የልሳን ዓይነት፣ (ለምልክት የሆነው) እንደ ምልክት የሚያገለግል በመሆኑ የማያምኑ ሰዎችን ይስባል፡፡ ሁለተኛው የልሳን ዐይነት፣ (ለመተርጐም የሚሆነው) ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ጥቅም ላይ የሚውል ነው፤ ይኸኛው ለማያምኑ ሰዎች ምልክት አይደለም፡፡ እንዲያውም ይኸኛው ልሳን ካልተተረጐመ በስተቀር፣ በሁለተኛው ዓይነት ልሳን ሲናገሩ የሚሰሙ የማያምኑ ሰዎች፣ እኛ አማኞች እብዶች እንደ ሆንን ማሰብ እንደሚችሉ ጳውሎስ ይናገራል!

እሑድ ጠዋት ስብሰባ ላይ ሰው ሁሉ በአንድ ጊዜ ቢሰብክ፣ ቢያስተምር፣ ወይም ትንቢት ቢናገር ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ትችላላችሁ? ያ ቅጥ ያጣና ውጤት የለሽ ነው የሚሆነው፡፡ መተርጐም በሚገባው ልሳን አለ አግባብ በመጠቀም፣ ግራ የሚያጋባ ሁኔታ መፍጠር እንደማይገባ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን የሚናገረው ከዚህ አንጻር ነው፡፡ ተገቢ ባልሆነ ቦታው ከዋለ፣ ይህ ዓይነቱ ልሳን ሥርዓትና ዓላማ የሌለው ይሆናል፡፡ በልሳን መናገር መረዳትንና መገለጥን እንጂ፣ ግራ መጋባትና ሁከትን ማምጣት እንደሌለበት ቀደም ሲል ጳውሎስ በዚሁ ምዕራፍ ግልጽ አድርጐ ነበር፡፡

> ከሁላችሁ የበለጠ በልሳን ስለምናገር እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፡፡ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎችን ለማስተማር ዐሥር ሺህ ቃላት በልሳን ከምናገር ይልቅ፣ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ብናገር ይሻላል (1 ቆሮንቶስ 14፥18-19)፡፡

በጣም ግልጽ ነው - ለጉባኤው የሚሆን ልሳን ከመጣ፣ እዚያ ያሉትን እንዲጠቅም መተርጐም አለበት፡፡ ያ ካልሆነ በሚታወቅ ቋንቋ ብቻ መናገር ይሻላል፡፡

ቀን 5

## ሦስት - ለግል ጸሎት ጥቅም ላይ የሚውል ልሳን

*በልሳን በምጸልይበት ጊዜ መንፈሴ ይጸልያል፤ አእምሮዬ ግን ያለ*

> ፍሬ ነው፡፡ ታዲያ፣ ምን ማድረግ አለብኝ? በመንፈስ እጸልያለሁ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመንፈስ እዘምራለሁ፤ በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ (1 ቆሮንቶስ 14፥14-15)፡፡

እስከ አሁን ያየናቸው የመጀመሪዎቹ ሁለት ልሳኖች ለሌሎች ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆኑ፣ ለሰዎች የእግዚአብሔርን መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡ ለምልክት የሚሆኑ ልሳኖች የማያምኑ ሰዎችን ለመጥቀምና ለማገልገል የታቀዱ ናቸው፤ የሚተረጐሙ ዓይነት ልሳኖች አማኞችን ለማገልገል የታቀዱ ናቸው፡ ፡ ከላይ በተመለከትነው ጥቅስ ጳውሎስ ሦስተኛውን ዓይነት ልሳን ማለትም ለግል ጸሎት፣ ጥቅም ላይ የሚውለውን ልሳን ያስተዋውቃል፡፡ ከእንግዲህ እየተናገረ ያለው ሌሎችን ስለ ማገልገል አይደለም፤ ይልቁንም ለግል ዓላማ ጥቅም ላይ ስለሚውለው ልሳን ነው የሚያስተምረው፡፡ ይህ ዓይነቱ ልሳን የግል ሕይወትን ለማነጽና ለጸሎት የሚውል ነው፡፡ ጳውሎስ፣ ‹‹በአእምሮ ስለ መጸለይ›› ማለትም ሰዎች በሚያደምጡት ቋንቋ ስለ መጸለይና፣ ‹‹በመንፈስ ስለ መጸለይ›› ማለትም በማይታወቅ ቋንቋ ስለ መጸለይ ለይቶ ይናገራል፡፡ በሁለቱም መንገድ መዘመር (ማምለክ) እንደምንችልም ይናገራል፡፡

ቀደም ሲል ከ1 ቆሮንቶስ 14፣ ‹‹በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርምና›› የሚል አንብበን ነበር (ቁጥር 2)፡፡ ይህ ዓይነቱ ልሳን ለምልክት የሚሆነው ልሳን እንዳይደለ እናውቃለን፤ ምክንያቱም በበዓለ ሃምሳ ቀን ደቀ መዛሙርቱ በሌሎች ቋንቋዎች የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ለሰዎች ተናግረው ነበር፡፡ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለሚተረጐመው ዓይነት ልሳን ሊሆንም አይችልም፤ ምክንያቱም ይህ ስጦታ ባልታወቀ ሰማያዊ ቋንቋ አማኙ ለቤተ ክርስቲያን እንደሚናገር (ሆኖም መተርጐም አለበት) ነው የሚያመለክተው፡፡ እዚህ ላይ ግን ጳውሎስ ለይቶ የሚናገረው በመንፈስ፣ ‹‹ለእግዚአብሔር እንጂ፣ ለሰዎች አይናገርም›› ስለ ተባለለት አማኝ ነው፡፡

ለግል ጸሎት የሚሆነው ልሳን በእግዚአብሔርና በሚጸልየው ሰው መካከል የሚደረግ መስተጋብር ነው፡፡ ዓላማው የሚጸልየውን ሰው ማበረታታት ወይም ማነጽ ነው፡፡ ‹‹እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፣ እጅግ ቅዱስ በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ፤ በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ፡፡ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያደርሳችሁን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ ሳለ፣

በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ›› (ይሁዳ 20-21)፡፡ በመንፈስ ቅዱስ፣ (በልሳን) ስንጸልይ ራሳችንን እንደምናንጽ ይሁዳ መናገሩን አስተውሉ፤ ይሁን እንጂ፣ በሚተረጐም ዓይነት ልሳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉት አማኞች ስንናገር፣ የምናንጸው ቤተ ክርስቲያንን ነው (1 ቆሮንቶስ 14፥5 ይመ)፡፡ እግዚአብሔር ሁለቱንም ይፈልጋል፤ ሁለቱም ጠቃሚ ናቸው፡፡

ብዙ አማኞች በመገረም፣ *በመንፈስ ቅዱስ ብሞላ እንኳ በልሳን ላልናገር እችላለሁ ወይ?* በማለት ይጠይቃሉ፡፡ አዎን፣ አንድ ሰው በመንፈስ ቢሞላ እንኳ በልሳን ላይናገር እንደሚችል አምናለሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ በመንፈስ የተሞላ ማንኛውም ሰው በልሳን የመጸለይ ችሎታ እንዳለውም ጨምሬ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ብዙ አማኞች በዚህ ስጦታ የማይጠቀሙት፣ የእምነት ርምጃ ባለ መውሰዳቸው ነው፡፡ ማንኛውንም የእግዚአብሔር ስጦታ የምንቀበለውና ጥቅም ላይ የምናውለው በእምነት ነው፡፡

እስቲ በዚህ መንገድ አስቡ፡፡ ሁለት ሰዎች ወንዝ ውስጥ እየሄዱ ነው፡ ፡ አንደኛው ሰው ውሃው ዙሪያውን እየሄደ ቢሆንም እርሱ ግን ቀጥ ብሎ መቆምን መርጧል፤ ሌላው ሰው ግን ዘና ብሎ ለወራጁ ውሃ መታዘዝ መርጧል፡፡ ወንዙ ውስጥ የቆመውና ራሱን ለወራጁ ውሃ የሰጠው ሰው ሁለቱም ውሃው ውስጥ ናቸው፤ ሆኖም ውሃው ወደ ወሰደው ቦታ መሄድ የሚችለው ሁለተኛው ሰውየ ነው፡፡ በልሳን የሚናገር ለወራጁ ውሃ ራሱን በሰጠው ሰው ሊመሰል ይችላል፤ ገና በልሳን የማይጸልየው አማኝ ወንዙ ውስጥ ቢሆንም፣ ከወራጁ ውሃ ጋር አብሮ እየሄደ አይደለም፡፡ (ራስን እንዴት ለመንፈስ መስጠት ወይም ማስገዛት እንደሚገባ ማወቅ ከፈለጋችሁ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንነጋገርበታለን፡፡)

ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ማድረግ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከተሰጡን ብዙ በረከቶች አንዱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ የዚህን ኅብረት ሙላት፣ ድነትን እንደ ተቀበልን ወዲያውኑ የምንለማመደው አይደለም፡፡ በጣም የሚያሳዝነው፣ ብዙ አማኞች የድነት ስጦታ አንዱን ገጽታ እንኳ እየተለማመዱ አለመሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን ሁሉ መፈለግ ወሳኝ ነገር ነው፡፡ ለእኛ ለመስጠት ሲል ኢየሱስ የሞተበትን ሁሉ መረዳት በክርስቶስ ባለን ጉዞ ውስጥ በጣም ሰፊው ክፍል ነው፡፡ ቀደም ሲል፣ እንደ ተነጋገርነው ለመንግሥቱ ተልዕኮ ኃይል የሚሰጠንና የሚያዘጋጀን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ በመንፈስ

በኩል ለእኛ የተሰጠውን ስጦታ ከዘነጋን፣ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀና የጠለቀ ግንኙነት አይኖረንም፤ እርሱን በሚገባ ለማገልገል የሚያስፈልገንን ኃይል መጠን እናጣለን፡፡

## አራት - ለምልጃ የሚሆን ልሳን

> እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል፡፡ ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመንፈስን ሐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና (ሮሜ 8፥26-27)፡፡

ጳውሎስ ይህን ክፍል የጀመረው፣ «መንፈስ በድካማችን ያግዘናል» በማለት ነው፡፡ ጳውሎስ የሚናገረው ስለ የትኛው ድካም ነው? መልሱ - «እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል፡፡» በቀላል አነጋገር የእኛ ደካማነት በዓለማችን ውስጥ እየሆነ ያለውን የማወቅ ዐቅማችን ውሱን መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ እንዴት ወይም ስለ ምን መጸለይ እንዳለብን የማናውቀበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ሆኖም፣ በእርሱ ስንተማመንና በመንፈስ (ሁሉንም ነገር በሚያውቀው) ስንማልድ፤ በእኛ ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ይጸልያል፡፡

በኮሌጅ በነበርኩ ጊዜ ፑርዱ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የነበሩ የወንዶችና የሴት ተማሪዎችን ማኅበር በወንጌል የሚደርስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እመራ ነበር፡፡ ስድሳ ያህል ተማሪዎች ይሳተፉ ነበር፤ አንዳንዶቹ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም ግንኙነት አልነበራቸውም፤ ሌሎቹ ከተለያዩ ቤተ ክርስቲያኖች የመጡ ነበሩ፡፡ በጥናቱ ይካፈሉ ከነበሩ ሴቶች አንዷ በልሳን የመናገር ዘመን ያለፈ መሆኑን በሚያምን ቤተ ክርስቲያን ያደገች ነበረች፡፡ አንድ ምሽት ስለ መንፈስ ቅዱስ ሳስተምር ከሰማች በኋላ፣ ልሳን ለዚህ ዘመን መሆኑን፣ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ እውነት መሆኑን ተረዳች! በዚያው ምሽትም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች፡፡

በሚቀጥለው ቀን 12፥30 ላይ በስልክ ጥሪ ተቀሰቀስኩ - እንደ እኔ ያለው የኮሌጅ ተማሪ በዚያ ሰዓት መቀስቀስ አይፈልግም! በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትካፈል ከነበረች አንዲት ልጃገረድ ጋር እንድገናኝ ተነገረኝ፤ ይህች ልጅ ትኖር የነበረው እኔ ከምኖርበት ቤት መንገዱን ተሻግሮ ነበር፡፡ ቅር እያለኝ ከአልጋ ወረድኩና እኔን እየጠበቀች ወደ ነበረበት ቦታ ሄድኩ፡፡

ከፊል እንቅልፍ ላይ ነበርኩ፤ በዚያ ጠዋት በመቀስቀሴም ቅር ብሎኝ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እርሷ በደስታ እየተጥለቀለቀች ነበር፡፡ ‹‹ምን እየሆነ ነው?›› በማለት ጠየቅሁ፡፡

‹‹ዛሬ ጠዋት እግዚአብሔር 11 ሰዓት ላይ ቀሰቀሰኝ፡፡ በልሳን እንድጸልይ በጣም ስለ ተሰማኝ መጸለይ ጀመርኩ፡፡ እየማለድኩ እንደ ሆነ ይሰማኝ ነበር፡፡ በእንደዚያ ባለ ግለት በልሳን እጸልይ የነበረው ለምን እንደ ሆነ እግዚአብሔርን ጠየቅሁ፡፡ ‹‹ለአንድ በዕድሜ የገፋ ሰው ሕይወት እየማለድሽ ነው›› በማለት እግዚአብሔር ነገረኝ፡፡ ስለዚህም በልሳን መጸለይ ቀጠልኩ፡፡

‹‹ከዚያ በኃላ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ እኔ ክፍል ውስጥ የነበረች ልጅ አስቸኳይ ጥሪ ደረሳት፡፡ ወንድ አያቷ ልብ ሕመም እንደ ደረሰባቸውና በአስቸኳይ ወደ ሆስፒታል እንደ ተወሰዱ ነበር የተነገራት፡፡ ሐኪሞቹም ሰውየውን ማትረፍ ቻሉ፡፡››

ልጅቱ መናገርዋን ቀጠለች፤ ‹‹መንፈስ ቅዱስ፣ ለእርሱ እየጸለይሽ ነበር›› አለኝ፡፡ ይኸ ለምልጃ የሚሆን ልሳን ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ የዚያ ሰው ሕይወት አደጋ ላይ መሆኑን እርሷ አታውቅም፤ መንፈስ ቅዱስ ግን ያውቃል፡፡ በአእምሮዋ ብቻ ብትጸልይ ኖሮ፣ ለእርሱ መማለድ አትችልም ነበር፡፡

ወላጅ እናቴ ያለችው ፍሎሪዳ ነው፤ አሁን በሕይወቷ ምን እየሆነ እንደ ሆነ አላውቅም፤ ካሊፎርኒያ የምትኖረው እኅቴ ላይ ምን እንደ ደረሰ አላውቅም፡ ፡ መንፈስ ቅዱስ ግን ለሁለቱም የእግዚአብሔርን ፍጹም ፈቃድ ያውቃል፤ በጸሎት ከእርሱ ጋር ለመተባበር ራሴን ስሰጥ በእኔ ውስጥ ይማልድላቸዋል፡ ፡ መንፈስ ሁሉን ነገር ይመረምራል፤ ሁሉን ነገር ያውቃል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እንዲጸልይ እየፈቀድንላት መሆኑን ስናውቅ ታላቅ ሰላሙ ይሞላናል!

## ለግል ጥቅም ላይ የሚውል ልሳንን የሚመለከት ገለጻ

እስከ አሁን «ለግል» በማለት ስናገር የነበረውን፣ ሁለቱ የልሳን ዓይነቶችን በተመለከተ፣ አንዳንዴ በግል ብቻ ሳይሆን በኅብረት ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል መረዳት ጠቃሚ ነው፡፡ በመንፈስ የተሞሉ አማኞች ሁሉ በአንድነት በልሳን የሚጸልዩበት ሁኔታ አለ፡፡ እንዲህ ባለው ጊዜ፣ ሁሉም በመንፈስ መጸለያቸው አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡ አንዳንዴ ደግሞ አማኞች በጉባኤ መሐል በጸሎት ቋንቋቸው ከመጸለይ ዝም ማለት የሚኖርባቸው ጊዜ አለ፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል፡፡

> እንግዲህ የቤት ክርስቲያን ምእመናን በአንድነት በተሰበሰቡበት ሁሉም በልሳን በመናገር ላይ ሳሉ፤ እንግዶች ወይም የማያምኑ ሰዎች ወደ ጉባኤው ቢገቡ አብደዋል አይሉምን? (1 ቆሮንቶስ 14፥23)፡፡

በዚህ ምንባብ ሁለት ዐይነት ወገኖች ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያ ጳውሎስ የጠቀሰው፣ የማያምኑ ሰዎችን ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ አድርገው ያልተቀበሉትን - ከእምነት ውጪ ያሉትን ሰዎች ነው፡፡ ሁለተኞቹ፣ እንግዶች የተባሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች በኢየሱስ የሚያምኑ ናቸው፤ ሆኖም ስለ መንፈስ ቋንቋ ገና አልተማሩም፡፡ ሁሉም በልሳን እየተናገሩ ያሉበት ክፍል ውስጥ ቢገቡ፣ በሁለቱም ምድብ ያሉ ሰዎች ደስ አይላቸውም፡፡ ምናልባትም፣ እየተናገሩ ያሉትን ሰዎች፣ *አበዳችሁ እንዴ?* በማለት ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

በጣም የሚያሳዝነው፣ ሰዎች ሁሉ ጮኽ ብለው በልሳን ይጸልዩ የነበረበትንና መሪዎችም ይህንኑ ያበረታቱ የነበረበትን አንድ ወይም ሁለት የእሑድ ጠዋት አገልግሎት ማየቴ ነው፡፡ እንዲያውም ባለፈው ጊዜ እኔ ራሴ ባለ ማወቅ፣ ሰዎችን በዚህ ሁኔታ የመራሁበት ጊዜ ነበር፡፡ እንደ ማንኛውም የእሑድ ጠዋት አገልግሎት ሁሉ፣ በእነዚህም አገልግሎቶች፣ *እንግዶች* ወይም *የማያምኑ* በተሰኙት ምድቦች ውስጥ የሚካተቱ ብዙ ጐብኚዎች ይኖራሉ፡፡ ምናልባትም፣ *እነዚህ ሰዎች አብደዋል እንዴ?* በማለት አስበውም ሊሆን

ይችላል፡፡ እንዲህ ያሉት ቤተ ክርስቲያኖች ለማደግና ማኅበረ ሰባቸውን በወንጌል ለመድረስ ትግል እንዳለባቸው ታዝቤአለሁ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ 1 ቆሮንቶስ 14፥23 ላይ የተሰጠውን ጥበብ ተግባር ላይ ባለማዋላቸው ይሆን? በዚህ መንገድ ከቀጠሉ እንግዶችና የማያምኑ ሰዎች በድጋሚ ወደዚያ ቦታ እንደማይመጡ ግልጽ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ቤተ ክርስቲያን አማኞችን ለጸሎት የምትጠራበት ጊዜ አለ (ቅዳሜ ጠዋት ወይም ሰኞ ማታ ሊሆን ይችላል)፡፡ በእነዚህ ስብሰባዎች የሚገኙት ሁሉ ቤተኞችና አማኞች ብቻ ናቸው፡፡ ጌታን ለማገልገል ወይም ለመማለድ ሲሰበሰቡ፣ ሁሉም በአንድነት በልሳን ቢጸልዩ ፍጹም ትክክልና ተገቢ ይሆናል፡፡

በቀላል አነጋገር፣ አማኞች በሚሰበሰቡበት ጊዜ፣ «የግል ልሳን» በምንለው በአንድነት መናገራቸው አግባብ የማይሆንበት ጊዜ ወይም ቦታ አለ አላለም፡ ፡ የማያምኑ ወይም እንግዳ ሰዎች በመካከላችን በሚኖሩበት ጊዜ በልሳን መናገራችን ላለንበት ሁኔታ የሚስማማ መሆን እንዳለበት ብቻ ነው ጳውሎስ የተናገረው፡፡

## እግዚአብሔር ለእናንተ የሚፈልገው

> ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፣ ትንቢት ለመናገር በብርቱ ፈልጉ፤ በልሳን መናገርንም አትከልክሉ፤ ነገር ግን ሁሉም በአግባብና በሥርዐት ይሁን (1 ቆሮንቶስ 14፥39-40)፡፡

ቤተ ክርስቲያን አስደናቂውን የልሳን ስጦታ አላግባብ ልትጠቀምበት እንደምትችል ጳውሎስ በሚገባ አውቋል፡፡ ስለዚህም፣ «በትክክለኛው ዓይነት ልሳን በትክክለኛው ቦታ ተጠቀሙ፡፡ ይህን ድንቅ የመንፈስ ስጦታ አንዳንድ አማኞች በተሳሳተ መንገድ ስለ ተጠቀሙበት ብቻ በልሳን መናገርን አትከልክሉ» በማለት ይመክራል፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ቤተ ክርስቲያን ስለ ብዙዎቹ የመንፈስ ነገሮች ቸልተኛ ሆናለች፡፡ ይህ አሳዛኝ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ የተላከው ለቤተ ክርስቲያን ኃይል ለመስጠት ነበር፡፡ መንግሥቱን የሚያስፋፋበት መሣሪያ እንድትሆን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን መርጧል፡

፣ በክርስቶስ ካለን ቦታ ጋር ለሚመጣው ኃይል ካልነቃን፣ የመንግሥቱን ሥልጣን ጥቅም ላይ ከማያውል ንጉሥ የተለየን አንሆንም፡፡

በልሳን የመናገር ዘመን አልፏል ብለው በማመናቸው እነዚህን ድንቅ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ያጡ ምን ያህል አማኞች ይሆኑ ይሆን? የእግዚአብሔር ፍላጐት ግን ግልጽ ነው፤ ‹‹ሁላችሁም በልሳን ብትናገሩ እወዳለሁ›› (1 ቆሮንቶስ 14፥5)፡፡ ምናልባት አንዳንዶች፣ ‹‹ይህን ያለው'ኮ ጳውሎስ እንጂ፣ እግዚአብሔር አይደለም›› በማለት ይከራከሩ ይሆናል፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት በእስትንፋሰ እግዚአብሔር የተጻፉ ናቸው፤ ይህም ጥቅስ ከዚያ የተለየ አይደለም (2 ጢሞቴዎስ 3፥16 ይመ)፡፡

የልሳኖች ስጦታ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እጅግ ጠቃሚ ገጽታ - እንዲያውም ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረን የጠበቀ ግንኙነት የሚገለጥበት ውብ ገጽታ መሆኑን መዘንጋት የለባችሁም፡፡ ስለሆነም እኔም ለእናንተ ያለኝ ተስፋ ጳውሎስ የነበረው ዓይነት ነው፡፡ ይህን ዐይነተኛ ስጦታ እንድትቀበሉና በእያንዳንዱ ቀን በመንፈስ ኃይልና መገኘት እንድትበረቱ እጸልያለሁ፡፡

ቀን 1 ማሰላሰያ

# መንፈስ እንቅስቃሴ ያመጣል!

*እግዚአብሔርም በምልክት፣ በድንቅና በልዩ ልዩ ታምራት፣ እንዲሁም እንደ ፈቃዱ በታደሉት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ስለዚሁ ነገር መሰከሮአል፡፡*

— ዕብራውያን 2፥4

መንፈስ ቅዱስ፣ በተለያዩ አያሌ ድንቅ መንገዶች የሚገለጽ እንቅስቃሴ አምጪ ኃይል ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ምሳሌያዊ በሆነ መልክ እንደ ርግብ፣ እሳት፣ ነፋስና ወይን ጠጅ ተወክሏል፡፡ እነዚህን መገለጾች መረዳት፣ ባሕርዩንና በእኛ ውስጥ እና በእኛ በኩል እንዴት መሥራት እንደሚፈልግ መገንዘብ ያስችለናል፡፡

**መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ ነው፡፡** አራቱም ወንጌሎች መንፈስ በርግብ አምሳል ኢየሱስ ላይ መውረዱን ያመለክታሉ፡፡ ርግቦች በባሕርያቸው ጨዋና ፍቅር የሞላባቸው ናቸው፤ በጣም ድንጉጥና በቀላሉ የሚባረሩ ናቸው፡፡ የሚያርፉት ምቾት በሚሰጣቸውና ሰላም ባለበት ቦታ ብቻ ነው፡፡ የትዳር ጓደኛ የሚመርጡት ለዘለቄታው ነው፡፡ ይህን እውነት መገንዘብ መንፈስ ቅዱስን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳትና ከእርሱ ጋር እንድትቀራረቡ የሚረዳችሁ እንዴት ነው?

ማቴዎስ 3፥16-17፤ ማርቆስ 1፥9-11፤ ሉቃስ 3፥21-22፤ ዮሐንስ 1፥32-33 ተመልከቱ፡፡

**መንፈስ እንደ እሳት ነው፡፡** ለሙሴ በሚቃጠል ቁጥቋጦ ውስጥ፣ ለእስራኤል በእሳት ዐምድ[1] ተገልጾአል፡፡ በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን፣ ‹‹የእሳት ምላሶች በሚመስሉ›› ልሳኖች አጠመቃቸው (ሐዋርያት ሥራ 2፥3)፡፡ እርሱ ኢየሱስ ወደ ምድር ያመጣው እሳት ነው፤ ያንን እሳት እንዳናዳፍን መጠንቀቅ አለብን፡፡ እስቲ ስለ እሳት ባሕርይ አስቡ፤ ያጠራል፤ ብርሃን ይሰጣል፤ ሙቀት ይሰጣል፤ ያቃጥላል፡፡ ይህ በሕይወትህ ያለውን የእግዚአብሔር መንፈስ እሳት መረዳት የሚያስችልህ እንዴት ነው? እሳቱ እንዲቀጣጠልና ነበልባሉ እንዲንበለበል የሚረዱ ነገሮች ምንድናቸው?

ሐዋርያት ሥራ 2፥3-4፣ ሉቃስ 12፥49፣ 1 ተሰሎንቄ 5፥19-21፣ ማቴዎስ 3፥11-12፣ ሉቃስ 3፥16-17፣ ኤርምያስ 20፥9፣ 23፥29፣ ዕብራውን 12፥29 ተመልከቱ፡፡

**መንፈስ እንደ ነፋስ ነው፡፡** በበዓለ ሃምሳ ቀን የተገለጸው እንደ እሳት ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ነፋስም ጭምር ነበር፡፡ ነፋስ ሲባል ረጋ ያለ ሽውታንና ኃይለኛ ዐውሎ ነፋስን ይጨምራል፡፡ እስቲ ነፋስ ማድረግ የሚችለውን አስቡ፡፡ የመንፈስ ነፋስ በሕይወትህ እንቅስቃሴ የሚያመጣው እንዴት ነው? ምንስ ሊያደርግ ይችላል?

ዮሐንስ 3፥5-8 ተመልከቱ፡፡

**መንፈስ እንደ ወይን ጠጅ ነው፡፡** በበዓለ ሃምሳ ቀን ደቀመዛሙርቱ በልሳኖች የእግዚአብሔርን ታላቅነት ተናገሩ፡፡ አንዳንዶች ብዙ የወይን ጠጅ ጠጥተው ሰክረዋል ብለው እስኪያስቡ ድረስ፣ ያ መገለጥ በጣም ብርቱ ነበር፡፡ ጴጥሮስ ግን ያንን ያደረገ መንፈስ እንደ ሆነ ነገራቸው! ቆም በሉና አስቡ፡፡ ወይን ጠጅ መጠጣት አንድ ሰው ስሜት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ምንድነው? አዲሱን የመንፈስ ወይን ጠጅ መጠጣት እናንተ ላይ ምን ለውጥ ማምጣት ይችላል?

ሐዋርያት ሥራ 2፥13-18፣ ሉቃስ 5፥37-38፣ (እንዲሁም ማርቆስ 2፥22፣ ማቴዎስ 9፥17)፣ ኤፌሶን 5፥18-19፣ አስቴር 1፥10፣ ኤርምያስ 31፥11-13 ተመልከቱ፡፡

*‹‹ሰማያት መንፈስ ቅዱስን መያዝ አይችሉም፤ ሆኖም የአገልጋዮቹን ልብ መኖሪያው አድርጓል፡፡ እኛ የእርሱ ቤተ መቅደስ ነን፡፡ እኛ ላይ የሚያሳድረው እያንዳንዱ ተፅዕኖ ምስጋና እንድናፈልቅ ያደርጋል፡፡ እርሱ እንደ ነፋስ ከሆነ፣ እኛ የነፋስ መተላለፊያዎች ነን፤ እርሱ እንደ ጤዛ ከሆነ እኛ የሚለመልሙ አበቦች ነን፤ እርሱ እንደ እሳት ከሆነ እኛ እንግላለን፡፡ በእኛ ውስጥ በማንኛውም መልኩ ሲንቀሳቀስ፣ እኛ ደግሞ ለእርሱ ድምፅ ምላሽ እንሰጣለን፡፡››*

— ቻርለስ ኤች ስፐርጂን[2]

ቀን 2 ማሰላሰያ

# የእርሱ መገኘት ማስረጃ ይኖረዋል

**ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው፡፡**

— 1 ቆሮንቶስ 12፥7

የእግዚአብሔር መንፈስ ሲገኝ ማስረጃ ይኖራል! ወንዞችና ባሕሮች ለደረቁ ምድር ስፍራ ይለቃሉ፡፡ የታወሩ ዐይኖችና የደነቆሩ ጆሮዎች ይከፈታሉ፡፡ ሽባዎች ይራመዳሉ፤ ዲዳዎች ይናገራሉ፡፡ ፍርሃት ይሸነፋል፤ ተስፋ ያብባል! ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር ጥሩ ኅብረት ሲኖረን ምልክቶችና ድንቆችም ይኖራሉ፡፡

መንፈስ ቅዱስ ሲገኝ ሰዎች የሚያዩትና የሚሰሙት ማስረጃ እንደሚኖር ሐዋርያት ሥራ ላይ ያሉ ታሪኮች በተደጋጋሚ ያረጋግጣሉ፡፡ እስቲ ወደ ኋላ ዘወር ብላችሁ፣ ሕይወታችሁን ተመልከቱ፡፡ ለመንፈስ ቅዱስ መገኘት ማስረጃ የሚሆን ምን የምታስታውሱት ነገር አለ? መንፈስ በቦታው ተገኝቶ በሕይወታችሁ ሥር ነቀል ለውጥ መደረጉን የሚያሳዩ አንድ ወይም ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ጻፉ፡፡

አንድ የማስታውሰው ____________________

አንድ ትዝ የሚለኝ ____________________

አንድ ሌላ የማስታውሰው ____________________

አትቸኩሉ፤ አትጣደፉ፡፡ ረጋ ብላችሁ የእግዚአብሔርን መልካምነት አሰላስሉ፡፡ ወደ ኋላ ዘወር ብላችሁ የእርሱን ታማኝነት ስታስታውሱ፣ መንፈስ በአዲስ ሕይወት ያለምልማችሁ!

*የእግዚአብሔርን ሥራ አስታውሳለሁ፤ የጥንት ታምራትህን በእርግጥ አስታውሳለሁ፤ ሥራህን ሁሉ አሰላስላለሁ፤ ድንቅ ሥራህን ሁሉ አውጠነጥናለሁ።*

*አምላክ ሆይ፣ መንገድህ ቅዱስ ነው፤ እንደ አምላካችን ያለ ታላቅ አምላክ ማን ነው? ታምራትን የምታደርግ አምላክ አንተ ነህ፤ በሕዝቦችም መካከል ኃይልህን ትገልጣለህ።*

— መዝሙር 77፥11-14

ባለፈው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ረድቶአችኃል፤ ዛሬም እንደ ገና ያንን ማድረግ ይፈልጋል! አሁን እንዲረዳችሁ የምትፈልጉት በምን ዐይነት ሁኔታ ነው? በፊቱ ጸጥ በል፤ እንደ ገና ያንን እንዲያደርግ ጋብዘው! እርሱ እውነት መሆኑንና ለእናንተም ሆነ በዙሪያችሁ ላሉት በእውነት እንደሚያስብ ማስረጃ እንዲያሳያችሁ ለምኑት። ጸጥ በሉ። በውስጣችሁ ምን ተናገራችሁ?

ጸጥ በሉ፤ ረጋ በሉ፤ ለጌታ ምስጋና አቅርቡ። ለእርሱ የምስጋናና የውዳሴ **ጸሎት ጻፉ**። እርሱ ምስጋናና ውዳሴ ይገባዋል!

# መሞላት ቀጣይ ልምምድ ነው

*በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፡፡*

– ኤፌሶን 5፥18

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በጣም አስፈላጊ መሆኑን እግዚአብሔር በጳውሎስ በኩል ነግሮናል፡፡ መሞላት ለሚለው የግሪኩ ፕሌይሩ ሲሆን፣ (Pleroo — ሲነበብ Play-ro-o) ‹‹መሙላት፣ አንድ ሰው ነፍስ ውስጥ መሰራጨት››[3] ማለት ነው፡፡ ከዚህም በላይ በጣም ጠቃሚው፣ ግሡ ተሻጋሪ አንቀጽ የትእዛዝና አሁን ጊዜ መሆኑ ነው፡፡ ተሻጋሪ አንቀጽ ሲባል፣ ‹‹እናንተ›› (ርዕሰ ጉዳዮቹ) ላይ የሚደረግ ነገር አለ ማለት ነው፤ ትእዛዝ ሲባል አስተያየት ሳይሆን፣ ጠንከር ያለ መመሪያን ያመለክታል፤ የአሁን ጊዜ መሆኑ ጉዳዩ ቀጣይነት ያለው መሆኑን ያመለክታል፡፡

አምፕሊፋይድ የተሰኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ኤፌሶን 5፥18 በጣም ጥሩ አድርጎ አስቀምጦታል፡፡ ‹‹በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ምክንያቱም ማባከን ነው፤ ግን ሁሌም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡፡›› ቀጣይነት ያለው በመንፈስ የመሞላት ልምምድ፣ እንደ ኢየሱስ ለመኖርና በሰማይ እንደ ሆነ ሁሉ በምድርም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም የሚያስፈልገንን ሁሉ እኛ ውስጥ ያኖራል፡፡ ወንጌላዊው **ስሚዝ ዊግለስወርዝ** እንዲህ አለ፤

> ‹‹ለእኔ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ መገመት እንኳ ከምችለው በላይ ነው… በመንፈስ መሞላት በፈቃዳችን የምናደርገው ነው፤ ያም ሆኖ መፈጸም ያለብን ትእዛዝ ነው… ዘወትር በመንፈስ በመሞላት ጠዋት፣ ቀንና ማታ በልሳን መናገር ትችላላችሁ እላለሁ፡፡ በመንፈስ ስትኖሩና ስትመላለሱ፣ ዲያብሎስ ይሸነፋል፤ ዲያብሎስ ላይ ከአሸናፊዎች በላይ ትሆኑበታላችሁ፡፡
>
> …በመንፈስ ስትኖሩና ስትመላሱ ብትበሉ፣ ብትጠጡ፣ ብትንቀሳቀሱና ማንኛውንም ነገር ብታደርጉ ሁሌም ለእግዚአብሔር ክብር ይሆናል፡ ፡ ስለሆነም ምንጊዜም ቢሆን የእኛ መልእክት፣ ‹‹በመንፈስ ተሞሉ›› የሚል ነው መሆን ያለበት፡፡ እግዚአብሔር እዚያ ቦታ እንድትሆኑ ነው የሚፈልገው፤ ሰማይ ከምድር ከፍ የማለቱን ያህል ይህ ሕይወት ከተፈጥሮአዊው ሕይወት እጅግ የበለጠ ነው፡፡ እንዲሞላችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ፡፡››[4]

ጴጥሮስ፣ ዮሐንስና ሌሎቹ ደቀመዛሙርት ሁሉ በበዓለ ሃምሳ ቀን በመንፈስ ቅዱስ ተጠምቀዋል፡፡ ከዚያ በኋላም ጥቂት ቆየት ብሎ ጸሎት ላይ እያሉ እንደ ገና ተሞልተዋል፡፡ ከሐዋርያት ሥራ 4፥23-31 ይህን ታሪክ በጥንቃቄ አንብብ፡

***፡ ዘወትር በመንፈስ የምትሞላበት ሁኔታ ላይ ለመሆን የሚረዳህ ከዚህ ምን መማር ትችላለህ?***

---

---

---

---

**በጳውሎስ በኩል እግዚአብሔር፣ ‹‹የተሰጠህን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል››፣ ይልቁንም፣ ‹‹በአንተ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ስጦታ እንድታቀጣጥል አሳስብሃለሁ›› ይላል (1 ጢሞቴዎስ 4፥14፤ 2 ጢሞቴዎስ 1፥6)፡፡ በሌላ አነጋገር ያለ ማቋረጥ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ ማለት ነው፡፡ ኤፌሶን 5፥18-19፤ 6፥18 እና ይሁዳ 20 በጥንቃቄ አንብብ፡፡ በውስጥህ ያለውን እሳት ማቀጣጠል እንደሚገባ መንፈስ ምን አስተማረህ?**

---

---

---

---

*እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፣ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኃለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው፡፡ መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ፡፡*

— ሮሜ 12፥1-2

ቀን 4 ማሰላሰያ

# ለዓላማ እናንተን ባለ ስጦታ አድርጐአችኋል

*ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው፡፡*

– 1 ቆሮንቶስ 12፥7

ኢየሱስ የጀመረውን ሥራ ለማስቀጠል መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አድሎናል፡፡ ምንም እንኳ ስጦታዎቹ ልዩ ልዩ ቢሆኑም፣ ‹‹እነዚህ ሁሉ የዚያው የአንዱ መንፈስ ስጦታዎች ሲሆኑ፣ ለእያንዳንዱ ሰው እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ ይሰጠዋል›› (1 ቆሮንቶስ 12፥1)፡፡

እነዚህ ስጦታዎች ለዚህ ዘመንም ጭምር ናቸውን? ኢየሱስ ያደረገውን እኛም ማድረግ አለብንን? አዎን፤ እንደዚያ መሆን አለበት፡፡ በአፍሪካ ክፍለ ዓለም፣ ሚሊዮኖች ወደ ክርስቶስ ሲመጡ የተመለከተው ወንጌላዊ **ራይንሐርድ ቦንኬ** እንዲህ ይላል፤

> ‹‹እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተአምራት አድራጊ መሆኑን በጣም አምናለሁ፡፡ ኢየሱስ በዚህ ምድር ሲመላለስ ይከተሉት የነበሩ ምልክቶች፣ በዚህ ዘመን በእኛም ሕይወት እንደሚፈጸሙ አምናለሁ፤ እንደዚያ መሆንም አለበት፡፡ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ፣ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ ይሠራል፤ እንዲያውም እኔ ወደ አብ ስለምሄድ ከእነዚህም የሚበልጥ ያደርጋል››[5] ብሎአቸዋል፡፡

**ሮሜ 12፥3-8** በጥንቃቄ አንብቡና የተጠቀሱትን ስጦታዎች አመልክቱ፡፡ አጠቃላይ በሆነ መልኩ እነዚህን እንዴት ትገልጿቸዋላችሁ (ዓላማና ተግባራቸውን አስመልክቶ)?

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

አሁን ደግሞ **1 ቆሮንቶስ 12፥4-11** አንብቡና ዘጠኙን ስጦታዎች ዘርዝሩ፡፡ አጠቃላይ በሆነ መልኩ እነዚህን እንዴት ትገልጿቸዋላችሁ (ዓላማና ተግባራቸውን አስመልክቶ)?

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________________

ሁለቱም ምንባቦች ላይ ያሉ ስጦታዎች ተመልከቱ፡፡ ከእነዚህ ስጦታዎች አንዳንዶቹ በሕይወታችሁ እየሠሩ ነውን? ከሆነ፣ የትኛው?

እርግጠኞች አይደላችሁምን? ከእነዚህ ስጦታዎች ወደ ማንኛው ነው የምትሳቡት ወይም የበለጠ የሚያጓጓችሁ የትኛው ነው? ስጦታዎቹን እንዴት እንደ ሰጣችሁ መንፈስ ቅዱስን ጠይቁት፡፡

ለሌሎች ያላችሁን ዝንባሌና መንፈስ ስጦታዎቹን እንዴት እንዳደላችሁ መገንዘብ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረው ያ አስተሳሰብ፣ በእናንተም ዘንድ ይሁን›› ይላል (ፊልጵስዩስ 2፥5)፡፡ ራይንሐርድ ይህንኑ በሚከተለው መልኩ ያረጋግጣል፡፡

> ‹‹የእግዚአብሔር ሥራ ስኬት በማንኛችንም ላይ የሚደገፍ አይደለም… በእርሱ ብቻ በመደገፍ ነው የሚከናወነው… እግዚአብሔር ካልተጠቀመብኝ በቀር እኔ ምንም ማለት አይደለሁም፤ ከሌሎች ድምፆች ሁሉ ይልቅ ለእርሱ ድምፅ ዋጋ እሰጣለሁ… ራሴን ከሌሎች የእግዚአብሔር አገልጋዮች አስበልጬ አላይም፡፡››[6]

1 ቆሮንቶስ 12፥12-26 እና ሮሜ 12፥3-5 በጥንቃቄ አንብቡ፡፡ ስለ ዝንባሌያችሁ መንፈስ ቅዱስ ምን አሳያችሁ? የእናንተ የራሳችሁን ጨምሮ የእያንዳንዱ ሰው ስጦታ ምን ያህል ጠቃሚ ወይም አስፈላጊ ነው ትላላችሁ? ስጦታህን ችላ ካልከው በክርስቶስ አካል፣ (በቤተ ክርስቲያን) ምን ዓይነት ጉድለት ሊኖር ይችላል?

**ተጨማሪ ጥናት…**
የትክክለኛ ዝንባሌ ወይም አስተሳሰብ አስፈላጊነት - ፊልጵስዩስ 2፥1-8፤ 2 ቆሮንቶስ 8፥9፤ ማቴዎስ 23፥11-12፡፡
መንፈስ ቅዱስ ለዓላማ አማኞችን ይሾማል፣
1 ቆሮንቶስ 12፥28-31፤ ኤፌሶን 4፥11-14፡፡

ቀን 5 ማሰላሰያ

# በእናንተ ውስጥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንዲጸልይ ፈቃደኞች ሁኑ

*እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል፡፡*

– ሮሜ 8፥26

እንዴት መጸለይ እንዳለባችሁ ግራ እስኪገባችሁ ድረስ ሕይወት በምታመጣቸው ውጣ ውረዶች ተጐድታችኋልን? ብቻችሁን አይደላችሁም፤ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቅዱሳን ይህን ተለማምደዋል፡፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ከእርሱ እንድትርቁ ሳይሆን፣ ወደ እርሱ እንድትቀርቡ ይፈልጋል፡፡ ራሳችሁን ዝግ እንድታደርጉ ሳይሆን፣ ለእርሱ ክፍት እንድታደርጉ ይፈልጋል፡፡ ምን ማለት ወይም እንዴት መጸለይ እንደሚገባችሁ እናንተ ባታውቁም፣ በውስጣችሁ የሚኖረው የክርስቶስ መንፈስ ግን ያውቃል፡፡

የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ እንደሚኖር እንዲሁ ላይ ላዩን ሳይሆን፣ ከልባችሁ ማወቃችሁ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በሚከተሉት ጥቅሶች ላይ ለማሰላሰል ጊዜ ይኑራችሁ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ምን ዓይነት መረዳት ነው የሰጣችሁ?

ገላትያ 4፥6፤ ሮሜ 8፥16፤ 1 ቆሮንቶስ 6፥19፤ ዮሐንስ 14፥23፤ 1 ዮሐንስ 3፥24፤ 4፥12-13 ላይ አሰላስሉ፡፡ ራሱን እውን እንዲያደርግላችሁ መንፈስ ቅዱስን ጠይቁት፡፡

‹‹በማንኛውም ሁኔታና በማንኛውም ጊዜ በመንፈስ›› እንድንጸልይ እግዚአብሔር ይፈልጋል (ኤፌሶን 6፥18)፡፡ ከፍተና አካላዊ ጉዳት የደረሰበትና ዓመታት እስር ቤት ያሳለፈው **ዋችማን ኒ** እንዲህ አለ፡፡

> ‹‹የሚረዳን ሁሉን ቻይ መንፈስ ስላለ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ በብርታቱ በውስጣችን በሚኖረውና በውስጣችን በሚሠራው መንፈስ ቅዱስ እንደገፍ፤ ምክንያቱም በድካማችንና ባለዋቂነታችን እርሱ ረዳታችን ነው፡፡ ምንም እንኳ እንዴት መጸለይ እንዳለብን ባናውቅም፣ እርሱ ራሱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውቅ በውስጣችን የሚኖር

*መንፈስ ቅዱስ፣ እንደ እግዚአብሔር ሐሳብ መጸለይ ያስተምረናል፡፡››[7]*

*ቆም በሉና አስቡ፡፡ ስለ ራሳችሁ፣ ስለ ሌሎችና ስለሚገጥሟችሁ ሁኔታዎች እንዴት መጸለይ እንዳለባችሁ የምታውቁት ምን ያህል ነው? በምንጸልየው ጸሎት ሁሉ ዝንባሌያችንና ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት ሁኔታ ምን መሆን አለበት፡፡*

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ምሳሌ 3፥5-8፤ 28፥26፤ ሉቃስ 18፥9-14፤ ያዕቆብ 4፥6-10 አንብቡ፡፡

*በእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ውስጥ መመላለስ ትፈልጋላችሁ? በሰማያዊ ቋንቋ በውስጣችሁ በመጮኽና በመቃተት በመጸለይ መንፈስ ያንን እውን ያደርገዋል፡ ፡ ‹‹ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመንፈስን ሐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማልዳልና›› (ሮሜ 8፥27)፡ ፡ ይህን ምንባብ በጥንቃቄ አንብቡ፡፡ በዚህ ውስጥ መንፈስ የሚናገራችሁ ምንድነው?*

በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ፣ ለሰው አይናገርምና ምስጢር የሆነውን በመንፈስ ስለሚናገር የሚረዳው የለም፡፡ …በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል… በልሳን በምጸልይበት ጊዜ መንፈሴ ይጸልያል፤ አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው፡፡ ታዲያ ምን ማድረግ አለብኝ? በመንፈስ እጸልያለሁ፤ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፣ በመንፈስ እዘምራለሁ፤ በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ፡፡

– 1 ቆሮንቶስ 14፥2፣4፥14-15

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

*‹‹እናንተ ራሳችሁን ለመንፈስ ስታቀርቡ፣ እርሱ ደግሞ እናንተንና ነገሮቻችሁን በአብ ዙፋን ፊት ያቀርባል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ሐሳብ፣ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ያውቃል፡፡ ልብን የሚመረምርና እናንተ ራሳችሁን ከምታውቁት በላይ የበለጠ የሚያውቃችሁ መንፈስ ቅዱስ፣ ያንን ችግር ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ያቀርባል፤ መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ውስጥ ሲጸልይ አንዳችም ነገር አይጐድልባችሁም፡፡››*

–ካትሪን ኩሁልማን[8]

# የውይይት ጥያቄዎች

1. በዳንን ጊዜ እኛ ውስጥ ለመኖር መንፈስ ቅዱስ የሚመጣ በመሆኑና፣ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህን ሁለት ድንቅ ልምምዶች፣ እንዴት ትገልጧቸዋላችሁ?

2. ለእርሱ መንግሥት አንዳች ነገር ለማድረግ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት በመንፈስ ቅዱስ እስኪሞሉ ድረስ እንዲቆዩ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ያዘዘው ለምን ይመስላችኋል? (ሐዋርያት ሥራ 1÷4-5)? «ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ» ቆዩ ከሚለው መርሕ ምን እንማራለን፤ ይህንኑስ በሕይወታችን እንዴት ተግባራዊ እናደርገዋለን?

3. በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በልሳን እንድንናገር ያስችለናል፡፡ ልሳን አእምሮአችን የማይገነዘበው ወይም መረዳት የማይችለው ቋንቋ ነው፡ ፡ ከሩቅ አገሮች መጥተው በበዓለ ሃምሳ ቀን ኢየሩሳሌምን እየጐበኙ ከነበሩ አይሁዳውያን አንዱ እንደ ነበራችሁ አስቡ፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን ድነት አስመልክቶ አማኞች በገዛ ራሳችሁ ቋንቋ ሲናገሩ ብትሰሙ ምን ታስቡ ነበር?

4. ከሐዋርያት ሥራ እንደምናነበው አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ፣ ከእያንዳንዱ ታሪክ ዘወትር ሲፈጸሙ የምንመለከታቸው ሁለት ነገሮች ምንድናቸው? ለቆርኔሌዎስና ለቤተ ሰቡ እግዚአብሔር ድነትንና በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን በአንድ ጊዜ የሰጠው ለምን ይመስላችኋል? እግዚአብሔር፣ የእናንተን «ሃይማኖታዊ ገደብ» እንዴት እንዳፈረሰውና፣ ስለ እርሱ ማንነት ያላችሁን መረዳት በእንዴት ዓይነት መንገድ እንዳሰፋው ታሪክ ካላችሁ ተናገሩ፡፡

5. ትንቢትና በልሳኖች መናገር በዚህ ዘመን ላሉትም አማኞች ከሆነ፣ ሁሉም በልሳኖች እንደማይናገሩ (1 ቆሮንቶስ 12÷27-30) እና ልሳንም ይሻራል ሲል ጳውሎስ ምን ማለቱ ነበር (1 ቆሮንቶስ 13÷8-12 ይመ.)? እነዚህን ጥቅሶች በጥንቃቄ አንብቡና ገለጻ ስጡ፡፡

6. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አራት ዓይነት ልሳኖች ይናገራል፡፡ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብቡና እግዚአብሔር እነዚህ የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ መገለጦችን ለቤተ ክርስቲያኑ የሰጠው ለምን እንደ ነበር በማስረዳት አራቱ የልሳን ምደቦችን አመልክቱ፡፡
   1 ቆሮንቶስ 14÷22
   1 ቆሮንቶስ 12÷10
   1 ቆሮንቶስ 14÷14-15
   ሮሜ 8÷26-28

በእነዚህ የልሳን ዐይነቶች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት በጣም ጠቃሚ ወይም አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

7. አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ቢሞላ እንኳ በልሳን ላይናገር ይችላልን? ከቻለ፣ ለምን? ካልቻለ፣ ለምን? ለዚህ የሚሰጡ በጣም የተለመዱ ምክንያቶች ምንድናቸው?

## ምዕራፉ በአጭሩ

- ከመንፈስ ኃይል መቀበል ለመንግሥቱ ሥራ ሁሉ አስፈላጊ ነው፡፡
- በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ድነትን ተከትሎ የሚመጣ የተለየ ልምምድ ነው፡፡
- ድነት በክርስቶስ ውስጥ ያኖረናል፤ በመንፈስ መሞላት እንደ እርሱ ለመኖር ኃይል ይሰጠናል፡፡
- ልሳኖች አልተሻሩም፤ ኢየሱስን ፊት ለፊት እስክናይ ድረስ ሥራ ላይ ናቸው፡፡
- አራት ዓይነት ልሳኖች አሉ - ለማያምኑ ሰዎች ምልክት የሚሆን ልሳን፣ የሚተረጐም ልሳን፣ በግል ጸሎት ጥቅም ላይ የሚውል ልሳን፣ ለመማለድ ጥቅም ላይ የሚውል ልሳን፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ለጉባኤ አገልግሎት ናቸው፤ ሁለተኛዎቹ ለግል ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው፡፡

5

# የመንፈስ ቋንቋ

*በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ ምስጢር የሆነውን በመንፈስ ስለሚናገር የሚረዳው የለም።*

– 1 ቆሮንቶስ 14፥2

በግላችሁ በምትናገሩት ልሳን ብታመሰግኑ እግዚአብሔር ይረዳችኋል… ምክንያቱም በእናንተና በእርሱ መካከል ብቻ ያለ ምስጢር እየነገራችሁት ነው።

- ሜሴጅ

## ቀን 1

ሜሴጅ የተሰኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ይህን ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን ግላዊ ግንኙነት የሚገልጥበትን መንገድ በጣም ነው የምወደው። ይህ ልሳን ወይም ቋንቋ፣ ‹‹በእናንተና በእርሱ መካከል›› የሚደረግ ብርቱ መስተጋብር ነው።

ባለፈው ምዕራፍ አዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉትን አራት የልሳን ዐይነቶች ማለትም፣ ለማያምኑ ሰዎች ምልክት የሚሆነውን ልሳን፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚተረጐመውን ልሳን፣ በግል ጸሎት ጊዜ ጥቅም ላይ የሚለውን ልሳን እና ለመማለድ የሚያስፈልገውን ልሳን ተመልክተን ነበር። የመጀመሪያዎቹ ሁለት የልሳን ዓይነቶች ለጉባኤ አገልግሎት (በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች) ጥቅም ላይ እንዲውሉ የታቀዱ ሲሆኑ፣ የተቀሩት ሁለቱ ለግል ጥቅም ላይ የሚሉ ናቸው። በዚህ ምዕራፍ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የሚኖረውን የግል መስተጋብር ባሕርይና ተግባር እንመለከታለን፤ ይህም በልሳን መናገርንና በአእምሮ መናገርን ይጨምራል። እነዚህ ሁለቱ በአንድነት በመሆን *የመንፈስ ቋንቋ* መገለጥን ያካትታሉ።

በድጋሚ ግልጽ ለማድረግ ያህል፣ ‹‹ለግል›› በሚለው ቃል ስጠቀም፣

ሰውየው ብቻውን በሚሆንበት ጊዜ ነው ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ማለት ብቻ እንዳደለ ግልጽ ማድረግ እፈልጋለሁ፡፡ ይልቁንም፣ የሰማያዊ ቋንቋ መገለጦች መጽሐፍ ቅዱስ፣ «እንግዶች» ወይም፣ «የማያምኑ» የሚላቸው ሰዎች ባሉበት ቦታ በጥንቃቄ ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ እነዚህ መገለጦች ሰውየው ብቻውን ሲሆን ወይም ይህን የመንፈስ መገለጥ ከሚረዱ ሌሎች አማኞች ባሉበት ቦታ ጥቅም ላይ መዋል ይችላሉ፡፡ ነገሩ አንድ ሰው በቅርቡ ባወቃቸው ሰዎች ፊት ሳይሆን፣ ከቤተ ሰቡ ጋር በሚሆንበት ጊዜ ብቻ የሚያደርገውን ጭውውት ወይም ውይይት ይመስላል (ለበለጠ ማብራሪያ 1 ቆሮንቶስ 14፥22-25 ይመ)፡፡

1 ቆሮንቶስ 14፥2 ላይ ጳውሎስ ስለ እነዚህ ልሳኖች ሲናገር፣ «የግል» መሆናቸውን በሚያመለክት ሁኔታ እንደጠራቸው ልብ አድርጉ፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን፣ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ወገኖች የጠበቀ መቀራረብ ትክክለኛ ጊዜንና ቦታን እንደሚጠይቅ ባለ መገንዘብ ይህን ድንቅ የግል ቋንቋ በተሳሳተ መንገድ መረዳታቸው ወይም ሙሉ በሙሉ ችላ ማለታቸው ነው፡፡

በትዳር ጓደኛሞች መካከል መቀራረብ እንዲኖር ከተፈለገ፣ ጊዜና ቦታ ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡ ይህ ማለት ከመጋባታቸው በፊት ያለው ጊዜ ማለት ነውን? አይደለም፡፡ ቦታ ሲባል ሕዝብ ባለበት ቦታ ማለት ነውን? በፍጹም አይደለም፡፡ አንድ ቦታ ላይ በጣም ውብና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነው ነገር፣ ሌላ ቦታ ተገቢና ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡ በግብረ ሥጋ ጊዜ የሚኖረው መቀራረብ ግላዊ እንዲሆን የእግዚአብሔር ሐሳብ ነው፤ ይህም የትዳር ቃል ኪዳን ከተደረገ በኃላ ብቻ ነው መደረግ ያለበት፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ አንዳንድ የልሳን ዓይነቶች በግል በሚኖረን የጸሎት ጊዜ ብቻ ነው ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው፤ ምክንያቱም የታቀደላቸው ዓላማ ጥብቅ መቀራረብ ባለበት ጊዜና ቦታ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ነው፡፡ እንደ አካላዊ መቀራረብ ሁሉ፣ ተገቢ የሆነ መንፈሳዊ ቅርርብም የተለየ ጊዜና ቦታ ይፈልጋል፡፡ የሰው ልጅ እግዚአብሔር ካቀደለት ዓላማ ውጪ ስለ ተጠቀመበት ብቻ፣ ክርስቲያኖች የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ መታቀብ አለባቸውን? በፍጹም የለባቸወም! በተመሳሳይ መንገድ የልሳን ስጦታን አቅልለን ማየት ወይም ችላ ማለት የለብንም፡፡

አንዳንድ የልሳን ስጦታ ገጽታዎች በተሳሳተ መንገድ ጥቅም ላይ ሲውሉ

በቤተ ክርስቲያን ያሉ ብዙዎች መታዘባቸውን አውቃለሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ሰዎች በልሳን ስጦታ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ስለ ተጠቀመበት ብቻ፣ ስለዚህ ስጦታ ለክርስቶስ አካል ከማስተማር ወደ ኃላ ማለት አይኖርብንም፡ ፡ በዚህ ምዕራፍ የሰማያዊ ቋንቋችንን ግላዊ ወይም ቅርርብ የሚፈልግ ባሕርይ መመርመርና በሕይወታችን ያለውን ዓላማና ፋይዳ በበለጠ መረዳት እንድትችሉ እናንተን ማገዝ የፈለግሁት በዚህ ምክንያት ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ የእውነት መንፈስ መሆኑን አስታውሱ፡፡ ለእግዚአብሔር ቃል ጥበብ ራሳችሁን ስታስገዙ፣ መንፈስ እውነቱን ይገልጥላችኋል፡፡ እስቲ ጥቂት ቆም በሉና እንዲህ ያለውን ከእርሱ የመማር ጊዜ እንዲሰጣችሁ ጋብዙት፡ ፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ማንኛውንም ቀድሞ የነበራችሁን የተሳሳተ ሐሳብና እምነት ከአእምሮአችሁ እንዲያስወግድ ለምኑት፡፡ የእርሱን ወሰን የለሽ ታላቅነት፣ ውሱን በሆነው አእምሮአችሁ መረዳትና መገደብ የምትሞክሩ ከሆነ፣ በፍጹም የእግዚአብሔርን ሙላት አትለማመዱም፡፡

## ፕሬዚዴንቱና ንጉሡ

እንደ አንድ አሜሪካዊ ዜጋ ከፕሬዚዴንታችን ጋር አብሬ ራት እንድበላ ብጋበዝ፣ ያ ለእኔ ታላቅ ክብር ነው የሚሆነው፡፡ ፕሬዚዴንታችን በዓለም ውስጥ ካሉ በጣም ዐዋቂና ኃያል ሰዎች አንዱ ነው፡፡ በእርሱ ዕዝ ሥር ያሉ ብዙ ምንጮች በመኖራቸው እርሱ ፈልጎ የሚያጣው ምንም ዓይነት መረጃ የለም፤ ቢኖር እንኳ በጣም ጥቂት ነው፡፡ የፕሬዚዴንቱ ዕውቀት እኔ ካለኝ ዕውቀት እጅግ የላቀ ነው፣ እርሱ ጠቅላይ አዛዥ ሲሆን፣ እኔ ደግሞ የመንግሥት ሥልጣን የሌለኝ አንድ የሀገሪቱ ዜጋ ነኝ፡፡ ስለሆነም፣ ሀገራችንን ስለሚመለከቱ ጉዳዮች ከእርሱ ጋር የምነጋገር ከሆነ፣ ፕሬዚዴንቱ በእኔ መረዳት ችሎታ መጠን ሊያናግረኝ ይገባል፡፡ እንደዚያ ካላደረገ ከእርሱ ጋር መግባባት አልችልም፤ ውጤታማ ግንኙነት ዕኩል ቦታ መሆንን ይጠይቃል፡

በተመሳሳይ መንገድ፣ ከአጽናፈ ዓለሙ ንጉሥ ጋር ግንኙነት ሳደርግ፣ እርሱ ካለበት ከፍታ አንጻር ከእርሱ ጋር መግባባት የምችልበት ምንም መንገድ የለም፡፡ የአሜሪካ ፕሬዚዴንት ሀገራችን ስላለችበት ሁኔታ በጣም ብዙ ያውቃል፤ እግዚአብሔር ግን ሁሉንም ያውቃል፡፡ ከእርሱ የሚደበቅ

ነገር የለም፡፡ በራሴ መረዳት ችሎታ መጠን ወደ እግዚአብሔር ስጸልይ፣ በማየውና በማውቀው ልክ እወሰናለሁ፡፡ እግዚአብሔር ግን ልጆቹ በዚህ ውሱን የመቀራረብ መጠን ብቻ ከእርሱ ጋር እንዲገናኙ አልፈለገም፡፡ ስለሆነም እርሱ ባለበት ደረጃ መጠን ከእርሱ ጋር መገናኘት የምንችልበትን መንገድ አዘጋጀ፡ ፡ ያን ያደረገው የእርሱ መንፈስ በሚሰጠን ስጦታ አማካይነት ነው፡፡ ነገሩን ልብ አድርገን ስንመለከተው እግዚአብሔር፣ «ከእኔ ዕውቀት፣ መረዳትና ጥበብ እጅግ በጣም ዝቅ ባለ ሁኔታ ብቻ ልጆቼ ከእኔ ጋር እንዲገናኙ አልፈልግም፡ ፡ ከእኔ ጋር ጥልቅ ኅብረት የማድረግ ችሎታ እንዲኖራቸው እፈልጋለሁ፡፡ ስለሆነም፣ ለልጆቼ ረዳት - መንፈሴ እሰጣቸዋለሁ» በማለት ያሰበ ይመስላል፡ ፡ የመንፈስ ቅዱስ መገኘትና ከእኛ ጋር ተራክቦ ማድረግ ከፈጣሪ ጋር ጥልቅ ግንኙነት ማድረግን እንድንለማመድ ያስችለናል፡፡

የእግዚአብሔር ፈቃድና መንገድ ውሱን ከሆነው አእምሮአችን እጅግ ይልቃል - በመንፈስ በምንጸልይበት ጊዜ ግን በእኛ መረዳት ደረጃ ብቻ አይሆንም፡፡ ይልቁንም የምንጸልየው እንደ መንፈሱ ፈቃድ ይሆናል፡፡ ይህን ተረዳችሁ? *በመንፈስ ስንጸልይ፣ እንደ እግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ እንጸልያለን!*

## የውጊያ ቋንቋ

> ተጋድሎአችን ከሥጋና ከደም ጋር ሳይሆን፣ ከዚህ ከጨለማ ዓለም ገዦች፣ ከሥልጣናትና ከኃይላት እንዲሁም በሰማያዊ ስፍራ ካሉ ከርኩሳን መናፍስት ሰራዊት ጋር ነው፡፡ (ኤፌሶን 6፥12)

ሰይጣን እኛ ላይ በግልጽ ጦርነት ያወጀ መሆኑን አንዳንዴ በቀላሉ እንዘነጋለን፡፡ ምንጊዜም ቢሆን እርሱ የሚጠቀምበት ዘዴ የሕይወታችን ምንጭ ከሆነው ፈጣሪ እኛን መለየት ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን የጠላትን ተንኰልና ሤራ ያውቃል፡፡ ወሰንና ገደብ በሌለው ጥበቡ ይህን የሰይጣንን ዕቅድ ከንቱ የሚያደርግበት አንድ ስውር አሠራር አዘጋጀ፡፡ 1 ቆሮንቶስ 2፥7-8 ላይ ጳውሎስ ይህን እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፤ «ነገር ግን ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔርን ምስጢር ጥበብ ነው፤ ይህም ጥበብ እግዚአብሔር ከዘመናት

በፊት ለክብራችን አስቀድሞ የወሰነው ነው፡፡ ከዚህ ዓለም ገገሮች አንዳቸውም ይህን ጥበብ አልተረዱም፤ ቢረዱትማ ኖሮ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉት ነበር፡ ፡›› የመስቀሉን ኃይል ጳውሎስ፣ ‹‹ተሰውሮ የነበረ››፣ ኢየሱስ ሞቶ ከተነሣ በኋላ ግን፣ ‹‹ግልጽ የሆነ ምስጢር›› በማለት ይገልጸዋል፡፡ ኢየሱስ መስቀል ላይ መሥዋዕት መሆኑ፣ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረት ማድረግ ለእኛ የሚቻል አድርጎታል - በዚህ መንገድ እግዚአብሔር ከጥንት የነበረውን የጠላትን ዕቅድ አፈረሰ፡፡

እግዚአብሔር ለመስቀሉ ያለው ዕቅድ ከዚህ ዘመን ገገሮች የተሰወረ ምስጢር እንዲሆን ብቻ አይደለም፡፡ በመንፈሱ የሚገለጡና ተለይተው የሚታወቁ አያሌ የእግዚአብሔር ጥበብ (የቃሉ) ገጽታዎችም አሉ፡፡ እንደ አማኞች ከመንፈስ ጋር በሚኖረን ግንኙነት አማካይነት፣ እነዚህን ምስጢሮች የመረዳት መብትም ተሰጥቶናል፡፡ ቀደም ሲል በዚህ መጽሐፍ እንዳነሣሁት፣ እግዚአብሔር እኛን፣ ‹‹በማዳን›› ብቻ አላቆመም፡፡ በክርስቶስ ውስጥ ስፍራ እንዲኖረን አድርጎአል፤ ለዘመናት ነፍሳችንን ሲያሰቃይ በነበረው ጠላትም ላይ ሥልጣንና ኃይል ሰጥቶናል፡፡ አሁን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ወራሾችና ተዋጊዎች አድርጎናል፤ ዓላማችን የክርስቶስን ዓላማ ማስፋፋት ነው፡፡ በገዛ ራሱ ጥበብ እግዚአብሔር ለእርሱ ዓላማ ለምንዋጋው ለእኛ ፍጹም ፈቃዱን የሚያሳውቅበት ረቂቅ የግንኙነት መስመር ዘርግቶአል፡፡

ጦርነት ውስጥ ያሉ ወታደሮች ውጤት ባለው መንገድ ዕቅድና መረጃዎችን የሚለዋወጡበት፣ ‹‹ቋንቋ›› ያበጃሉ፡፡ ጠላት መረዳት በማይችለው ፍሪኪዌንሲ ግንኙነት ማድረግ እንዲያስችላቸው ውስብስብና ረቂቅ ኮዶችን ያዘጋጃሉ፡፡ እንዲህ የሚያደርጉት ለምንድነው? ሕይወትን ከአደጋ ለመጠበቅና፣ ዕቅዶችን ተግባር ላይ ለማዋል፣ በምስጢር መንቀሳቀስ እጅግ ወሳኝ ነገር በመሆኑ ነው፡፡ ጠላት ዕቅዳቸውን ካወቀ፣ ሌላ ዕቅድ ያወጣና መረጃ ላይ የተመሠረተ ጥቃት ይሰነዝራል፡፡ እንደ እግዚአብሔር ልጆች በመንፈስ አማካይነት፣ ሰማያዊ የምስጢር ፍሪኩዌንሲ ተሰጥቶናል፤ ይህም አዛዦችን ለጠላት ያለውን ዕቅድ እንዳያውቅ በማድረግ የእግዚአብሔርን ምስጢር ተግባር ላይ ለማዋል ይረዳናል፡፡ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡፡

በጸሎትና በልመና ሁሉ፣ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤

ይህንም በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ (ኤፌሶን 6÷18)።

እንድንጸልይ ሲያዝዘን እግዚአብሔርን በቂ ምክንያት አለው። በዚህ ምድር የእርሱ ተዋጊዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ የጨለማ ኃይላትን የምንዋጋ የእርሱ ሰራዊት ነን። ጠላትን ከምናጠቃበት እጅግ ብርቱ መሣሪያዎች አንዱ በመንፈስ መጸለይ ነው። ከእግዚአብሔር አሠራር በስተ ጀርባ ያለው ዕቅድና ዓላማውን ጠላት እንዳያውቅ ያደርጋል።

አንዳንዴ አንዲት እናት ለልጇ እንድትጸለይ እግዚአብሔር ልቧን ይቀሰቅሳል። ያቺ እናት ልጇ ላይ ምን እየሆነ እንደ ነበር ላታውቅ ትችላለች፤ መንፈስ ሐሳቡን ልቧ ውስጥ ስላደረገ ግን፣ መጸለይ እንዳለባት ታውቃለች። በተሰጣት ሰማያዊ ቋንቋ ስትማልድ፣ በመንፈሳዊው ክልል ትእዛዝ ትሰጣለች፤ እግዚአብሔር ለልጇ ባለው ፍጹም ፈቃዱ መሠረትም ትጸልያለች። «ምክር ጠይቀህ ዕቅድ አውጣ፤ ጦርነት የምትገጥም ከሆነ መመሪያ ተቀበል» ተብሎ የተነገረን በዚህ ምንክያት ነው። (ምሳሌ 20÷18)።

ሰማያዊ ቋንቋችን ከእኛ መረዳት በላይ ነው፤ በጊዜና በስፍራም አይወሰንም። በመንፈስ ስንጸልይ፣ የምንደገፈው በእኛ መረዳት ችሎታ ሳይሆን፣ እጅግ ሰፊ በሆነ በእርሱ ዘላለማዊ ጥበብ ነው። «ሁላችሁም በልሳን ብትናገሩ እወዳለሁ» በማለት ጳውሎስ ከጻፈበት ብዙ ምክንያቶች አንዱ ይኸው ነው።

ሰማያዊ ቋንቋችንን ጠላት ሰንጥቆ መግባት አይችልም፤ ምክንያቱም ይህ በእግዚአብሔርና በልጆቹ መካከል ያለ እጅግ ጥብቅ የሆነ ልውውጥ ነው፤ ስለሆነም በእኛና በሌሎች አማኝ ወገኖቻችን ላይ ጠላት ያዘጋጀውን ተንኰልና ሤራ በማፍረስ ረገድ እጅግ ውጤታማ ነው።

እንግዲህ… በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ። (ሉቃስ 10÷19)

እኛ አማኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት በዚህ ምድር እንድናስፋፋ በሚያስፈልገው ትጥቅ ሁሉ ታጥቀናል (ማቴዎስ 11÷12 ይመ.)። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ምድር ያለች የክርስቶስ አካል ናት። ቀደም ሲል

በተመለከትነው መሠረት፣ ከእንግዲህ ክርስቶስ በአካል በዚህ ምድር እየኖረ አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር እንደራሴዎችና ተዋጊዎች እኛ ነን፤ መታደስ፣ ነጻነትና ድነት ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ የእርሱን ለዋጭ ኃይል የምናስፈጽም ነን፡፡ ይሁን እንጂ፣ የመንፈሱን ኃይል ካልተቀበልን በስተቀር፣ እየጠፋና እየሞተ ላለው ዓለም፣ በፍጹም ውጤታማ የክርስቶስ አካል መሆን አንችልም፡ ፡ ሰይጣንና ሰራዊቱ እኔና እናንተን የሚፈሩበት ምንም ምክንያት አይኖርም፤ እንደ ልዑል አምላክ ወንዶችና ሴቶች ልጆች በክርስቶስ ውስጥ ያሉትንና በእርሱ ኃይል የሚጠቀሙትን ግን እጅግ ይፈራሉ፤ ይንቀጠቀጣሉ፡፡

ቀን 2

## የመቀራረብ ቋንቋ

እኔና ሚስቴ ብዙ ዘመን አብረን ከመኖራችን የተነሣ የራሳችንን ትንሽ ቋንቋ ፈጥረናል፡፡ እኔ አንድ ነገር ከተናገርኩ ከማንም ይልቅ ሚስቴ ምን ማለቴ እንደ ሆነ ትረዳለች፡፡ ሌሎች ግን ምን ማለታቸው ነው? በማለት ግራ ሊጋቡ ይችላሉ፡፡ አዎን፣ ቋንቋው ይህን ያህል የሚረባ ላይሆን ይችላል፤ ያም ሆኖ ግን እኔና ሊዛ ብቻ የምንግባባበት የራሳችን መቀራረብ ቋንቋ ሆኖአል፡፡ ይህ እርስ በርስ እንድንግባባ ከፈጠርነው ብዙ የመቀራረብ ዘዴዎች አንዱ ነው፡፡

በተመሳሳይ መንገድ፣ በሰማያዊ ቋንቋ መጸለይ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በቅርበት ለመገናኘት ያስችለናል፡፡ ምናልባት አንዳንዶች፣ ‹‹እኔ'ኮ የምጸልየውን መረዳት አልችልም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስስ ቢሆን፣ ‹‹በልሳን በምጸልይበት ጊዜ መንፈሴ ይጸልያል፤ አእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው›› ብሎ የለ ትሉኝ ይሆናል (1 ቆሮንቶስ 14፥14)? አዎን፣ እውነት ነው፡፡ ቀደም ሲል ያለው ጥቅስ፣ ‹‹በልሳን የሚናገር ሰው የሚናገረውን መተርጐም እንዲችል ይጸልይ›› የሚለው በዚህ ምክንያት ነው (ቁጥር 13)፡፡ ስጸልይ ወይም በልሳን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሳደርግ፣ የጸሎቴን ትርጉም እንዲሰጠኝ እጠይቀዋለሁ፡፡ ምን እንደሚሆን ታውቃላችሁ? ሐሳብ፣ ጥበብና መገለጥ መንፈሴ ውስጥ ይፍለቀለቃል፡፡ ይህን በጣም በተሻለ ሁኔታ ለመግለጥ ያህል፣ እነዚህ ግንዛቤዎች ጥልቁ ባሕር ውስጥ የነበሩ አየር የሞሉ ፍልቅላቂዎች ከጥልቁ ወደ ላይ የመውጣታቸውን ያህል ነው፡፡ እነዚህ ግንዛቤዎች ከጥልቁ ውስጣዊው ሰው ወደ ላይ ወደ

አእምሮዬ ወይም ወደ መረዳት ችሎታዬ ይወጣሉ፡፡

እስቲ አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ኢያነበብኩ እያለ፣ አንድ መረዳት ያቃተኝ ቃል ሲገጥመኝ፣ «መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ አስተምረኝ» በማለት እጸልያለሁ፡፡ ከዚያ በልሳን መጸለይ እጀምራለሁ፡፡ የምፈልገው መገለጥ ወዲያውኑ ላይመጣ ይችላል፤ ብዙ ጊዜ ግን እየነዳሁ፣ ገላዬን እየታጠብሁ፣ ዘና ብዬ እያለሁ ወይም እየተጨዋወትሁ እያለና የመሳሰሉትን እያደረግሁ እያለ የጠየቅሁት መገለጥ ሊመጣ ይችላል፡፡ ያ ሲሆን፣ በድንገት ይበራልኛል! ይህ መገለጥ ከመንፈስ ጋር ተቀራርቦ የመኖር ውጤት ነው — መረዳት እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት፤ እርሱም የጠየቅሁትን ሰጠኝ፡፡ እግዚአብሔር ምስጢሮቹን ለትሑታን ማለትም የመንፈሱን ምሪት ለሚጠይቁ ይገልጣል፤ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ቅርርብ እንለማመዳለን፤ የበለጠውን ትልቅ መንፈሳዊ መገለጥም እንቀበላለን፡፡

መንፈሳዊ ኃይልን በተመለከተም ይኸው ነው፡፡ ጳውሎስ በቀጥታ ከእግዚአብሔር መንፈስ የተቀበለውን እንዲህ በማለት ጽፎአል፡፡

> «ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ ፍጹም የሚሆነው በድካም ጊዜ ነውና» አለኝ፡፡ ስለዚህ የክርስቶስ ኃይል በእኔ ያድር ዘንድ፣ ይበልጥ ደስ እያለኝ በድካሜ እመካለሁ (2 ቆሮንቶስ 12፥9)፡፡

ትሑት ለሆኑት የእግዚአብሔር ጸጋ፣ ማለትም የእግዚአብሔር ኃይል ይሰጣቸዋል (እዚህ ላይ ጳውሎስ ኃይልን፣ «ድካምን» ከመገንዘብ ጋር አያይዞታል)፡፡ ገደብና ወሰን ለሌለው የመንፈስ ጥበብ ራሳችሁን በመስጠት ራሳችሁን ትሑት ስታደርጉ፣ የበለጠ ታላቅ የእግዚአብሔር ኃይል ያርፍባችኋል፡ ፡ ይህም ቢሆን፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተቀራርቦ የመኖር ውጤት ነው፡፡

ባሕልና ልምዳችን ውጤት ተኮር ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከምናደርገው ጥረት፣ ወይም ገንዘብና ጉልበታችንን ካዋልንበት ነገር፣ ወዲያውኑ ውጤት ካላየን፣ በቀላሉ ተስፋ እንቆርጣለን፡፡ አንድ መረዳት ያለብን ነገር በመንፈስ ስንጸልይ ለወደ ፊት ጥሪት እያኖርን መሆኑን ነው፡፡ አንዳንዴ ብዙም ሳይቆይ መገለጡ ተፍለቅልቆ ወዲያውኑ ወደ መረዳት ችሎታችን ሊመጣ ይችላል፡፡ በመንፈስ መጸለይ እምነትን ይጠይቃል፤ ምክንያቱም የሚጀምረው የእኛ ተፈጥሮአዊ

የመረዳት ችሎታ ከሚያበቃበት ቦታ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ልምምድ እምነታችንን ያሳድጋል፤ የእግዚአብሔርን ጥበብ የመረዳት ችሎታችንን ይጨምራል፡፡

## በአእምሮ መጸለይ

የዚህ ምዕራፍ ትኩረት በመንፈስ መጸለይ ቢሆንም፣ በአእምሮ መጸለይም እጅግ በጣም ጠቃሚ መሆኑንም መዘንጋት የለብንም፡፡ በመንፈስም ሆነ በአእምሮ መጸለይ እንዳለብን ጳውሎስ ግልጽ አድርጎአል፡፡

> በመንፈስ እጸልያለሁ፤ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፣ በመንፈስ እዘምራለሁ፤ በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ (1 ቆሮንቶስ 14፥15)፡፡

በአእምሮ በምጸልይበት ጊዜ በቀጥታ አእምሮዬን ያንጻል፡፡ ስሜትና ፍላጎቴን ያነቃቃል፡፡ ከምጸልይላቸው ሰዎች ጋር ያያይዘኛል፤ እየጸለይኩ ያለሁት ለሚስቴ፣ ለልጆቼ፣ ለጓደኞቼ፣ ለሥራ ባልደረቦቼ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ በአእምሮዬ በምናገርበት ጊዜ መረዳት በምችለው ቃል የአባቴን ታላቅነት ዐውጃለሁ፤ በምስጋናና በውዳሴ እሞላለሁ፡፡

መንፈስ በሚሰጠኝ ምሪት መሠረት በአእምሮ የምጸልይበትም ጊዜ አለ፡ ፡ ይህ በመንፈስ የመጸለይ አንዱ መንገድ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ግን፣ በመጀመሪያ በመንፈስ እጸልያለሁ፤ ከዚያም የጸለይኩበትን ትርጉምና መረዳት እግዚአብሔር ይሰጠኛል፡፡ ይህ የመረዳት ቃል እንደ ወንዝ ከአንደበቴ ይወጣል፡፡

እየጻፍኩ ያለሁት ስለ በመንፈስ የመጸለይ ጥቅም ቢሆንም፣ በምንም ዓይነት በአእምሮ የመጸለይን አስፈላጊነት ዝቅ እያደረግሁ አይደለም፡፡ ይልቁንም አንድ ጤናማ የጸሎት ሕይወት፣ በመንፈስ መጸለይንና በአእምሮም መጸለይን እንደሚያካትት ግልጽ እያደረግሁ ነው፡፡ ሁለቱም በእግዚአብሔር ላለን ሕይወት እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡

## የሕይወት ምንጫችን

ምሳሌ 20፥27፣ ‹‹የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው፣ ውስጣዊ

ማንነቱን ይፈትሻል›› ይላል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ድንቅ ነገር፣ መጀመሪያ የሚበራውና የሚገለጠው መንፈሳችን ውስጥ እንጂ አእምሮአችን ውስጥ አይደለም፡፡ በመንፈስ ስንጸልይ ትርጉሙንም እንዲሰጠን ማመንና መጠይቅ ያለብንም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳችን የሚሰጠን መገለጥ፣ የእርሱን ሐሳብ ወደ አእምሮአችን ወይም ወደ መረዳት ችሎታችን ይመጣል፡፡

ምሳሌ 20፥5፣ ‹‹የሰው ልብ ሐሳብ እንደ ጥልቅ ውሃ ነው፤ አስተዋይ ሰው ግን ከዚያ ቀድቶ ያወጣዋል›› ይላል፡፡ በመስቀሉ ኃይል እግዚአብሔር አዲስ ልብ ሰጥቶናል (ሕዝቅኤል 36፥26)፡፡ አዲስ ከሆነ ልባችን ጥልቅ ምክር (መንፈስ ቅዱስ መካሪ ተብሏል) እንቀዳለን፡፡ ዮሐንስ 7፥38-39 ላይ ኢየሱስ የተናገረው ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

> በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል፡፡ ይህን ያለው በእርሱ የሚያምኑ ስለሚቀበሉት መንፈስ ነበር፡፡ ምክንያቱም ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ አልተሰጠም ነበር፡፡

> ይህ ጥቅስ ኢሳይያስ 12፥3 ላይ ያለውን ወደ አእምሮአችን ያመጣል፣

> ከድነቴ (የሕይወት) ምንጮች ውሃ በደስታ ትቀዳላችሁ!

ከልባችን እንደሚፈልቅ ኢየሱስ የተናገረለት፣ ‹‹የሕይወት ውሃ›› - ‹‹መንፈስ›› መሆኑን ዮሐንስ በግልጽ አመልክቷል፡፡ ኢየሱስ መንፈስን ከውሃ ጋር ያመሳሰለው ለምንድነው? ውሃ ሕይወትና ኃይል ይሰጣል፤ ያለ እርሱ ሕይወት በምድር መኖሩ ይቋረጣል፡፡ ኢየሱስ መንፈስን፣ ‹‹የሕይወት ውሃ›› በማለት የጠራው እርሱ ለሕይወት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ለማመልከት ነበር፡፡

እግዚአብሔር፣ ‹‹ሕዝቤ ዕውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል›› አለ (ሆሴዕ 4፥6)፡፡ ስለ ምን ዓይነት ዕውቀት ነው የሚናገረው? መንገዶቹንና ዓላማውን ስለ ማወቅ ነው እግዚአብሔር ለይቶ የሚናገረው፡፡ በጣም አስደናቂው ዜና፣ የእርሱን ሐሳብ ከማወቅ በሚመጣ ሕይወት ሙላት እንድንኖር እግዚአብሔር

መንፈሱን ወደ እኛ የላከ መሆኑ ነው፡፡

የአገልግሎት ድርጅታችን ሠራተኞች መጀመሪያ የእኔን ሐሳብና ዓላማ ሳያውቁ ከእኔ ጋር አብሮ ለመሥራት እንደማይመጡ ሁሉ፣ በመጀመሪያ እርሱ ማን መሆኑን ሳናውቅ፣ እግዚአብሔርንም ማገልገል አይቻልም፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብና ሰፋ ያለ ጊዜ በጸሎት ስናሳልፍ፣ መንፈስ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ ይህ ደስተኛ ሕይወት ለመኖር የሚያስፈልግ ኃይል ሙላት ነው፡፡ ነህምያ 8፥10፣ «የእግዚአብሔር ደስታ ብርታታችሁ ነው» ይላል፡፡ በሌላ አነጋገር በእርሱ ደስ ስንሰኝ (ከመንፈሱ የሚመጣውን መታደስ ስንለማመድ)፣ ፊት ለፊታችን ላለው የሚያስፈልገንን ብርታት ሁሉ ይሰጠናል፡፡ የእናንተን ባላውቅም፣ በበኩሌ ግን በእርሱ ደስ ከመሰኘት ውጪ አንድ ቀን እንኳ ማሳለፍ አልፈልግም፡፡

## የእግዚአብሔር ምስጢሮች

ከመጽሐፈ ምሳሌና ከዮሐንስ ወንጌል ካነበብናቸው ጥቅሶች ከልባችን ውስጥ የሚፈልቀው የሕይወት ውሃ የእግዚአብሔርን ምስጢሮች ወይም ጥበብ የሚይዝ መሆኑን እናያለን፡፡ እነዚህን ምስጢሮችና ግንዛቤዎች እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል እንደሚገልጥልን እናውቃለን፡፡ እስቲ 1 ቆሮንቶስ 2፥7 ላይ ጳውሎስ የሚናገረውን እንመልከት - «የእግዚአብሔርን ጥበብ በምስጢር እንናገራለን፡፡»

ምስጢር ተብሎ የተተረጐመው ግሪክኛ ቃል፣ «ምስጢራዊ» ወይም «ግራ አጋቢ» ማለት ሳይሆን «ስውር ወይም በሚገባ ያልተገለጠ»[1] ማለት ነው፡፡

እስቲ በዚህ መንገድ እንየው፤ አንድ ጥሩ ሬስቶራንት ውስጥ ናችሁ እንበል፡፡ አስተናጋጁ ወደ እናንተ ይመጣና ምርጫችሁን ይጠይቃችኋል፡ ፡ ከዚያ በእናንተ ምርጫ መሠረት ምግቡን ያዘገጃጃል፡፡ ምግቡ ሲደርስ አስተናጋጁ ይመጣና ዋናውን ምግቡ እፊታችሁ ያኖራል፡፡ እስቲገለጥ ድረስ ያ ምግብ እንደ ተሸፈነ ይቆያል፡፡ እፊታችሁ ያለው እናንተ ያዛችሁት ምግብ እንደ ሆነ ብታውቁም፣ ሙሉ በሙሉ ተገልጦ ስላላያችሁ በተወሰነ መልኩ ቢሆን እንኳ፣ ምስጢር ነው ማለት ይቻላል፡፡

ትክክለኛው ጊዜ ሲደርስ አስተናጋጁ፣ «መልካም ምግብ!» ይልና ሽፋኑን

ከምግቡ ላይ ያነሣዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ወጥ ቤቱ ያዘጋጀውን ምግብ በግልጥ ማየት ትችላላችሁ፡፡ ሽፋኑ እስኪነሣና በዐይናችሁ እስክታዩት ድረስ ምግቡ አልነበረም ማለት አይደለም፤ እናንተ በዓይናችሁ ባታዩት እንኳ ምግቡ እዚያ ነበር፡፡ አስተናጋጁ ምስጢር የነበረውን ገለጠ ማለት ይቻላል፡፡ ከመሸፈኛው ሥር የነበረው ምግብ ሁሌም ለወጥ ቤቱ የታወቀ ቢሆንም፣ እስኪገለጥ ድረስ ለእናንተ የተሰወረ ነበር፡፡

በመንፈሱ አማካይነት እግዚአብሔር ተሰውሮ ከነበረው ዕቅዱ - ማለትም ከምስጢሩ መሸፈኛውን ያነሣል፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ካለን ቅርርብ የተነሣ አሁን፣

> …ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔርን ምስጢር እንናገራለን… ይህም እግዚአብሔር በነጻ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ ነው፡፡ እኛ የምንናገረው ይህን ነው፤ ከሰው ጥበብ በተማርነው ቃል ሳይሆን፣ ከመንፈስ በተማርነው ቃል እንናገራለን፤ መንፈሳዊ እውነትንም የምንገልጸው በመንፈሳዊ ቃል ነው (1 ቆሮንቶስ 2፥7፣ 12-13)፡፡

በኋላ ላይ ደግሞ ጳውሎስ በዚሁ መልእክት፣ «በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርምና ምስጢር የሆነውን በመንፈስ ስለሚናገር የሚረዳው የለምና» በማለት ጽፎአል (1 ቆሮንቶስ 14፥2)፡፡ ተጓዳኝነቱን አያችሁ? በልሳን በምንናገርበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ምስጢር እየተናገርን ነው፡፡ እነዚህ ምስጢሮች በጥልቅ ልቦናችን ውስጥ ተደብቀው የነበሩ መሆናቸውንና (ምሳሌ 20፥5 ይመ.) የመንፈስ ጥበብ ሕያው ውሃ ከውስጣችን ሲፈልቅ እንደሚቀዱ በሚገባ እናውቃለን (ዮሐንስ 7፥38-39 ይመ.)፡፡ ስለሆነም በልሳን መጸለይ፣ የራሱ የመንፈስን ጥልቅ ምክር መረዳት እንድንችል፣ በእኛ ውስጥ ካለው «የሕይወት ውሃ ምንጭ» ስለሚቀዳ እኛን ያንጸናል!

ቀደም ሲል እንደ ተናገርኩት፣ ከእኔ መረዳት ችሎታ በላይ የሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች አጋጥመውኝ ነበር፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ፣ በመንፈስ እጸልያለሁ፤ ያኔ መረዳት ይመጣል፡፡ ብዙ ጊዜ መጽሐፍ እያዘጋጀሁ እያለ በድንገት ነገሩ ሁሉ ይደርቅብኛል፤ እንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ስሆን ምንም

ማድረግ እንደማልችል ነው የሚሰማኝ፡፡ ያኔ ካለሁበት ቦታ ተነሥቼ በልሳን እጸልያለሁ፡፡ እንዲህ በማደርግበት ጊዜ ብዙ ጊዜ ራሴን እጅግ ድንቅ መገለጥ ውስጥ አገኘዋለሁ፡፡ ታዲያ፣ በዚያ ጊዜ የሚሆነው ምንድነው? የእግዚአብሔር መንፈስ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከልቤ ይፈስሳል!

ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢ ቅርርብ ከሌላችሁ፣ አንዳንድ ምስጢሮች ከተፈጥአዊ አእምሮአችሁ እንደ ተሰወሩ ይቀራሉ፡፡ እነዚህ ምስጢሮች ወደ የትኛው ቤተ ክርስቲያን መሄድ እንዳለባችሁ፣ ማንን ማግባት እንዳለባችሁ፣ የትኛውን ሥራ መምረጥ እንዳለባችሁ፣ የትኛውን ቤት መግዛት እንዳለባችሁ፣ ለመሪዎቻችሁ እንዴት መጸለይ እንዳለባችሁ፣ እንዴት ጥሩ ባል ወይም ጥሩ ሚስት መሆን እንደምትችሉ፣ ከልጆቻችሁ ከአንዱ ጋር ያጋጠማችሁን ተግዳሮት እንዴት መፍታት እንደሚገባችሁ፣ በምትሠሩት ሥራ እንዴት ልቃችሁ መገኘት እንደምትችሉና የመሳሰሉትን የሚያካትቱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በራሳችን መረዳት ችሎታ ብቻ እንድንወጣው እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ለእኛ አለመተው ደስ አይላችሁም? እርሱ ቃል የገባለትን ሰላም መለማመድ እንድንችል ለሕይወታችን ያለውን ዕቅድ (የተሻለ የሆነውን)፣ በመንፈስ በኩል መረዳት እንችላለን፡፡

ቀን 3

## ሰላም - የመቀራረብ ስጦታ

ሰላም የመንፈስ ቅዱስ መገኘትና በሕይወታችን ስምምነት ለመኖሩ ማስረጃ እንደ ሆነ ገላትያ 5 ይነግረናል፡፡ ይህ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ብዙ ተግባራዊ ገጽታዎች ያሉት አስደናቂ በረከት ነው፡፡

ወንደላጤ በነበርኩ ጊዜ ወደ ፊት የማገባትን ሴት በተመለከተ ለእኔ ምስጢር ነበር፡፡ በዚያ ዘመን ሊዛ ቶስካኖ ከምትባል ሴት ጋር እቀራረብ ነበር፡፡ ከልቤ እንደምወዳት አውቅ ነበር፡፡ ሰብዕናዋን እወደዋለሁ፤ ወደ እርሷ እየተሳብኩም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ማግባት ያለብኝ፣ ለእኔ ደስ ያለችኝን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለእኔ የመረጣትን ልጃገረድ ብቻ እንዲሆን ወስኜ ነበር፡፡ ሊዛ የምትኖረው በአሪዞና ሲሆን፣ እኔ ደግሞ በቴክሳስ ነበር የምኖረው፡፡ የወደ ፊት ግንኙነታችንን በተመለከተ፣ ሁለታችንም የእግዚአብሔርን ምሪት

እየጠየቅን ነበር፡፡ ስለዚህም፣ «ከዛሬ ጀምሮ ለሚቀጥለው ሰላሣ ቀን በየቀኑ ለሰላሣ ደቂቃ በመንፈስ እንጸልይ፤ ልባችንን እናዳምጥ፡፡ አንድ ዐይነት ሁከት ወይም ሰላም ማጣት የሚሰማን ከሆነ፣ ግንኙነታችን ርቆ መሄድ እንደሌለበት እግዚአብሔር እየነገረን ነው ማለት ነው፡፡ ሰላም የሚሰማን ከሆነ ግን ግንኙነታችን በተመለከተ ቀጣይ እርምጃ መውሰድ እንዳለብን መንፈስ ቅዱስ እየተናገረን ነው» በማለት ለሊዛ ነገርኳት፡፡ በዚህ ሁኔታ እየጸለይን እያለ ሁለታችንም በየግላችን ሰላም ልባችንን ይሞላው ነበር፤ የወደ ፊቱን በታላቅ ተስፋ የመጠበቅ ደስታም ነበረን፡፡ በእነዚያ ሰላሣ ቀኖች ውስጥ ስንጸልይ የተሰማንን በኋላ ላይ በግልጽ ስንነጋገር ሁለታችንም ተመሳሳይ ዓይነት ልምምድ እንደ ነበረን ተረዳን፡፡ መቀራረባችን እያደገ ሄዶ፣ መጨረሻ ላይ ተጋባን፡፡ አሁን ከተጋባን ከሰላሣ ዓመት በላይ ሆኖአል፤ ሁለታችንም ያንን ሰላም በመለማመዳችን በጣም አመስጋኝ ነኝ!

ሮሜ 8÷14፣ «በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና» ይላል፡፡ ምንባቡ በመቀጠል፣ መንፈስ እንዴት የእግዚአብሔርን ልጆች እንደሚመራ ይገልጻል፤ «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል» (8÷16)፡፡ መንፈስ እኛን የሚመራበት ዋናው መንገድ - በሰላሙ ወይም በምስክርነቱ ነው፡፡

ትክክለኛና ምክንያታዊ የሚመስል፣ ሆኖም፣ ስለዚያ ባሰባችሁ ጊዜ ሁሉ ምቾት የማይሰጣችሁ ማድረግ የምትፈልጉት ነገር አለ? ምናልባትም - ችግሩ ምንድነው? ማድረግ የወሰንኩትን በተመለከተ ነገሮች ሁሉ ትክክል ይመስላሉ ታዲያ፣ እንዲህ የሚሰማኝ ለምንድነው? በማለት እየጠየቃችሁ ይሆናል፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ያላችሁ ከሆነ፣ ያ ምቾት የማይሰጥ ስሜት፣ «በዚያ አቅጣጫ አትሂዱ» በማለት እርሱ ለእናንተ መናገሩ ነው፡፡ ይህን ብዙ ጊዜ ተለማምጃለሁ፡፡ አንዳንዴ ዓመቶች እስኪያልፉ ድረስ የመንፈስን ምሪት ለመከተል ያደረግሁት ውሳኔ ያን ያህል ትርጉም ላይሰጥ ይችላል፡፡ ሆኖም፣ በእንዲህ ያሉ ሁኔታዎችም ውስጥ በእርሱ መተማመንን ተምሬአለሁ፡ ፡ የእርሱ ጥበብ በጊዜና በቦታ የሚወሰን አለመሆኑን አስታውሱ፤ ይህም ማለት በአሁኑ ሕይወታችሁ እየመራችሁ እያለ፣ የወደ ፊት ሕይወታችሁንም ግምት ውስጥ ያስገባል ማለት ነው፡፡

> አንዳንዴ ደግሞ ያደረግሁት ውሳኔ ከባድ አደጋ ያጠላበት ቢመስል እንኳ፣ ታላቅ ሰላም የሚሰማኝ ጊዜ አለ፡፡ ያ የክርስቶስ ሰላም ልቤን ሲሞላ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚለውን ስሙ፤ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ፤ የምታመሰግኑም ሁኑ (ቈላስይስ 3፥15)፡፡

አምፕሊፋይድ የተሰኘው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መንፈስ ቅዱስን፣ ከአንድ ስፖርት ዳኛ ጋር ያመሳስለዋል፡፡ አንድ ጥሩ ዳኛ ድጋሚ ማውጣትና ማውረድ ሳያስፈልገው ውሳኔ ያሳልፋል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ መንፈስ ቅዱስም አእምሮአችሁ ውስጥ ለሚነሡ ጥያቄዎች ሁሉ (ውሳኔዎችና የሚያሳስቡዋችሁ ነገሮች) የማያዳግም ብያኔ ይሰጣል፡፡ እርሱ እንዲወስን ከፈቀዳችሁለት፣ የእርሱ የራሱን ጥበብ ያካፍላችኋል፡፡ ብዙ ጊዜ የእርሱ፣ «ጥሪ» የሚመጣው ከሰው አእምሮ በላይ በሆነ ሰላም ውስጥ ነው፤ ይህ የመንፈስ ምስክርነት ነው፡ ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡፡

> ከማስተዋል በላይ የሆነው የእግዚአብሔር ሰላም፣ ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል (ፊልጵስዩስ 4፥7)፡፡

በክርስቶስ ውስጥ ስፍራ ተሰጥቶናል፤ ያም ማለት፣ ዓለም ወደማያውቀው ሰላም የመግባት መብት አለን ማለት ነው፡፡ ኢየሱስ የሰላም አለቃ ነው፤ የእርሱ የሆኑትም ሰላም እንደሚኖራቸው ቃል ተገብቶላቸዋል፡፡ ማድረግ ወደ ፈለግነው ውሳኔ መንፈስ ቅዱስን ስንጋብዘው፣ ምንጊዜም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ ሰላም ለልባችን ይመሰክርልናል፡፡

## ሰላምና - ውሳኔ ማድረግ

የሜሴንጀር ኢንተርናሽናል መሪ እንደ መሆኔ መጠን በሰላሙ ማረጋገጫነት ብዙ ውሳኔዎች አድርጌአለሁ፡፡ አንዳንዴ ጉዳዩ ጨርሶ የማይቻል ይመስል ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ ሜሴንጀር ኢንተርናሽናል ሊኖረው የሚችለውን ዐቅም በራሴ አእምሮ እንዳልገድብ የእግዚአብሔር ሰላም ጠብቆኛል፡፡

መንፈስ በግልጽ ሲናገረኝ የሰማሁበት ብዙ ጊዜዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ እየተዘጋጀሁ እያለ፣ ከዚህ በጣም የተለየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለመጻፍ ነበር ያቀድሁት፡፡ ጾምና ጸሎት ላይ በነበርኩበት ጊዜ ግን፣ ስለ እርሱ ማንነት እንድጽፍ መንፈስ ቅዱስ መመሪያ ሰጠኝ፡፡

ቀጥተኛ መመሪያ ባልቀበል እንኳ፣ አብዛኞቹ ውሳኔዎችን ያደረግሁት በእግዚአብሔር ሰላም ተመርቼ ነበር (አብዛኛውን ጊዜ ከቃሉ ጋር በመስማማት)፡፡ ይሁን እንጂ፣ በቀጥታ የእግዚአብሔር መንፈስ የተናገረኝም ጊዜ ነበር፡፡ ብዙውን ጊዜ እንዲህ የሚሆነው፣ እግዚአብሔር ለእኔ ጨርሶ አዲስ የሆነ መመሪያ ሊሰጠኝ በሚያስብበት ጊዜ እንደ ሆነም ተረድቻለሁ፡፡ እስቲ፣ ይህን በተመለከተ ምሳሌ ልስጣችሁ፡፡

የሜሴንጀር ኢንተርናሽናል ዋናው ግብ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያንን ማነጽ ነው፡፡ ወደ ጠፉት በመድረስ፣ ችግር ላይ ላሉት ተስፋና ርዳታ በማድረግና ከሕዝቦች ሁሉ ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ረገድ፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እጅግ ውጤታማ የእግዚአብሔር ስልታዊ መንገድ መሆንዋን እናምናለን፡፡ በሰሜን አሜሪካ ከ20,000 የሚበልጡ አብያተ ክርስቲያናት እኛ ባዘጋጀነው ካሪኩለም እየተጠቀሙ ነው፡፡ ለአያሌ ዓመታት ዋናው ትኩረታችን በአሜሪካ፣ በካናዳ፣ በአውስትራሊና በኢንግላንድ ያለ አብያተ ክርስቲያናትን መድረስ ነበር፡፡

ሜይ 31,2010 ትንቢተ ዳንኤልን እያነበብኩ እያለ፣ «እንግሊዝኛ ተናጋሪ በሆነው ዓለም ያሉ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖችን በመድረስ ረገድ ታማኝ ሆነህ ተገኝተሃል፡፡ አሁን ደግሞ በዓለም ወዳሉት ሕዝቦች ሁሉ እልክሃለሁ» በማለት እግዚአብሔር ተናገረኝ፡፡ በጣም ነበር የተገረምሁት፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህ እንዴት እውን ሊሆን እንደሚችል ሐሳቡ እንኳ አልነበረኝም፡፡ ስለዚህ የአገልግሎታችን ዳይሬክተሮችን ለስብሰባ ጠራሁ፡፡ እግዚአብሔር ልቤ ውስጥ ያኖረውን ራእይ አካፈልኳቸው፤ በ2011 ለታዳጊ አገር መሪዎች 250,000 መጻሕፍት መስጠት እንደምፈልግ ነገርኳቸው፡፡ ሁሉም በጣም ደነገጡ፡፡ በአንድ ዓመት ይህን ያህል ብዛት ያለው ቀርቶ ከዚያ የሚቀራረብ መጻሕፍት እንኳ ሰጥተን አናውቅም ነበር፡፡ ዋናው የሥራ እንቅስቃሴ ሹም እና የሌሎች ክፍሎች ዳይሬክተሮች ይህን ራእይ በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎች አቀረቡልኝ፡፡ በመጨረሻም ዋናው የሥራ እንቅስቃሴ ሹም ይህን ዓላማ እንደ ገና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንዳቀርብ ጠየቀኝ፡፡

በዓለም ዙሪያ ያሉትን ፓስተሮችና መሪዎች እንድደርስ በግልጽ ከእግዚአብሔር ሰምቻለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ይህን ግብ በማሳካት ረገድ የመጀመሪያው ርምጃ በሚቀጥለው ዓመት 250,000 መጻሕፍት መስጠት እንደሚሆን እግዚአብሔር ለይቶ አልተናገረኝም፡፡ ስለሆነም፣ ይህንኑ ግብ በጸሎት ለእርሱ አቀረብኩ፡፡ እርግጥ ነው፣ ሰላሙ ልቤን እንደ ሞላ ነበር፡፡ ይህ ግብ ከእርሱ የመጀመሪያ ምሪት ጋር የተጣጣመ መሆኑን ስለማውቅ፣ መንፈስ ቅዱስ ለእኔ መናገር አልነበረበትም፡፡ በዚያ ውስጥ የእርሱ ምስክርት መኖሩ ይሰማኝ ነበር፡፡ በእርግጥም እግዚአብሔር በተአምራዊ መንገድ ተንቀሳቀሰ፤ እኛም በ47 አገሮች ላሉ ፓስተሮችና መሪዎች ከ270,000 የበለጡ መጻሕፍት መስጠት ቻልን፡፡

በ2011 ቤይሩት ሊባኖስ ካለ አንድ ኢራቃዊ ፓስተር ጋር ተገናኘቼ ነበር (በዚያ ወቅት መካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ለ2,500 ፓስተሮችና መሪዎች ንግግር እያደረግሁ ነበር)፡፡ ይህ ሰው ከተማው ውስጥ ያለ አንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መሪ ሲሆን፣ የሰላሣ ስድስት ዓመት ወጣት ነበር፡፡ «ሚስተር ቢቨሬ አንተ ለእኔ የአባት ያህል ነህ፡፡ እጄ የገቡ መጻሕፍትህን በሙሉ አንብቤአለሁ፡፡ አንዳንድ ጽሑፎች ከዌብሳይት ወስጃለሁ» አለኝ፡፡

ያንን ስሰማ እጅግ በጣም ነበር የተደነቅሁት፡፡ ይህ ጦርነት ባመሰቃቀላት ከተማ ውስጥ የሚኖር ሰው የሜሴንጀር ኢንተርናሽናልን ሥራ ውጤቶች ለማግኘት ሲል እጁ ያለውን ጥቂት ገንዘብ እንኳ ለማውጣት ወደ ኋላ አላለም፡፡ መሪዎቻቸውን በማስታጠቅ ረገድ እነዚያን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖች ለመርዳት ማድረግ ያለብኝን እንዳደርግ ጥበብ እንዲሰጠኝ እንደ ገና ወደ እግዚአብሔር ጸለይኩ፡፡ በመንፈስ ስጸልይ፣ በታዳጊ አገሮች ውስጥ ላሉ ፓስተሮች መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን ሙሉውን ካሪኩለም እንዴት መስጠት እንዳለብን ሐሳብ ተቀበልኩ፡፡ በሚቀጥለው ዓመት 1.3 ሚሊዮን መጻሕፍትና ሌሎች ጠቃሚ ነገሮች ለእነዚህ ፓስተሮችና መሪዎች ሰጠን፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ቁጥሩ በጣም እያደገ ነው፡፡

በመንፈስ እየጸለይኩ እያለ ሌላው ወደ ልቤ የመጣው ሐሳብ እነዚህ ፓስተሮችና መሪዎችም ሆኑ የሚመሩዋቸው ክርስቲያኖች በሙሉ ያለ ምንም ክፍያ በገዛ ራሳቸው ቋንቋ መጻሕፍትና ሌሎች ጠቃሚ ነገሮች መውሰድ የሚችሉበት CloudLibrary.org, ዌብሳይት ማዘጋጀት ነበር፡፡ በ2011, 270,000

ጠቃሚ ጽሑፎች መስጠት በጣም ብዙ ቁጥር ቢሆንም፣ አሁን ቁጥሩ በየወሩ እያደገ በመሄድ ላይ ነው! የመንፈስ ቅዱስን ሰላም ምስክርነት ተከትለን ስንሄድ፣ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥና በእኛ በኩል መሥራት ለሚችለው ይህ ዓይነተኛ ማስረጃ ሊሆነን ይችላል፡፡

ቀን 4

## ምሪት መቀበል

ብዙ አማኞችን ችግር የሚገጥማቸው የእግዚአብሔርን ምሪት መቀበልን አስመልክቶ ነው፡፡ ‹‹እግዚአብሔር በሕይወቴ ምን እንዳደርግ እንደሚፈልግ በእርግጠኝነት አላውቅም›› በማለት ሰዎች ብዙ ጊዜ ሲናገሩ እሰማለሁ፡ ፡ ምሪት ማግኘት ከፈለግን ምን ማድረግ እንዳለብን ያዕቆብ ይናገራል፤ ‹‹ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጎድለው እግዚአብሔርን ይለምን›› (1÷5)፡፡ ጥበብ ለሚለው የግሪኩ ቃል ሶፊያ ሲሆን፣ የተሟላ ትርጕሙ፣ ‹‹የመረዳት ዐቅም ወይም ብቃት፣ በዚያም መሠረት በማስተዋል ማድረግ››[2] ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ አስቡት - መጀመሪያ በእግዚአብሔር ጥበብ አማካይነት መረዳት እናገኛለን፤ ከዚያም ወደ ተግባር እንገባለን፡፡

የእግዚአብሔርን ጥበብ የመረዳት ዐቅም የሚሰጠንና ያንኑ ተግባር ላይ የማዋል ብቃት የሚሰጠን ማን ነው? መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ምሪት መቀበል የሚያስፈልገኝ ሁኔታዎች ውስጥ ገብቼ አውቃለሁ፡፡ በልሳን በምጸልይበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ጥበብና ምሪት ከመንፈሴ ይፈልቅና መረዳት ችሎታዬ ውስጥ ይገባል፡፡ በልሳን መጸለይ የእግዚአብሔርን ምሪት ለሕይወታችን ያበራል፡፡

እንደ ገና ምሳሌ 20÷5 እናንብብ፤ ‹‹የሰው ልብ ሐሳብ እንደ ጥልቅ ውሃ ነው፤ አስተዋይ ሰው ግን ከዚያ ቀድቶ ያወጣዋል፡፡›› በክርስቶስ አንድ ዐይነት ሥራ ወይም ዓላማ ተሰጥቶአችኋል፤ ያ ለእናንተ ብቻ ተለይቶ የተሰጠ ነው፡፡ ይህ ዓላማ የሕይወታችሁን አቅጣጫ ይወስናል፤ይህ ዓላማ ያለው ጥልቅ ልቦናችሁ ውስጥ ነው፡፡ በመንፈስ ስትጸልዩና የእግዚአብሔርን ምክር ወይም ሐሳብ ስትፈልጉ፣ እርሱ ለሕይወታችሁ ያለውን ዓላማ ይገልጽላችኋል፡ ፡ ሆኖም፣ ወዲያውኑ የሚሆን ስላልሆነ፣ ትዕግሥት ይኑራችሁ፡፡ በጸሎትና

የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ጊዜ ስታሳልፉ፣ ለሕይወታችሁ ያለውን ዓላማ ይገልጽላችኋል፡፡ ከልጆቼ አንዱ ይህን በተመለከተ ሲናገር፣ የእግዚአብሔር ቃል ካርታችን (ማፓችን) ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ መሪያችን ነው ይላል፡ ፡

የእግዚአብሔር ምሪት ለማንኛውም የሕይወታችሁ ገጽታ ይሆናል፡ ፡ ለምሳሌ ከልጆቻችሁ ከአንዱ ጋር ችግር ከገጠማችሁ፣ ነገሩን ተወት አድርጋችሁ በመንፈስ የምትጸልዩበት ጊዜ ወስኑ፡፡ ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ ያሳያችኋል፡፡ በንግድ ሥራ ውስጥ ከሆናችሁና ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ካላወቃችሁ፣ ክፍላችሁን ዘጉና ማስተዋል እንዲሰጣችሁ ሁሉን የሚያውቀውን ለምኑት፡፡ በመሠረቱ እርሱ ያለው እናንተ ውስጥ ነው፤ እናንተ ማድረግ ያለባችሁ እርሱ ለእናንተ ግልጽ ያላደረገውን ከዚያ መውሰድ ነው፡፡ የእርሱ ፍላጎት ለእናንተ ምሪት መስጠት ነው! ኢሳይያስ 48፥17፣ ‹‹እኔ እግዚአብሔር አምላክህ፣ የሚበጅህ ምን እንደ ሆነ የማስተምርህ፣ መሄድ በሚገባህ መንገድ የምመራህ ነኝ›› ይላል፡፡ እግዚአብሔር በመንግሥቱ ውስጥ ባላችሁ ዓላማ እንድትኖሩ ይፈልጋል፤ እያንዳንዱ ርምጃችሁን መምራት ይፈልጋል፡፡

አንዳንዴ ሰዎች፣ ‹‹ጆን፣ ይኸማ በጣም ያልተለመደ እንግዳ ዓይነት አካሄድ ነው፡፡ እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ለእግዚአብሔር ማቅረብ የለብንም፡፡ እርሱን የሚያሳስበው ከአገልግሎት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ብቻ ነው›› ሲሉ እሰማለሁ፡፡ ከሁሉም ነገር በፊት፣ እግዚአብሔርን በተመለከተ ያልተለመደ እንግዳ ነገር የለም፤ በማንኛውም የሕይወት ገጽታችን ውስጥ የእርሱን ጣልቃ መግባት በተመለከተ ምንም አዲስ ነገር የለም፡፡ ሰዎች ለአንዳንድ ነገሮች እንግዳ ሊሆኑ ይችላሉ፤ እግዚአብሔር ግን እንደዚያ አይደለም፡፡ በተጨማሪም፣ አንዳንድ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ ስለ ተጠቀሙበት ብቻ፣ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ተስፋ ችላ ማለት ወይም አቅልለን ማየት የለብንም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹ሳታቋርጡ ጸልዩ›› በማለት ነግሮናል (1 ተሰሎንቄ 5፥17)፡፡ ይህ ጥቅስ ምን ማለት እንደ ሆነ ብዙ ክርስቲያኖች በዐውዱ መሠረት አላጠኑትም፡፡ መቼም ጳውሎስ፣ ‹‹በቀን ውስጥ ባሉት ደቂቃዎች ሁሉ ጸሎት ማነብነብ አለባችሁ›› ማለቱ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡ ፡ በዚህ ላይ ደግሞ፣ ወንጌልን ለሌሎች እንድናካፍልና አንዳችን ሌላውን እንድናበረታታ መጽሐፍ ቅዱስ ነግሮናል፡፡ እያንዳንዱን ደቂቃ በአንደበታችን

ጸሎት የምናነበንብ ከሆነ እንዲህ ማድረግ አንችልም፡፡

እዚህ ላይ ጳውሎስ እያለ ያለው፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የማያቋርጥ ኅብረት ይኑራችሁ ነው፡፡ ግን ይህን ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው? ጳውሎስ መልሱን ጥቂት ቁጥሮች ወረድ ብሎ ሰጥቶናል፤ «የመንፈስን እሳት አታዳፍኑ» (ቁጥር 19)፡፡ ያለ ማቋረጥ መጸለይ፣ የመንፈስ ቅዱስን መገኘት አለማዳፈን ማለት ነው፡፡ መገኘቱን መረዳትና ድምፁን ለመስማት ንቁ መሆን ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር እርሱ በሕይወታችሁ እያደረገ ያለውን ተሳትፎ አታፍኑ፣ አትጫኑ ማለት ነው፡፡ መንፈስ በእያንዳንዱ የሕይወት ገጽታችሁ ተሳትፎ ማድረግ ይፈልጋል፡፡ ሊመራችሁ ይፈልጋል፡፡ የእርሱ ፍላጎት ዘወትር ከእናንተ ጋር ኅብረት፣ ማድረግ ነው፡፡ ይህ የማያቋርጥ ኅብረት በሕይወታችሁ የእርሱ ሰላም፣ ብርታትና ምሪት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

የንግድ ሰው እንድሆን አልተጠራሁም፡፡ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ፣ ሥራዬን በተመለከተ ረዘም ያለ ሰዓት በመንፈስ እጸልይ ነበር፡፡ ልቤ ውስጥ በሚኖረኝ ሰላም መሠረት ውሳኔ አደርግ ነበር፡፡ «የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች» ስላልሆናችሁ ብቻ፣ ከፈጣሪያችሁ ምሪት የመቀበል መብታችሁን አቅልላችሁ አትመልከቱት፡፡ የእኔን መንገድ እንደ መራ ሁሉ፣ የእናንተንም መንገድ ይመራል፡፡

## የግል ጸሎት ጊዜ

መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከጀመርኩ የጸሎት ጊዜዬ በጣም ውጤታማ እንደሚሆን ተረድቻለሁ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል አእምሮዬን ያጠራል፤ ከመንፈሴ ወደ አእምሮዬ ያለውን መተላለፊያ የሚከፍተውም ይመስለኛል፡፡ ከዚህ የንባብ ጊዜ በኃላ ይበልጥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እያያዛለሁ፤ ከእርሱ መገኘት የተነሣ የጸሎት ጊዜዬ ጥልቀት ይኖረዋል፡፡

ለእርሱ በሕይወቴ መገኘት እውነት፣ በዓላማ ክብር ስሰጥ፣ እግዚአብሔር ራሱን ለመግለጥ ፈጣን መሆኑንም ተረድቻለሁ፡፡ የእርሱን ታላቅነትና መልካምነት ሳሰላስል፣ መንፈስ ወዲያውኑ ራሱን ይገልጻል፡፡ ለምን? ዘማሪው መልሱን ይሰጠናል፤ «እግዚአብሔር… በዙሪያው ካሉት ሁሉ በላይ እጅግ የሚከበር ነው» (መዝሙር 89፥7)፡፡ የእግዚአብሔርን ሓልዎት መለማመድ

ከፈለጋችሁ፣ በአክብሮት ልትቀርቡት ይገባል፡፡ የእግዚአብሔር ሓልዎት ከእናንተ እንዲርቅ ለማድረግ ፈጣኑ መንገድ መንፈሱን ችላ በማለት እርሱን አለማክበር ነው፡፡

ኢየሱስ አርአያ የሆነውን ጸሎት ለደቀ መዛሙርቱ (ለእኛም ጭምር) ባስተማረ ጊዜ፣ «አባታችን ሆይ፣ በሰማያት የምትኖር፤ ስምህ ይቀደስ» (ይከበር) በማለት ነበር የጀመረው (ማቴዎስ 6፥9)፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ወደ አባታችን ስንቀርብ፣ በመጀመሪያ በቅዱስ አክብሮት ወደ ሓልዎቱ መግባት ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ እንደዚያ ስናደርግ ተገቢውን ክብር ስለ ሰጠነው መንፈስ ቅዱስ የበለጠ ሓልዎቱን ይገልጻል፡፡ የእርሱ ሓልዎት ወይም መገኘት – ትክክለኛ ዕይታ፣ ጥበብ፣ ዕውቀትና ኃይል ይሰጠናል፡፡ እርሱ በእውነት የሕይወታችን ምንጭ ነው! ታዲያ፣ ለምን ራሳችንን ከእርሱ እንለያለን?

## በመንፈስ መማለድ

ከአንድ ፓስተር ወዳጄ ጋር ዘወትር አብረን እንጸልያለን፡፡ አብረን እየጸለይን እያለ ብዙ ጊዜ በልሳን እንማልዳለን፡፡ አንድ ጊዜ በመካከለኛው ምሥራቅ ውስጥ ስላለ አንድ አካባቢ እየማለድን እንደ ሆነ አወቀን ነበር፡፡ በሚቀጥለው ቀን ቱርክ ውስጥ ከባድ የመሬት መንቀጥቀጥ እንደ ነበር ሰማን፡፡ እኔና ጓደኛዬ ለዚያ አገር በልሳን እየማለድን እንደ ነበር አምናለሁ፡፡ በመንፈስ አማካይነት እዚያ ካሉ ወገኖች ጋር ግንኙነት ፈጥረናል፤ ምክንያቱም ሁላችንም ውስጥ ያለው ያው አንዱ መንፈስ ነው፡፡ በእኛ አማካይነት እግዚአብሔር ቱርክ ውስጥ ስላሉት ወገኖች ፈቃዱን እየተናገረ ነበር፡፡

ይህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ምልጃ፣ በዚህ ምድር የእግዚአብሔርን መንግሥት በማስፋፋት ረገድ፣ እጅግ ፋይዳ ያለው ነው፡፡ በሩቅ ላሉ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወጅ መቻላችንን ጠላት በጣም ይጠላዋል፡፡ የእርሱ ዋናው ዓላማ ቤተ ክርስቲያንን መለያየትና መከፋፈል ነው፤ ምልጃችን በአእምሮ መረዳት በምንችለው ብቻ የተወሰነ ሲሆን ማየትን ይወዳል፡፡ ምናልባትም፣ በዓለም ዙሪያ ካሉ ሌሎች አማኞች ጋር ምን ያህል በቅርበት የተያያዛችሁ እንደ ሆነ ገና አልተረዳችሁም ይሆናል፡፡ ምንም እንኳ ከእነርሱ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ባይኖራችሁም፣ በሌሎች አገሮች ላሉ

አማኞች በሚገባ መማለድ ትችላላችሁ፡፡

አንድ ጊዜ ኬንያ እያለሁ ከአንድ የማሳይ ጐሳ አባል ከሆነ ሰው ጋር ተገናኝቼ ነበር፡፡ በኃላም፣ ዩናይትድ ስቴትስን በጐበኘ ጊዜ ያረፈው ፔንሲልቫን ባሉ አንዳንድ ወዳጆቼ ዘንድ ነበር፡፡ ያ ሰው ከእነርሱ ጋር አንድ ወር ያህል ቆይቶ ነበር፡፡ በተለያየ ጊዜ አፍሪካ ያሉት ቤተ ሰቡ ስላሉበት ወቅታዊ ሁኔታ በእንግድነት ለተቀበሉት ሰዎች ይነግራቸው ነበር፡፡ በመጨረሻም፣ «ቤተ ሰብህ ባለበት አካባቢ ስልክ እንደሌለ እናውቃለን፤ ታዲያ፣ ቤተ ሰብህ ላይ እየሆነ ያለውን እንዴት ማውቅ ቻልህ?» በማለት ጠየቁት፡፡ «እርሱ የነበረው ከእነርሱ በጣም ርቆ ቢሆንም፣ ጳውሎስ የቈላስይስና የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች የነበሩበትን ሁኔታ ያውቅ ነበር፡፡ በመንፈስ በምጸልይበት ጊዜ ጌታ ቤተ ሰቤ ላይ እየሆነ ያለውን ያሳየኛል» በማለት ነበር የመለሰላቸው፡፡ ሰውየው ያመለከተው፣ «ምንም እንኳ በሥጋ ከእናንተ ርቄ ብገኝ፣ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና በሥርዐት መኖራችሁንና በክርስቶስ ያላችሁን ጽኑ እምነት እያየሁ ደስ ይለኛል» የሚለውን ቈላስይስ 2፥5 ላይ ያለውንና፣ «ምንም እንኳ እኔ በአካል አብሬአችሁ ባልሆንም፣ በመንፈስ ግን ከእናንተ ጋር ነኝ» የሚለውን 1 ቆሮንቶስ 5፥3 ላይ ያለውን ነበር፡፡ ጳውሎስ ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ሰዎች ጋር በመንፈስ የተያያዘ ስለ ነበር፣ በአካል ከእነርሱ ጋር ባይሆንም፣ ያሉበትን ሁኔታ ማወቅ ችሎ ነበር፡፡

ከሥራ ባልደረቦቼ ወይም ከወዳጆቼ አንዱ፣ ለእኔ እየጸለየ መሆኑን በተለያየ ጊዜ ማውቅ ችዬ ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ በጣም አስፈሪና አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነበርኩ፤ እግዚአብሔር ግን ድንገት በተአምር ጣልቃ ገባ፡፡ በእነዚያ ጊዜዎች ከጥቃት እንድከለል አንድ ሰው እየጸለየልኝና በመንፈስ እየማለደልኝ እንደ ነበር አውቃለሁ፡፡

## ዕረፍት መለማመድ

ወንድሞች ሆይ፣ በአስተሳሰባችሁ ሕፃናት አትሁኑ... በሕግም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፣ «ቋንቋቸው እንግዳ በሆነ ሰዎች ለዚህ ሕዝብ እናገራለሁ፡፡ (1 ቆሮንቶስ 14፥20-21)፡፡

ምናልባት ልብ አድርጋችሁ ከሆነ፣ በዚህ ጊዜ ጳውሎስ ልሳንን በተመለከተ 1 ቆሮንቶስ 14 ላይ ብዙ ተናግሮአል፡፡ ከላይ በተመለከትናቸው ቁጥሮች ጳውሎስ የነቢዩ ኢሳይያስን ቃል በራሱ አቀራረብ ማቅረቡን አይተናል፤ ምክንያቱም፣ ኢሳይያስ 28፥11-12 እንዲህ ነው የሚለው፣

> እግዚአብሔር በባዕድ ልሳን፣ በእንግዳ ቋንቋ፣ ለዚህ ሕዝብ ይናገራል፡
> ፡ እርሱ፣ ‹‹ይህቺ የዕረፍት ቦታ ናት፤ የደከመው ይረፍ፡፡››

በልሳን መናገር ዕረፍትና መታደስ እንደሚሰጥ፣ እግዚአብሔር በኢሳይያስ በኩል አስቀድሞ ተናግሮ ነበር፡፡ አንድ ጊዜ የአንድ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ፓስተር የሆነ ጓደኛዬ፣ ከሌላ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ጋር እየተነጋገረ ነበር፡፡ የሁለተኛው ቤተ ክርስቲያን ፓስተር፣ ‹‹አገልግሎት ልተው ነው፡፡ በጣም ደክሞኛል፤ ታክቶኛል፣ ዐቅሜ ሁሉ ተሟጥጦአል›› በማለት ለጓደኛዬ ይነግረዋል፡፡

ጓደኛዬም፣ ‹‹በልሳን መጸለይህን አቁመሃል አይደል?›› በማለት ጠየቀው፡፡ ሌላው ፓስተር መልስ ለመስጠት እያቅማማ እያለ፣

ጓደኛዬ ቀጠል አድርጐ፣ ‹‹ለመሆኑ፣ በመንፈስ በመጸለይ ምን ያህል ጊዜ ታሳልፋለህ?›› አለው፡፡

ሌላው ፓስተር አሁንም ጥቂት ካቅማማ በኋላ፣ ‹‹እንደምታውቀው 15,000 አባሎች ያሉት ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ነኝ፡፡ በየጊዜው መልእክቶች አዘጋጃለሁ፤ በጣም ሥራ ይበዛብኛል…›› አለ፡፡

‹‹ለመሆኑ በመንፈስ ትጸልያለህ?›› በማለት ጠየቀ ጓደኛዬ፡፡

በመጨረሻም ፓስተሩ፣ ‹‹እውነቱን ለመናገር አልጸልይም›› አለ፡፡

ጓደኛዬም፣ ‹‹በመንፈስ መጸለይ ጀምር›› አለው፡፡

ብዙም ሳይቆይ፣ ያ በጣም ተዳክሞና ታክቶት የነበረ ፓስተር አገልግሎት የማቋረጥ ሐሳቡን ተው፡፡ በአሁኑ ጊዜ እርሱም ሆነ ቤተ ክርስቲያኑ በጣም እየበረቱ ናቸው!

ለዚያ ፓስተር በልሳን መጸለይ በጣም ጠቃሚ የሆነው ለምን ነበር? በመንፈስ ስንጸልይ፣ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ዕረፍትና የዐቅም መታደስ እንቀበላለን፡
፡

800,000 አባሎች ያሉት ቤተ ክርስቲያን መሪ ቢሆንም፣ ዶክተር ቾ ዐቅሙ ያልተሟጠጠውና ጉልበቱ ያልላሸቀው ለምንድነው? በመንፈስ ስለሚጸልይ ነው፡፡ የዶክተር ቾን ያህል ጫና ያለበትና ኃላፊነት የሚበዛበት ሌላ ፓስተር አላውቅም፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ አብዛኛውን ደቡብ ኮርያ ለውጦአል፤ እርሱ በዓለማችን እጅግ ከተከበሩ ፓስተሮች አንዱ ነው፡፡ በራሳቸው ጉልበት ይህን ያህል ከባድ ሸክም መሸከም ለማንኛውም ወንድ ወይም ሴት በጣም ከባድ ይሆን ነበር፡፡ ዶክተር ቾ ግን በራሱ አእምሮና ጉልበት እንደማይተማመን አውቃለሁ፡፡ በየዕለቱ ለሰዓቶች ያህል በአእምሮና በልሳን በመጸለይ ያሳልፋል፡፡ ይህ የጸሎት ጊዜ ታላቅ ኃይልና ዕረፍት ይሰጠዋል፡፡

ሌስተር ሱመራል ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነበሩ፡፡ በተለያዩ ወቅቶች ከእርሳቸው ጋር ጊዜ የማሳለፍ ዕድል ገጥሞኝ ነበር፡፡ ዶክተር ሱመራል ሌሊት አራት ሰዓት ብቻ ነበር የሚተኙት፣ በአንድ ጊዜ አራት የተለያዩ መጻሕፍት ይጽፉ ነበር! የእርሳቸው ግማሽ ያህል ዕድሜ ከነበራቸው የሥራ ባልደረቦቻቸውና ከብዙ ወጣት ሰባኪዎች የበለጠ ብርታት ነበራቸው፡፡ ለመሆኑ፣ ይህን ብርታት ከየት አገኙት? በመንፈስ በመጸለይ ብዙ ጊዜ ያሳልፉ ስለ ነበር ነው፡፡

እባካችሁ በትክክል ተረዱኝ፤ በምንም ዓይነት ሁኔታ ሰውነታችንን አላግባብ ልንጠቀምበት አይገባም፡፡ እግዚአብሔር ሰንበትን እንድንጠብቅና እንድናከብር አዝዞናል፡፡ ማንኛችንም ብንሆን ዕረፍት ያስፈልገናል፡፡ ከሥራ ዘወር ለማለትና የአእምሮና የአካል መታደስ ለማግኘት አልፎ አልፎ ጐልፍ እጫወታለሁ፡፡ ያ ለእኔ ትልቅ የዕረፍት ምንጭ ይሆንልኛል፡፡ ሆኖም፣ አካላዊ ዕረፍት ከማድረግ በተጨማሪ በመንፈስ መጸለይም አካልና ነፍሳችንን ያድሳል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው፣ በመንፈስ ዕረፍት ስለማያደርጉ የብዙዎች ዐቅምና ጉልበት ያለ ጊዜያቸው ተሟጥጦአል፡፡

ቀን 5

## ውስጣዊ ሰውነታችን

በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል (1 ቆሮንቶስ 14፥4)፡፡

ማነጽ ለሚለው የግሪኩ ቃል ኦይኮዶሚዮ (oikodomeo) ነው፡፡ ቃል በቃል ሲወሰድ፣ ‹‹መገንባት ወይም ማነጽ››[3] ማለት ነው፡፡ በልሳን ስንጸልይ፣ የእግዚአብሔር ሓልዎትና ኃይል የሚያድርበት ቤት የመሆን ዐቅማችንን እናንጻለን፡፡ ‹‹ይህን ቃሌን ሰምቶ በተግባር የሚያውል ቤቱን በዐለት ላይ የሠራ (ኦይኮዶሚዮ) ብልኅ ሰውን ይመስላል›› በማለት ኢየሱስ ሲናገር የተጠቀመው በዚሁ ግሪክ ቃል ነበር (ማቴዎስ 7፥24)፡፡

በተጨማሪም በሐዋርያው ይሁዳ በኩል እግዚአብሔር፣

> እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፣ እጅግ ቅዱስ በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ - ብሎናል (ይሁዳ 20)፡፡

አንድ ጊዜ ልጁ በጣም የታመመበት ጓደኛ እንደ ነበረኝ አስታውሳለሁ፡፡ ዶክተሮች ችግሩ ምን እንደ ነበር ማግኘት አልቻሉም፤ ጓደኛዬም ምን እንደሚያደርግ አላወቀም፡፡ በመጨረሻ፣ ቢሮው ገብቶ ረጅም ሰዓት በመንፈስ ጸለየ፡፡ ከቢሮው ሲወጣ፣ በቀጥታ ወደ ቤት ሄዶ፣ ወደ ልጁ መኝታ ቤት ገባ፡፡ ልጁ ከዐልጋው እንዲነሣ በታላቅ ሥልጣን አዘዘ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ልጁ ሙሉ በሙሉ ተፈወሰ፡፡ አጥብቆ በመንፈስ በመጸለይ ረጅም ጊዜ ማሳለፉ፣ እንደሚገባ እንዲማልድና ልጁን ማገልገል እንዲችል የጓደኛዬን ዐቅም አሳደገው፡፡ ከእግዚአብሔር የምንቀበለውን ማንኛውንም ነገር የምንቀበለው በእምነት ነው፡፡ ሌላ ምንም አማራጭ መንገድ የለም፡፡ ከመንፈስ ጋር ጊዜ ማሳለፍ ተስፋዎቹን የመቀበል ችሎታችንን ይጨምራል፤ ውስጣዊ ሰውነታችን ስለሚታነጽ የእግዚአብሔር ሓልዎት ይገለጻል፡፡

## ጥልቀት ያለው አምልኮ

በሰማያዊ ቋንቋችን መጸለይ ጥልቀት ባለው ሁኔታ እግዚአብሔርን እንድናመልከውና እንድናመሰግነው ያስችለናል፡፡ ጳውሎስ እንዲህ አለ፤

> እንዲህማ ካልሆነ እግዚአብሔርን በመንፈስ በምታመሰግንበት ጊዜ ለነገሩ እንግዳ የሆነ ሰው አንተ የምትናገረውን ካልተረዳ እንዴት

አድርጎ ለምስጋናህ፣ ‹‹አሜን›› ሊል ይችላል? አንተ በሚገባ ታመሰግናለህ (1 ቆሮንቶስ 14፥16-17)፡፡

ጳውሎስ እየተናገረ ያለው በኅብረት ስለሚቀርብ ምስጋና ሲሆን፣ ‹‹በመንፈስ ስናመሰግን›› (ማለትም በልሳን እግዚአብሔርን ስናመሰግን) ሌላውን ሰው እንደማይጠቅመው ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም በልሳን ማመስገን፣ በግል የሚደረግ በመሆኑ ራስን ያንጻል እንጂ፣ ጉባኤውን አያንጽም፡፡ እዚህ ላይ ጳውሎስ በልሳን እግዚአብሔርን ማመስገንን እያቃለለ አይደለም፡፡ ለዚያ ጊዜና ቦታ እንዳለው ብቻ ነው ማመልከት የፈለገው፡፡

ጳውሎስ ዐረፍተ ነገሩን እንዴት እንደ ደመደመ ልብ አድርጉ፤ ‹‹አንተ በሚገባ ታመሰግናለህ!›› በልሳን እግዚአብሔርን ስናመሰግን፣ በእኛ አማካይነት መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ምስጢር ውብ በሆነ ቋንቋ እንዲያመሰግን እንፈቅድለታለን፡፡ በሰማያዊ ቋንቋ እግዚአብሔርን ስናመሰግን እጅግ የጠለቀና የጠበቀ አምልኮ ይሆናል፡፡ ጳውሎስ በመንፈስና በአእምሮ ያመሰግን የነበረው በዚህ ምክንያት ነው (1 ቆሮንቶስ 14፥15)፡፡

## ማንኛውም ሰው በመንፈስ መሞላት ይችላል

አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈስ የማይጸልዩ አማኞችን ዝቅ አድርገው ሲመለከቱ ልቤ በጣም ያዝናል፡፡ እነዚህ በክርስቶስ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን የሆኑ ወገኖች ይህን ድንቅ የመንፈስ ስጦታ አልተለማመዱም፡፡ ሁላችንም በክርስቶስ አንድ ስለ ሆንን በምንም ዓይነት ቅር መሰኘት ወይም ዝቅ ተደርገው መታየት የለባቸውም፡፡

ባለፈው ምዕራፍ እንደ ተመለከትነው፣ በልሳን የመናገር ስጦታ ለማንኛውም አማኝ ነው፡፡ በልሳን የማይናገሩትም ከዚህ ተስፋ ቃል ውጪ አይደሉም፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹የሚያምኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል… በአዲስ ልሳንም ይናገራሉ›› ብሏል (ማርቆስ 16፥17)፡፡ ጳውሎስም፣ ‹‹ሁላችሁም በልሳን ብትናገሩ እወዳለሁ›› ብሏል (1 ቆሮንቶስ 14፥5)፡፡ የእግዚአብሔር ሐሳብ ልጆቹ ሁሉ የሰማያዊ ቋንቋን ድንቅ ጠቀሜታ እንዲለማመዱ ነው፡፡

## አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስን የሚቀበለው እንዴት ነው?

ወደ ፊት ከመግፋቴ በፊት፣ አንዳንድ እኔ የማውቃቸው ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉት መኪና እየነዱ፣ ቤት ውስጥ እያሉ፣ ሌላው ቀርቶ ቢሮ ውስጥ እያሉ እንደ ነበር መናገር እፈልጋለሁ፡፡ እኛ ማድረግ ያለብን መጠየቅ ብቻ ሲሆን፣ የሰማዩ አባታችን መንፈስ ቅዱስን ይሰጠናል፡፡ ይህን ስጦታ እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን ጠይቀህ ከሆነ፣ በዚያው ዝንባሌ ውስጥ መኖርን ተማር፡፡

በመጀመሪያና በተቀዳሚ ደረጃ፣ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ከመቀበልህ በፊት የሕይወትህ ጌታና አዳኝ እንዲሆን ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል ይኖርብሃል፡፡ ዓለም – ማለትም ድነትን ያላገኙ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን መቀበል እንደማይችሉ ኢየሱስ ተናግሮአል፡፡ (ዮሐንስ 14፥17 ይመ.)፡፡ ኢየሱስን የሕይወትህ ጌታ ያላደረግህ ከሆነ፣ አሁኑኑ ለጌትነቱ ራስህን መስጠት ትችላለህ (ድነትን መቀበልን በተመለከተ ሰፋ ላለ ማብራሪያ፣ ተጨማሪ ምዕራፉን አንብብ)፡፡

የእግዚአብሔር ልጅ ብትሆን እንኳ፣ ሆን ብለህ የምትለማመደው አለመታዘዝ በሕይወትህ ካለ የመንፈስን ሙላት እንዳትቀበል መሰናክል ይሆንብሃል፡፡ እግዚአብሔር፣ «ለሚታዘዙት መንፈሱን ይሰጣል» (ሐዋርያት ሥራ 5፥32)፡፡ እንዲህ ሲባል ግን፣ ፍጹም መሆን አለብህ ማለት አይደለም፡፡ ይልቁን፣ ራስህን በፊቱ ትሑት ማድረግ አለብህ ማለት ነው፡፡ ይህ ራስህን ለፈቃዱ የመስጠትህ ምልክት ነው፡፡ ራስህን ዝቅ (ትሑት) ስታደርግ፣ እግዚአብሔር የኃጢአትን ወጥመድ የምታሸንፍበት ጸጋውን ይሰጥሃል፤ የመንፈስን ሙላት ለመቀበልም እንደ ገና ራስህን ዝግጁ ታደርጋለህ፡፡

በብዙ አማኞች ሕይወት ትልቁ ያለ መታዘዝ ወጥመድ መሰናክል ነው፡፡ ሆን ብላችሁና ፈቅዳችሁ፣ የበደሉዋችሁን ይቅር ማለት አለባችሁ፡፡ በመንፈስ መሞላት የሚፈልጉ፣ በሌሎች በደል የተፈጸመባቸው አማኞች፣ ይቅር ሲሉ ያለ ምንም ልዩነት መንፈስ ሲገለጥ ብዙ ጊዜ አይቻለሁ፡፡ በደል ያደረሱብህን ሰዎች ለመፍታት አሁኑኑ ጊዜ ውሰድ፤ እነርሱን በተመለከተ የእርሱን ልብ እንዲሰጥህ እግዚአብሔርን ጠይቀው፡፡ (መሰናክል በተመለከተ፣ የሰይጣን ሽንገላ በተሰኘው መጽሐፌ በስፋት ገልጫለሁ፤ ያን መጽሐፍ እንድታነብ

አጥብቄ እመክርሃለሁ)፡፡

## በእምነት መጠየቅ ብቻ...

> ከእናንተ መካከል አባት ሆኖ ሳለ፣ ልጁ ዓሣ ቢለምነው እባብ የሚሰጠው ይኖራልን? ወይስ ዕንቁላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን? እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ ሳላችሁ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠት ካወቃችሁበት የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ፣ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ! (ሉቃስ 11፥11-13)፡፡

መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጣችሁ ብትለምኑ እንኳ፣ አንዳንዴ ክፉ መንፈስ ልትቀበሉ ትችላላችሁ በማለት አንዳንድ ሰዎች ያስተምራሉ፡፡ ሆኖም፣ ይህ ኢየሱስ የተናገረው ቃል፣ ያንን ፍርሃት ጨርሶ ሊያስወግደው ይገባል፡፡ እግዚአብሔር የማንኛውም መልካምና ፍጹም ስጦታ ሰጪ ነው (ያዕቆብ 1፥17 ይመ)፡፡ መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጥህ አባትን ጠይቀህ ከሆነ፣ ጋኔን አይሰጥህም፤ የእርሱን መንፈስ ነው የሚሰጥህ፡፡ ስለሆነም የመንፈሱን ሙላት ለመቀበል ራስህን ነጻ ማድረግን መፍራት የለብህም፡፡

ራስህን ለመንፈሱ ክፍት ብታደርግም፣ መንፈስ ቅዱስ በግድ በልሳን እስኪያናግርህ አትጠብቅ፡፡ እርሱ ነጻ ፈቃድ ሰጥቶሃል፡፡ መንፈስ ጨዋ በመሆኑ፣ አያስገድድህም፡፡ ሰይጣን ያስገድዳል፤ መንፈስ ቅዱስ ግን በፈቃደኝነት ይመራል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ቃላቱን ይሰጥሃል (በትንንሽ የቃላት ክፍልፋዮች፣ በድምፅ ወይም በመንተባተብ ሊጀምር ይችላል)፣ አንተ ደግሞ ከንፈሮችህን፣ ምላስህንና ሕብለ ሰረሰርህን ለእርሱ አስገዛ፡፡ እንደዚያ ስታደርግ፣ ልክ እንደሚፍለቀለቅ ምንጭ ከመንፈስህ ሰማያዊ ቋንቋ ይፈለቀለቃል፡፡ መጀመሪያ ላይ አንድ የቃል ክፍል ወይም ቃል ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም፣ በእምነት ያንኑ መናገር ስትቀጥል የበለጠው መምጣት ይጀምራል፡፡ እንደ ገና እናገራለሁ፤ ማንኛውንም ነገር ከእግዚአብሔር የምንቀበለው በእምነት ነው፤ በልሳን የመናገር ስጦታም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ በእምነት የሚሰጥህን ተናገር፤ በመንተባተብ ብትጀምር እንኳ፣ እየተናገርህ ስትሄድ የተሟላ ቋንቋ ወደ መሆን ደረጃ ያድጋል፡፡

# ላቅ ያሉ ደረጃዎች

ባለፉት ሁለት ምዕራፎች ሰፊውን ስፍራ በልሳን ስለ መናገር የሰጠሁበት ምክንያት፣ በጥልቀት ከእርሱ ጋር የሚያያይዘን፣ ለመንግሥቱ ሥራ ዓላማ ከሕዝቡ ጋር የሚያስተባብረን፣ ሰማያዊ ቋንቋ እንዲኖረን እግዚአብሔር እንደሚፈልግ በማመኔ ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ፍላጐት ወንዶችና ሴቶች ሁሉ ኢየሱስን እንዲያውቁ ነው፡፡ ከእርሱ ጋር ባለን መቀራረብና አጋርነት እያደግን ስንሄድ፣ ዓይኖቻችንን ይከፍታል፤ ዓለምን ከዚህ በፊት ባልነበረን አዲስ ብርሃን ማየት እንድንችል ይገልጽልናል፡፡ ዓለም እጅግ በጣም ክርስቶስ እንደሚያስፈልገው እናያለን፤ ክርስቶስ እንዲታወቅ በማድረግም ረገድ እኛ ያለንን ድርሻ በመንፈስ አማካይነት እናውቃለን፤ እናያለን፡፡

የእግዚአብሔርን መንፈስ አስመልክቶ እንደ መግቢያ የቀረበውን ይህን መጽሐፍ እንደ ወደዳችሁት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ በእነዚህ ምዕራፎች የተማራችሁት ሁሉ የእርሱን ወሰንና ገደብ የለሽነት፣ ወደር የለሽ ድንቅ በተመለከተ፣ በጥቂቱ እንደ ቅምሻ ብቻ መሆኑን አውቃለሁ - እርሱ በእያንዳንዱ የዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ እጅግ ወደ ላቀው ደረጃ ሊወስዳችሁ ይፈልጋል፡፡ በአዲስና የበለጠ ጥልቀት ባለው ሁኔታ እርሱን ለማወቅ ልባችሁን እንዲያነቃ ይህን መጽሐፍ አልፎ አልፎ በየጊዜው እንድታነቡ አበረታታችኋለሁ፡፡

ኢየሱስን ለእናንተ ለመግለጽ መንፈስ ቅዱስ ደስ ይሰኛል፡፡ ሐልዎቱን አክብሩ፣ ‹‹መንፈሳዊ›› ለምትሉዋቸው ብቻ ሳይሆን፣ ወደ ማንኛውም የዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ ገጽታዎች እርሱን ጋብዙት፡፡ እንደማይጥላችሁ ደግሞም እንደማይተዋችሁ ቃል ገብቷል፤ በእያንዳንዱ ቀን ውስጥ ባሉ ደቂቃዎች ሁሉ፣ በዚህ ድንቅ ተስፋ ቃል ደስ ይበላችሁ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ስታነቡና በፊቱ ጊዜ ስታሳልፉ በበለጠና በጠለቀ ሁኔታ መንፈስን እያወቃችሁ ትሄዳላችሁ፡፡ በጣም አስገራሚው ደግሞ፣ ማለቂያ የሌለው ጉዞ መሆኑ ነው፡ ፡ ምን ጊዜም ቢሆን፣ እርሱ ለእናንተ መግለጽ የሚፈልገው ገና የበለጠ ይኖራል፡፡ በሰማችሁት፣ ባያችሁትና ባወቃችሁት ብቻ አትወሰኑ፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሕይወታችሁን እንዲገዛ በመፍቀድ ከውሱን አእምሮአችሁ

ገደብ አልፋችሁ ሂዱ። እንደዚያ ስታደርጉ፣ ከዚያ በፊት ከነበረው ይበልጥ የእግዚአብሔር ክብርና ግርማ በኑሮአችሁ ሲገለጥ ታያላችሁ።

## ቀን 1 ማሰላሰያ

### በመንፈስ መጸለይ…

# የጠለቀ መቀራረብ እንዲኖር በር ይከፍታል

*በልሳን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ፣ ለሰው አይናገርምና*

—1 ቆሮንቶስ 14፥2

በመንፈስ የመጸለይ ትልቁ በረከት፣ ከእግዚአብሔር ጋር በጣም እንድንቀራረብ ማድረጉ ነው፡፡ የፍጥረት ሁሉ ጌታ ከእኛ ጋር በጣም ኅብረት ማድረግ ከመፈለጉ የተነሣ፣ ከእርሱ ጋር ግንኙነት የማድረግ ኃይል እንዲሰጠን የራሱን መንፈስ እኛ ውስጥ አኑሮአል፡፡ እንዴት ይገርማል! **ፓስተር ኬኔዝ ሔገን** እንዲህ እንዲህ ይላል፣

> ‹‹እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ በልሳን ስንጸልይ መንፈሳችን መንፈስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያደርጋል፡፡ ልዕለ ተፈጥሮአዊ በሆነ መለኮታዊ መንገድ ከእርሱ ጋር እንገናኛለን… በልሳን መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት የመጀመሪያ ማስረጃ ብቻ ሳይሆን፣ በአንድ ሰው ቀሪ የሕይወት ዘመን ሁሉ ቀጣይ ልምምድ ነው፡፡ ለምን ዓላማ? እግዚአብሔርን በጥልቀት ለማምለክ እንዲረዳን፡፡
> በልሳን መጸለይና እግዚአብሔርን ማምለክ መቀጠል፣ እርሱ በውስጣችን የመሆኑን እውነት የበለጠ እንድንገነዘብ ይረዳናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በየዕለቱ በውስጤ መሆኑን መገንዘብ፣ የአኗኗሬ ሁኔታ ላይ ውጤት ይኖረዋል፡፡››[1]

በመንፈስ ስንጸልይ፣ በራሳችን አእምሮ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር አእምሮ እየጸለይን ነው፡፡ የእርሱ መንፈስ በእኛ ውስጥ፣ እንደ እግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ይጸልያል!

በየዕለቱ በመንፈስ መጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ራሳችንን ከእርሱ ጋር የምናያይዘው በዚህ ሁኔታ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለማድረግ የምትሰጠው ጊዜና ቦታ ምን ያህል ነው? የእርሱን ጥልቅና ግላዊ ፍቅር መንፈስ የሚያሳይህ ምን ያህል ነው?

*ጊዜና ስፍራ ከሌለህ መቼና የት ከአንተ ጋር መገናኘትና ጥልቅ ፍቅሩን እንዲያሳይህ እንደሚፈልግ መንፈስ ቅዱስን ጠይቀው፡፡*

**በልሳን የመናገር ስጦታን እየናቅህ ወይም ችላ እያልህ ይሆን? ከሆነ፣ ለምን? ይበልጥ ቀና በሆነና ብርቱ በሆነ ብርሃን የመንፈስን ቋንቋ አስፈላጊነት ማየት እንድትችል ይህ ትምህርት የረዳህ እንዴት ነው?**

_____

_____

_____

_____

*የልሳን ስጦታን ንቀህ ወይም ችላ ብለህ ከሆነ፣ ይቅር እንዲልህና በአዲስ ሁኔታ በመንፈሱ እንዲሞላህ እግዚአብሔርን ለምነው፡፡*

**በልሳን በሚናገሩበት ጊዜ አንድ ወይም ሁለት ቃላት ብቻ በመጠቀማቸው፣ አንዳንዶች የጸሎት ቋንቋቸውን ትክክለኛነት መቀበል ከብዷቸዋል፡፡ ይህ አንተንም ይመለከት ይሆን? እንደዚያ ከሆነ፣ ለስለስ ባለ ድምፁ መንፈስ ቅዱስ፣ ‹‹እወድሃለሁ፡፡ አንተስ እኔ በሰጠሁህ ትጠቀምበታለህ? በተሰጡህ ቃሎች፣ በመጠቀም እኔን ትወደኛለህ፤ ደግሞስ ታከብረኛለህ? ምንም እንኳ ጥቂት ቢሆኑም፣ በእኔና በአንተ መካከል ያሉ ልዩ ቃላት ናቸው›› በማለት ሲናገርህ አስብ፡፡ ጥቂት ጊዜ ውሰድ፤ ከዚያ ምላሽህን ጻፍ፡፡**

_____

_____

_____

_____

*የአንተን ልሳን ከሌሎች ጋር አታወዳድር፡፡ መንፈስ የሰጠህን ቃላት በአደራ ተጠቀምባቸው፡፡ በጥቂቱ የታመንህ ከሆነ፣ እርሱ የበለጠ አደራ ይሰጥሃል፡፡ በተለይ ከ20-23 ላሉት ቁጥሮች የተለየ ትኩረት ሰጥተህ ማቴዎስ 25፥14-23 አንብብ፡፡*

ቀን 2 ማሰላሰያ

በመንፈስ መጸለይ…

# የእግዚአብሔርን ምስጢር ግልጽ ያደርጋል

*ለእናንተ የመንግሥተ ሰማይን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቷችኃል፤ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም። ላለው ይጨመርለታል፤ ይበዛለትማል።*

— ማቴዎስ 13፥11-12

የመንግሥቱን ምስጢር መረዳት እንደ ተሰጣችሁ ኢየሱስ ተናግሮአል። ይህን ምስጢር መረዳትን ያገኛችሁት እንዴት ነበር? ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተቀራርቦ በመኖር። የእግዚአብሔር ምስጢር የሚገለጸው በመንፈስ ስትጸልዩና ከእርሱ ጋር ጊዜ ስታሳልፉ ነው።

**ኦዝዋልድ ቻምበርስ** ጸሐፊ፣ ተናጋሪና ለእግዚአብሔር በመሰጠት ረገድ አርአያነት ያለው ሰው ነበር። በጣም ተወዳጅ በሆነው፣ ሁለንተናዬ ለእርሱ ክብር በተሰኘው መጽሐፉ እንዲህ ይላል፣

> የእውነተኛ ጓደኝነት ምልክት ምንድነው? ሐዘኑን በምስጢር ማካፈሉ ነውን? አይደለም፤ ይልቁን የእውነተኛ ጓደኝነት ምልክት ደስታን ማካፈል ነው። ብዙዎች ሐዘናቸውን በምስጢር ይነግሯችኃል፤ የመጨረሻው የመቀራረብ ምልክት ግን የደስታን ምስጢር ማካፈል ነው።›› [2]

የእግዚአብሔር መንፈስ ለእናንተ ከገለጠው እጅግ በጣም አስደናቂ ምስጢር አንዱ ምንድነው? ያ ለእናንተ ልዩ የሆነው ለምንድነው?

የግል ሐሳብህን፣ ስሜቶችህንና ምኞቶችህን ለመንፈስ ታካፍለዋለህ? ስላሉህ ትልልቅ ሕልሞችህና ፍርሃቶችህ ከእርሱ ጋር ትነጋገራለህ? እውነተኛ ወዳጆች እንደዚያ ያደርጋሉ። እስቲ ጥቂት ቆም በልና በጣም ምስጢር የምትለውን፣ ከዚህ በፊት ለማንም ያልነገርከውን ወይም ከረጅም ጊዜ ወዲህ ጨርሶ ያላነሣኸውን የልብህን ደስታ ንገረው።

በጣም ምስጢር ወይም የግሌ የምትለውን ለመንፈስ ያላካፈልህ ከሆነ፣ ለምን? ያን እንዳታደርግ የያዘህ ምን እንደ ሆነና በልብህ ያለውን ሁሉ በነጻነት ለማካፈል እንዲረዳህ ጠይቀው፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግ ሲባል መናገር ብቻ ሳይሆን፣ መስማትም ነው፡፡ ሁለቱም ሚዛን መጠበቅ አለባቸው፡፡ ለማድመጥ ጊዜ የማትሰጥ ከሆነ፣ መንፈስ የሚነግርህን መስማት አትችልም፡፡ ቻምበርስ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡ ፡

> ‹‹ደስ ስለሚያሰኙት ነገሮች እግዚአብሔር እንዲነግረን ጊዜ ሰጥተን ይሆን ወይስ፣ እርሱ ለእኛ የሚናገርበት ምንም አጋጣሚ እስከማይኖር ድረስ ሁሌም የእኛን ሐሳብ ብቻ ነው የምንናገረው? የክርስትና ሕይወትን በጀመርን ጊዜ ለእግዚአብሔር ብዙ ልመናዎች እናቀርብ ነበር፤ ከዚያም ከእርሱ ጋር እንድንቀራረብ፣ የእርሱን ዓላማ እንድንረዳ፣ እግዚአብሔር እንደሚፈልግ ግልጽ ሆነልን፡፡ የእግዚአብሔር ምስጢር ግልጥ እንዲሆንልን - ‹‹ፈቃድህ ይፈጸም›› የሚለው የክርስቶስ ጸሎት የእኛም ሆኖ ይሆን?››[3]

እግዚአብሔር ለማንኛውም ነገር ጊዜ እንዳለው ይናገራል፤ ይህም መናገርንና በጸሎት መንፈስ ውስጥ ሆኖ ጸጥ ማለትንም ይጨምራል (መክብብ 3፥1-7 ይመ.)፡፡ ‹‹በጸሎት ጊዜዬ ሁሌም የምናገረው እኔ እሆን ይሆን? ምስጢርህን እንድትገልጥልኝ ለአንተ ጊዜ እየሰጠሁ ነውን? አንተ አንዳች ነገር ልትነግረኝ ስትሞክር እኔ ግን ለመስማት ጸጥ ሳልል ቀርቼ ይሆን?›› በማለት መንፈስን ጠይቅ፡፡ እንደዚያ ከሆነ፣ ምንድነው? ጸጥ ብለህ አድምጥ፡፡ መንፈስ ቅዱስ እየተናገረህ ያለው ምንድነው?

*የክብር አባት የሆነው የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክ ይበልጥ እንድታውቁት፣ የጥበብና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ ያለ ማቋረጥ እለምናለሁ፡፡ እንዲሁም በእርሱ የተጠራችሁለት ተስፋ፣ ይህም በቅዱሳኑ ዘንድ ያለውን ክቡር የሆነውን የርስቱን ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ የልባችሁ ዐይኖች እንዲበሩ፣ ለእኛ ለምናምነው ከሁሉ በላይ ታላቅ የሆነውን ኃይሉን እንድታውቁ እጸልያለሁ፡፡*

— ኤፌሶን 1፥17-19

ቀን 3 ማሰላሰያ

በመንፈስ መጸለይ...

# ከውስጥ ሰላም ያስገኛል

*የመንፈስ ፍሬ ግን... ሰላም... ነው፡፡*

— ገላትያ 5፥22

ሰላም ምንድነው? አንዳንዴ ትክክል ያልሆነውን ነገር ማወቅ፣ ትክክለኛውን ለይተን ለማወቅ ሊረዳን ይችላል፡፡ እውነተኛ ሰላም፣ በመንፈሱ አማካይነት ኢየሱስ የሚሰጠው ሰላም፣ ባንክ ውስጥ ብዙ ብር በማኖር፣ ፍጹም ጤነኛ በመሆን፣ የሚያምር ቤት ውስጥ በመኖር፣ እንደ ልብ የምናባክነው ብር ሲኖረን፣ ወይም ከሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት የተመቻቸ ሲሆን የሚመጣ አይደለም፡፡

እውነተኛ ሰላም - የእግዚአብሔር ሰላም - ውጫዊ በሆነ ሁኔታ ወይም አካባቢ አይገለጥም፡፡ እውነተኛ ሰላም በአዳጋች ሁኔታ ውስጥ አለመናወጥ ነው፡ ፡ በችግሮች መካከል በአእምሮ፣ በስሜት፣ በመንፈሳዊ ሕይወት፣ ጸጥተኛና የተረጋጋ የመሆን ችሎታ ነው፡፡

ቆም በልና፣ ስለ ሰላም ያለኝ ግንዛቤ ምንድነው? አለኝ የምለው ሰላም ምን ላይ የተመሠረተ ነው? ስለ ሰላም ያለኝ ዕውቀት፣ ከመንፈስ ከሚገኘው እውነተኛ ሰላም የተለየ የሆነው እንዴት ነው? መለወጥ ያለበት ምንድነው? በማለት ራስህን ጠይቅ፡፡

ክርስቶስ በከፈለው መሥዋዕት አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀናል፡፡ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት በኩል የእግዚአብሔር ሰላም ተሰጥቶናል፡፡ ኢየሱስ ራሱ እንዲህ ብሏል፤

> *‹‹ሰላምን እተውላችኃለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኃለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም፡፡ ልባችሁ አይጨነቅ፣ አይፍራም፡፡*
>
> – ዮሐንስ 14፥27

ከሰላም አለቃ ባገኘነው ሰላም ምንድነው ማድረግ ያለብን?

የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ፤ የምታመሰግኑም ሁኑ፡፡

—ቈላስይስ 3፥15

ከላይ ያለውን ጥቅስ በጥንቃቄ አንብቡ፤ ክርስቶስን የሰላማችሁ ምንጭ ማድረግን አስመልክቶ መንፈስ ቅዱስ ምን እየተናገራችሁ ነው?

መንፈስ እኛን ወደ እግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ከሚመራበት መንገድ አንዱና ዋናው፣ ሰላሙ በውስጣችን እንዲኖር በማድረግ ነው፡፡ ‹‹የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል›› በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ይህን ማለቱ ነው (ሮሜ 8፥16)፡፡ እግዚአብሔር እንዲመራህ የምትፈልገው በአሁኑ ጊዜ ማድረግ ያለብህ ውሳኔ ምንድነው? ቆም በልና በመንፈስ ጸልይ፡፡ ከዚያ የእርሱ ሰላም እስኪመሰክርልህ ጠብቅ፡፡ ምን እየተናገረህ ነው?

ቀን 4 ማሰላሰያ

## በመንፈስ መጸለይ...

# ጥበብና ምሪት ይሰጣል

*ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጐድለው፣ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፤ ለእርሱም ይሰጠዋል፡፡*

— ያዕቆብ 1፥5

ጥበብና ምሪት የሚሰጥ ማነው? መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ኢሳይያስ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የዕውቀትና የምክር መንፈስ፣ በማለት ጠርቶታል፡፡ ኢየሱስም ወደ እውነት ሁሉ የሚመራን መምህራችን እንደ ሆነ ተናግሮአል፡ ፡ ለመሆኑ፣ መምህሩ የት ነው የሚኖረው? እኛ ውስጥ - ቤተ መቅደሱ ውስጥ፡ ፡ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ጥበብ ሲጐድላችሁ፣ በአእምሮና በመንፈስ ጸልዩ፤ እርሱም የሚያስፈልጋችሁን ምሪት ይሰጣችኋል!

ጌታ እና መንፈስ አንድ መሆናቸውን በማስታወስ፣ እነዚህን ድንቅ የተስፋ ቃሎች ረጋ ብለህ ለማሰላሰል ጊዜ ውሰድ፡፡

> እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ‹‹እኔ እግዚአብሔር አምላክህ የሚበጅህ ምን እንደ ሆነ የማስተምርህ፣ መሄድ በሚገባህ መንገድ የምመራህ ነኝ፡፡››
>
> – ኢሳይያስ 48፥17

> ወደ ቀኝም ወደ ግራም ዘወር ብትል ጆሮህ ከኃላህ፣ ‹‹መንገዱ ይህ ነው፤ በእርሱ ሂድ›› የሚል ድምፅ ይሰማል፡፡
>
> – ኢሳይያስ 30፥21

> አስተምርሃለሁ፤ በምትሄድበትም መንገድ እመራሃለሁ፤ እመክርሃለሁ በዐይኔም እከታተልሃለሁ፡፡
>
> – መዝሙር 32፥8

> አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፡፡
>
> – ዮሐንስ 14፥26

> የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡፡
>
> – ዮሐንስ 16፥13

*እግዚአብሔር ሆይ፣ አካሄድህን እንዳውቅ አድርገኝ፤ መንገድህንም አስተምረኝ፡፡ አንተ አዳኜ አምላኬም ነህና በእውነትህ ምራኝ አስተምረኝም፤ ቀኑን ሙሉ አንተን ተስፋ አድርጌአለሁ፡፡ …ዝቅ ያሉትን በፍትሕ ይመራቸዋል፤ ለትሑታንም መንገዱን ያስተምራቸዋል፡፡ … እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ማን ነው? በመረጠለት መንገድ ያስተምረዋል፡፡*

– *መዝሙር* 25፥4-5፣ 9፣12

ጥበብና ምሪት እየፈለግህ ያለው ለምንድነው? ሥራህን? ጤናህን? ትዳርህን? ልጆችህን? ወይም ኢኮኖሚህን በተመለከተ ይሆን? ሁኔታው ምንም ይሁን ምን፣ በእነዚህ ርምጃዎች መሠረት ለመኖር ሞክር፣

1. *ባለፈው ጊዜ በሰጠህ ምሪት እርሱን በማመስገን፣ ጥበብ የምትፈልግበትን ምክንያት ለእግዚአብሔር ግለጥ (ፊልጵስዩስ 4፥6-7 ይመ)፡፡*
2. *በመንፈስ ጸልይ፡፡ መንፈስ በአንተ ውስጥ መጸለይ የፈለገውን ያህል ረዘም አድርገህና በጋለ ፍላጐት በልሳን ጸልይ (ኤፌሶን 6፥18፤ ሮሜ 8፥26-27 ይመ)፡፡*
3. *ትርጉሙን እንዲሰጥህ መንፈስን ለምን፡፡ ስትጸልይበት የነበረውን ምስጢር እርሱ ይገልጥልሃል (1 ቆሮንቶስ 14፥13 ይመ)፡፡*
4. *የሚገልጥልህን ጻፍ (ወዲያውኑ እውን ባይሆን እንኳ፣ መፈጸሙ እንደማይቀር በመገንዘብ)፡፡*
5. *በሰጠህ ምሪት መሠረት ለመኖር መንፈስ ቅዱስን ጸጋ ለምነው፡፡*

**ጥበብና ምሪት የምፈልግበት ትልቁ ችግር** ------------------------ ነው፡፡

---

**ይህ መንፈስ ቅዱስ የሰጠኝ ጥበብና ምሪት ነው፣**

---

---

---

---

### በመንፈስ መጸለይ…

# ያበረታሃል ደግሞም ያንጽሃል

*በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል…*

— 1 ቆሮንቶስ 14፥4

በልሳን እንዳትጸልይ ለማድረግ ጠላት የሚዋጋው ለምንድነው? 1 ቆሮንቶስ 14፥4 አሳማኝ ምክንያት ይሰጣል፡፡ ብርቱ እንድትሆን ስለማይፈልግ ነው፡፡ በመንፈስ ስትበረታ፣ ለክርስቶስም ብርቱ ትሆናለህ፤ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ለሰይጣን መንግሥት ትልቅ ስጋት ትሆንበታለህ፡፡

የመኪናህ ኦልተርኔተር፣ ባትሪህን ሪቻርጅ እንደሚያደርገው ሁሉ፣ በመንፈስ መጸለይም መንፈስህን ሪቻርጅ ያደርጋል፡፡ ፍርሃትን፣ መደበትንና አሉታዊነትን ያርቃል፡፡ ሊገለጥ በማይቻል መንገድ አንተን ራስህን ያንጽሃል፡፡ በልሳን ስትጸልይ፣ የእግዚአብሔር ሓልዎትና ኃይል ማደሪያ ቤት የመሆን ዐቅምህ ይጨምራል፡፡

በመንፈስ የምትጸልየው ዘወትር ነው ወይስ አልፎ አልፎ ብቻ? ዘወትር ከሆነ፣ ምን ያህል ዘወትር? ለምን ያህል ጊዜ? አልፎ አልፎ ከሆነ፣ ለምን?

በመንፈስ በመጸለይ ጊዜ ስታሳልፍ ውስጥህ ምን ይሆናል? ከዚህ የተነሣ የተመለከትካቸው ሌሎች የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችና መገለጦች ምንድናቸው? እነዚህ ይበልጥ ለመጸለይ ምን ያህል አበረታቱህ?

አድካሚና አታካች ሁኔታዎች ሲገጥሙህ ብዙ ጊዜ የምትሰጠው ምላሽ ምንድነው? በመንፈስ መጸለይ ሞክረሃል? ቆም በልና፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ የእኔን ተፈጥሮአዊና አሉታዊ ምላሽ፣ በልሳን ወደ መጸለይ ልዕለ ተፈጥሮአዊና አዎንታዊ ምላሽ ለውጠው፡፡ ከዚህ በፊት ከማውቀው ይበልጥ በአንተ በራስህ ልሞላ!›› በማለት ጸልይ፡፡

ከዕለት ተዕለት ሕይወትህ የበለጠውን ድርሻ እንዲወስድ መንፈስ ቅዱስ ምን ርምጃ እንድትወስድ እየነገርህ ነው? ጻፋቸው፣ ተግባር ላይም አውላቸው፡፡

በልሳን እንዳትጸልይ ለማድረግ ጠላት የተለያዩ ሐሳቦችን ወደ አእምሮህ ማምጣቱና ሥጋዊ ስሜቶችህንም ማወኩ ጥርጥር የለውም፡፡ በአብዛኞቹ አማኞች ላይ እንዲህ ያደርጋል፡፡ ከታች ያሉት እርሱ ከሚያቀርባቸው አንዳንድ ምክንያቶችና ሰበቦች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በጣም የተለመዱ ናቸው አይደል? አንተ የምታስባቸው ሌሎች ምክንያቶችና ሰበቦችንም ጻፍ፤ ከዚያም ጠላት ለሚያመጣቸው ሐሳቦች የእግዚአብሔር ኃይል ያለባቸው መልሶች እንዲሰጥህ መንፈስ ቅዱስን ጠይቀው፡፡

ያ የእግዚአብሔር ሳይሆን የአንተ ነው፡፡

ሌላው የሚለውን በድጋሚ እየተናገርህ ነው፡፡

ምንም አይጠቅምህም፡፡

በልሳን እየጸለይሁ እንደ ሆነ አይሰማኝም፡፡

ሁለት ቃሎች ብቻ እየተናገርኩ ነው፡፡

እገሌና እገሌ ቢሰሙኝ ምን ይሉኛል?

ወዳጆቼ፣ በልሳን መጸለይ እንደሌለባችሁ ጠላት አያታልላችሁ፡፡ የእርሱን ሐሳብ አፍርሱ፤ እነዚህን ስሜቶች አልፋችሁ ሂዱ፡፡ በየዕለቱ አንደበታችሁን በመክፈት፣ ‹‹እጅግ ቅዱስ በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ፤ በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ›› (ይሁዳ 20)፡፡

# የውይይት ጥያቄዎች

1. በልሳን መጸለይ፣ (መንፈስ በሚሰጠው ቋንቋ) በጣም ጠቃሚ ነው፡፡፡ የምትችለውን ያህል የምታስታውሳቸውን ጥቅሞች ዘርዝር፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አሁን ባለበት ሁኔታ በሕይወትህ በጣም ጠቃሚ ሆኖ ያገኘኸው የትኛውን ነው? ነጻነት ከተሰማህ ለምን እንደ ሆነ አካፍል፡፡

2. እግዚአብሔር የልሳንን ስጦታ ለእኛ ከሰጠበት ምክንያት አንዱ፣ እየሆነ ያለውን ጠላት እንዳያውቅ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ዐዋቂ ነው፤ ሰይጣን ግን አይደለም፡፡ ጠላት የመንፈስ ቋንቋ መለኮታዊ ፍሪኩዌንሲ መረዳት አይችልም፡፡ በልሳን ስትጸልይ (ስትማልድ)፣ በሕይወትህም ሆነ በሌሎች ሕይወት ዲያብሎስ የነበረው ዕቅድ የከሸፈበት አጋጣሚ ካለ አካፍል፡፡

   *መሪዎች - ግምት ውስጥ የምታስገቧቸው ጥቅሶች ሉቃስ 10፥19፤ ኤፌሶን 6፥10-18፤ 2 ቆሮንቶስ 10፥3-5፤ ማቴዎስ 11፥12፤ ራእይ 12፥11 ናቸው፡፡*

በጸሎትና በልመና ሁሉ በማንኛውም ሁኔታ በመንፈስ ጸልዩ፤ ይህን በማሰብ ንቁ፤ ስለ ቅዱሳንም ሁሉ በትጋት ልመና አቅርቡ፡፡

— ኤፌሶን 6፥18

3. በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ ስንሆን፣ ምን ማድረግ እንዳለብን ለማወቅ ጥበብ ካስፈለገን፣ መለኮታዊ ምሪት ለመቀበል በመንፈስ ቅዱስ መጸለይ እጅግ በጣም ጠቃሚ ቁልፍ ነው፡፡ ምሳሌ 20፥5፤ 1 ቆሮንቶስ 14፥13 እና ዮሐንስ 7፥38-39 በጥንቃቄ አንብብ፡፡ በልሳን መጸለይ በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ልባችን ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔር ሐሳብ እንደሚያወጣ ግለጽ፡፡

4. ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት በማድረግ መኖር፣ የተሰወረ የመንፈስ ቅዱስን «ምስጢር» (ሐሳብ) ይገልጻል፡፡ እነዚህ ምስጢሮች ወደ የትኛው ቤተ ክርስቲን መሄድ እንዳለብን፣ ማንን መግባት እንዳለብን፣ የትኛውን ሥራ መምረጥ እንዳለብን፣ የትኛውን ቤት መግዛት እንዳለብን፣ ለሌሎች እንዴት መጸለይ እንዳለብን፤ እንዴት ጥሩ የትዳር ጓደኛ ወይም ጥሩ ወላጅ መሆን እንደምንችል፣ በመሥሪያ ቤት የሚገጥሙንን አዳጋች ሁኔታዎች በተመለከተ ምን ማድረግ እንዳለብን የመሳሰሉትን ሁሉ ያካትታሉ፡፡ ፈቃደኛ ከሆንህ ከእነዚህ ሁኔታዎች ለአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑት መልስ በማግኘት ረገድ በመንፈስ መጸለይ ምን ያህል እንደ ረዳህ ለቡድኑ አካፍል፡፡

5. 1 ቆሮንቶስ 14፥15 ላይ በመንፈስ መጸለይና በአእምሮ መጸለይ ስላላቸው ጠቀሜታ እናያለን፡፡ በአእምሮ የመጸለይ አንዳንድ ጥቅሞች ምንድናቸው?

በመንፈስ መጸለይ በበለጠ ትክክለኛነትና በማስተዋል እንድንጸልይ የሚረዳን እንዴት ነው?

6. 1 ተሰሎንቄ 5፥17፣ ‹‹ያለ ማቋረጥ ጸልዩ›› በማለት ይመክረናል፡፡ እንዲህ ማለት ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ መጸለይ አለብን ማለት ነው ወይስ ስለ ሌላ ጉዳይ ነው የሚናገርው? 1 ተሰሎንቄ 5፥16-19 አንብቡና እግዚአብሔር በሚነግረን ላይ ተወያዩ፡፡

7. በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አንዳንድ አማኞች፣ ይህን አስደናቂ ስጦታ ያልተቀበሉ ወገኖችን ዝቅ አድርገው ያዩዋቸዋል - እንደ ሁለተኛ ዜጋ ክርስቲያኖች ይቆጥሩዋቸዋል፡፡ ሰዎች በዚህ መልኩ አይተውህ ያውቃሉ? ከሆነ፣ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች አማኞች ጋር የነበረህን ግንኙነት የጐዳው እንዴት ነበር? በማወቅም ይሁን ባለማወቅ፣ አንተስ ሌላውን ወገን በዚህ መልኩ አይተህ ታውቃለህ? በመንፈስ መሞላትን በተመለከተ ምን ዓይነት ዝንባሌ ሊኖርህ ይገባ ነበር?

## ምዕራፉ በአጭሩ

- ከመንፈስ ጋር ያለን ቀረቤታ ከሚገለጥበት መንገድ አንዱ፣ ትክክለኛ ጊዜና ቦታ በመምረጥ በልሳን መጸለይ ነው፡፡
- አንዳንዶች አላግባብ ስለ ተጠቀሙበት ብቻ የልሳንን ስጦታ አትናቅ፣ ችላ አትበል፣ ወይም በልሳን መጸለይህን አትተው፡፡
- በልሳን ስትጸልይ፣ የእግዚአብሔርን ምስጢር እየተናገርህ ነው፤ የጸሎትህን ምስጢር ትርጉም እንዲሰጥህ መጠየቅ ትችላለህ፡፡
- የመንፈስ ኃይል የሚሰጠው ለትሑታን ነው፡፡ ትሕትና የእግዚአብሔር ምስጢሮችን በር ይከፍታል፡፡
- ጥበብ ሲያስፈልግህ፣ በጥልቀት እግዚአብሔርን ማምለክ ስትፈልግ፣ ወይም ለሌሎች ስትማልድ፣ በመንፈስ መጸለይ ትችላለህ፡፡ ከእነዚህ አቅጣጫዎች አንጻር መንፈስ ችሎታችንን ያሰፋዋል፡፡
- ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ምሪት ልባችን ውስጥ በሚሰማን ሰላም ይመጣል፤ ስለ አንድ ነገር በመንፈስ ስንጸልይ ሰላም የሚሰማን ከሆነ፣ ወደ ፊት መሄድ እንዳለብን መንፈስ ቅዱስ ለመንፈሳችን እየመሰከረ ነው፡፡
- በመንፈስ መጸለይ መላው ሁለንተናችንን ያድሳል፣ ያለመልማል፣ ያንጻል፡፡ በየቀኑ በመንፈስ ቋንቋ ጸልይ!

# ጥያቄና መልስ

*የሚከተለው ጆን እና ሊዛ ቢቨሬ ካደረጉት ጥያቄና መልስ ቀጥታ ስርጭት የተወሰደ ነው፡፡*

**ሊዛ - አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ሌሎችን ቅር ላለ ማሰኘት፣ የመንፈስ ቅዱስን ሕልዎት ችላ ማለታቸውን ተናግረሃል፡፡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት፣ ‹‹እንግዳ ልምምድ›› ወይም አላስፈላጊ ረጅም አገልግሎት የሌለበት የመንፈስ ቅዱስ አሠራር እንደ ገና እንዲመጣ እየፈለጉ ነው፡፡ ያን እንዴት ነው ማድረግ የሚችሉት?**

**ጆን** - ቀደም ሲል እንዳልኩት መንፈስ ቅዱስ ጨዋ ነው፡፡ ምንጊዜም ቢሆን የመጀመሪያውን ርምጃ መውሰድን ለእኛ ነው የሚተወው፡፡

ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ወይም ለሰዎች እያገለገልኩ እያለ፣ ሰዎች ድነትን ለመቀበል ወደ ፊት እንዲመጡ ጥሪ ሳቀርብ፣ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ሆይ፣ እባክህ ንካቸው›› እላለሁ፡፡ ብዙም ሳይቆይ የእርሱ መገኘት ይገለጽና በቦታው ያሉ ሰዎች ማልቀስ ይጀምራሉ፡፡ እንደዚያ መሆኑን በጣም ነው የምወደው፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ሰማያዊ ስጦታን ስለ መቅመስ ይናገራል (ዕብራውያን 6፥1-6 ይመ.) ሰማያዊ ስጦታን ከቀመሱ ወይም የመንፈስን መገኘት ከተለማመዱ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ከእምነት ወደ ኃላ እንደማይመለሱ ተረድቻለሁ፡፡

አንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን መለማመድ ያቆመ አንድ

ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያገለገልኩ ነበር፡፡ ከስብሰባዎቹ በአንዱ የእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት ይገለጽ ጀመር፡፡ በቦታው የነበሩ ሰዎች እያለቀሱ ነበር፤ የእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት ጉልህ በሆነ መልኩ ይሰማን ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ፣ ‹‹አሁን እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ንገራቸው›› በማለት እግዚአብሔር ተናገረኝ፡፡ እንደዚያ ካደረግሁ በኃላ፣ ስብሰባውን አበቃሁ፡፡ በኃላም ፓስተሩ ወደ እኔ መጥቶ፣ ‹‹በጣም ይገርማል! ስብሰባው ለተጨማሪ አንድ ሰዓት መቆየቱ አይቀርም፤ ብዙ ጊዜ ሲሆን እንደሚታየው አንዳንድ ከሥርዐት ወጣ ያሉ ነገሮች መሆናቸው አይቀርም›› በማለት እያሰብኩ ነበር፡ ፡ እግዚአብሔር አንተን የመራበት መንገድ ደስ ብሎኛል፡፡ እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን እንዳበቃ ስትናገር፣ እኔም ዓላማውን እንደ ፈጸመ ይሰማኝ ነበር፡፡ በኃላም፣ አሁን ስብሰባው አብቅቷል›› በማለት ተናገርህ አለ፡፡ ሁለት ደቂቃ እንኳ ባልሞላ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ መገኘት ሲገለጥና ሰዎችም ጥልቀት ባለው ሁኔታ ሲነኩ አይቻለሁ፡፡

**ሊዛ** - ጆንና እኔ ይህን ውይይት ያደረግነው በቅርቡ ነበር፡፡ አንዳንዴ ስብሰባው ላይ ለመስበክ ሰላሣ አምስት ደቂቃዎች ብቻ ይበቃን ነበር፤ በመሠረቱ ያ የእኛ ሰላሣ አምስት ደቂቃ ነበር፡፡ ስለዚህ ለሰላሣ አምስት ደቂቃ ከመስበክ ይልቅ-

**ጆን** - ለሰላሣ ደቂቃ ብቻ እንሰብካለን፡፡

**ሊዛ** - ወይም በመልእክቱ መካከል የራሱን ሐሳብና ዓላማ እንዲፈጽም ለመንፈስ ቅዱስ ጊዜ እንሰጣለን፡፡ አንዳንዴ አገልጋዮች ጊዜውን እነርሱ ብቻ በመያዛቸው፣ መንፈስ ስፍራውን እንዲይዝ ጊዜ አይሰጡም፡፡

**ሊዛ - በመንፈስ ቅዱስ ‹‹መሞላትን›› የሚሆነውን በተመለከተ ብዙ ብለሃል፡ ፡ ግን እርሱ ሲከለክለን የሚሆነውን በተመለከተስ ምን ትላለህ? ሁኔታው ምን ይመስላል?**

**ጆን** - የቈላስይስ መልእክት፣ ‹‹የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይንገሥ›› ይለናል

(ቈላስይስ 3፥15 ይመ.)፡፡ ሮሜ ምዕራፍ 8 ደግሞ፣ ‹‹በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና›› ይላል (ቁጥር 14)፡፡ እዚያ ላይ ያለው ልጆች የሚለው ቃል ወንዶችንም ሆነ ሴቶች ልጆችን የሚመለከት ሲሆን፣ ሑዮስ (huios) ከሚለው ግሪክ ቃል የተተረጐመ ነው፤ ቃሉ፣ ‹‹በሳል ወይም አስተዋይ ልጆች››[1] ማለት ነው፡፡ እንደምናውቀው ክርስቲያን የተባለ ሁሉ፣ በመንፈስ የሚመራ አይደለም፡፡ ብዙዎቹ እየተመሩ ያሉት በስሜታቸው፣ በአእምሮአቸው፣ በሁኔታዎችና ባሉበት አካባቢ መሠረት ነው፡ ፡ እግዚአብሔር ግን በሳልና አስተዋይ ልጆች፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ይመራሉ ይላል፡፡ መንፈስ የሚመራን እንዴት ነው? መንፈሳችን ውስጥ በመመስከር ነው (ቁጥር 16)፡፡ ለምሳሌ ወደ አንድ አገር መሄድ እፈልጋለሁ እንበል፤ መንፈስ ግን ያንን እንዳደርግ ካልፈለገ መንፈሴ ውስጥ ቅርታ፣ መታወክና ሌላም ዓይነት ነጻነት ማጣት ሊሰማኝ ይችላል፤ ያ የመንፈስ ምስክርነት ነው፡፡

**ሊዛ** - እንደዚያ አድርገህ ማለት መሄድ ወዳልነበረብህ ቦታ ሄደህ ታውቃለህ?

**ጆን** - አዎን፡፡

**ሊዛ** - ታዲያ ውጤቱ ምን ሆነ?

**ጆን** - ውጤቱማ፣ ‹‹ሁለተኛ እንደዚያ አላደርግም!›› እስክል ድረስ መራራ ነበር፤ በጣም አስከፊ ነበር፡፡ የዚያ ዓይነት ምስክርነት ካለ ማቆም እንዳለብኝ ነው የተማርኩት፡፡

አንድ ጊዜ ደግሞ አንድ ሌላ ቦታ እንዳገለግል ግብዣ ተቀብዬ ነበር፤ እዚያ እንደምገኝም ቃል ገብቼ ነበር፤ በኋላ ግን ወደዚያ እንድሄድ ጌታ እንደማይፈልግ ተሰማኝ፡፡ ስለዚህም፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ አንዴ ቃል ከገባሁ የሚጐዳኝ ቢሆን እንኳ፣ የገባሁትን ቃል ማክበር እንዳለብኝ ቃልህ ይናገራል፡፡ ወደዚያ ስብሰባ መሄዴ ነው፡፡ የአንተ ጥበቃ ያስፈልገኛል›› በማለት ጸለይኩ፡፡ ያን በማድረጌ አልገሠጸኝም፡፡ ጉዞው ጥሩ የሚባል ዐይነት አልነበረም፤ ያም ሆኖ

እንኳ የእርሱ ጥበቃ ይሰማኝ ነበር፡፡

ሆኖም፣ ገና ከመጀመሪያው፣ አታድርገው ወይም የአገልግሎት ግብዣውን አትቀበል የሚለውን የመንፈስ ምስክርነት መቀበሉ ጥሩ ይሆን ነበር፡፡ የመንፈስ ምስክርነት ድንቅ ነው፤ ተለይቶ መታወቅ ይችላል፡፡ የበለጠ ከእርሱ ጋር በተመላለሳችሁ መጠን፣ በዚያው ልክ ምሪቱን ለመቀበል ንቁ ትሆናላችሁ፡፡

**ሊዛ** - ስለ ዶክተር ቾ እና ስላከናወኑት ድንቅ ሥራ ተናግረሃል፤ በመንፈስ በመጸለይም ራሳቸውን በእግዚአብሔር ኃይል ይሞሉ እንደ ነበር አመልክተሃል፡ ፡ ሰፋ ያለ ጊዜ ከመንፈስ ጋር ለማሳለፍ በመፈለግ ብዙ ጥሪዎችን ወይም ግብዣዎችን እንደማይቀበሉ እኔም አውቃለሁ፤ ይህ በዶክተር ቾ ሕይወት ውስጥ ብዙዎች ልብ ያላሉት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ የማይቻለውን ነገር በሕይወታችን ለማድረግ አንዳንድ እኛ ማድረግ የምንችላቸውን ነገሮች እንዳናደርግ፣ ‹‹አይሆንም›› ወይም ‹‹እንዳታደርጉት›› በማለት መንፈስ ቅዱስ፣ ይነግረን ይሆናል፡፡

**ጆን** - ደቀ መዛሙርቱ በመንፈስ ተሞልተው እንደ ነበር የሐዋርያት ሥራ ያመለክታል፤ በኋላ ደግሞ ጴጥሮስ፣ ‹‹በመንፈስ ተሞልቶ›› ለመሪዎቹ እንደ ተናገረ ሐዋርያት ሥራ 4፥8 ላይ እናነባለን፡፡ ከሐዋርያት ሥራ 4፥31 ደግሞ አማኞች በመንፈስ ቅዱስ እንደ ተሞሉ እንመለከታለን፡፡ በመንፈስ መሞላት አንድ ጊዜ ብቻ የሚሆን ጉዳይ አይደለም፡፡ ሁልጊዜ፣ ‹‹በመንፈስ ተሞሉ እንጂ፣ በወይን ጠጅ አትስከሩ›› በማለት እግዚአብሔር ነግሮናል (ኤፌሶን 5፥18)፡፡ በመንፈስ የምንሞላው ዘወትር በዚያው መንፈስ መሞላታችንን እንድንቀጥል እንጂ፣ አንድ ደረጃ ላይ ባዶ እስክንሆን ድረስ ጠብቀን የምናደርገው አይደለም፡ በትዳራችን ውስጥ ፍቅራችንን ማደስና፣ እንደ ገና በዚያው ፍቅር መሞላት ያለብን ጊዜ አለ፡፡ በተለያየ ጊዜ ከትዳር ጓደኞችን ጋር አብረን ላንሆን እንችላለን፤ ይሁን እንጂ፣ እንደ ገና ስንገናኝ ቀድሞ በነበረን ፍቅር እንዲያውም ከቀድሞው በበለጠ ፍቅር እንሞላለን፡፡

**ሊዛ** - ያን ሆን ብለን እናድርግ ነው እያልህ ያለኸው፡፡

**ጆን** - አዎን፣ ሆን ብለን እናድርገው ነው እያልኩ ያለሁት፡፡ እንደ ተሞላን እንዝለቅ፡፡ በመንፈስ መሞላት መቋረጥ የሌለበት ሂደት ነው፡፡ በመንፈስ መሞላት በመዝሙና በውዳሴ፣ በመንፈሳዊ ዝማሬ ይገለጣል (ኤፌሶን 5÷18-20 ይመ.)፡፡ በዚህ ሳምንት ብዙ እንድዘምር እየተሰማኝ ነው -

**ሊዛ** - ቴሌቪዥንን የመሳሰሉ የሚያደናቅፉ ነገሮችን በመዝጋት?

**ጆን** - አዎን፣ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ቴሌቪዥኑን እዘጋለሁ፡፡

**ሊዛ** - ጊዜያችንንና ትኩረታችንን የሚያደናቅፉ ነገሮችን ማራቅ አለብን፡፡

**ሊዛ - አማኞች ሁሉ መንፈሳዊ ስጦታዎችን መለማመድ ይችላሉ ወይስ ያ ለአገልጋዮች ብቻ ነው?**

**ጆን** - ማንኛውም አማኝ የመንፈስ ስጦታዎችን መለማመድ እንደሚችል ነው የማምነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ተአምር የሚያሻው ሁኔታ ውስጥ ካለ፣ ማንኛውም አማኝ ያን ተአምር መለማመድ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የተለያዩ ስጦታዎችን አኑሮአል፤ ሰዎቹ በተገኙበት ወይም በሄዱበት ሁሉ እነዚያ ስጦታዎች እውን ይሆናሉ፡፡

ሊዛና እኔ የልብ ሕመም ያለባቸውን ሰዎች ብቻ የመፈወስ ስጦታ ያለው አንድ ግለ ሰብ እናውቃለን፡፡ የልብ ሕመም ያለባቸው ሰዎች ከተለያዩ አካባቢዎች እርሱ ወደሚያደርገው ስብሰባ ሄደው ይፈወሳሉ፡፡ ይህ የፈውስ ስጦታ የተጠራበትን አገልግሎት በመፈጸም ረገድ በጣም ረድቶታል፡፡

ልጁ መታጠቢያ ገንዳ ውስጥ በመስጠም ሞቶ የነበረ፣ አንድ ጓደኛዬን አስታውሳለሁ፡፡ ልጁ ከሞተ 45 ደቂቃዎች አልፈው ነበር፡፡ ያ ሰው የሆነውን ነገር ሲነግረኝ፣ ‹‹ጆን ለሰላሣ ደቂቃ ያህል ጸለይኩ ግን ምንም ነገር አልሆነም፡፡ የድንገተኛ ክፍል ሐኪሞችም ርዳታ ተስፋ ሰጪ አልነበረም፡፡ ከዚያ አንድ ነገር ዐናቴን መታኝ፡፡ ከዚያም ለልጄ አስክሬን፣ ‹‹በሕይወት ትኖራለህ እንጂ አትሞትም›› በማለት ተናገርኩ አለ፡፡ ከዚያም ልጁ ከሞት ተነሣ፡፡ በዚያ

ጊዜ በእርሱ ውስጥ የሠራው፣ ‹‹የእምነት ስጦታ›› እንደ ነበር ነው ሰውየው የሚያምነው፡፡ በዚያ ወቅትና በዚያ ሁኔታ ውስጥ ያ ስጦታ አስፈልጐት ነበር፤ ጌታ ደግሞ ያንኑ ሰጠው፡፡

**ሊዛ** - በዚያ ጊዜ ሰውየው አገልጋይ አልነበረም አይደል፡፡

**ጆን** - የፖሊስ ባለ ሥልጣን ነበር፡፡

**ሊዛ** - ስብሰባ እየመራ አልነበረም፡፡

**ጆን** - በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የሆነውን ስብከት ሰብኮ መመለሱ ነበር፡፡

**ሊዛ** - ግልጽ ማድረግ የፈለግሁት -

**ጆን** - ማንኛውም አማኝ፣ አዎን፣ ማንኛውም አማኝ የመንፈስ ስጦታዎችን መለማመድ ይችላል፡፡

**ሊዛ** - በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ማንኛውም አማኝ፣ በሕይወት በሚገጥመው ማንኛውም ሁኔታ ማለት ነው፡፡

**ጆን** - የፈውስ ስጦታ እስኪሰጣችሁ መጠበቅ የለባችሁም፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹የሚያምኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል... እጃቸውን በሕመምተኞች ላይ ይጭናሉ፤ እነርሱም ይፈወሳሉ›› ብሏል (ማርቆስ 16፥17-18)፡፡ ያ የሚያመለክተው አንድ ሰው እንዲፈወስ በእምነት ስትጸልዩ፣ የሚሆነውን ነው፤ እግዚአብሔር ቃሉን ስለሚጠብቅ ያንን ያከብራል፡፡

**ሊዛ** - ፓስተሩ መድረክ ላይ ቦታ እስኪሰጣችሁ መጠበቅ የለባችሁም፡፡ የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል አጥብቃችሁ ከያዛችሁ፣ የእግዚአብሔር ኃይል በዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ፣ ተራ በሚመስል ነገራችሁ ላይ ሊገለጥ ይችላል፡ ፡ ለአንድ ሰው ለመናገር፣ አንድን ሰው ለመንካት፣ ወይም ለአንድ ሰው

ለመጸለይ ወይም ለአንድ ሰው ችሮታ ለማድረግ፣ መንፈስ ከመራችሁ ችሮታ አድርጉ፤ ውጤቱ አስደናቂ ይሆናል፡፡ ደግሞም ያን ማድረግ እንችላለን፡፡

ጆን - ያ ከስጦታዎቹ አንዱ ነው - ማለት የመስጠት ችሎታ፣ ችሮታ የማድረግ ስጦታ አንድ የመንፈስ ስጦታ ነው፡፡

**ሊዛ - መንፈስ ቅዱስ የመጣው ኢየሱስን ለመግለጥ እንደ ሆነ እናውቃለን፡፡ ሆኖም፣ ስለ መንፈስ መገለጦች ስንነጋገር፣ ካለፉት ጥቂት ዐሥርት ዓመታት ወዲህ በመንፈስ መገለጥ ስም መንዘፍዘፍ፣ መሣቅ፣ መሬት መውደቅና መንከባለልን የመሳሰሉ ሁኔታዎች እያየን ነው፡፡ እንደዚህ ያሉ ነገሮች እንዴት ክርስቶስን መግለጥ ይችላሉ?**

**ጆን** - መልካም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስላልተለመዱ ዐይነት ምልክቶች ይናገራል፤ ሆኖም፣ እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ያልተለመዱ ዐይነት ምልክቶችና ድንቆች የሚሆኑበትና የሰዎችን ትኩረት ወደ ኢየሱስ የሚስቡበት፣ ወደ ኢየሱስ የሚያመለክቱበት፣ ጊዜ አለ፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ግን፣ ብዙ ጊዜ ሰዎች ትኩረታቸውን ‹‹ገላጩ›› ላይ ሳይሆን መገለጦቹ ላይ ማድረጋቸው ነው፡፡

ሲንጋፖር በነበርኩ ጊዜ አንድ የፈውስ አገልግሎት የነበረው ወንጌላዊ እኔ አገለግል ወደ ነበረበት ቤተ ክርስቲያን መጥቶ ነበር፡፡ ሰዎች ከቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ እንዲስቁ በማድረግ የሚገለጥ ስጦታ ነበረው፡፡ በዚያ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሓልዎት ወይም መገኘት በጉልህ ይሰማኝ ነበር፡፡ ምንም ሳይነካቸውና ምንም ሳይደረግ ሰዎች በድንገት ይስቁ ነበር፡፡

**ሊዛ** - ያ ሁኔታ ትክክል ቢሆንም፣ ያለ ጊዜው የተደረገ ይሆን?

**ጆን** - አዎን፣ ትኩረታችሁን ሁሉ መገለጡ ላይ አድርጋችኋልና አቁሙ ያልኩት በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ እየተከተላችሁ

አይደለም፡፡ አሁን እዚህ ማድረግ የፈለገው ይህን አይደለም፡፡ ሕዝቡ ጥልቅ እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ እንዲያድርባቸው ያደርጋል፡፡ በዚህ መልኩ የእግዚአብሔር መንፈስ ሕዝቡን ያገለግላል›› አልኩ፡፡ ከዚያም እንደ ገና እንዲጸልዩ አደረግሁ፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል መንቀሳቀስ ጀመረ፤ በዚያ አዳራሽ የነበሩ ሰዎች ማልቀስ ጀመሩ፡፡

በአንዳንድ ሁኔታዎች ቅር የሚያሰኙ መገለጦች በሚታዩበት ጊዜ ሰዎች ለታይታ የሚሆን ነገር ላይ ያተኩራሉ፡፡ መቼም፣ ባልና ሚስት በመካከላቸው ያለውን መቀራረብ በሰዎች ፊት አይገልጡትም፡፡ አንዳንዴ ግን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን መቀራረብ ለታይታ ያደርጉታል፡ ፡ «ይህን እዩ፤ እኛ'ኮ መንፈሳዊ ነን» የሚሉ ይመስላል፡፡ መንፈስ ቅዱስን ባወቅሁት ልክ ስጦታዎቹን፣ ችሎታዎቹንና ኃይሉን እርሱን በሚያስከብር ሁኔታ ጥቅም ላይ ማዋል እንዳለብኝ ነው የተረዳሁት፡፡ እርሱን የሚያሳዝን፣ እርሱን የማያስከብርና የእርሱን ክብር በሚሻማ ሁኔታ ማገልገል የለብኝም፡ ፡ 1 ተሰሎንቄ 5፥19-21 የመንፈስን እሳት አታዳፍኑ ይላል፡፡ መንፈስን ማዳፈን የሚመጣው፣ ኃይሉንና ስጦታዎቹን ችላ ስንል ነው፡፡ በፍጹም እንደዚያ አታድርጉ! ይልቁንም በጣም አክብሩት፡፡ እንደ አንድ ርካሽ ነገር ወይም ኃይል አትውሰዱት፡፡

**ሊዛ** - እግዚአብሔር የፈለገውን እንዲያደርግ መጠየቅና መጋበዝ እንዳለብን መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ አንዳንዴ መንፈስ ቅዱስ ሥራውን የሚሠራው ያልተለመደ በሚመስል መንገድ ሊሆን ይችላል፤ ያም ሆኖ በኃይል ወይም በማስገደድ አይሆንም፡፡ ትኩረት ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እንጂ፣ በምንም ዓይነት ሰዎች ላይ እንዲሆን አያደርግም፡፡

በቅርቡ ከተለያዩ ቤተ እምነቶች ከመጡ ሰዎች ጋር አብሬ ነበርኩ፡ ፡ በአንድ ወቅት ትክክል እንደ ነበረ የማምነውን፣ በኋላ ግን ከዚያ በፊት እግዚአብሔር ሕዝቡን በባረከበት ሁኔታ አሁንም በዚያው መንገድ እንዲባረክ ተስፋ በማድረግ ሰዎች ያበላሹትን ነገር አንሥተው አንዳንዶች እያፌዙ ነበር፡ ፡ እንቅስቃሴው በሂደት ቢቋረጥ እንኳ፣ አሁንም እርሱን መሳይ ነገር ነበር፤ ሰዎች እያፌዙ የነበረውም በዚያ ምክንያት ነበር፡፡ በእውነተኞቹ የመንፈስ

ቅዱስ መገለጦች ላይ ማፌዝ ተገቢ አይደለም፡፡ ከመንፈስ የሆነ ነገርን እንፈልጋለን፤ ሆኖም የምንፈልገው በእምነት እንዲሆን ነው፡፡ ሥርዐትና ጨዋነት ባለው መንገድ እንዲመጣ፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር መገኘት የታጀበ እንዲሆን ነው የምንፈልገው፡፡

**ሊዛ - አንድ ሰው ሰላም እንዳለው ቢያስብም፣ ያ ሰላም ግን ከእግዚአብሔር ላይሆን የሚችልበት ሁኔታ ይኖር ይሆን?**

**ጆን** - አዎን፣ በጣም እንጂ፡፡ ሕዝቅኤል ምዕራፍ አሥራ አራትን ብትመለከቺ፣ ጣዖቶችን በልባቸው ይዘው ወደ እርሱ ስለ መጡ ሰዎች እግዚአብሔር ሲናገር ታያለሽ፡፡ በዚህ ዘመን ጣዖት የምንለው ምንድነው? አዲስ ኪዳን ጣዖት የሚለው ምድራዊ ምኞትን፣ አግባብ ባልሆነ መልኩ አንድን ነገር መፈለግን ነው (ቈላስይስ 3፥5 ይመ.)፡፡ እንዲህ ያለ ጣዖት በልባቸው የያዙ ሰዎች ትንቢት የመናገር ስጦታ እንዳለው ወደሚያስቡት ሰው ይሄዱና፣ ‹‹እስቲ ጸልይልኝ፤ የእግዚአብሔር ቃል እኔ ላይ ተናገር›› ይሉታል፡፡ እግዚአብሔር ግን፣ ‹‹እኔ እግዚአብሔር እንደ ጣዖቱ ብዛት እመልስለታለሁ›› ይላል (ሕዝቅኤል 14፥4)፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቤ አንድ ነገር ስጠይቅ፣ ልቤ ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ አለብኝ፡፡ እንዲህ ያላደረግሁበት ጊዜ አለ፡፡ ልቤ ነጻ ባለ መሆኑ፣ ሰላም ቢኖረኝ እንኳ፣ ያ ከእግዚአብሔር አልነበረም፤ በኋላም ብዙ ሐዘንና ስብራት አምጥቶብኛል፡፡

እኔና ሊዛ ከመጋባታችን በፊት በሁለት የተለያየ ከተሞች የነበርን መሆኑ ደስ የሚለኝ በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ግንኙነታችን መቀጠል ወይም አንድ ቦታ መቆም ያለበት መሆኑን ለመወሰን የሰላሣ ቀን ጸሎት አስፈልጎናል፤ በተለይ እኔ በእርሷ በጣም ተስቤ ስለ ነበር፣ ከዚህ ተፅዕኖ ለመላቀቅ ምናልባት ሃያ አምስት ቀን ሳይወስድብኝ አልቀረም፡፡ በእነዚያ ሰላሣ ቀኖች ጸሎት እግዚአብሔር፣ ‹‹አይሆንም›› ቢለኝ ኖሮ እንኳ፣ ምንም ቅር የማይለኝ ደረጃ ላይ ደርሼ ነበር፡፡ አይሆንም ቢለኝም ለእኔም ሆነ ለእርሷ የራሱ ሰዎች አሉት ማለት ነው፡፡ እዚያ ልቤ ነጻ የሆነበት ደረጃ ላይ ስደርስ፣ በትክክል ከእግዚአብሔር መስማት ጀመርኩ፡፡

ወደ ጸሎት ስቀርብ ልቤ ነጻ እንዳይደለ ከተሰማኝ፣ ነጻ እስኪሆን ድረስ የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብና በመጸለይ አሳልፋለሁ፡፡ የግድ ከሁለት አንዱን ብቻ የምጠብቅ ከሆነ፣ የውሸት ሰላም ሊሰማኝ ስለሚችል መልሱ አዎን ቢሆን ወይም አይደለም ቢሆን፣ እግዚአብሔር የወሰነውን በደስታ መቀበል እንዳለብኝ ተምሬአለሁ፡፡

**ሊዛ** - ‹‹እንደዚህ ነው የሚሆነው፤›› ‹‹እንዲዚያ ነው የሚሆነው›› ብንልም፣ በኃላ ግን እኛ ከጠበቅነው ውጪ ሲሆን ስላየን፣ በየጊዜው ልባችንን ነጻ ማድረግ እንደሚገባ እንረዳለን፡፡ የእኛን ግምት ትተን፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ በምትፈልገው ሁሉ እንስማማለን›› ማለት መቻል አለብን፡፡

ከመንፈስ ስለሚገኝም ‹‹ማወቅ›› ተናግረሃል፡፡ Nurture የሚለው መጽሐፌን ለመጻፍ ዝግጅት እያደረግሁ እያለ ውስጣዊ መረዳት (ኢንቱይሽን) የተሰኘውን ቃል ተመልክቼ ነበር፡፡ ቃሉ ኢን እና ቲዮተር ከተሰኙ ላቲን ቃሎች የተገኘ ሲሆን፣ ‹‹ውስጣዊ መምህር››[2] ማለት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ውስጣዊ መምህራችን ነው፡፡ አዲስ ልብ ይሰጠናል (ሕዝቅኤል 36፥26 ይመ.)፣ እኛንም ያስተምራል፡፡

**ሊዛ - አንዳንድ ሰዎች ወይም ሁኔታዎች ትክክል ቢመስሉም፣ ትክክል እንዳልሆኑ የሚሰማን ጊዜ አለ፡፡ ያን በተመለከተ የምትለው አለ?**

**ጆን** - ያንን ውስጣዊ መምህር ሳላዳምጥ በቀረሁ ጊዜ ሁሉ - በውጪ ሲታይ ትክክል ቢመስልም፣ መንፈሴ ውስጥ ግን ስሕተት መሆኑ ከተሰማኝ ያንን ችላ ብዬ መሄድ ለሕይወቴ መሰናክልና ወጥመድ ነው የሚሆነው፡፡

**ሊዛ** - ብዙ ጊዜ ያ የሚሆነው የመጀመሪያ ምላሽ ብታገኝም፣ ለዚያ የራስህን ምክንያት በማቅረብ ሳትቀበለው ስትቀር ነው አይደል?

**ጆን** - አዎን፡፡ ብዙ ጊዜ ያ የመጀመሪያ ምላሽ የሚመጣው ከእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ የአንቺን ምክርና ሐሳብ ችላ ባልኩ ጊዜም ተመሳሳይ ነገር

ሲሆን አይቻለሁ፡፡

እስቲ ለባልና ሚስቶች ይህን ልናገር፡፡ እኔና ሊዛ በተጋባን ጊዜ በቀን ውስጥ አንድ ሰዓት ተኩል ያህል እጸልይ ነበር፡፡ ሊዛ ግን ለዚውም ሻውር ውስጥ ለአሥር ደቂቃ ብቻ እንደምትጸልይ አውቅ ነበር፡፡

**ሊዛ** - በዚያ ጊዜ እኔ የሙሉ ጊዜ ሠራተኛ ስለ ነበርኩ'ኮ ነው!

**ጆን** - ‹‹ሊዛ፣ እንዲህ ማድረግ እንዳለብኝ ይሰማኛል፤ እንደዚያ ማድረግ እንዳለብኝ ይሰማኛል›› በማለት ብዙ እናገር ነበር፡፡ እርሷ ደግሞ፣ ‹‹እኔ ግን እንደዚያ አይሰማኝም›› ትለኝ ነበር፡፡ ግማሹን ያህል እርሷ ትክክል እንደ ነበረች ሳይ በጣም ግራ ይገባኝ ነበር፡፡

ታዲያ አንድ ቀን፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔ በየጠዋቱ አንድ ሰዓት ተኩል ያህል እጸልያለሁ፤ ሊዛ ግን፣ ለዚያውም ሻወር ውስጥ ሆና አሥር ደቂቃ ብቻ ነው የምትጸልየው፤ ያም ሆኖ ግማሹን ያህል ትክክል የምትሆነው እርሷ ናት›› አልኩ፡፡

ጌታም፣ ‹‹ክበብ ሥራ›› አለኝ፡፡ አንድ ወረቀት ላይ ክበብ ሠራሁ፡፡ ቀጥሎም፣ ‹‹ክበቡን በ x ሙላው›› አለኝ፡፡ እኔም ክበቡ ውስጥ ብዙ x መሥራት ጀመርኩ፡፡ ከዚያም፣ ‹‹አሁን ክበቡን ዕኩል በዕኩል የሚከፍል መስመር ሥራ›› አለኝ፡፡ ክበቡን ዕኩል በዕኩል የሚከፍል መስመር አሰመርኩ፡፡



‹‹ግማሽ ኤክሶች በአንድ በኩል፣ ግምሾቹ ደግሞ በሌላ በኩል መሆናቸውን ልብ አደረግህ? ጆን ብቻህን በነበርክ ጊዜ፣ በእኔና በራስህ ሙሉ ነበርህ፡፡ ከሊዛ ጋር አንድ አካል ከሆንህ በኋላ ግን፣ ክበቡ አንተንና ሊዛን ይወክላል፡፡ አንተ በግራ በኩል ያለው ግማሽ ነህ፤ እርሷ ደግሞ በቀኝ በኩል ያለው ግማሽ ነች›› አለኝ፡፡

ከዚያም እግዚአብሔር፣ «ኤክሶቹ ምን እንደሚወክሉ ታውቃለህ? ትክክለኛ ውሳኔ ለማድረግ ከእኔ የምትፈልገውን መረጃ ነው የሚወክሉት፡፡ ችግሩ ውሳኔዎችህን ሁሉ የምታደርገው ከፊሉን መረጃ መሠረት በማድረግ መሆኑ ነው፡፡ እንደ የቤት ሰብ ራስ መረጃዎቹን አሟልተህ ውሳኔ ለማድረግ እንዲያስችልህ፣ ለሚስትህ የማሳያትን ከእርሷ መውሰድ መማር ይኖርብሃል» አለ፡፡

ውስጣዊውን መምህር በተመለከተ መጀመሪያ የሰጠኝን ምሪት ችላ በማለቴ ዋጋ የከፈልኩበት ጊዜ አለ፡፡ አንዳንዴ ደግሞ የተናገረችው ከመንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ ጥልቅ ልቦናዬ ቢያውቅም፣ ሊዛ የምትናገረውን ችላ ያልኩበት ጊዜ አለ፤ በዚህ ጊዜ - መንፈስ ቅዱስ ምንድነው የሚያደርገው? እውነቱን ይመሰክራል፡፡

አንዳንዴ ደግሞ፣ ሊዛ እምነትን መሠረት ያላደረገ ነገር የምትናገርበት ጊዜ አለ፤ ያ ፍርሃትን መሠረት ያደረገ አነጋገር ነው፤ ከዚያ ጋር አልስማማም፤ እንዲህ የሚሆነው በጣም አልፎ አልፎ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን ሊዛ ስትናገር ትክክል እንደ ሆነች ጥልቅ መንፈሴ ያውቃል፡፡ ያንን ምስክር ችላ ብል፣ ዋጋ የምከፍለው እኔ እሆናለሁ፡፡

**ሊዛ** - ጆን ለእኔ ለጋስ እየሆነ እንደ ሆነ አስባለሁ፤ ሆኖም፣ እግዚአብሔር ለእነርሱ አንድ ነገር ከተናገረ ሰዎች ሊተማመኑበት እንደሚገባ መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ ጥናት ያደረጉ ሰዎች እንደሚናገሩት መንፈስ እኛ ከተረዳነው የበለጠ እጅግ የላቀ የማወቅ ችሎታ አለው፡፡ በራሳችን መረዳት ርምጃ ስንወስድና ነገሮችን እንደ ገና ማውጣት ማውረድ ስንጀምር፣ ራሳችንን ሳይሆን ራሱ እግዚአብሔርን እየተጠራጠርን ነው፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ መናገር ከጀመረ፣ ያንን ይዘን መጓዝ አለብን፡፡

በቅርቡ የተወሰኑ ሰዎች ባሉበት አውቶብስ ውስጥ የገጠመኝን አንድ ልምምድ አስታውሳለሁ፤ በዚሁ አጋጣሚ በአውቶቡስ መሄድ እንደማልወድ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ከእኛ ጋር መሆን ይገባት የነበረች አንዲት እህት በቦታው አልተገኘችም ነበር፤ ልናገኛት ብዙ ብንሞክርም አልቻልንም ነበር፡ ፡

በመጨረሻ መገኘት በነበረብን ቦታ ሳይሆን፣ ታክሲዎች ባሉበት አካባቢ እጆቿን ስታውለበልብ አየኋት፡፡ በሰዓቱ በቦታው ባለ መገኘቷ መናደድ ቃጥቶኝ ነበር፡፡ ሆኖም ገና እንዳየኋት ግን'ኮ እወዳታለሁ በማለት አሰብኩ፡፡ ያ ቅጽበታዊ ልብ ለልብ ግንኙነት ነበር፡፡ በኋላም በእኔና በእርሷ መካከል የጠበቀ ግንኙነት ሊኖር ቻለ፡፡

እግዚአብሔር ይህን የመሳሰሉ ግንኙነቶችን ይሰጣችኋል፡፡ በተፈጥሮአዊው አስተሳሰቤ ተገፋፍቼ ያቺን ሴት ለመውደድ ምን ምክንያት አለኝ? ብዬ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ እርሷን ወድጄ ተገኘሁ፡፡ በቅርቡ ከእርሷ በደረሰኝ አንድ ረጅም ኢ-ሜል፣ «እንደ ተገናኘን ወዲያውኑ ነበር የወደድሽኝ፤ በዚህ ሁኔታ እኔን መውደድሽ፣ በሕይወቴ እጅግ ብቸኛ በነበርኩበት በዚያ ጊዜ የእግዚአብሔር ፍቅር እንዲሰማኝ አድርጎአል» ብላኛለች፡፡ አካባቢ ወይም ሁኔታ እኛ ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድር ከመፍቀድ ይልቅ፣ በእንደዚህ ዓይነቶች እግዚአብሔር በሚያመጣቸው ግንኙነቶች ስንንቀሳቀስ፣ ከሕይወታችን የሚገኘው ይህን ይመስላል፡፡

«ሊዛ፣ ያቺን ሴት በተመለከተ ጥሩ ነገር አይሰማኝም» በማለት ጆን የነገረኝ ጊዜ ነበር፡፡ እኔም፣ «ሴት ስለ ሆንኩ፣ እንዲህ ያሉ ነገሮችን ከአንተ የበለጠ አውቃለሁ» በማለት መልሼለት ነበር፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሦስቴ ወይም አራቴ ቢያስጠነቅቀኝም፣ እኔ ግን መስማት ባለ መፈለጌ የተፈራው ደርሶብኛል፡፡

**ጆን** - ከሐዋርያት ሥራ 15 እንደምንመለከተው ከአሕዛብ ወገን የሆኑት አማኞች የሙሴን ሕግ መከተል አለባቸው ወይስ የለባቸውም? የሚለውን ጥያቄ አስመልክቶ ጳውሎስና በርናባስ አለመግባባት ገጥሞአቸው እንደ ነበር እናነባለን፡፡ ከሐዋርያትና ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር እንዲገናኙ ቤተ ክርስቲያን ወደ ኢየሩሳሌም ልካቸው ነበር፡፡ ጳውሎስና በርናባስ በራሳቸው መንገድ ያልወሰኑት ለምን ነበር? እዚያ ከነበሩት ሰዎች ጋር ለመገናኘት ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ ለምን አስፈለጋቸው? ምክንያቱም፣ በኅብረት ውስጥ የበለጠ ኃይል ወይም ሥልጣንና ምሪት ስላለ ነው፡፡ ስለሆነም ባልና ሚስት ኅብረታቸውን ለመጠበቅ የሚቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ኅብረትና አንድነት በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ከእግዚአብሔር መልስ

መቀበል ያስችለናል፡፡

**ሊዛ - በመንፈስ ስጦታ እና በመንፈስ ፍሬ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?**

**ጆን** - የመንፈስ ስጦታ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ፣ ሲገኝ አንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የሚያኖረው ነው፡፡ ማሳደግ ወይም ማዳበር የሚገባው ነገር ቢኖር አጠቃቀሙን በተመለከተ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም፣ ስጦታ የምንቀበለው ሲሆን፣ ፍሬ ግን የምናሳድገው ወይም የምናዳብረው ነው ማለት ነው፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በመንፈስ የተሞላ ሕይወት ውጤት ነው፡ ፡ በመንፈስ ስትመላለሱ በሕይወታችሁ እያደገ የሚሄደው ፍሬ የበለጠ ደስታ፣ የበለጠ ሰላም የበለጠ ትዕግሥት፣ የበለጠ ፍቅር ወዘተ እንዲኖራችሁ ያደርጋል (ገላትያ 5፥22-23)፡፡ እየተመላለሳችሁ ያለው በመንፈስ ከመሆኑ የተነሣ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ከሕይወታችሁ ይንጸባረቃል፡፡ የመንፈስ ፍሬ በአገልግሎት ሕይወት ስትናወጡ የሚያቆማችሁ መሠረት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የመንፈስ ስጦታ አገልግሎታችሁን የሚመለከት ሲሆን፣ በጣም አሳዛኙ ነገር ሰዎች ከፍሬ ይልቅ ስጦታን አጥብቀው መፈለጋቸው ነው፡፡

‹‹ጌታ ሆይ፣ ሕይወቴ ላይ ያኖርካቸው ስጦታዎች፣ ለዘመናት በውስጤ ያዳበርከው ፍሬ ላይ ጫና እንዲያደርጉ አልፈልግም›› በማለት የጸለይኩበትን ጊዜ አስታውሳለሁ፡፡ እንደዚያ የጸለይኩት በሚገባ መጨረስ እንድችል ነው፤ ብዙ ጊዜ ግን ሰዎች አጥብቀው የሚፈልጉት ስጦታዎችን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹ፍቅርን ተከታተሉ፤ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በብርቱ ፈልጉ›› ይላል (1 ቆሮንቶስ 14፥1)፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች ስጦታዎችን ይከታተላሉ፤ የመንፈስ ፍሬ የሆነው (ፍቅርን) ግን ችላ ይላሉ፡፡

ስጦታዎቹ ሰዎች በተለያየ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ የሚያስችላቸውን መልካም ባሕርይ አያስገኙም፤ እንዲያውም ለአንዳንዶቹ መጥፊያ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይሁዳ አጋንንትን አስወጥቶ ነበር፤ በሽተኞችን ፈውሶ ነበር፤ ሆኖም ከጥፋት አላዳነውም፡፡ እርሱን በተመለከተ ኢየሱስ፣ ‹‹ያ ሰው (ይሁዳ) ሳይወለድ ቢቀር ይሻለው ነበር›› ብሏል (ማቴዎስ 26፥24)፡ ፡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በይሁዳ ሕይወት ተገልጠው ነበር፤ ሆኖም፣ በሕይወቱ የመንፈስ ፍሬ እንዳልነበር ግልጽ ነው፡፡

**ሊዛ - በአንዳንድ ሰዎች ሕይወት በጣም ኃይለኛ ስጦታዎች ሲያንቀሳቅሱ ቢታይም፣ የመንፈስ ፍሬ ግን የላቸውም፤ ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?**

**ጆን** - ለአፍታ ያህል በለዓምን እንይ፡፡ በለዓም ትንቢት የመናገር ስጦታ ነበረው፡፡ ትንቢቶቹ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፍረዋል! የተናገራቸው ቃሎች የእግዚአብሔር ቃሎች ናቸው፡፡ ሆኖም፣ በጣም ዐመፀኛና የማይታዘዝ ስለ ነበር፣ እግዚአብሔር በሰይፍ እንዲገደል አድርጓል፡፡ ንጉሥ ሳኦል የአንድ እብድ ያህል ነበር፡፡ እንዲያውም፣ በአንድ ወቅት እግዚአብሔር የቀባው ዳዊትን ለመግደል እያሳደደው ነበር፡፡ በዚህ ውስጥ ሆኖ እንኳ፣ አንድ ቀን ከነቢያቱ ጋር በአንድነት ትንቢት ተናግሮ ነበር (1 ሳሙኤል 19)፡፡

በአንድ ሰው ሕይወት መንፈሳዊ ስጦታዎች መገለጣቸው፣ የግድ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሰው መሆኑን አያመለክትም፡፡ ይህን አስመልክቶ ኢየሱስ ሲናገር፣ «ብዙዎች ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህ ብዙ ታምራት አላደረግንምን? ይሉኛል በዚያ ጊዜ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ክፉዎች ከእኔ ራቁ! ብዬ በግልጽ እነግራቸዋለሁ» ብሏል (ማቴዎስ 7፥22-23)፡ ፡ አንድ ቀን እግዚአብሔር ለእኔ ሲናገር፣ «እነዚህ ሰዎች፣ 'በስምህ ድኾችን መግበናል፡፡ በስምህ የታሰሩትን ጠይቀናል' አለማለታቸውን ልብ አድርገሃል? እንዲህ ያሉ ነገሮችን የሚያደርጉ ሰዎች መንፈሳዊ ፍሬ ያሳደጉ ወይም ያዳበሩ ናቸው» ብሎኝ ነበር፡፡ መንፈሳዊ ፍሬ የጀመርነውን እንደሚገባ መፈጸም የምንችልበት ሁኔታ ላይ ያደርገናል፡፡

መጀመሪያ ይህን የተማርኩት፣ ከአንድ በዓለም ውስጥ በጣም ትልቅ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ጋር እየሠራሁ በነበረ ጊዜ ነበር፡፡ ይህ ቤተ ክርስቲያን በጣም ታዋቂ የነበሩና ይህን ያህል ታዋቂነት ያልነበራቸው ሰባኪዎች የሚመጡበት ሲሆን፣ የእኔ ሥራ እነዚህን ሰዎች ከአውሮፕላን ማረፊያው ተቀብሎ ማምጣትና በቆይታቸው ጊዜ ሁሉ እነርሱን ማስተናገድ ነበር፡፡ አንዳንድ አገልጋዮች ገና መኪናው ውስጥ ሲገቡ፣ ኢየሱስ አጠገቤ ያለ ያህል ይሰማኝ እንደ ነበረም አስታውሳለሁ፡፡ ተነሥተው ሲሰብኩም፣ ኢየሱስ ራሱ በአካል ቆሞ የሚሰብክ ያህል ነበር፡፡

*አንዳንዶቹ መኪናው ውስጥ ሲገቡ ግን፣ ምን እየሆነ ነው? ደስ የማይል ስሜት የሚሰማኝ ለምንድነው? ንግግራቸው ይህን ያህል ተራና የወረደ የሆነው ለምንድነው?* እል ነበር፡፡ ግን እነዚሁ አገልጋዮች መድረክ ላይ ሲወጡ፣ ሰዎች ይድኑ ነበር፤ ይፈወሱና ይገለገሉ ነበር፡፡ እንዲህ ስል በእውነት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይገለጥ እንደ ነበር መናገሬ እንጂ፣ እንዲሁ የሐሰት ድነት ወይም ፈውስ ይደረግ ነበር ማለቴ አይደለም፡፡ *ታዲያ፣ ይህን ስመለከት፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ሊገባኝ አልቻለም! ምን እየሆነ ነው? እነዚህ በአገልግሎታቸው ሰዎች ሲድኑና ሲፈወሱ የሚታይ አገልጋዮች፣ ቀደም ሲል እፊቴ ተራና የወረደ ቃል ሲናገሩ የነበሩ አይደሉም ወይ?* እል ነበር፡፡ ይሁዳ የመንግሥቱን ወንጌል ሰብኮ እንደ ነበር፣ አጋንንትን አስወጥቶ፣ ሕመምተኞችን ፈውሶና ተአምራት አድርጎ የነበረ ቢሆንም፣ ያ ሁሉ ግን ከፍርድ እንዳላዳነው እግዚአብሔር ያሳየኝ በዚያ ጊዜ ነበር፡፡ በለዓም ትንቢት ተናግሮአል፣ ሆኖም፣ እግዚአብሔር በሰይፍ እንዲገደል አድርጓል፡፡ ሳኦል ትንቢት ተናግሮአል፤ ሆኖም ፍጻሜው አላማረም፡፡ ‹‹የእግዚአብሔር ቅባት አንድ ሰው ሕይወት ውስጥ መኖሩ - የእግዚአብሔር ስጦታዎች በአንድ ሰው አገልግሎት መገለጣቸው፤ ያ ሰው በሁሉም አቅጣጫ ትክክል ነው ማለት አይደለም›› በማለት ነበር ጌታ በዚያ ጊዜ የተናገረኝ፡፡ በፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ (ማቴዎስ 7፥16)፡፡

**ሊዛ - የእግዚአብሔር ስጦታ እንዲሁ ወደ አንድ ሰው ሕይወት የሚመጣ ሲሆን፣ ፍሬ ግን በውስጣዊ ባሕርያቸው የሚያድግና እየጐለበተ የሚሄድ ነገር ነው እያልህ ነው?**

**ጆን** - አዎን፣ በትክክል ገልጠሽዋል፡፡

**ሊዛ - በውስጥ በሚሰማ ሰላም መሠረት ስለ መመራት ተናግረሃል፤ መንፈስ አንድን ነገር እንዳናደርግ ወይም እንዳንናገር ሲከለክል፣ ውስጣችን አንድ ዐይነት መታወክና ምቾት የማይሰጥ ስሜት እንደሚኖር ተናግረሃል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ግን አሁንም ቢሆን፣ እግዚአብሔር በቃሉ በኩል እየተናገረን ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች እግዚአብሔር በመጽሐፍ**

**ቅዱስ ብቻ እንደሚናገር ነው የሚያምኑት፡፡ አንተስ ዛሬም እግዚአብሔር እንደሚናገርና የሚናገረውም ከቃሉ ጋር በሚስማማ መንገድ ብቻ እንደ ሆነ ነው የምታምነው?**

**ጆን** - ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ፣ ‹‹አረማውያን በነበራችሁበት ጊዜ ወዲያና ወዲህ በመነዳት ድዳ ወደ ሆኑ ጣዖቶች እንደ ተወሰዳችሁ ታውቃላችሁ›› ብሏል (1 ቆሮንቶስ 12÷2)፡፡ ድዳ ማለት፣ ‹‹የማይረቡ›› ጣዖቶች ማለት ሲሆን፣ በዚህ ዐውድ መሠረት ግን ‹‹የማይናገሩ›› ማለት ነው፡ ፡ በሌላ አነጋገር የቆሮንቶስ ሰዎች ሲገዙላቸው የነበሩ አማልክት አይናገሩም ነበር፡፡ ከዚህ ጋር አያይዞ ጳውሎስ፣ ‹‹ልዩነቱ የእኛ አምላክ የሚናገር መሆኑ ነው›› ይላል፡፡ እርሱ በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ይናገራል፡፡

ለመሆኑ፣ እግዚአብሔር የሚናገረው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ለእኛ በተለያዩ መንገዶች እንደሚናገር አዲስ ኪዳን ያመለክታል፡፡ በመጀመሪያና በተቀዳሚ ደረጃ፣ በውስጥ ባለን ምስክር፣ ማለትም በውስጣችን በሚሰማን ሰላም ነው የሚናገረን፡፡ ይህ እርሱ የሚናገርበት ቁጥር አንድ መንገድ ነው፡፡
ሊዛ - እንዲህ ስትል ከቃሉ የበለጠ ማለት ነው?

**ጆን** - አይደለም፤ ሁልጊዜ ቃሉ ከዚያ ጋር ይስማማል፡፡ ሰላም የሚሰማችሁ ቢሆን እንኳ፣ ያ ሰላም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይጣጣም ከሆነ፣ በፍጹም አትቀበሉት፡፡ ምናልባትም በልባችሁ ያለው ግፊት ወይም ዓላማ የተሳሳተ ሊሆን ስለሚችል ነጻና ገለልተኛ ወደ ሆነው መመለስ ይኖርባችኋል፡፡ የመጨረሻውን ቃል ወይም ውሳኔ የሚሰጥ ቃሉ ነው፡፡

**ሊዛ** - ሁሌም ቢሆን፣ መሠረቱና አጠቃላይ ይዘቱ ቃሉ ነው፡፡

**ጆን** - አዎን፣ ትክክል ነው፡፡ ስለዚህ ቁጥር አንድ፣ ውስጣዊው ምስክር ሲሆን፣ ቁጥር ሁለት ደግሞ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለስለስ የሚል ድምፅ የሚለው ነው፡፡ ኢየሱስ ‹‹በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ›› ብሏል (ዮሐንስ 10÷27 ይመ)፡ ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ከኢየሱስ የሰማውን ይናገራል፤ ያ ደግሞ ለስለስ

የሚል ድምፅ የተባለው ነው፡፡

አንዳንድ ሰዎች ምንም ውስጣዊ ምስክር ሳይኖራቸው፣ የተለያዩ ድምፆችን መከተል በመጀመራቸው ችግር ውስጥ ወድቀዋል፡፡ የእግዚአብሔርን ድምፅ በምሰማበት ጊዜ ሁሉ፣ ውስጣዊ ምስክርም አብሮት ይኖራል፤ ሁለቱም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይስማማሉ፡፡ እዚህ ላይ መሠረት የሚሆነንን እያስቀመጥን ነው - ቃል፣ ምስክር፣ ድምፅ፡፡ የምትሰሙት ድምፅ ውስጣዊ ምስክር ከሌለው፣ በፍጹም አትቀበሉ፡፡ አንዳንድ ስብሰባዎች ውስጥ እያለሁ፣ አንዳንድ ሰዎች እኔ ላይ ትንቢት ተናግረው ነበር፤ ሆኖም በዚያ ውስጥ የእግዚአብሔር መገኘትና ውስጣዊውን ምስክር አላገኘሁም፡፡ እንዲህ ያሉትን አልቀበልም፡፡

አዲስ ኪዳን እንደሚነግረን ሌላው እግዚአብሔር የሚናገርበት መንገድ ሕልም ነው፡፡ ሐዋርያት ሥራ 16 ጳውሎስ ስላየው ሕልም ያመለክታል፡ ፡ አንድ የመቄዶንያ ሰው በሕልም ወደ ጳውሎስ መጥቶ፣ «ወደ መቄዶንያ ተሻግረህ እርዳን» አለው፡፡ ያ፣ «ወደ መቄዶንያ ሂድ» ብሎ ለጳውሎስ ለመናገር እግዚአብሔር የተጠቀመበት ሕልም ነበር፡፡ ለአንዳንድ ሰዎች ከሌሎች በበለጠ ሁኔታ እግዚአብሔር በሕልም ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር ለሚስቴ በጣም ግልጽ በሆኑ ሕልሞች ይናገራታል፡፡ ለእኔ ግን ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የሚናገረኝ፣ በውስጣዊው ምስክርና ለስለስ ባለው ድምፅ ነው፡ ፡

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያመለክተው ሌላው እግዚአብሔር የሚናገርበት መንገድ ራእይ ነው፡፡ ጳውሎስም ራእይ አይቷል፡፡ ስለ ራእዩ ሲናገር፣ «በሥጋ ይሁን፣ ወይም ከሥጋ ውጭ አላውቅም» ብሎ ነበር (2 ቆሮንቶስ 12፥2)፡፡ ራእይ በምታዩበት ጊዜ በአካል መሆናችሁን ወይም ከአካል ውጭ መሆናችሁን አታውቁትም፤ ግን በቀጥታ መንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ያለውን ታያላችሁ፡፡ በ1989 ዓ.ም ፓስተሬ አገልግሎት እንደምንጀምር እኔና ሊዛን የነገረን ካየው ራእይ የተነሣ ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ ወደ አንድ የአገልጋዮች ስብሰባ መጥቶ፣ «ትናንት ሌሊት ራእይ አይቼ ነበር፡፡ ራእዩ ልክ በቴሌቪዥን የማየት ያህል ግልጽ ነበር፡፡ ከእናንተ ከፓስተሮቼ አንዱ፣ ከእንግዲህ ከእኛ ጋር አይሆንም፡፡ ከአገር አገር እየተዘዋወርክ ታገለግላለህ፤ ለክርስቶስ አካል በረከት ትሆናለህ» ካለ በኃላ አያይዞ፣ «ጆን ቢቨሬ ያ ሰው አንተ ነህ» አለ፡

፡ ከስምንት ወር በፊት ጸሎት ላይ እያለሁ፣ እግዚአብሔር ተመሳሳይ ነገር ነግሮኝ ነበር፤ ስለዚህ ፓስተሩ የተናገረው ለእኔ ማረጋገጫ ነበር፡፡

አዲስ ኪዳን እንደሚያመለክተው እግዚአብሔር ለእኛ የሚናገርበት የመጨረሻ መንገድ ተመስጦ ነው፡፡ ሐዋርያት ሥራ 10 ጴጥሮስ ተመስጦ እንደ ተለማመደ ይናገራል፡፡ ተመስጦ ስሜቶቻችሁ ሲወሰዱ ማለት ነው፡ ፡ ይህ ከራእይ ይለያል፣ ምክንያቱም ራእይ በምታዩበት ጊዜ ስሜቶቻችሁ ከእናንተ ጋር እንዳሉ ነው የሚሆኑት፤ መንቀሳቀስ ትችላላችሁ፡፡ ጳውሎስና ዮሐንስ ወደ ሰማይ በተወሰዱ ጊዜ ወዲያ ወዲህ ተመላልሰዋል፡፡ ተመስጦ ውስጥ ስትሆኑ ግን አንድ ነገር ታያላችሁ የእግዚአብሔን ድምፅ ትሰማላችሁ፡ ፡ የተቀሩት ስሜቶቻችሁ ግን ከእናንተ ይወሰዳሉ፡፡

ምናልባትም አንዳንዶች፣ ‹‹የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ እንደ ማረጋገጫ የምንጠቀምባቸው ነገሮችን በተመለከተ ምን ታስባለህ?›› ትሉኝ ይሆናል፡፡ ይህ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ከእግዚአብሔር የሚሰሙበት ዘዴ ነበር፡፡ በብሉይ ኪዳን ያሉ ነገሮችን ሁሉ በመስቀሉ ማጥለል ይኖርብናል፡ ፡ መስቀሉ ባለበት ሁኔታ ያሳለፈው ይሆናል፤ ያስተካከለው ወይም ጨርሶ ያስወገደው ይሆናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው›› ይላል እንጂ፣ በአንዳንድ ውጫዊ ማረጋገጫዎች የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው አይልም (ሮሜ 8፥14 ይመ)፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን በነበሩ ሰዎች ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አልነበረም፤ ስለሆነም እግዚአብሔር በአንዳንድ ውጫዊ ማረጋገጫዎች ይናገራቸው ነበር፡ ፡ በበኩሌ በአዲስ ኪዳን ዘመን ያሉ አማኞች ውጫዊ ማረጋገጫ እንዲጠብቁ አልመክርም፡፡ ምንጊዜም ቢሆን መጨረሻ ላይ በእግዚአብሔር ቃልና በውስጣዊው ምስክር መረጋገጥ አለባቸው፡፡ ውጫዊ ማረጋገጫ መሠረት የሚያደርገው ቁሳዊውን ዓለም ሲሆን፣ በዚህ ተሳትፎ በማድረግ ነገሮችን ማምታታት የለብንም፡፡ የተጠራነው በመንፈስ እንድንኖርና በመንፈስ እንድንመላለስ ነው፡፡

**ሊዛ** - አንተ በተናገርከው ላይ መጨመር እፈልጋለሁ፡፡ መልሶችህ ሁሉ ከመንፈሳዊው ዓለም አሠራረ ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፡፡ ወንድማችን ችግር ላይ ሆኖ ብናገኘው፣ በእርሱ መጨከን እንደሌለብን ግልጽ ትእዛዝ ተሰጥቶናል

(1 ዮሐንስ 3፥16-18)፡፡ አንዳንዴ ይህን ለማድረግ ከሰማይ ድምፅ መጠበቅ የለብንም፡፡ አንዳንዴ ግን ያንን ችግር በተመለከተ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ እውነቱን ማየትና መስማት ይኖርብናል፡፡ መጽሐፎቻችንን በተመለከተ ከፍተኛ ፍላጐት መኖሩን ስንሰማ፣ ‹‹በዚህ ጉዳይ ልባችንን መዝጋት የለብንም›› አልን፤ ችግሩን ሰማን እንጂ አላየንም፤ ያን መሠረት በማድረግ ‹‹መልስ መስጠት አለብን›› አልን፡፡

**ጆን** - ለወሲብ መጠቀሚያ እንዲሆኑ ልጃገረዶች ከአገር ወዳገር እንደሚወሰዱ ስሰማ፣ እግዚአብሔር አልተናገረኝም፤ ይሁን እንጂ፣ ‹‹ሊዛ አንድ ነገር ማድረግ አለብን›› አልኩ፡፡

**ሊዛ** - እኔም ያንን አንድ መጽሔት ላይ አንብቤ ነበር፡፡ ከአገር ውጪ በነበርኩ ጊዜ በዐይኔ አይቻለሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹ችግር መኖሩን ካያችሁ›› አንድ ርምጃ ውሰዱ ማለቱ ግልጽ ሆኖ እያለ፣ አንዳንዴ ሰዎች ምልክት ወይም ተመስጦ ወይም ራእይ ወይም ሕልም ይጠብቃሉ፡፡

**ጆን** - ‹‹ወንድሙ ሲቸገር አይቶ…››

**ሊዛ** - ችግር ላይ ባለ ወንድማችን ወይም እኅታችን በጐ ማድረግን እንጀምራለን፡፡ ችግር በደረሰበት ክርስቲያን እንጀምራለን፡፡ በምንሰማው፣ በምንዳስሰው፣ ድምፁን በምንሰማው እንጀምራለን - ለዚያ ልባችንን መዝጋት የለብንም፡፡ በተፈጥሮአዊው ዓለም ላለው ምላሽ በምንሰጥበት ጊዜ ሁሉ፣ በመንፈሳዊው ዓለም ባለውም ላይ እግዚአብሔር ኃላፊነት ይሰጠናል፤ ምክንያቱም እርሱ፣ ‹‹አንተ ታማኝ አገልጋይ በጥቂቱ ታማኝ ሆነህ ተገኝተሃል፤ በእምነት ዓለም ባለው ላይ ተጨማሪ ኃላፊነት እሰጥሃለሁ›› ይላል፡፡

## ከጆን - ተጨማሪ መልሶች

**ጥያቄ - አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስን ሰደበ የሚባለው ምን ሲያደርግ ነው?**

**ጆን** - መንፈስ ቅዱስን ስለ መሳደብ ኢየሱስ የተናገረውን፣ ከማቴዎስ 12፥22-32፤ ማርቆስ 3፥22-30 እና ከሉቃስ 12፥10 መመልከት ይቻላል፡፡ ማቴዎስና ማርቆስ ከሰጡት ገለጻ ዐውዱን በግልጽ ማየት ይቻላል፡፡ አጋንንት የሚያወጣው በአጋንንት አለቃ በቡዔል ዜቡል ነው በማለት የሃይማኖት መሪዎቹ ኢየሱስን ከሰሰውት ነበር፡፡ «ኃጢአት መሥራትና የስድብ ቃል ሁሉ መናገር፣ ለሰዎች ይቅር ይባልላቸዋል፤ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚነገር የስድብ ቃል ይቅር አይባልም» በማለት ኢየሱስ የተናገረው በዚህ ጊዜ ነበር (ማቴዎስ 12፥31)፡፡ ስለሆነም መንፈስ ቅዱስን መስደብ በእርሱ ላይ ክፉ ቃል፣ በተለይም የመንፈስ ቅዱስ መገለጦች የዲያብሎስ ሥራ እንደ ሆነ መናገር ማለት ነው፡፡

**ጥያቄ - ለአብና ለወልድ እንደሚደረገው ለመንፈስ ቅዱስ መጸለይና ለእርሱ መዘመር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን?**

**ጆን** - አዎን፣ በትክክል፡፡ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፤ እንደ እግዚአብሔር መመለክ አለበት ዮሐንስ 4፥24፣ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል» ይላል፡፡ አብና ወልድን እንደምናመልክና እንደምናመሰግን ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስንም ማምለክና ማመስገን እንዳለብን አምናለሁ፡፡

**ጥያቄ - ለመንፈስ ቅዱስ መቅረብ ያለባቸው ጸሎቶች ወይም መዝሙሮች የትኞቹ እንደ ሆኑ እንዴት ታውቃለህ?**

**ጆን** - ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር፣

> ብዙ የምነግራችሁ ነበረኝ፤ አሁን ግን ልትሸከሙት አትችሉም፡፡

የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኃል፡፡ እርሱ ከራሱ አይናገርም፤ የሚሰማውን ብቻ ይናገራል፤ እንዲሁም ወደ ፊት ስለሚሆነው ይነግራችኃል፤ የእኔ ከሆነው ወስዶ እንድታውቁ በማድረግ ያከብረኛል…
ከጥቂት ጊዜ በኃላ አታዩኝም፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኃላ ደግሞ ታዩኛላችሁ፣ እኔ ወደ አብ ስለምሄድ…
*በዚያ ቀን ከእኔ ምንም አትለምኑም፤ እውነት እላችኃለሁ፤ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኃል - ብሎአቸው ነበር (ዮሐንስ 16፥12-14፣ 16፣23)፡፡*

*በኢየሱስ ስም (ሥልጣን)* ወደ እግዚአብሔር አብ ልመናችንን እናቀርባለን፡ ፡ ከዚያም በዚህ መጽሐፍ እንደ ተነጋገርነው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት እናደርጋለን (ማለትም እንገናኛለን እነነጋገራለን) ጥያቄዎቻችንን ለእርሱ እናቀርባለን

**ጥያቄ - እርሱ በአንድ ጊዜ በሁሉም ቦታ የሚገኝ ሆኖ ሳለ፤ - ወደ እኛ እንዲመጣ መንፈስ ቅዱስን መጠየቅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን?**

**ጆን** - አዎን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ፣ ሁሉም ቦታ የሚገኝ ቢሆንም፣ ልዩ በሆነ ሁኔታ መገኘቱ የሚገለጥበት ጊዜ እንዳለ ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ ሁሉም ቦታ የሚገኝ (ምሉዕ በኩለሄ) መሆኑን በተመለከተ ዳዊት እንዲህ ይላል፣

ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ?
ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?
ወደ ሰማይ ብወጣ፣ አንተ በዚያ አለህ፤
መኝታዬንም በሲኦል ባደርግ በዚያ ትገኛለህ፡፡
በንጋት ክንፍ ተነሥቼ ብበር፣
እስከ ባሕሩ ዳርቻ መጨረሻ ብሄድ፣
በዚያም ቢሆን እጅህ ትመራኛለች፤

ቀኝ እጅህም አጥብቃ ትይዘኛለች (መዝሙር 139፥7-10)።

እግዚአብሔር እንደማይተወንና እንደማይጥለንም መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (ዕብራውያን 13፥5)። ይህም ቢሆን፣ የእርሱን ሁሉም ቦታ መገኘት ማለትም መገኘቱ ምንጊዜም የትም ቦታ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር፣ በተለየ ሁኔታ ሓልዎቱን ይገልጣል። መገለጥ ማለት የማይታየው ሲታይ፣ የማይሰማው ሲሰማ ወይም የማይታወቀው ሲታወቅ ማለት ነው። ለስሜቶቻችን በሚታወቅ ሁኔታ ራሱን ሲገልጥ፣ እግዚአብሔር መገኘቱን መግለጡ ነው (ዮሐንስ 14፥19-24)። ለዚያ መጸለይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደ ሆነ አምናለሁ።

**ጥያቄ - እግዚአብሔር መንፈሱን እንዲያፈስ የምንጸልየው ለምንድነው? ያንን አንድ ጊዜ አድርጐ የለ?**

**ጆን** - ዘካርያስ 10፥1፣ «የበልግ ዝናብ እንዲሰጣችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁ» ይላል። በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ዝናብ ምንጊዜም የመንፈስ ቅዱስን መፍሰስ ይወክላል። እግዚአብሔር መንፈሱን እንዲያፈስ በምንጠይቀበት ጊዜ በማኅበረ ሰቦች፣ በከተሞችና በአገሮች ላይ በአዲስ ሁኔታ መንፈሱን እንዲያፈስ መጠየቃችን፣ የእርሱን ሥራ ለመሥራት ኃይል የሚሰጠንና ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለማምጣት የሚያስችለን ኃይል እንዲኖረን መጠየቃችን እንደ ሆነ አምናለሁ። የመንፈስ መፍሰስ ቀድሞውኑ የነበረው መገኘቱ በታላቅ ኃይል ሲለቀቅ ማለት ነው።

**ጥያቄ - ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የጠበቀና የጠለቀ ግንኙነት ሊኖረኝ የሚችለው እንዴት ነው?**

**ጆን** - ከእግዚአብሔርና ከቃሉ ጋር ጊዜ በማሳለፍ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን መቀራረብ ማጥበቅን በተመለከተ በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ሁለት እና ሦስት ላይ በስፋት ይገኛል።

**ጥያቄ - መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም የሚያውቅ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የሚያስፈልገው ለምንድነው?**

**ጆን** - ‹‹ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት፣ በጽድቅም መንገድ ለመምከር›› እንዲጠቅመን እግዚአብሔር የእርሱ መንፈስ ያለባቸው መጻሕፍትን ሰጠን ( 2 ጢሞቴዎስ 3፥16-17)። የተነገረውን ቃሉን (ሬማ) ለእኛ ለማምጣት፣ መንፈስ ቅዱስ በዚህ በጽሑፍ በሰፈረ ቃል (በግሪኩ ሎጐስ) ይጠቀማል። መንፈስ ሎጐስን ሕያው ያደርግና፣ ሬማ ማለትም በቀጥታ የተነገረ ቃል ያደርገዋል። አንድ ሰው ለመንፈስ ክፍት በሆነ ልብ ከሎጐስ ማለትም በጽሑፍ ከሰፈረው ቃል ጋር ጊዜ የማያሳልፍ ከሆነ፣ ሬማ መቀበል በጣም አዳጋች ነው የሚሆነው። በቻይና በኅቡዕ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ቢሆኑም፣ ከፍተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ችግር አለባቸው። በእርሱ በኩል መንፈስ ቅዱስ እንዲናገራቸውና ሕያው አድርጐ ለልባቸው እንዲናገር የእግዚአብሔር ቃል ማንበብ ይፈልጋሉ። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ በጣም አስፈላጊ ነው። የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ተስማምተው ይሠራሉ። ይህ የአጋርነት ሥራ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ምስጢሮች የያዘ መጽሐፍ መሆኑንና እነዚህን ምስጢሮች የሚገልጥልን መንፈስ ቅዱስ መሆኑን አስታውሱ። ያለ መንፈስ ቅዱስ አስተማሪነት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ብታነቡ፣ ምንባቡ በሰዎች ቋንቋ የሚለውን ብቻ ትመለከታላችሁ። በመንፈስ አማካይነት ከሆነ፣ ግን፣ ከሰዎች አእምሮ በላይ የሆነውን የዐውዱን መንፈሳዊ ትርጉም መረዳት ትችላላችሁ፣ ምክንያቱም፣ መንፈስ የክርስቶስ አእምሮ አለው።

> የምንናገረው ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔርን ምስጢር ጥበብ ነው፤ ይህም ጥበብ እግዚአብሔር ከዘመናት በፊት ለክብራችን አስቀድሞ የወሰነው ነው። ከዚህ ዓለም ገዦች አንዳቸውም ይህን ጥበብ አልተረዱትም፤ ቢረዱትማ ኖሮ፣ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉት ነበር። ይሁን እንጂ፣ እንደ ተጻፈው፣
> ‹‹ዐይን ያላየውን፣
> ጆሮ ያልሰማውን

የሰውም ልብ ያላሰበውን፣ እግዚአብሔር ለሚወዱ አዘጋጅቶአል›› - እግዚአብሔር ግን ይህን በመንፈሱ አማካይነት ለእኛ ገልጦልናል፡፡

መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር እንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራል፡፡ በውስጡ ካለው ከራሱ መንፈስ በስተቀር ከሰው መካከል የአንድን ሰው ሐሳብ የሚያውቅ ማን አለ? እንደዚሁም ከእግዚአብሔር መንፈስ በስተቀር፣ የእግዚአብሔርን ሐሳብ የሚያውቅ ማንም የለም፡፡ የእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ፣ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንምና፤ ይህም እግዚአብሔር በነጻ የሰጠንን እናውቅ ዘንድ ነው፡፡ እኛ የምንናገረው ይህን ነው፤ ከሰው ጥበብ በተማርነው ቃል ሳይሆን፣ ከመንፈስ በተማርነው ቃል እንናገራለን፤ መንፈሳዊ እውነትንም የምንገልጸው በመንፈሳዊ ቃል ነው፡፡ መንፈሳዊ ያልሆነ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆነውን ነገር ሊቀበል አይችልም፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር ለእርሱ ሞኝነት ነው፤ በመንፈስም የሚመራመር ስለ ሆነ ሊረዳው አይችልም፡ ፡ መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ነገር ይመረምራል፤ ራሱ ግን በማንም አይመረመርም፡፡

‹‹ያስተምረው ዘንድ፣
የጌታን ልብ ማን አወቀው?››
እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን፡፡
(1 ቆሮንቶስ 2፥7-16)

**ጥያቄ - ቤተ ክርስቲያኔ፣ መንፈሳዊ ቅባት የሌላት ደረቅ ናት፡፡ የመንፈስ እንቅስቃሴ እንዲኖር እንደ አንድ ግለ ሰብ ምንድነው ማድረግ ያለብኝ?**

***ጆን*** - ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ መሪ ካልሆንክ በስተቀር፣ ማድረግ ያለብህ መጸለይ ብቻ ነው፡፡ በአንተ ውስጥ ሆኖ በዚያ ቤተ ክርስቲያን እንዲገኝ፣ በመጀመሪያ አንተ ወደ ራስህ ሕይወት ጋብዘው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፣ ለመንፈስ ቅዱስ መገኘት የበለጠ ክፍት እንዲሆኑና የመሪዎችህን ልብ እንዲነካ እግዚአብሔርን ጠይቀው፡፡

# የውይይት ጥያቄዎች

1. አማኞች ሁሉ መንፈሳዊ ስጦታዎችን መለማመድ ይችላሉ፡፡ በተለምዶ፣ ‹‹አገልግሎት›› ከምንለው ከባቢ ውጪ፣ እነዚህ ስጦታዎችን መለማመድ ምን መልክ ሊኖረው እንደሚችል ታስባላችሁ?

2. አንድን ውሳኔ በተመለከተ እግዚአብሔር ሰላሙን እንደ ሰጠህ የምታምን ከሆነ፣ ከእግዚአብሔር ለመስማትህ እርግጠኛ የሚያደርግህ ምንድነው?

3. በቀጥታ ለእናንተ ከመናገር ይልቅ፣ መንፈስ ቅዱስ በትዳር ጓደኞችሁ በኩል ተናግሮአችሁ ያውቃል? በዚህ መንገድ ማድረግ የፈለገው ምን እንደ ሆነ ታስባላችሁ፣ ያንን ምሪት የምታገኙትስ እንዴት ነው?

4. አንድ በጣም አስፈላጊ ውሳኔ ማድረግ ሲኖርባችሁ፣ ሆኖም ምሪት ሳታገኙ ከቀረ ምንድነው የምታደርጉት?

   ምሳሌ 11፥14፤ 15፥22፤ 24፥6 እና ሮሜ 8፥26-27 ይመ፡፡

5. ዛሬም እግዚአብሔር እንደሚናገር ታምናላችሁ? ተናግሮአችሁ የሚያውቅ ከሆነ እንዴት ነበር የተናገራችሁ

# ድነት እንዴት እንደምትቀበሉ

*ኢየሱስ ጌታ ነው ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህ፡፡ የምትጸድቀው በልብህ አምነህ ነው፤ የምትድነውም በአፍህ መስክርህ ነውና፡፡*

– ሮሜ 10፥9-10

መንፈስ ቅዱስ በማንኛውም ቅጽበት ከእናንተ ጋር መገናኘት ይፈልጋል፤ እግዚአብሔርን እንድታውቁና መንግሥቱን እንድታስፋፉ ያበረታታችኋል፤ ኃይልም ይሰጣችኋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከመንፈስ ጋር የጠበቀ መቀራረብ እንዲኖረን ከተፈለገ፣ የመጀመሪያው እርምጃ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚገኘውን ድነት መቀበል ነው፡፡

በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ አማካይነት፣ እንደ ተወደዱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፣ ወደ መንግሥቱ እንድትገቡ እግዚአብሔር መንገድ አዘጋጅቶአል፡፡ ኢየሱስ መስቀል ላይ መሥዋዕት መሆኑ፣ የዘላለምንና የተትረፈረፈ ሕይወትን በነጻ እንድንቀበል አስችሎናል፡፡ ድነት ለእናንተ የተሰጠ ስጦታ ነው፤ እንደ ክፍያ ወይም የሚገባችሁ ስለ ሆናችሁ የምትቀበሉት አይደለም፤ ያንን ለማግኘት እናንተ ምንም ማድረግ አትችሉም፡፡

ይህን ክቡር ስጦታ ለመቀበል፣ በመጀመሪያ፣ ከፈጣሪህ ውጪ በመኖርህ ኃጢአተኛ መሆንህን እመን (የሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ ሥረ-መሠረት ይኸው ነው)፡፡ ንስሐ ድነትን ለመቀበል እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ከሐዋርያት ሥራ እንደምንመለከተው 5,000 ሰዎች ድነት ባገኙበት ቀን ጴጥሮስ ይህን ግልጽ አድርጎታል፤ ‹‹ኃጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሐ ግቡ፤ ከመንገዳችሁም ተመለሱ›› (ሐዋርያት ሥራ 3፥19)፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት እያንዳንዳችን

የኃጢአት ባሪያዎች ሆነን እንደ ተወለድን ይናገራል፡፡ ይህ ባርነት መሠረት ያደረገው ሆን ብሎና ፈቅዶ ባለ መታዘዝ አዳም የፈጸመውን ኃጢአት ነው፡፡ ንስሐ ለራሳችሁና፣ የሐሰት ሁሉ አባት ከሆነው ሰይጣን ከመታዘዝ ተመልሳችሁ፣ ሕይወት ለሰጣችሁ ለአዲሱ ጌታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ መታዘዝ ማለት ነው፡፡

ኢየሱስን የሕይወታችሁ ጌታ ልታደርጉት ይገባል፡፡ ኢየሱስን፣ ‹‹ጌታ›› ማድረግ፣ የሕይወታችሁና (መንፈስ፣ ነፍስና ሥጋ) የማንኛውም ነገራችሁ ባለቤት ማድረግ ማለት ነው፡፡ ከእንግዲህ እርሱ ሙሉ በሙሉ በሕይወታችሁ ሥልጣን ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ይህን ባደረጋችሁበት ቅጽበት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃንና ወደ መንግሥቱ ክብር እግዚአብሔር ያሻግራችኋል፡፡ ከሞት ወደ ሕይወት ትሄዳላችሁ - የእርሱ ልጆች ትሆናላችሁ!

በኢየሱስ በኩል ድነት ማግኘት ከፈለጋችሁ እንደዚህ በማለት ጸልዩ፤

*በሰማይ ያለህ አባት፣ ኃጢአተኛ መሆኔንና ከአንተ ጽድቅ መስፈርት የጎደልሁ መሆኔን እቀበላለሁ፡፡ ለኃጢአቴ የዘላለም ቅጣት ይገባኝ ነበር፡፡ በዚያ ሁኔታ ስላልተውኸኝ ተመስገን፤ ለእኔ እንዲሞትና የእኔን ፍርድ መስቀል ላይ እንዲሸከም፣ ከድንግል ማርያም የተወለደው አንድ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ላክኸው አምናለሁ፡ ፡ በሦስተኛው ቀን ከሞት መነሣቱንና አሁን ጌታዬ ሆኖ በአንተ ቀኝ መቀመጡን አምናለሁ፡፡ ስለዚህ በዚህ ቀን ከአንተ ውጪ በኖርኩት ሕይወት ንስሐ አደርጋለሁ፤ ሕይወቴንም ሙሉ በሙሉ ለኢየሱስ ጌትነት እሰጣለሁ፡፡*

*ኢየሱስ፣ ጌታዬና አዳኜ መሆንህን እመሰክራለሁ፡፡ በመንፈስህ አማካይነት ወደ ሕይወቴ ግባ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ወደ መሆን ለውጠኝ፡፡ በአንድ ወቅት ይገዙአቸው የነበሩ የጨለማ ሥራዎች እክዳለሁ፤ ከዚህ ቀን ጀምሮ ለራሴ ሳይሆን፣ በአንተ ጸጋ ርዳታ እኔ ለዘላለም እንድኖር፣ ራስህን ለሰጠኸኝ ለአንተ እኖራለሁ፡፡*

*አሁን ሕይወቴ ሙሉ በሙሉ በአንተ እጅ ስለ ሆነና ቃልህ እንደሚለው በፍጹም ስለማላፍር ተመስገን፡፡*

እንኳን ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ መጣችሁ! ይህን ድንቅ እውነት ለሌላ አማኝ እንድታካፍሉ አበረታታችኋለሁ፡፡ የአንድ መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆንና፣ አዲስ ባገኛችሁት እምነት ከሚያበረታቷችሁ ሌሎች አማኞች ጋር ግንኙነት መፍጠር፣ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አሁን ከልዑል አምላክ ጋር የመቀራረብ አስደናቂ ጉዞ ጀምራችኋል፡፡ ከእርሱ ጋር ባላችሁ ወዳጅነት ዕለት ዕለት እንድታድጉ እርሱ ይርዳችሁ!

# ማስታወሻ


**ምዕራፍ 1**

1. James Strong, **ቅጽ** 1, *A Concise Dictionary of the Words in the Greek Testament and The Hebrew Bible*, 44 (Bellingham, WA: Logos Bible Software, 2009) (**ከዚህ በኋላ** Strong's Concise Dictionary **ተብሎ ተጠቅሶአል**).
2. **ቀደም ሲል የተጠቀሰው የተወሰደው ከ** R.A. Torrey's *The Prson and Work of the Holy Spirit*. R.A. Torrey, *The Person and Work of The Holy Spirit* **ከሚለው መጽሐፍ ነው ገጽ** 4 (New York: Fleming H. Revll Company, 2010), Kindle Edition
3. W. E. Vine, Merrill F. Unger and William White, Jr., **ቅጽ** 2, *Vine's Complete Expository Dictionary of Old and New Testament Words*, 29 (Nashville, TN: T. Nelson, 1996) (**ከዚህ በኋላ** Vine's Expository Dictionary **ተብሎ ተጠቅሶአል**).
4. **ዝኒ ከማሁ** 111.
5. Rick Renner, *Sparkling Gems from the Greek* (Tulsa, OK: Teach All Nations, 2003), 737 (**ከዚህ በኋላ** Sparkling Gems **ተብሎ ተጠቅሶአል**).
6. **ዝኒ ከማሁ** 26.

**ምዕራፍ 1 ማሰላሰያ**

1. A.W. Tozer, *A Treasury of A.W. Tozer* (Harrisburg, PA: Christian Publications, Inc., 1980) **ገጽ** 290- 291.
2. **ዝኒ ከማሁ ገጽ** 295-296.
3. Andrew Murray, "The Holy Spirit In The Family," *Herald of His Coming*, February 2013, **ገጽ** 8.
4. Lester Sumrall, *Spirit, Soul & Body* (New Kensington, PA: Whitaker House, 1995) **ገጽ** 113.

5. R.A. Torrey, "The Holy Spirit's Power in the Believer," **ማስታወሻ** 3, **ገጽ** 1. **ይመ.**

**ምዕራፍ 2**

1. Spiros Zodhiates Th.D., ed., *The Complete Word Study Dictionary: New Testament* (Chattanooga, TN: AMG Publishers, 1992), s.v. "metochos." ‹‹**ሜቶኮስ**››

**ምዕራፍ 2 ማሰላሰያ**

1. Henry T. Blackaby & Clause V. King, *Experiencing God* (Nashville, TN: Broadman & Holman Publishers, 1994) **ገጽ** 86-87.
2. **ዝኒ ከማሁ ገጽ** 87.
3. **ዝኒ ከማሁ ገጽ** 87-88.
4. Brother Lawrence, *The Practice of the Presence of God* (New Kensington, PA: Whitaker House, 1982) **ገጽ** 61, 65.
5. **ዝኒ ከማሁ ገጽ** 37.
6. **ዝኒ ከማሁ ገጽ** 41, 46, 47, 49.
7. Kathryn Kuhlman, *The Greatest Power in the World* (North Brunswick, NJ: Bridge-Logos Publishers, 1997) **ገጽ** 122.
8. *Sparkling Gems*, **ገጽ** 116.

**ምዕራፍ 3 ማሰላሰያ**

1. Francis Frangipane, *Holiness, Truth and the Presence of God* (Cedar Rapids, IA: Arrow Publications, 1999) **ገጽ** 56-57.
2. **ዝኒ ከማሁ ገጽ** 58-59.
3. Romans 1:17; 2 Corinthians 3:18. **ይመ.**
4. C.H. Spurgeon, *All of Grace* (New Kensington, PA: Whitaker House, 1981) **ገጽ** 115.
5. Jeanne Guyon, *Experiencing the Depths of Jesus Christ* (Jacksonville, FL: SeedSowers Publishing, 1975) **ገጽ** 3.
6. **ዝኒ ከማሁ ገጽ** 11.

**ምዕራፍ 4**

1. Rick Renner, *The Dynamic Duo: The Holy Spirit and You*, 105 (Lake Mary, FL: Charisma House, 1994).
2. Joseph Henry Thayer, *A Greek-English Lexicon of the New Testament: Being Grimm's Wilke's Clavis Novi Testamenti*, 509 (New York: Harper & Brothers, 1889).
3. M. G. Easton, *Easton's Bible Dictionary* (New York: Harper & Brothers, 1893).

**ምዕራፍ 4 ማሰላሰያ**

1. Exodus 3:2-4; 13:21; 14:24; Psalm 78:14. ይመ.
2. Charles Spurgeon, *The Power in Praising God* (New Kensington, PA: Whitaker House, 1998) ገጽ 31.
3. Joseph Henry Thayer, D.D., *Thayer's Greek-English Lexicon of the New Testament* (Grand Rapids, MI: Baker Book House, 1977) ገጽ 517, የተወሰደ
4. Smith Wigglesworth, *Ever Increasing Faith* (Springfield, MO: Gospel Publishing House, 1971) ገጽ 96-97.
5. Reinhard Bonnke, *Living a Life of Fire* (Orlando, FL: E-R Productions LLC, 2009) ገጽ 237.
6. ዝኒ ከማሁ ገጽ 274, 369.
7. Watchman Nee, *Let Us Pray* (New York, NY: Christian Fellowship Publishers, Inc., 1977) ገጽ 71.
8. Kathryn Kuhlman, *The Greatest Power in the World* (North Brunswick, NJ: Bridge-Logos Publishers, 1997) ገጽ 79.

**ምዕራፍ 5**

1. Spiros Zodhiates Th.D., ed., *The Complete Word Study Dictionary: New Testament* (Chattanooga, TN: AMG Publishers, 1992), s.v.

"mysterion." ‹‹ሚስትሪዮን››
2. Johannes P. Louw and Eugene Albert Nida, ቅጽ 1, *Greek-English Lexicon of the New Testament: Based on Semantic Domains*, electronic ed. of the 2nd edition., 383 (New York: United Bible Societies, 1996).
3. *Strong's Concise Dictionary*, 51.

**ምዕራፍ 5 ማሰላሰያ**
1. Kenneth E. Hagin, *Why Tongues?* (Tulsa, OK: Rhema Bible Church, 1975) ገጽ 14-16.
2. Oswald Chambers, ሁለንተናዬ ለእርሱ ክብር (Uhrichsville, OH: Barbour Publishing, Inc., 1997) ገጽ 155.
3. ዝኒ ከማሁ

**Chapter 6**
1. *Vine's Expository Dictionary*, 585. *teknon* and *huios*. በቴክኖን እና በሑዮስ መካከል ያለውን ልዩነት ለማመልከት የተሰጠውን ማስታወሻ ይመ.
2. *Noah Webster's First Edition of an American Dictionary of the English Language* (San Francisco: Foundation for American Christian Education, 1967, 1995), 113.




## የሰይጣን ሽንገላ

ከአደገኛ የጠላት ወጥመድ አምልጡ! የሰይጣን ሽንገላ አማኞችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ለማስወጣት ሰይጣን የሚጠቀምበትን እጅግ አሳሳች ወጥመድ ያጋልጣል - ያም መሰናከያ ነው። በሰይጣን ሽንገላ የተጠመዱ አብዛኞቹ ወገኖች፣ ሌላው ቀርቶ መጠመዳቸውን እንኳ አያውቁትም። አትታለሉ! መሰናከያ መምጣቱ አይቀርም፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁ ግንኙነት ላይ የሚያመጣውን ውጤት በተመለከተ ምርጫው የእናንተ የራሳችሁ ነው። የምትሰጡት ምላሽ የወደፊት ሕይወታችሁን ይወስነዋል። መሰናከያን በአግባቡ ከያዛችሁት መራራ ከመሆን ይልቅ ብርቱዎች ትሆናላችሁ።

የሚከተሉትን ለመሳሰሉ ጠንካራ ጥያቄዎች መልስ ታገኛላችሁ -

- ለእኔ መስሎ የታየኝን ብቻ እንድናገር የምገፋፋው ለምንድነው?
- የጥርጥርንና ሌሎችን ያለ ማመንን ሐሳብ መዋጋት የምችለው እንዴት ነው?
- ያለፈ ዘመን ጉዳቴን ማውጣት ማውረድን መተው የምችለው እንዴት ነው?
- አንድ ሰው በጣም ከጐዳኝ በኋላ ያንኑ ሰው እንደ ገና ማመን የምችለው እንዴት ነው?

ይህ መጽሐፍ ከጠላት፣ <<አደገኛ ወጥመድ>> እንድታመልጡ፣ ከመሰናከልም ነጻ ሆናችሁ እንድትኖሩ ይረዳችኃል፣ ከእግዚአብሔርም ጋር ያልተቋረጠ ኅብረት እንዲኖራችሁ ያስችላችኃል።




## ጽናት

ይህን ሕይወት ብርቱዎች እንደ ሆናችሁ እንድትዘልቁ ተወስናችኃል!
ጽናት ከተሰኘው ከዚህ መጽሐፍ አዳጋች ሁኔታዎችን በተመለከተ አሸናፊዎች ያላቸውን ዕይታ ትመለከታላችሁ፤ የሚገጥማችሁን ፈተናና መከራ እንዴት በአሸናፊነት መወጣት እንደምትችሉ ትማራላችሁ።

- በክርስቶስ ያላችሁን ተስፋ ቃልና ኃይል አጥብቃችሁ ያዙ።
- የችግር የመከራችሁን ምንጭ ለይታችሁ ዕወቁ።
- በድል አድራጊነት ወደ መንፈሳዊ አገዛዝ ግቡ።

ለተጨማሪ ትምህርቶች
www.CloudLibrary.org

ሌላም ትፈልጋለሀ?
እዚህ እስካን አድርግ

# ስለ እርሱ ታውቃላችሁ
# ግን እርሱ ራሱን ታውቁታላችሁ?

ደቀ መዛሙርቱ ሦስት ዓመት ሙሉ ከኢየሱስ ጋር ነበሩ፤ ከእርሱ ጋር ተመላልሰዋል፤ የተናገረውን ማንኛውንም ቃል ሰምተዋል። ያም ሆኖ ግን፣ መንፈስ ቅዱስ እንዲመጣ እርሱ መሄድ እንዳለበትና ያም መሆኑ የተሻለ እንደ ሆነ ኢየሱስ ለቅርብ ወዳጆቹ ነግሮአቸው ነበር (ዮሐንስ 16፥7፤ 13-14)። እያንዳንዱን ቀን ከኢየሱስ ጋር ያሳልፉ የነበሩ ደቀ መዛሙርትን በተመለከተ ይህ እውነት ከሆነ፣ በዚህ ዘመን መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን እንዲሠራና እንዲንቀሳቀስ ለእኛ ምን ያህል አስፈላጊ ይሆን?

በጣም የሚያሳዝነው፣ መንፈስ ቅዱስ ሰዎች በተሳሳተ መንገድ የተረዱት ርዕሰ ጉዳይ መሆኑ ነው፤ ስለ ማንነቱና ራሱን ለእኛ ስለሚገልጥበት ሁኔታ ብዙዎች ሐሳቡ እንኳ የላቸውም። ብዙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደ አንዳች ዐይነት፣ <<ግራ አጋቢ>> ጉዳይ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን መንፈስ ቅዱስ አንዳች ነገር ሳይሆን፣ ከጐናችሁ እንደማይለይ ቃል የገባ አካል መሆኑን ግልጥ አድርጐአል። በዚህ አሳታፊ መጽሐፍ ጆን ቢቨሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ ችላ የተባለውንና ብዙዎች በተሳሳተ መንገድ የተረዱትን አካል ማለትም፣ መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ በግል ሕይወታችሁ እንድትረዱ ይጋብዛችኋል።

እንደ መግቢያ የቀረበው ይህ መጽሐፍ አያምልጣችሁ።



**ጆን ቢቨሬ** እና ሚስቱ ሊዛ የሜሴንጀር ኢንተርናሽናል መሥራቾች ናቸው። አገልጋይና ከፍተኛ ተነባቢነት ያለው ደራሲ ጆን በድፍረትና በጋለ ተነሳሽነት የማያወላውል እውነት ያለበትን መልእክት ያቀርባል። የእርሱ ፍላጐት አገርን፣ ቋንቋን ወይም የኢኮኖሚ ሁኔታን ግምት ውስጥ ሳያስገባ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኖችን መርዳትና መሪዎችን ማስታጠቅ ነው። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሥራዎቹ ከ60 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ተተርጐመዋል።


መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ አጋዥ ዲቪዲ የታከለበት




www.CloudLibrary.org
www.MessengerInternational.org
ከተሰኘው ድረ ገጽ እነዚህንና ሌሎች ጠቃሚ ትምህርቶችን መውሰድ ይቻላል

Messenger International
MessengerInternational.org

ይህ መጽሐፍ የደራሲው ስጦታ ነው አይሸጥም